የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት

ቮልዩም ፲፪ (፲፱፻፸፬ ዓ.ም.)

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Vol. 12 (1982)

የኢትዮጵያ ሕግ

መጽሔት

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት

ከሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር

የሚያዘጋጀው

ቮልዩም 12/1974 ዓ.ም.

ትምህርት ሊሰጡ የሚችሉ ሕግን የሚመለከቱ የምርምር ጽሑፎችን ፤ በፍርድ ቤት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ ጠቃሚ የፍርድ ትችቶችን ፤ በሕጎችና በሌሎችም ሕግ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ብት ልኩልን በደስታ የምንቀበል መሆናችንን እንገልጻለን ።

አድራሻችን፡—

የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤
የሕግ ትምህርት ቤት
ፖ.ሣ.ቁ. 1176
አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ ።

ስልክ ቁጥር፡ 11-17-33 ወይም 11-08-44 /108) ነው ።

የሕግ ትምህርት ቤት መምህራን (1974 ዓ.ም.)

በ1956 ዓ.ም. ተቋቁሞ በአሁኑ ጊዜ የኤል ኤል ቢ ዲግሪና የሕግ ዲፕሎማ ትምህርቶችን የሚሰጠው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት መምህራን የሚከተሉት ናቸው ።

ዳንኤል ኃይሌ ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ረዳት ፕሮፌሰርና የፋኩልቲው ዲን
ኤፍሬም የማነብርሃን ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ሌክቸረርና ረዳት ዲን
አንዳርጋቸው ጥሩነህ ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ሌክቸረር
በላይነህ ሥዩም ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ሌክቸረር ፤ በትምህርት ላይ ያሉ
ፋሲል ናሆም ፤
ኤል ኤል ቢ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ጀይ ኤስ ዲ ፤ ተባባሪ ፕሮፌሰር
ግርማ ወልደሥላሴ ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ጀይ ኤስ ዲ ፤ ረዳት ፕሮፌሰር
መስፍን ገብረሕይወት ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ሌክቸረር
ሚካኤል ኸርማን ፤
ኤል ኤል ኤም ፤ ኤል ኤል ዲ ፤ ጎብኚ ፕሮፌሰር
ንጋቱ ተስፋዬ ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ረዳት ሌክቸረር
ሆርስት ኬልነር ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ኤል ኤል ዲ ፤ ጎብኚ ፕሮፌሰር
ሰላሙ በቀለ ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ረዳት ፕሮፌሰር
ሰሎሞን ጁሩ ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ በትምህርት ላይ ያሉ
ወርቁ ተፈራ ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ኤል ኤል ኤም ፤ ረዳት ፕሮፌሰር
ይታይህ ዘላለም ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ሌክቸረር ፤ በትምህርት ላይ ያሉ
ዮሴፍ ገብረእግዚአብሔር ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ረዳት ፕሮፌሰር
ዘካርያስ ቀነዓ ፤
ኤል ኤል ቢ ፤ ረዳት ሌክቸረር

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ሕ ግ መ ጽ ሔ ት

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት
ከሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
የሚያዘጋጀው

የ ቦ ር ድ አ ባ ሎ ች

ጌታቸው ክብረት
ሊቀ መንበር
የሕግና ፍትሕ ሚኒስትር

ዳንኤል ኃይሉ
የሕግ ፋኩልቲ ዲን
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ከበደ ገብረማርያም
የሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ

ፋሲል ናሆም
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሕግ ፋኩልቲ ተባባሪ ፕሮፌሰር

አሰፋ ሊበን
የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት

አ ዘ ጋ ጆ ች

ፋሲል ናሆም
ዋና አዘጋጅ

ሚካኤል ኸርማን
የምርምር ጽሑፎች አዘጋጅ

ዮሴፍ ገብረእግዚአብሔር
የአስተያየቶችና የፍርድ ትችቶች
አዘጋጅ

ንጋቱ ተስፋዬ
ሥራ አስኪያጅ አዘጋጅ

ማውጫ

ገጽ

ከሕግ ፋኩልቲ የተሰጠ የ1973 ዓ.ም. ሪፖርት

በዳንኤል ኃይሌ 1

የሕግ ምርምር ጽሑፎች

ቅጣትና ኅብረተሰብ ፤ ዕድገታዊ አመለካከት

በፋሲል ናሆም 8

በኢትዮጵያ ንግድ ሕግና በኢንሹራንስ ፖሊሲ መካከል ያለ አለመጣጣም ፤ በአካል አደጋና በሕይወት ፖሊሲዎች ላይ የተደረገ ልዩ ትኩረት......

በበላይነህ ሥዩም 29

በ1969 ዓ.ም. የወጣው የገንዘብ ኖትና የባንክ አዋጅ ለውጦች ውጤቶች

በበፈቃዱ ደግፌ 47

የተመረቱ ዕቃዎች ለሚያስከትሉት ጉዳት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ያለው ኃላፊነት

በጆርጅ ክሽቹናቪች 62

ፍርዶችና የፍርድ ትችቶች

የወንጀል ይግባኝ መ. ቁ. 4/71 ጠቅላይ ፍርድ ቤት 82

ተገድዶ ክስን ስለማመን ፤ በወንጀል ይግባኝ መ. ቁ. 4/71 የፍርድ ጉዳይ ትችት

በዮሴፍ ገብረእግዚአብሔር 87

የወንጀል ይግባኝ መ. ቁ. 1515/71 ጠቅላይ ፍርድ ቤት 94

የወንጀል ሙከራና ሌሎች ጭብጦች ፤ በወንጀል ይግባኝ መ. ቁ. 1515/71 የፍርድ ጉዳይ ትችት

በዮሴፍ ገብረ እግዚአብሔር 100

ይህ ቮልዩም 12/1974 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ከአብዮቱ ወዲህ ሁለተኛው እትም ነው ። የመጀመሪያው እትም (ማለትም ቮልዩም 11) የወጣው በ1972 ዓ. ም. ነው ። ከአብዮት በፊት የመጨረሻው የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት እትም በ1965 ዓ.ም. የወጣው ቮልዩም 9 ቁጥር ቁ 2 ነው ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሕግ ፋኩልቲ

የዲኑ የ1973 ዓ. ም. መግለጫ ።

ዳንኤል ኃይሌ ረዳት ፕሮፌሰርና የሕግ ፋኩልቲ ዲን

ዩኒበርስቲው የተቋቋመበትን ሠላሳኛውን ዓመት በዓል ያከበርንበት ያሁኑ የትምህርት ዘመን ለየት ያለ ዓመት ነበር ። ዩኒቨርስቲው የተቋቋመበትን ሠላሳኛ ውን ዓመት በማክበር ለበሳልነት ዕድሜ መድረሳችን ብቻም ሳይሆን ወደ ቀድሞ የትምህርት አሰጣጥ ዘይቤ በመመለስ የአካዳሚውን የትምህርት ደረጃ ለማሻሻል ወሳኝ እርምጃዎችን ወስደናል ። በዚህም መሠረት በሕግ ፋኩልቲ ለድግሪው ፕሮ ግራም የሚሠጠው የትምህርት ጊዜ በአንድ ዓመት እንዲራዘም ሲደረግ ይህም ብቃትና ብስለት ያላቸውን የሕግ ባለሙያዎች ለማፍራት እንደሚያስችለን እር ግጠኞች ነን ።

በዚህ አጭር ሪፖርት ውስጥ ስለፋኩልቲው መምህራንና ተማሪዎች አጠቃ ላይ ሁኔታ፣ በምርምር ሥራዎችና የሥርዓተ ትምህርት ጥናት በኩል ስላለው እንቅ ስቃሴና፣ የቀድሞ የሕግ ተማሪዎችን ማህበር ለማቋቋም ስለተደረገው ጥረት አጠር ያለ መግለጫ ሲሰጥ በመጨረሻም ጐላ ብለው የሚታዩ አንዳንድ ፍላጐቶችንና እክሎችን ለመጠቆም ተሞክሯል ።

1. ተማሪዎች

በ1973 ዓ. ም. የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ ለዲግሪው ፕሮግራም የተ ቀበልናቸው መደበኛ ተማሪዎች ቁጥር 214 ሲደርስ በማታው የትምህርት ክፍል ለዲፕሎማ ፕሮግራም የተመዘገቡት 176 ተማሪዎች ነበሩ ።

የተማሪዎቹ ዝርዝር በዓመታቸውና በአካዳሚክ አቋማቸው መሠረት ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ እንደተመለከተው ነው ።

በ1973 ዓ. ም. የትምህርት ዘመን ለኤል ኤል ቢ ዲግሪ ፕሮግራም በሕግ ፋኩልቲ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት

አንደኛ ሴሚስተር ።

	ጠቅላላ ተመዝጋቢ	በማስጠን ቀቂያ ላይ የነበሩ	በመጨረሻ ማስጠንቀ ቂያ ላይ የነበሩ	የወደቁ	አስፈላጊ ውን ፎርማ ሊቲ ሳያሟ ሉ የቀሩ	በልዩ ልዩ ምክንያት የለቀቁ
1ኛ ዓመት ሕግ	78	7	7	—	2	3
2ኛ ዓመት ሕግ	84	24	4	4	3	1
3ኛ ዓመት ሕግ	43	14	1	—	—	—
4ኛ ዓመት ሕግ	9	—	—	—	—	—
	214	45	12	4	5	4

ሁለተኛ ሴሚስተር ።

ሕግ ት/ቤት	ጠቅላላ ተመዝጋቢ	በማስጠን ቂያ ላይ የነበሩ	በመጨረሻ ማስጠንቀ ቂያ ላይ የነበሩ	የወደቁ	አስፈላጊ ፎርማሊቲ ሳያሟሉ የቀሩ	በልዩ ልዩ ምክንያት የለቀቁ
1ኛ ዓመት	73	2	5	2	3	—
2ኛ ዓመት	84	8	9	4	1	2
3ኛ ዓመት	45	—	1	—	—	—
4ኛ ዓመት	8	—	—	—	1	1
	210	10	15	6	3	3

የማታው ዲፕሎማ ፕሮግራም ፤

በ1973 የትምህርት ዘመን የዲፕሎማ ፕሮግራም በተሟላ ሁኔታ ሲካሄድ የቆየ ሲሆን በመጀመሪያው ሴሚስተር 101 የ1ኛ ዓመት ፣ በሁለተኛ ሴሚስተር 75 የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች ነበሩ ።

በዓመቱ መጨረሻ 7 ተማሪዎች በድግሪ ፣ 61 ደግሞ በዲፕሎም ተመርቀዋል።

በአንደኛው ሴሚስተር ያብዛኞቹ ተማሪዎች ውጤት አጥጋቢ ስላልነበረ ይህንኑ ለማሻሻል ሲባል በትምህርትታቸው ደከም ብለው የተገኙትን ተማሪዎች ከፋካልቲው መምህራን አማካሪዎች እንዲመደብላቸው ተደረገ ። በዚህ መሠረት እያንዳንዱ መምህር ከሶስት እስከ አራት የሚደርሱ ተማሪዎችን በቅርብ ሆኖ የማማከሩን ሥራ ይዞ በመጨረሻው ዓመት የተማሪዎቹ ውጤት ማሻሻል የዚህን ዕቅድ መሳካት የሚያሳይ ነው ብለን እናምናለን ።

የተማሪዎችን የትምህርት ይዞታ ለማሻሻል ሌላው የተወሰደው እርምጃ ቀደም ብሎ ሲደረግ እንደነበረው የክረምት የጥናት ፕሮግራም በማዘጋጀት አንብበው መጥተው ዩኒበርስቲው ሲከፈት ለፈተና እንዲቀመጡ ማድረግ ነበር ።

በመጨረሻም በውጤቱ ብልጫ ለሚያሳይ ተማሪ በየዓመቱ ሽልማት ለመስጠት የሚያስችል በፕሮፌሰር ጆርጅ ኪችኖብች ስም የሚጠራ የሽልማት እቅድ የገንዘብ ምንጭ ለመፍጠር ታስቧል ። ይህ ውጥን ገና ፍጻሜ ያላገኘ ቢሆንም የአካዳሚውን የትምህርት ይዞታ የላቀ ለማድረግ ጥሩ ማበረታቻ ይሆናል ብለን እናስባለን ።

2. *መምህራን*

ሀ/ የድግሪ ፕሮግራም ፤

በዚህ ዓመት ካሉን አሥራ አራት መምህራን አሥራ አንዱ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ሶስቱ የውጪ አገር ዜጎች ነበሩ ። ከነዚህ በዓመቱ መጨረሻ ፕሮፌሰር ጆርጅ ክችኖቢች የፋካልቲው የ29 ዓመት ከፍተኛ አገልግሎት ካበረከቱ በኋላ ጡረታ ወጥተዋል ።

በዓመቱ መጨረሻ ሁለት የውጪ ዜጎች ማለትም ዶክተር ሄንሪክ ሌስቼናና ዝጅስዋብ ጋሊትስኪ የኮንትራት ጊዜያቸውን ጨርሰዋል ። እኒሁ ከፖላንድ ዋርሶ ዩኒቨርስቲ የተላኩልን መምህራን በፋካልቲያችን በቆዩበት ሶስት ዓመታት ከፍ

ተኛ ተሳትፎ አሳይተዋል ። በዚህም ረገድ በፋካልቲያችንና በዋርሶ ዩኒቨርስቲ መካከል የተፈጠረው ጥሩ አርአያነት ያለው ግንኙነት የበለጠ እንደሚጠናከር እርግጠኞች ነን ።

በተጨማሪም ያሉንን መምህራን ዕውቀት ለማዳበር ባለን ዕቅድ መሠረት ዘንድሮ ሁለት መምህራን ማለትም አቶ በላይነህ ስዩም ወደ ካናዳ ማክጊል ዩኒቨ ርስቲ ፣ አቶ ሰለሞን ጅሩ ዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ በሚገኘው ኮለምቢያ ዩኒበርስቲ ትምህርታቸውን ለመከታተል ተልከዋል ።

ከላይ የተጠቀሱትን ብቁ መምህራን የመተካቱ ተግባር ዘግየት ብሎ የተጀ መረ ሲሆን በተረገው ያላሰለሰ ጥረት ሌሎች ጥልቅ ዕውቀት ያላቸውን ምሁራንን ለማግኘት በመቻላችን ጥረታችን አኩሪ ውጤት ማሳየቱን ልገልጽ እወዳለሁ ። ስለሆነም በመጪው የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ ዶክተር ሚካኤል ሄርማን ከፖላንድ ሕዝባዊት ሪፑብሊክ ፣ ዶክተር ሐርስት ከልነር ከጀርመን ዲሞክራትክ ሪፓብሊክ ፣ አቶ መስፍን ገ/ሕይወትና አቶ ዘካርያስ ቀንዓ በፋካልቲያችን ለማስ ተማር ይመጣሉ ።

እንደተለመደው የፋካልቲው መምህራን ትምህርት በሚነኩና ከዚያም ውጪ አስተዳደርን በሚመለከቱ ብዙ ጠቃሚ ጉዳዮች ተካፋዮች ነበሩ ። ይህም እያንዳ ንዱ አስተማሪ የሚያበረክተው ብቻ ሳይሆን የሕግ ትምህርት ቤት የሚሳተፍባቸ ውን ተግባሮች ስፋት ያሳያል ። በተቻለ መጠን እያንዳንዱ መምህር በተለይ ጥናት የሚያደርግበትን አካባቢ በቅርብ እንዲከታተል ለማድረግና በየወቅቱ በሚፈጠ ሩት አዳዲስ ሁኔታዎች ላይ ለመወያየት እንዲያስችለን የፋካልቲ ሴሚናር የተሰኘ መድረክ ከፍተናል ። ምንም እንኳን በዚህ ዓመት የተካሄዱት ሴሚናሮች የመጨ ረሻ ዓመት ተማሪዎችንና መምህራንን ብቻ የሚያቅፍ ቢሆንም ለወደፊቱ ተስፋፍ ተው በሰሚናሩ ለመሳተፍ ፍላጐታቸውን የገለጹልንን የቀድሞ ተማሪዎች ለመ ጨመር እንደሚበቃ ተስፋ አለን ። ባለፈውም የትምህርት ዘመን በሚከተሉት ርዕሶች ላይ ሴሚናሮችና ተከታታይ ንግግሮች ተደርገዋል ።

1. « የሶሻሊስት ዲሞክራሲ መስፋፋት ችግሮች » በዶክተር አለክሳንደር ፓፓቭ ከሞስኮ ዩኒቨርስቲ
2. « ከማርክሳዊ የመንግሥት ቲዎሪ ውስጥ የእኩልነት ጽንሰ ሃሳብ በዶክተር ሄንሪክ ሌስቼና (ከሕግ ፋካልቲ)
3. ስለ ዘመናዊ መንግሥት ሕጋዊነት በአፍሪካ » ፤ በዶክተር ሄንሪክ ሾለር (ከሙኒክ ዩኒበርስቲ)
4. « ከፋብሪካ በሰው የሚመረቱ ዕቃዎች የሚያስከትሉት ሃላፊነት » በፕሮፌ ሰር ጃርጅ ቺችኖብች ።

ለ/ የማታው ዲፕሎማ ፕሮግራም ፤

የሕግን ተከታታይ የትምህርት ፕሮግራም ከመደበኛው የትምህርት ክፍል ጋር በተቻለ መጠን ለማዋሐድ የፋካልቲው የምን ጊዜም ፖሊሲ እንደሆኑ መጠን ይህንንም ለማድረግ በተቻለበት አንደኛው መንገድ የሙሉ ጊዜ መደበኛ መምህራን በማታውም የማስተማር ፕሮግራም ለመሳተፍ እንዲችሉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ነው ። ስለሆነም በአንደኛውና በሁለተኛው ሴሚስተር ሲያስተምሩ ከነበሩት አሥራ አራት መምህራን መካከል ከሕግ ፋካልቲ ውጪ ያመጣናቸው ሁለት ብቻ ነበሩ ። ጥሩ ውጤት ለማስገኘት እንዲቻል መምህራኑ በማታውም ፕሮ

ግራም መደበኛ ተማሪዎችን የሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት እንዲይዙ ሲደ ረግ በዩኒቨርስቲው ደንብ መሠረት ከአንድ የትምህርት ዓይነት በላይእንዳያስተ ምሩ የተደረጉ አስተማሪዎችም አልነበሩም ።

3. የሥርዓተ ትምህርት ጥናትና ግምገማ ፡፡

የሥርዓተ ትምህርት ጥናትና ግምገማ የዘወትር ሂደት እንደመሆኑ መጠን ፋካልቲው ባጠቃላይም ሆነ የትምህርት ደረጃዎች ዕድገትና የሥርዓት ትምህርት ኰሚቴው በተለይ የሚያስቡበት ጉዳይ ነው ። ምንም እንኳን የኰሚቴው አብይ ተግባር የሆነው አዲሱ የአምስት ዓመት የኤል ኤል ቢ ዲግሪ ከሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶ የመቅረብ ሥራ በ1972 የትምህርት ዘመን የተጠናቀቀ ቢሆንም ተደቅኖ የነበረው ይህንን ፕሮግራም ትምህርታቸውን በደሮው ፕሮግራም የጀመ ሩት ነገር ግን ትምህርታቸውን ያላገባደዱት ተማሪዎች ሥራ ላይ ማዋሉ ነበር ። የሕግ ሶስተኛ ዓመት ማለትም የዩኒቨርስቲ አራተኛ ዓመቱ ተማሪዎች ምረ ቃ በ1973 ዓ. ም. የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ሴሚስተር ፍጻሜ ላይ እንዲሆን ኮሚቴው ያቀረበው ሃሳብ ለፋካልቲው የአካዳሚክ ጉባኤና ለዩኒበርስቲው የሥ ርዓተ ትምህርትና የደረጃዎች ግምገማ ኮሚቴ ቀርቦ ጸድቋል ።

የአምስት ዓመቱን የኤል ኤል. ቢ. ዲግሪ ፕሮግራም ተግባራዊ ከማድረጉም በተጨማሪ ኰሚቴው የአካዳሚክ ጥራትን ጉዳይ በሚገባ አጢኖታል ። በዚህም ረገድ ፤

ሀ/ የኰረምት ምንባቦች እንዲዘጋጁ
ለ/ ተማሪዎች በአነስተኛ ክፍሎች እንዲከፋፈሉ
ሐ/ ለተግባራዊ ትምህርት ትኩረት እንዲሰጥ
መ/ የትምህርት ዓይነት መደበኛ ይዘት እንዲኖረው ሀሳብ አቅርቧል ።

ባለፈው የትምህርት ዓመት መጨረሻ ላይ የቀረቡትም ሐሳቦች በመጪው የትምህርት ዓመት ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ይውላሉ ። ኮሚቴው የተወያየበት ሌ ላው ጉዳይ ደግሞ የፋካልቲው አካዳሚክ ጉባኤ ፈተናዎችን የሚቆጣጠርበት ሁኔታ ነው ። እስካሁንም ቢሆን ፈተናዎች ከመሰጠታቸው በፊት አስቀድሞ በአካዳሚክ ኮሚሽን ሲታይ የነበረ ቢሆንም የኰሚሽኑን ሥልጣንና የመምህሩን ነጻነት ማገ ናዘብ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ። ይህንን በሚመለከት ኰሚቴው ያቀረበው ሀሳብ ገና በአካዳሚክ ጉባኤው ይጠናል ።

4. ምርምርና የኅትመት ሥራዎች ፤

የምርምርና የጽሑፍ ሥራዎች እንደገና በማንሰራራት ላይ ቢገኙም ባለብን የመምህራን እጥረት የተነሳ ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ አልዋለም ። ቢሆንም በቂ መምህራን ለማግኘት ባለን ተስፋ መሠረት ሥራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማ ካሄድ በሚያስችሉን ጉዳዮች ላይ ተነጋግረናል ።

ሀ. በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ጥናቶች ዕቅድ ፤

1. የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት

አንጋፋ የሆነው ይህ መጽሔት ለጥቂት ጊዜ መታተሙ ሲቋረጥ ከሁለት ዓ መት ወዲህ ቀጥሎ ቅጽ 11 ቁጥር 1 በዚህ ዓመት ታትመ ። ተከታዩን ቅጽ 11 ቁጥር 2 ለማውጣት ሥራው የተገባደደ ስለሆነ በመጪው የትምህርት ዘመን በመ ጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ገደማ ይታተማል ተብሎ ይጠበቃል ።

2. የተጠቃለሉ የኢትዮጵያ ሕጎች ፤

የዚህ ዕቅድ ሥራ ባለፈው የትምህርት ዘመን ተጀምሮ አሁን ሁለተኛውን ክፍል በማዘጋጀት ላይ ስለለን ሁለተኛው ክፍል በሐምሌ ወር በ1974 ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል ።

3. የአፍሪካ ሕግ ዳይጀስት ፤

ይህ መጽሔት ከ1966 ወዲህ ኅትመቱ ተቋርጧል ። ፋካልቲው መጽሔቱን መታተም እንደገና ለመቀጠል በየጊዜው ባደረጋቸው ስብሰባዎች የተነጋገረበት ቢሆንም በገጠመን የልዩ ልዩ ቋንቋ አዋቂዎች እጥረት ምክንያት እስካሁን ድረስ ሳይሳካ ቀይቷል ። ይህንንና የመሳሰሉት ችግሮች በመጪው ዓመት መጀመሪያ አጋማሽ ላይ እንደምንወጣውና ኅትመቱ እንደሚቀጥል ተስፋ አለን ።

ለ/ የግል ምርምር ጥናት ፤

ከላይ ከተጠቀሱት በፋካልቲው በመካሄድ ላይ ከሚገኙት የምርምር ጥናቶች ሌላ መምህራን በየግላቸው ያደረጉት ጥናት ለማስተማሪያ የሚሆኑ ማቴሪያሎችንና በመጽሔት የሚታተሙ አጫጭር ጹሑፎችን በማዘጋጀት በኩል ረድቷል ። ከነዚህም ሳይጠቀስ የማይታለፍ ስለ ውል አመሠራረት በፕሮፌሰር ጆርጅ ቺቾሮብች የተዘጋጀው ጽሑፍ ነው ። እኚህ ፕሮፌሰር በውል አመሠራረት ላይ ያዘጋጁትን ትችት ረቂቅ አጠናቅቀው በዓመቱ መባቻ ገደማ ለፋካልቲው አቅረበዋል ። ሥራቸውም በውስጥና በውጭ ገምጋሚዎች ታይቶ ለኅትመት ብቁ መሆኑ የታመነበት ሲሆን የገምጋሚዎቹ አስተያየት ታክሎበት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለዩኒቨርስቲው የምርምርና የኅትመት ክፍል ቀርቧል ።

የምርምርና የኅትመት ጥረታችን በሽያጭ አንጻር የታየ እንደሆነ የሚያመረቃ ሊሆን አልቻለም ። እስካሁን እትሞቻችን ገበያ የሚቀርቡት አራት ኪሎ ግቢ በሚገኘው የዩኒቨርሲቲ መጻሕፍት መሸጫ ብቻ ነው ። ለሌሎች የመጻሕፍት መሸጫ መደብሮች ከሚሸን ተከፍሎ እትምታችን ለሕዝብ የሚቀርቡበት ሌላ ዘዴ ካልተገኘ ሥራችን ተስፋ ቢስ ሆኖ ይቀራል ። እትምታችን ሕዝቡ እንዲያገኛቸው ካልተደረገ የምናካሂደው ሥራ እንኳን ፍሪያማ ሊሆንና መቀጠሉም አጠራጣሪ ነው ። በዚህ አንጻር እስካሁን ችግሮች የገጠሙን ቢሆንም የሥራችን ውጤት ጠቀም ያለ እንዲሆን ማረጋገጥ ብቻም ሳይሆን በሕግ ሙያ የተሰማሩትን ሰዎች በማስተማር አቢይ ዓላማችንን እግቡ ለማድረስ የሚያስችል አሠራር መቀየስ ይኖርበታል ።

5. ቤተ መጻሕፍትና መረጃዎች ፤

በያዝነው ዓመት የቤተ መጻሕፍታችን ይዘት ጉልህ የሆነ መሻሻል አሳይቷል። ከጀርመን ፌደራል ሪፑሊክ መንግሥትና ከዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማህበር በስጦታ ያገኘናቸው በዛ ያሉ መጻሕፍት የመጻሕፍታችንን ብዛት ከፍ አድርገውታል ። ከዚህ የሚከተለው ዝርዝር እ. ኤ. አ. ከነሐሴ 1 ቀን 1980 እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1981 ዓ. ም. መጻሕፍት ቤቱ ያሳየውን ዕድገት ያመለክታል ።

አዲስ ጭማሪ በርዕስ	130
በስጦታ የተገኙ ማቴሪያሎች በጥቅል	170

በደምበኝነት የተገኙ ወቅታዊ እትሞች በርዕስ ——————76
በልውውጥ የተገኙ ወቅታዊ እትሞች በርዕስ ——————25
በስጦታ የተገኙ ወቅታዊ እትሞች በርዕስ ——————20

በአገልግሎት በኩል ተጠቃሚው በብዛት ከመጨመሩም በላይ የአዘውታሪውም ቁጥር ፈጣን ዕድገት አሳይቷል ። ቤተ መጻሕፍቱ ለ390 ተማሪዎች ፣ ለ16 መምህራንና በቴክኒክና በአስተዳደር ሥራዎች ለተሰማሩ 21 ሠራተኞች አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው ። ከዚህም በላይ ለዩኒቨርስቲው የሌሎች ክፍሎች ተማሪዎችን መምህራንና በሌላም ሙያ የተሰማሩ ግለሰቦችን ያገለግላል ።

6. የቀድሞ ተማሪዎች ፤

ባለፉት ጊዜያት የቀድሞ የሕግ ተማዎችን ማህበር ለመመሥረት ጥረት የተደረገ ቢሆንም በያዝነው ዓመት ከተወሰዱት ትላልቅ እርምጃዎች መካከል ለሕግ ፋካልቲ የቀድሞ ተማሪዎች ማህበር መቋቋም መሠረት መጣሉ ነው ። የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ አቶ ኃይሌ ከበደ (ጠበቃ) አቶ ግርማ አስፋው (ከሕግና ፍትሕ ሚኒስቴር የሕግ ክፍል)፤ አቶ መክብብ ጸጋው (የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ) አቶ ዮሴፍ ገ/እግዚአብሔር (በሕግ ፋካልቲ ረዳት ፕሮፌሰር) እና አቶ ዘርዓ ብሩክ አበራ በኤች ቢ. ኤ. ዋና የሕግ አማካሪ በአባልነት በሚገኙበት አርቃቂ ኰሚቴ ተዘጋጅቷል ።

የተዘጋጀውም የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ የየክፍሉ ተወካዮች በሚገኙበት አስተባባሪ ኰሚቴ ከተጠና በኋላ የማህበሩን መመሥረት የሚያረጋግጥ ሰነድ እንደገና በመዘጋጀት ላይ ነው ። ማህበሩም ከመጪው የትምህርት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል የሚል ተስፋ አለን ።

7. የሚያስፈልጉ ነገሮችና ያሉት ችግሮች

<u>በቂ የሆነ ሕንጻ አለመኖር</u> በተማሪዎችና በሚያየርገው እንቅስቃሴ አንጻር የሕግ ፋካልቲ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ የሚሄድ ቢሆንም ቀድሞ በተመሠረተበት ቅጽር ተወስኖ ይገኛል ። ዋናው ሕንጻና ሌሎችም በዙሪያው ተበታትነው የሚገኙት ለተግባሩ ብቁ አለመሆናቸውም ብቻ ሳይሆን በእርጅና ወይም በጥገና እጦት የተነሣ ወይም በሁለቱም ምክንያት በውስጣቸው ለሚካሄደው ሥራ ሥጋት እየተፈጠሩ ነው ። በእኔ አስተያየት ለፋካልቲው መንቀሳቀሻ የሚበጅ ብቃት ያለው የሕንጻ ሥራ የሚታሰብበት ጊዜ አሁን መሆን አለበት ።

የውጭ ግንኙነቶች ፤

የፋካልቲው ዕድገትና ታዋቂነት የሀሳቦች ልውውጥና ከብዙ የውጭ ተቋሞች በሚያረግለት ትልቅ የገንዘብ ዕርዳታ ውጤት ነው ። የቀድሞ ግንኙነቶቻችን ጨርሰው የተቋረጡ ሲሆን ከሌሎች ተቋሞች ጋር አዲስ ግንኙነት ለመፍጠር የተወሰደ እርምጃ እምብዛም ነው ። እያንዳንዱ ፋካልቲ በአንጻሩ የሚያደርገው ጥረት የማይናቅ ቢሆንም ቅሉ ማዕከላዊነት ያለው ዩኒቨርስቲ አቀፍ የሆነ አሠራር የበለጠ ፍሬያማ ስለሚሆን ለችግሩ በዚህ አንጻር መፍትሔ ቢፈለግለት ጠቃሚ ነው ።

መደምደሚያ ፤

የገጠሙን ችግሮች ታዳጊ ተቋሞችን ከሚገጥማቸው የተለየ አይደለምና ያለንን አጥብቀን እንደያዝን በአስተሳሰብ ወደ ፊት መራመድ አለብን የፋካልቲያችን የቀድሞ ዲን አንድ ጊዜ እንዳወሱት አንድ ነገር ባለበት እንዲንቀሳቀስ ከማድረግ ይልቅ ካለበት ማንቀሳቀሱ የበለጠ ከባድ መሆኑን የሳይንስ ሕጐች ያስተምሩናል ። ሰብአዊ ተቋሞች ግን ሁላችንም እንደምናውቀው ሌላ ሕግ አላቸው፣ አንድን ተቋም ወይም ፕሮጀክት መጀመሩ ሳሆይን ማካሄድ ወይም አሳክቶ ከፍጻሜ ማድረሱ የበለጠ አድካሚ ነው ። ሆኖም ግን በፋካልቲው የሥራ ባልደረቼና በተማሪዎቻችን የኅብረት መንፈስ እርምጃችን እንዲቀጥል ማድረግ ብቻም ሳይሆን ፋኩልቲው በትክክለኛ አመለካከት የታነጸና በእርአያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ባለሙያዎችን በማፍራት የሚጠበቅበትን ለማሟላት እንደሚችል ቅንጣት ያህል አልጠራጠርም ።

ቅጣትና ኅብረተሰብ ፤ ዕድገታዊ አመለካከት

በፋሲል ናሆም*

I በኅብረተሰብና በቅጣት መካከል ያለው ግንኙነት

በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ የቅጣቱ ስልትና ዓይነት[1] መደጋገሙና ክብደቱ፡ በአንድ አፈንጋጭ (ወንጀለኛ) ላይ ቅጣቱን ለመፈጸም የሚደረገው ሂደት ህብረተሰቡ ራሱ ምን እንደሚመስል አመልካች ነው ። ኅብረተሰብ ዋጋ የሚሰጣቸው ወጐችና ልማዶች ሁሉ በሚጥላቸው ቅጣቶች ውስጥ ተጠቅለው ይገኛሉ ። አንድ ሕብረተሰብ በሕይወቱ ውስጥ ለምን ነገር ትልቅ ግምት እንደሚሰጥ ፤ ትልቅ ግምት ከሚሰጣቸው ነገሮች የቱ ከየትኛው እንደሚበልጥ ፣ እንደዚሁም ኅብረተሰቡ እነዚህን ዋጋ የሚሰጣቸውን ወጐችና ልማዶች የቱን ያህል እንደሚንከባከባቸው ፤ በአንድ አፈንጋጭ ላይ በሚጥለው ቅጣት በግልጽ ይንጸባረቃሉ ፣ ስለሆነም ቅጣት አንድ ኅብረተሰብ የቱን ያህል ጨዋ ፣ የፈጠራ ችሎታ ያለውና ተራማጅ መሆንና አለመሆኑን መለኪያ ሆኖ ያገለግላል[2] ።

ተስፋ እንደምናደርገውና በምንም ዓይነት ቢሆን ኅብረተሰብን በቁጥር ስሌት አማካይነት በሚያጠኑ የህብረተሰብ ሳይንስ ሊቃውንት ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ቢችልም ፣ ኅብረተሰብ ዋጋ የሚሰጣቸውን ወጐችና ልማዶች በቁጥር ስሌት መግለጽ ከፍተኛ ትክክለኛነት ባለው ቁጥራዊ አሠራር ማህበራዊ ማጠቃለያዎች መስጠት ከዚህ ጽሁፍ ዓላማ ውጭ ነው ። እዚህ ላይ የጸሐፊው መጠነኛ ዓላማ ቅጣትን በአጠቃላይ መልኩ በማየት በዚህ ወሳኝ መስክ ውይይትን ለመቀስቀስ ነው ። ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀው ከሌላው ዓለም ጋር በማነጻጸር ሆኖ ሳለ ዝርዝር ሁኔታ መስጠት በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ የኢትዮጵያ ልምድ በብዛት ሰፍሯል[3] ። የዚህ ጽሑፍ ርዕስ በኅብረተሰብ ሳይንስ ላይ በመሆኑ በዚህ መቅድም ላይ ስለ ኅብረተሰብ ሳይንስ በመጠኑም ቢሆን ማውሳት አግባብነት ያለው ሳይሆን አይቀርም ። የኅብረተሰብ ሳይንስ አዝማሚያ በአንዳንድ ክፍሎች ዕድገት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ሰው ለእንጀራና በእንጀራ ብቻ ይኖር ይመስል በጠባቡና በደረቅ ኢኮኖሚያዊ መስኩ ማጥናት ሆኖ ይታያል ። ዕድገት በተለይም የሰው ማህበራዊ ዕድገት በሰው ልጅና በኅብረተሰብ ዕርምጃ አጠቃላይ ዕውነታ ላይ ከእጅ ወደ አፍ እስከ ምርት መቅረፍረፍ ያለውን ቁስ አካላዊ ዕድገት ብቻ ሳይሆን ከማይረባ አምልኮ እስከ ሳይንሳዊ ዕውቀትና ከአውሬነት ባሕርይው እስከ ጨዋነት ባሕርይው ባለው ዕድገቱ ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል ። እነዚህ የዕድገት መስኮች የተያያዙ ቢሆኑም በጠባቡ የተወሰኑ ግምት ማየት ያልተለመደ አይደለም ፣ ይኸውም አንዱ የዕድገት ዘርፍ ኖሮ ሌላው ላይኖር ይችላል ። ጉዳዩን በምሳሌ ለማስረዳት የዘር መድልዎ አገዛዝ የሰፈነበትን ደቡብ አፍሪካን መጥቀስ ይበቃል ። የዕድገት ደረጃዋ በአንጻራዊ ሁኔታ ሲታይ ከእጅ ወደአፍ ኢኮኖሚ ይልቅ ወደዳበረ ኤኮኖሚ ይመደባል ። ይህም ሆኖ ግን የአብዛኛው ዜጐቹን አያያዝ እንዲሁም ስለዘር ልዩነት ያላትን አጠቃላይ አመለካከት ስናይ የደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት መቆጠር ያለበት እንደሰለጠነ ሆኖ ሳይሆን ኋላ ቀርና የአረመ

ኔነት ባህርይ እንዳልተለየው ሆኖ ነው ። የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች በኢኮኖሚ አቋማቸው ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች የተሻሉ ሊሆኑ መቻላቸው የሐቁ አንድ ገጽታ ብቻ ነው ። ሌላ የሐቁ ገጽታ ደግሞ በደቡብ አፍሪካ ጥቁር ሠርቶ አደር ላይ ኢሰብአዊ ተጽዕኖ በሚያደርጉ ብዙ ሕጎች ውስጥ ይገኛሉ ።

የ1911 ብሔራዊ የሠራተኛ ጉዳይ ድንጋጌና ማንኛውም ጥቁር በኮንትራት እንዲሠራ የሚያስገድደው ፣ የ1964 የባንቱ የሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ፣ የ1913 ብሔራዊ የመሬት ስሪት ሕግና ጥቁር አፍሪካውያንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለ ሀብትነት የሚከለክለው የ1936 የመሬት ሕግ ፣ የ1911 የማዕድናትና የሥራዎች ሕግና ፣ አውሮፓውያን ካልሆኑት በአንድ ሙያ የመሰልጠን ዕድልን የሚዘጋው የ1944 ሥራ መልመጃ ውል ሕግ የአፍሪካውያን ነባር መኖሪያ ለጥቁሮች ከተከለለው ሥፍራ ውጭ እንዳይሆን የሚደነግገው የ1964 የባንቱ ሕግጋት ማሻሻያና ለባንቱ አገር አስተዳደርና የሠራተኛ ጉዳይ ሚኒስትሮች ማንኛውም ጥቁር በማንኛውም ቦታ ፣ በማንኛውም አሠሪ ፣ ለማንኛውም ዓይነት ሥራ እንዳይቀጠር ለመከልከል የሚያስችላቸው ሥልጣን የሚሰጠው የ1970 የባንቱ ሕግጋት ማሻሻያ[4] ከብዙዎቹ አድላዊ ሕጎች ጥቂቶቹ ናቸው ። የዓለም ሕዝብ አስተያየት ከሶሻሊስት ጐሬ እስከ ካፒታሊስት ጐሬ ታዳጊውን ዓለም ጨምሮ በደቡብ አፍሪካ ላይ ጠንካራና ያላሰለሰ ውግዘት በማሰማት ላይ መሆኑ የሚያንጸባርቀው የሰውን ልጅ ዘላቂ ፍላጐት ይኸውም የሰው ማኅበራዊ ዕድገት ማለትና መሆን ያለበት ሌላ ሳይሆን በአጠቃላይ መልኩ የሰብአዊ ክብር ከፍ ማለት ነው ።

በሰው ህልውና እንጀራ አስፈላጊ ቢሆንም ፣ የሰው ልጅ እድገት በእንጀራ ብቻ የተወሰነ አይደለም ፤ በምንም ብቸኛ ነገር የተወሰነም አይደለም ። ታዲያ ፣ ይህ ማለት ደግሞ ስለሰው ማህበራዊ እድገት እጥጋቢ ቲዎሪ እንዲሁም ለታለመ ተግባር መሰረት ሆኖ ሊያገለግል ከሚችል ትክክለኛ ማጠቃለያ ላይ ለመድረስ የሰውን ልጅ የሚመለከቱ መስኮች ሁሉ መጠናት አለባቸው ። የሰውን ማኅበራዊ ዕውነታና ፍላጐት ፣ በኋላ ቀርነት እስከ ዕድገት ያለውን ጠመዝማዛ ጉዞ በአጥጋቢ ሁኔታ እንዲያንጸባርቅ ከተፈለገ ጥናቱ የግድ ብዙ ሁኔታዎችን ያቀፈ መሆን አለበት ። «ቅጣትና ሕብረተሰብ» የሚለው የመጀመሪያ ጥናት የቀረበውም በዚህ አግባብ (መሠረት) ነው ።

II ፍትሕና የቅጣት ዓላማዎች

ፍትሕ በአንድ በተወሰነ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ መዋቅር (ሥርዓት) ውስጥ ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ መንከባከብና መጠበቅ ጋር አንድ ሊመስል ይችላል[5] ቅጣት የሚፈጸመው ይህ አስፈላጊና ምቹ የሆነው ሚዛን በሚቃወስበት ጊዜ ድሮ የነበረውን ሥርዓት ለመገንባትና ለወደፊቱ ያለውን ሁኔታ ሳይቃወስ ለመጠበቅ ነው ። አባባሉን ምሳሌ ግልጽ ሊያደርገው ይችላል ። አንድ ሌባ ከአንድ ገበሬ አንዲት ላም በሚሰርቅበት ጊዜ ያለው ሁኔታ ይናጋል ፣ ሁኔታዎች እንዳሉ እንዲቀጥሉ መተው በፍትሕ ላይ ወንጀል መፈጸም ይሆናል[6] ። ኅብረተሰቡ አንድ ዓይነት ዕርምጃ መውሰድ አለበት ፣ ግን ምን ዓይነት ? የላሚ መመለስ ፣ ማለትም የቀድሞውን ሁኔታ መመለስ ወይም ጥፋተኛው በደል ላደረሰበት ሰው ተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያስረክብ ፣ ለምሳሌ ተመሳሳይ ላም ወይም ገንዘብ ማለትም በተቻለ መጠን ከድሮው ጋር ተቀራራቢ የሆነ አዲስ ሥርዓት መገንባት ከግዙፋዊ አመለካከት አኳያ ያለውን ሁኔታ ሊያረካ ይችል ይሆናል ። ነገር ግን ግዙፋዊ ካልሆነ አመለካከት አኳያ አሁን ታሪካዊ ዕውነት የሆነው ያለውን ሁኔታ

ያናወጠው ድርጊት ትዝ ይለናል ። ለወደፊቱ በዚሁ ወንጀለኛ እንደዚሁም የሱን አርአያ በሚከተሉት ተመሳሳይ ወንጀለኞች የድርጊቱ መፈጸም አደጋ ይታየናል ። የደረሰው ቁስአካላዊ ጉዳት ወደነበረው ሁኔታ ከተመለሰ በኋላ ወንጀለኛው በነጻ እንዲሄድ መፍቀድ አሁን ያለው ሁኔታ ለወደፊቱ እንዲናጋ መጋበዝ ይሆናል ። ለወደፊት ሊደርስ የሚችለውን የጸጥታ መናጋት ለመቀነስ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት ከነበረበት ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር በከፋ (በጐጂ) ሁኔታ ላዕ እንዲገኝ ሊያደርገው የሚችል ግዴታ በወንጀለኛው ላይ መወሰድ አለበት[7]።

ይህን የመሰለውን አባባል ሁለት የተያያዙ ጥያቄዎችን ሊያነሳ ይችላል ፣ ይኸውም 1ኛ. የቱን ያህል መጐዳት አለበት ? እና 2ኛ. ይህን ለማድረግ ኅብረተሰብ ምን ዓይነት ዕርምጃ መውሰድ አለበት ? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው ። በጥንቱ (ጊዜ) ዘመናት (በጣም ጥንታዊ ያልሆኑ ኅብረተሰብቦችም ጭምር) የበቀል ፍርድ (LEX TALIONI)[8] ማለትም ዐይን ያጠፋ ዐይኑ ይጥፋ ፣ ጥርስ ያወለቀ ጥርሱ ይውለቅ በማለት የተዘጋጀና አጠቃላይ የሆነ ፍትህ ይሰጡ ነበር ። ሌሎች ማህበሮች እንደዚህ ቀላልና ቀጥታ የሆነ መልስ ላይሰጡ ይችላሉ ። በዚህ አስቸጋሪና ውስብስብ መስክ እንደዚህ ያለ መልስ መስጠት አለባቸው ብለንም ሀሳብ አና ቀርብም ። ሕብረተሰብ በቅጣት ምን ጥቅም እንደሚያገኝ (ግብ እንደሚመታ) ካላወቁ ውጤቱ አሳዛኝ ይሆናል ።

በመሆኑም ሕብረተሰብ ሁልጊዜ የቅጣት ጥቅም ምንድነው ከሚለው ጥያቄ ጋር እንደተፋጠጠ ነው ። ችግሩን የማስወገጃ አንዱ መንገድ ኅብረተሰብ የነበረውን ሁኔታ ወደ ቦታው ለመመለስ ወይም ያለውን ሁኔታ ከወደፊት ሁከት ለመጠበቅ የደረሰውን ሁኔታ (የተፈጸመውን) ከምን አኳያ እንደሚመለከተው በመወሰን ሊሆን ይችላል ።

ኅብረተሰብ ማተኮር ያለበት በደረሰው ሁኔታ ላይ ነው ? ወይስ ጉዳት በደረሰበት የኅብረተሰቡ አካል ላይ ነው ፣ ወይስ ደግሞ በአፈንጋጩ ላይ ወይስ በኅብረተሰብ አጠቃላይ ፍላጐት ላይ ነው መሆን ያለበት ? ጥያቄውን ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስቀመጥ ኅብረተሰብ በልቦናው ውስጥ ምን ዓላማ ሊኖረው ይገባል ? ጉዳት የደረሰበት ሰው ላይ ማተኮር መሆን አለበት ? አስፈላጊ ከሆነም በበቀል የቆሰለውን ጉዳት የደረሰበትን ሰው ስነልቡናዊ ወዘና እስከ ማርካት ድረስ ማለትም ክፉን መበቀል እስከሚለው መሄድ አለበት ? ወይስ ከዚህ ትንሽ ለየት ባለ አመለካከት በደረሰው ሁኔታ ላይ ማተኮርና አጸፋውን ለመመለስ መሞከር ፣ ለም ሳሌ ነፍስ ግዳይን በሚመለከት ረገድ «ያለደም ስርየት የለም» ማለት አለበት ? ወይስ ኅብረተሰብ አፈንጋጩ ለምን እንዳፈነገጠ ለመረዳትና እሱን ወደ ኅብረተሰቡ ለመመለስ ብሎም ኅብረተሰቡ እርሱና እርሱን ከመሰሉ አፈንጋጮች ወደ ፊት እንዲጠበቅ ፣ ኅብረተሰብ እንደዚህ ላለው ማፈንገጥ ዋናውን መንስኤ ለማጥፋት እንዲችል በአፈንጋጩ ላይ ማተኮር አለበት ?

ኅብረተሰብ አንድን አፈንጋጭ በመቅጣት ለማግኘት የሚሞክራቸው ግቦች (ውጤቶች) በሶስት ታላላቅ (ሠፋፊ) ፈርጆች ሊጠቃለሉ ይችላሉ ። ከባሪያ ሥርዓት እስከ ፊውዳሊዝምና አሁን እስካለንበት ዘመን ባለው የሰው ልጅ ረጅም ታሪክ ውስጥ የሚታወቀው የመጀመሪያው የቅጣት ግብ ክፉን መበቀል የሚለው ነው ። ከጥንት ኅብረተሰብ ቴዎሪያዊ ጥናት ጀምሮ ከአውሬነት እስከ ጨዋነት ባለው የሰው ማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት ክፉን በክፉ መበቀል የሚለው የቅጣት ግብ ብዙም ተቀባይነት የሌለው ነው ። የሌክስታሊዮን ፍልስፍና ተከታዮች ክፉን በክፉ መበቀል የሚለውን የቅጣት ግብ በመጠቀም ይታወቁ ነበሩ ። በአሁኑ ዘመን

በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ዋዜማ በብዙ ዘመናዊ ኅብረተሰቦች ያለውን ልዩ ልዩ ዓይነት ቅጣት በሚቀጥሉት ጥቂት ገጾች ስንመለከት እሁንም ቢሆን የሰው ልጅ እራሱን ክፉን በክፉ መበቀል ከሚለው የቅጣት ግብ ማላቀቅ እንዳላበት ግልጽ ይሆናል ።

ኅብረተሰብ በቅጣት አማካይነት ለማግኘት የሚሞክረው ሁለተኛው ግብ ወንጀለኛውን ማረምና ወደኅብረተሰቡ መመለስ ሲሆን ፣ ይህ ግብ ግን ከኅብረተ ሰቡ ጋር መቶ በመቶ ገና ያልተዋሐደ ሆኖ ይገኛል ። ይህ ግብ በሰው ልጆች ዘንድ ገና አስፈላጊውን ትውውቅ ያላገኘና ፣ በመከሰት ላይ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሳ በሥነ አዕምሮ ሳይንስ በኩል የሳይንሳዊ ዕውቀት መስፋፋት በቅጣት ላይ ያለ ጥርጥር ዘላቂ ተጽዕኖ ይኖረዋል ። ዕርማት በቅጣት ዓላማነቱ ኅብረተሰቡንም ሆነ አጥፊውን በጥሩ አኳኋን ይጠቅማል ። ኅብረተሰብ በቅጣት አማካይነት ሊያገ ኘው የሚሞክረው ሶስተኛው ግብ ማስጠንቀቂያ ሲሆን አጥፊውን ለወደፊቱ በማ ስጠንቀቅና ኅብረተሰቡን በአጠቃላይ በማስጠንቀቅ በሁለት መንገድ ያገለግ ላል[9]። ግለሰባዊ ማስጠንቀቂያ ወንጀለኛውን ወንጀል ዘላቂ ቁምነገር እንደሌለው በማስተማር ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲሆን በአጠቃላይ ሁኔታው እጅግ በጣም ብዙ ነገር የሚጠይቅና ስቃይ የተሞላበት እንደሆነም ጭምር ነው ። ግለሰባዊ ማስጠ ንቀቂያ ወንጀለኛውን በለስላሳ ማግባባት ሳይሆን ኃይል በተሞላው ጠንካራ ክንድ እንደገና ወንጀል መፈጸም ረብ እንደሌለው በማሳመን ልማደኛ ወንጀለኛ ነት ለማሸነፍ ይሞክራል ። እንደዚሁም በአፈንጋጩ ላይ የሚፈጸመው ቅጣት ኅብረተሰቡን በአጠቃላይ ለማስተማር ያገለግላል ። ስለዚህ የቅጣት ግብ ለወደፊት ወንጀል ሊፈጽሙ ከሚችሉ ሰዎች የወንጀል ውጤቱ መራራ እንደሆነ አጠቃላይ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ላይ ያተኩራል ።

ማንኛውም የቅጣት ዓይነት ቢሆን ከሕብረተሰብ ደህንነትና ጥበቃ ሌላ በቂ ምክንያት ሊኖረው አይችልም ። ኅብረተሰብ ደግሞ ቅጣትን ከወንጀለኛና ወደ ፊት ወንጀለኛ ሊሆኑ ከሚችሉ ግለሰቦች አንጻር እስተዋይ ትኩረት በማድረግ በይብልጥ ራሱን ይከላከላል ። በዚህ አባባል ትክክለኛነት ላይ የተመሠረቱ በር ከት ያሉ ግምቶችና ምሳሌዎች ከተቻለም ዘላቂነት ያላቸው ማጠቃለያዎች (መደ ምደሚያዎች) መነሳታቸው አይቀርም ። አንዱ መሰረታዊ ግምት በኅብረተሰብ ብቻ ሳይሆን በወንጀለኛውም አስተዋይነት ላይ የተመሰረተ ነው ። ኅብረተሰብ ሊያስተላልፍ የሚሞክረው ማንኛውም መልዕክት በትክክል ከወንጀለኛው ሊደ ርስ የሚችለው ወንጀለኛው አስተዋይ ከሆነ ብቻ ነው ። በሌላ አነጋገር በአንድ ሰው የሚፈጸመው ቅጣት ሊያስተውል የሚችለውን ያህል መሆን አለበት ፤ የሚ ሠራውን ለማወቅ የማይችል ወይም የፈጸመው ተግባር ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት ለመረዳት የማይችል ሰው የፈለገው ሌላ ነገር ሊፈጸምበት ቢችልም ቅጣት ሊፈጸምበት አይገባም[10]።

ሌላው ግምት ደግሞ አንድ ሰው ቅጣት የሚፈጸምበት ግዴታውን ከመወ ጣት ላይ እያለ በራሱ ጥፋት በኅብረተሰቡ ላይ ወንጀል ሲፈጸም ነው ። ጥፋት አንድ ሰው በኅብረተሰቡ ላይ ያለውን መጥፎ አስተያየት የሚያመለክት ረቂቅ ቃል ነው ። እንደዚህ ያለ መጥፎ አስተያየት ደግሞ ሆን ተብሎ የሚሰወድ ሊሆን ይችላል ፣ ይኸውም እያወቀና የሚያስከትለውን ጉዳት እየተረዳ ውጤቱን በመቀበል ጸረ ኅብረተሰብ ድርጊት መፈጸም ሊሆን ይችላል ። ወይም ደግሞ በቸልተኛነት ሊሆን ይችላል ። ይህም ማለት በአንድ በተወሰነ ሁኔታ ሊያደርጋቸው የሚገቡትን

ጥንቃቄዎች ባለማድረግ ሊሆን ይችላል ። ኅሊናዊ (አዕምሮአዊ) የጥፋት መለኪያ፣
ሆን ብሎ (አውቆ) ማጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሳይኖር በአጋጣሚ የደረሰ ጸረ
ኅብረተሰብ ድርጊት በቅጣት ክልል ውስጥ መውደቅ የለበትም[11]።

ትክክለኛ የቅጣት አሠራር የአንድን ወንጀለኛ ግለሰባዊ ፍላጐቶች ግምት
ውስጥ በማስገባት ለአንድ የተወሰነ ወንጀለኛ በግፈኛነቱና በሚወስደው ዕርምጃ
ደረጃ ተስማሚ የሆነ ለዚያ ወንጀለኛ በተለይ የተዘጋጀ ቅጣት ይወስናል ። ይህን
ለማድረግ ደግሞ ኅብረተሰብ ሳይንሳዊ የሆነ አመለካከት ሊኖረው ይገባል ፣ ማለ
ትም በሁኔታዎች ግንዛቤና ትንታኔ ላይ የተመሠረተ ማጠቃለያ ላይ መድረስ
ይኖርበታል ።

በመጨረሻ ኅብረተሰብን ከወንጀል ለመከላከል በወንጀለኞችና ወደፊት
ወንጀለኞች ሊሆኑ በሚችሉ ግለሰቦች ላይ ትክክለኛ (አስተዋይ) ትኩረት ማድረግ
በቀል ትክክለኛ የሆነ የቅጣት ግብ እንዳልሆነ ያሳየናል ። ይህም ማለት ማስጠን
ቀቂያ (ማህበራዊና ግለሰባዊ) እና እርማት ብቻ የቅጣት ትክክለኛ ግቦች በመሆን
ይቀራሉ ። ሆኖም ቅጣት ጠቃሚና ገንቢ ለመሆን ሁለት መለኪያዎችን ማለፍ
አለበት ፣ ለማስጠንቀቂያነትና ለዕርማት ማገልገል አለበት ። አስጠንቃቂና
አራሚ ያልሆነ ማንኛውም ቅጣት ፍቱንነት ስለሌለው በኅብረተሰቡ ውስጥ ቦታ
ሊኖረው አይገባም ። እንዲያውም እነኝህ መለኪያዎችን የማያሟላ ቅጣት በአ
ማራጭ ሊተካ ይገባዋል ። አንድ ዓይነተኛ አርአያነት ያለው የቅጣት አሠራር
ሁለቱንም የቅጣት ግቦች ማስጠንቀቂያነትንና አራሚነትን በተለያየ ደረጃ መያዝ
ይኖርበታል ። ማስጠንቀቂያና ዕርማት በአንድ ቅጣት ውስጥ የሚኖራቸውን ተመ
ዛዛኝነት የሚወስኑት ነገሮች የወንጀለኛው አደገኛ ባሕርይ ፣ የወንጀሉ ጸባይ እን
ዲሁም ወንጀሉ እንዲፈጸም ያነሳሱትና ወንጀሉ የተፈጸመበት ሁኔታዎች ናቸው ።

ቅጣት የሚያስከትለው ማህበራዊ ጉዳት መናቅና መታለፍ የሌለበት አስ
ፈላጊ ነገር ነው ። ከማስጠንቀቂያነትና ከአራሚነት ያለፈ ቅጣት የሚጭን አደ
ገኛ የቅጣት አሠራር ፣ አፈንጋጩ እንደ ጤነኛ የኅብረተሰብ አባል የሚቻለውን
ሁሉ ለኅብረተሰቡ አስተዋጽኦ እንዳያደርግ በመላ ሕይወቱ በአካልና በአእምሮ
ሽባና ስንኩል እንዲሆን ስለሚያደርግ አስፈላጊ አይደለም ። በዚህ ጊዜ የሚቀ
ጣው አፈንጋጩን ብቻ አይደለም ። ነገር ግን አፈንጋጩን ከመጠን በላይ ከመቅ
ጣቱም አልፎ ኅብረተሰቡንም ጭምር ይቀጣል ። ቅጣት የሚያስከትለው ማኅበ
ራዊ ጉዳት በመጀመሪያ ደረጃ የሚመለከተውና ዋና የሚሆነው ለተቀጭው አፈን
ጋጭ የቅርብ ቤተሰቦችና እንዲሁም ወዳጆች ነው ። ለምሳሌ ያህል ጥገኞቹ የሚ
በሉትና የሚቀምሱት ሳይሰጣቸው የአንድ ቤተሰብ አስተዳዳሪ መታሰር በወንጀ
ለኛው ላይ ብቻ የተወሰደ ዕርምጃ ሳይሆን በንጽሕ ጥገኞች ላይ ጭምርም የተ
ወሰደ ነው ። በመሆኑም በብዝበዛ ላይ የተመሰረቱና ትክክለኛ ያልሆነ ዕርምጃ
የሚወስዱ ኅብረሰቦች ለብዙ ጊዜ የሚቆይ መጥፎ ውጤት ያለው ተግባር ይፈጽ
ማሉ ።

የባሕላዊ ቅጣት ዓይነቶች ጥናት የትኞቹ የቅጣት ግቦች ከፍተኛ ግምት እን
ደተሰጣቸው በትክክል ያሳያል ። ቀደም ሲል እንዳስገነዘብነው ሁሉ ቅጣትን
አንድ ኅብረተሰብ የቱን ያህል ጨዋ የፈጠራ ችሎታ ያለውና ተራማጅ መሆንና
አለመሆኑን እንደ መለኪያ ሆኖ እንዲያገለግል ያደርገዋል ። በማስከተል በጥቂት
ባሕላዊ የቅጣት ዓይነቶች ላይ እናተኩራለን ።

III ባሕላዊ (ልማዳዊ) ቅጣቶች

ሀ. እሥራት

ኅብረተሰብ ከድሮ ጀምሮ በአንድ አፈንጋጭ ላይ የሚወስዳቸውን ልዩ ልዩ የቅጣት ዕርምጃዎች ስናስብ ቶሎ ብሎ በአዕምሮአችን የሚመጣው የቅጣት ዓይነት እሥራት ነው ። በእርግጥም በዘወትር የቋንቋ አጠቃቀም ቅጣትና እስራት ተመሳሳይ ናቸው ። እስር ቤቶች የመላው ዓለም መንግሥታት መለያ ባሕርይ ስለሆኑ አንድ እስርቤት የአንድ መንግሥት አካልና አምሳል ፣ መንግሥት ሲመሰረት ጀምሮ የነበረ ነባራዊ ተቋም ነው ብሎ ሊያስብ ይችል ይሆናል ። ምንም እንኳ መቼና የት እንደተጀመረ ለመናገር አስቸጋሪ ቢሆንም እሥራት በጣም የጥንት ልማድ እንደነበር አያጠራጥርም ። ኅብረተሰብ ለጊዜው በአፈንጋጮች ላይ ምን ዕርምጃ መውሰድ እንዳለበት ባለማወቁና የሚወስደውን ዕርምጃ እስኪወሰድ ድረስ ባዶ ቤት ውስጥ ይቆልፍባቸው ስለነበር እሥራት በዚህ ዓይነት ተጀመረ የሚል ቴዎሪ ለመንደፍ መሞከር በጣም ድፍረት (ማጋነን) ይሆን ? ሌላ የተሻለ ሃሳብ ሲጠፋ ይህ ጊዜያዊ እሥራት ደንበኛ የቅጣት ዓይነት እየሆነ ይመጣል ።

በልዩ ልዩ አገሮች ዛሬ እሥራት ቀላልና ጽኑ በመባል ይመደባል[12]። ቀላል እሥራት የሚባለው ከባድ ወንጀል ባልፈጸሙ ሰዎች ላይ ነው።ቀላል እሥራት በአንጻራዊ አመለካከት ሲታይ የአጭር ጊዜ ቅጣት ነው ። በሌላ በኩል ጽኑ እሥራት የሚባለው ለኅብረተሰቡ በጣም አደገኞች ናቸው ተብለው በሚገመቱ በጣም ከባድ ወንጀል በፈጸሙ ወንጀለኞች ላይ ነው ። ጽኑ እስራት የተፈረደባቸው እስረኞች አብዛኛውን የሕይወት ዘመናቸው በማዕከላዊና በከፍተኛ ሁኔታ በሚጠበቁ እሥር ቤቶች ያሳልፉታል[13]።

እሥር ቤቶች በምንም ዓይነት የደስታ ቤቶች አይደሉም ፣ ኅብረተሰብ ብዙውን ጊዜ የመበቀያ መሣሪያ አድርጐ ስለሚጠቀምባቸው ይህ ሊያስደንቅ አይችምል ። በፊውዳል ኢትዮጵያ ስለእሥር ቤቶችና እስረኞች ከ16ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ኢትዮጵያን አቋርጠው ማለፍ ዕድል ባጋጣማቸው ተጓዦች የተነገሩ አንዳንድ መግለጫዎች እናገኛለን ።

ፖርቱጋላዊ ቄስ አልባሬዝ በድንኳን እሥር ቤት ውስጥ በእግረ ሙቅ ታሥረው ስለነበሩ እሥረኞች ይነግረናል ። እነዚህ እሥረኞች የራሳቸውን ቀለብ ብቻ ሳይሆን የሚጠብቋቸውን ዘበኞች ቀለብ ጭምር መቻል ይጠበቅባቸው ነበር ። እንግሊዛዊው ተጓዥ ሪቻርድ ባርቶን በ1850 የኢትዮጵያን እሥር ቤት «የቆሻሻ ጉድጓድ» ብሎ ጠርቷል ። ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ የአዲስ አበባን እሥር ቤት የተመለከተች ፕርሐም የተባለች ሌላ እንግሊዛዊት ተጓዥ እስረኞቹ ተረስተው በበሽታ እየማቀቁ በአስከፊ ሁኔታ ላይ እንደነበሩ ፣ ይህም ሁኔታ በየጊዜው በበሽታ እየማቀቁ በአስከፊ የጤና ሁኔታ ላይ እንደነበሩ ፣ ይህም ሁኔታ በየጊዜው በእሥር ቤቱ ተስቦ እያነሳ ብዙ እስረኞች እንዲሞቱ ምክንያት መሆኑን በመግለጽ አሰቃቂ እንደነበር አመልክታለች[16]። እሥርቤቶች የፈለገውን ያህል መሻሻል አድርገዋል ቢባልም ብዙ ኅብረተሰቦች በዚህ ረገድ ያደረጉት እሥርቤቶችን ተቀባይነት ወዳለው ሰብዓዊ ተቋም ደረጃ ከፍ ሊያደርጋቸው የሚችል አነስተኛ መሻሻል ነው ።

አንድ ሰው እሥር ቤትን እንደ አስፈላጊ ፣ የእሥር ቤት መቅረትም በኅብረተሰቡ ላይ የአማልክትን ቁጣ ሊያወርድ እንደሚችለው አድርጎ ሊገምት ይችል ይሆናል ። እሥር ቤት በቅርብ መጠናት ይኖርበታል ። የቅጣት ጉዳይና

የቅጣት አስተዳደር የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሁም ይህን በገንዘብና በሰው ጉልበት አንጻር ብዙ ወጪ የሚያስከትለው አሠራር ለማካሄድ የሚደክመውና የሚጥረው ሁሉ የእሥር ቤትን ፍቱንነትና ጠቃሚነት የመመርመር ኃላፊነት አለበት ። የእሥር ቤት አሠራር ለወደፊቱ እንዲቀጥል ከተፈለገ ሁለት ሳይንሳዊ መለኪያዎችን ማሟላት ይኖርበታል ። ይኸውም ቅጣት በማስጠንቀቂያነትና በማረሚያነት ማገልገል ይኖርበታል ። እሥራት አስጠንቃቂና አራሚ ነው ብሎ በሐሳብ መገመት ብቻ አይበቃም ። የእሥር ቤት አሠራር የማስጠንቀቂያነትና የአራሚነት ባሕርያት አሉት ከሚል በማስረጃ የተደገፈ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ትክክለኛ ሁኔታው መመርመር ይኖርበታል ።

ለ. በአካል ላይ የሚደረግ ቅጣት

ሌላው ዓይነት ልማዳዊ ቅጣት እንዳጋጣሚ በአሁኑ ጊዜ ጨርሶ ባይጠፋም በመክሰም ላይ የሚገኘው በአካል ላይ የሚደረገው ቅጣት ነው ። በአካል ላይ የሚፈጸመው ቅጣት በብዙ ኅብረሰቦች በተለያየ መልክ ተከስቷል ። ወንጀለኞች እጅግ በጣም ኋላ ቀር በሆነ የህክምና አሠራር ማንኛውም ዓይነት የአካል መቆራረጥ ቅጣት ሲፈጸምባቸው ቆይቷል ። ለምሳሌ ያህልም በመዋሸት ጥፋተኛነት የተወሰነበት ሰው ምላሱ እንዲቆረጥ ሊፈረድበት ሲችል የሐሰት ምስክርነት በመስጠት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ዓይኑ እንዲወጣ ሲፈረድበት ቆይቷል ። በብዙ ኅብረተሰቦች አፍንጫ መፎነን ፣ ጆሮ መቁረጥ የወንድን ብልት መስለብና እጅና እግርን በመጥረቢያ መቆረጥ የተለመዱ ባሕላዊ ቅጣቶች ነበሩ ። በባሕላዊ ሕብረተሰቦች ሁሉ በፊውዳል ኢትዮጵያም ጭምር በአካል ላይ የሚፈጸመው ቅጣት የተለመደ የቅጣት ዓይነት ነበር ። እነዚህ ቅጣቶች ሲፈጸሙ ያጋጠሟቸው ተጓዦች ምስክርነታቸውንና የሁኔታውን አሻራ ትተውልን አልፈዋል ። በ1830 ዓ.ም. አንድ አገር ጎብኚ ንጉሡ የአንድ ሌባ አንድ እጅና ሁለት እግሩ እንዲቆረጥ አዞ ቅጣቱም ገበያ ውስጥ በአደባባይ መፈጸሙንና በኋላም እጅና እግሩን ያጣው ሌባ በዚያኑ ዕለት ማታ በጅብ መበላቱን የዓይን ምስክርነት ሰጥቷል[17]። በ19ኛው ምዕተ ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው አንድ ተጓዥ በጊዜው የነበረው ንጉሡ ጭካኔ የተሞላበት አሰቃቂ ቅጣት እንዲፈጸም ለምሳሌ የልማደኛ ሌባ እጅ እንዲቆረጥ ፣ የአሽሟጣጪና ምላስ እንዲቆረጥ ሲያዝ ትንሽ እንኳ ሰቅቅ አይለውም ነበር ሲል ገልጿል ። አንድ ጊዜ አንድ ጠበቃ የደንበኛውን ጉዳይ ሲከላከል መንግሥትን የሚቃረን ነገር በመናገሩ ንጉሡ የጠበቃውን ምላስ አስቆረጠው[18]። አንድ ሌላ ሰው የአካል መቆራረጥ ቅጣት እንዴት ይፈጸም እንደነበር በመግለጽ የሚከተለውን ዘገባ አቅርቧል ። . ለሁለተኛ ጊዜ በሰረቀ ሌባ ላይ ይፈጸም የነበረው ቅጣት አንድ እጁን እንዲያጣ ማድረግ ነው ። የጥፋተኛነት ውሳኔ እንደተሰጠ ወዲያውኑ ቆራጩ የወንጀለኛውን የእጅ አንጓ ጅማት ይጠመዝዝና በፋስ ይቆርጠዋል ። በዚህ ጊዜ ሴቶች ቅቤ በማሰሮ ያነጥራሉ ። የወንጀለኛው እጅ እንደተቆረጠ ወዲያውኑ ዱሹ በፈላው ውስጥ ይጨመራል ። በዚህ ዓይነት ደሙ እንዳይፈስ በማቆም የጥፋተኛው ሕይወት እንዳያልፍ ይደረግ ነበር[19]።

በኢትዮጵያ የአካል መቆረጥ ቅጣት የተወገደው በ1923 ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕገ በመውጣቱ ነው ። ስለቅጣት የሚናገረው ምዕራፍ በግልጽ እንዳስቀመጠው በአካል ላይ የሚፈጸም ቅጣት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በግርፋት ፍርድ ላይ ብቻ እንዲወሰን ተደረገ ። ከዚህም ሌላ የ1923ቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስለጉዳዩ የተጨነቀበት ከመምሰሉም በላይ የግርፋት ቅጣት በቅርቡ እንደሚወገድ ቃል ገብቶ ነበር[20]። ይሁን እንጂ በ1949 ዓ.ም. አዲስና ከፍተኛ የወንጀለኛ መቅጫ

ሕግ ሲወጣ የተሰጠው የተስፋ ቃል ታጥፎ ግርፋት ከቅጣት ዓይነቶች አንዱ ሆኖ ወጣ[21]።የሕጉ አርቃቂ በረቂቁ ላይ ባይጨምረውም በፓርላማ የሞቀ ክርክር ከተደረገ በት በኋላ ተጨምሮ ገብቷል[22]።የሆነ ሆኖ አርቃቂው የመጨመሩን ተገቢነት እንዲህ በማለት ገልጿል ። «. ስቃይን ሳይሆን የክብር መዋረድን በሚፈራ ኩሩና ጠንካራ ሕዝብ መካከል የግርፋትን ልማድ ጥቅም ዝቅ አድርጌ መገመት አይቻልም ፤ ግርፋት ባለው ሥነ ምግባራዊ ዋጋ ምክንያት ሕዝቡ እንደትልቅ ቅጣት አድርጎ ነው የሚቀበለው[23]። በመጀመሪያ የግርፋት ቅጣት ተወስኖ የነበረው ለከባድ ስርቆትና ለከባድ የውንብድና ወንጀል ብቻ ነበር[24]። ነገር ግን ከ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ብዙ ወንጀለኞች በግርፋት እንዲቀጡ ተደረገ ፤ ከእነሱም መካከል በንጉሱ ላይ የሚፈጸም ስድብ ፡ ዘለፋና ስም ማጥፋት ይገኙበታል[25]። ቢሆንም የ1949 ዓ.ም. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የግርፋት ቅጣት የሚፈጸመው ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 50 ዓመት በሆኑ ወንዶች ላይ ብቻ ከመሆኑም በላይ የግርፋቱም ቁጥር ከአርባ እንዳይበልጥና የሚፈጸመውም ወንጀለኛው ቅጣቱን የሚችል መሆኑ በሐኪም ከተመሰከረ በኋላ ነው ስለሚል በከፊል የዘመናዊነትና የመሻሻል ምልክት ይታይበታል[26]።

ግርፋት የበቀል ዓላማ እንዳለው አጠያያቂ አይሆንም ። አከራካሪ የሚሆነው ግርፋት የአራሚነትና የማስጠንቀቂያነት ዓላማ ነው በዚህ ጥያቄ ላይ የተደረገ ጥናትና ሁኔታውን የሚያሳይ ሠንጠረዥ ባይኖርም ይህ ጽሑፍ ከግርፋት መሰረታዊ ዓላማ (በቀል) በመነሳት ግርፋት ከማስጠንቀቂያነትና ከአረሚነት አንጻር ያለውን ጥቅም ለመወሰን ይቸገራል ። በዚህ ረገድ ይህ ጽሑፍ ሊያቀርበው የሚችለው ሃሳብ ጠቃሚነቱ በሚያሳምን ሁኔታ እስካልተረጋገጠ ድረስ በአካል ላይ የሚፈጸመው የግርፋት ቅጣት እንደ ጎደኛው የአካል መቆራረጥ ቅጣት መቅረትና መረሳት የለበትም ወይ ከሚል የተለየ አይሆንም[27]።

ሐ. የሞት ቅጣት

የሞት ቅጣት በሁሉም ሕብረተሰቦች ዘመናት ከፍተኛ ቅጣት ሆኖ ቆይቷል ። የሞት ቅጣት በአጠቃላይ በተለየ ሁኔታ ከባድ ተብለው በሚገመቱ ወንጀሎች ላይ ሲፈጸም ቆይቷል ። ኅብረተሰብ እነዚህ ወንጀለኞች ሊረዱና ሊመለሱ ከሚችሉበት ገደብ ያለፉ ናቸው ብሎ በማሰብና እራሱን በማሳመን እነርሱን የሚያጠፉበትን አሰቃቂ ዘዴ ሲጠቀም ቆይቷል ። በጥንታዊ አውሮፓ ልማድ የሞት ቅጣት በካራ ፤ በፋስ ፤ በጐራዴ ጭንቅላትን ከሳንቃ ላይ በመፈጥፈጥ ወይም በማረሻ በመቁረጥ ፤ አንድን ሰው ከነሕይወቱ በመቅበር ፤ በርሃብ እንዲሰቃይ እንዲሞት ጉድጓድ ውስጥ በመጣል ወይም እራሱን በመቸንከር ውሀ በመድፈቅና ደም በብዛት ፈሶ እንዲሞት በማቁሰል ፤ በመሬት ላይ በመጐተትና አካልን በመሰነጣጠቅ ፤ ከአንድ ተሽከርካሪ ወይም መንኰራኩር ላይ አድርጎ በማሰቃየት ፤ በጋለ ወረንጦ (መቆንጠጫ) በማሰቃየት ቆዳን ገፎ የጎን አጥንትን በመቆራረጥ አካልን በሙሉ በመበጣጠስ ፤ ብረት ላይ ወይም እንጨት ላይ አጋድሞ በመጋዝ በመቁረጥ ከግንድ ላይ አስሮ በማቃጠልና በብዙ ሌሎችም አስከፊ መንገዶች ይፈጸም እንደነበረ አንድ ጽሁፍ ይገልጻል[28]። በዘመናችን ያሉና የሞት ቅጣትን የያዙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎችና ድንጋጌዎች የሞት ቅጣት አስፈላጊ ካልሆኑ ጭካኔዎች ነጻ በሆነ መንገድ መፈጸም እንዳለበት እስከ መደንገግ ድረስ ተሻሽለዋል ። የ1949 የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጥሩ ምሳሌ ነው ። የሞት ቅጣትን የያዘው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስለቅጣቱ አፈጻጸም ልዩና ግልጽ መመሪያዎች

ይሰጣል ። ቅጣቱ የሚፈጸመው በስቅላት ሲሆን በወታደሮች ላይ ሲሆን ግን በጥይት በመደብደብ እንደሆነ ይገልጻል ። ስለሆነም የሞት ቅጣት ያለአንዳች ጭካኔ ፣ የአካል መቆራረጥ ወይም ሌላ ዓይነት የአካል ጉዳት መፈጸም አለበት ይላል[29]።

የሞት ቅጣት በአጠቃላይ በተለየ ሁኔታ ከባድ ተብለው በሚገመቱ ወንጀሎች ላይ ሲፈጸም መቆየቱን አውስተናል ፣ ሌላው መታወስ ያለበት ነገር ደግሞ የአንድ ወንጀል ከባድነትና አብሮት የሚሄደው ቅጣት በአንድ በተወሰነ ጊዜና ቦታ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚገኙትን የሥልጣን ቁንጮዎች (የገዥ መደቦች) ወግና ልማድ ወይም ጥቅም የሚያንጸባርቁ አንጸባራቂ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው ። አንድ ምሳሌ ብንጠቅስ በድሮ ጊዜ በእንግሊዝ አገር በስቅላት የሚያስቀጡ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ የወንጀል ዝርዝሮች እንደነበሩ ነው ። ከነዚህም መካከል ጥንቸል መግደል መሐረብ መስረቅ እንጆሪ ዛፍ መቁረጥ ያለፈቃድ አሳ ማስገር ይገኙበት ነበር[30]። ከዚህ ሁሉ በስተጀርባ የነበረው ግምት የመሬት ከበርቴ ዎች የባለሀብትነት መብት ፍጹም ስለነበርና ጥብቅ በሆነ መንገድ በመደብ በተከፋፈለ ፊውዳላዊ ኅብረተሰብ ይህ መብት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ነበርና ነው ። በመሆኑም ፊውዳላዊ ኅብረተሰብ ዛሬ ቀላል የደንብ መተላለፍ በምንላቸው ወንጀሎች ላይ እንኳ ሳይቀር የሞት ቅጣት በመፈጸም ጥቅሙን ያስከብር ነበር (በሌላ በኩል ደግሞ የሃየኛው ምዕተ ዓመት ብሪታንያ የሞት ቅጣትን አስወግዳለች ።)

እ.ኤ.አ. በ1962 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት በሞት ቅጣት ላይ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው ከተጠኑት ከአንድ መቶ በላይ ከሆኑ ሀገሮች 35ቱ በሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጐች የሞት ቅጣትን በግልጽ ሲያስቀሩ ዘጠኙ ደግሞ በተግባር ትተውታል ፣ አብዛኛዎቹ ግን በሕጋቸው ውስጥ አስገብተውት ይገኛሉ ።

(የሞት ቅጣትን በሕግ ጨርሶ ማስቀረት የተጀመረው 1786 ዓ.ም. የቱስካኒው ዳግማዊ ሌዎፖልድ በሙሁሩ በቤካሪያ አነሳሽነት የሞት ቅጣትን ለማስቀረት ሕግ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው ። የአውስትሪያው ዳግማዊ የሴፍ ደግሞ በ1787 ባወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሞት ቅጣትን አስቀርቷል[31]።)

አንዳንድ ኅብረተሰቦች ቀደም ብለው ማለትም በ18ኛው ምዕተ ዓመት የሞት ቅጣትን ለማስቀረት ምን እንዳነሳሳቸው ሌሎች ግን እስከ አለንበት ዘመን 20ኛው ምዕተ ዓመት ይዘውት እንዲቆዩ ምን እንዳደረጋቸው ማሰብና መመራመር አስቸጋሪ ጥያቄን ያስነሳል ። ይህ ጥያቄ እጅግ በጣም የተወሳሰበ ቢሆንም ቢያንስ በዘመናችን የሞት ቅጣትን መያዝ ጥቅምና ጉዳት በማመልከት ረገድ የሚነሱትን ጥያቄዎች (ነጥቦች) መመርመር ይቻላል ።

ጂን ግራቨን የ1949ኙ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አርቃቂ የሞት ቅጣት በሕጉ ውስጥ የገባበትን ምክንያት በመግለጽ ሲጽፉ «. በኢትዮጵያ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ የሞት ቅጣትን ማስቀረት የማይታለፍ ከመሆኑም በላይ የማይቻልም ነው ። የሞት ቅጣት አስፈላጊነት ለማህበራዊ ደህንነት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ የፍትሕና የስርዓት ጥልቅ ስሜት በርሱ ላይ የመተመሠረተ ነው ። የፈጣሪ ታላቅ ፍጥረት የሆነው የሰው ሕይወት መጥፋት ሊካስ የሚችለው በጥፋተኛው ሕይወት መስዋዕትነት ብቻ ነው ። እንደመካከለኛው ዘመን የአውሮፓ ክርስቲያኖች ዕምነት ሞት ሁልጊዜ ለኃጢአተኛው ምሕረትና ስርየት አስፈላጊ

የሆነ ሁኔታ ነው ። በተጨማሪም ለፈጸመው እርኩስ ተግባር መፋቅ አስፈላጊ ነው ። ይህ በሁሉም ዘንድ በተለይም በወንጀለኛው ተቀባይነት ያለውና የታመነ ነው ። የሞት ቅጣቱም የሚፈፀመው ቀደም ሲል ከገለጽነው በፋሰና አንገት መቁረጫ ከሚፈጸመው ለየት ባለ ግርማ ሞገስ ባለው ሁኔታ ነው ። » ብለዋል[32]።

የሞት ቅጣት ከሰው መግደል ወንጀል አኳያ በመመልከት አንድ ዘገባ «ሰው መግደል አሰቃቂ እንደሆነ ሁሉ የሞት ቅጣትም የዚያኑ ያህል ከባድ ነው» ሲል ገልጿል ። ምክንያቱም ሰው መግደል ይህ ነው በማይባል ሁኔታ እጅግ በጣም ለመልካም ምግባር ተቃራኒ የሆነ ጥፋት ስለሆነ ሕብረተሰብ በዚህ ወንጀል ላይ ያለውን ከፍተኛ ቁጣ ለወደፊቱ ወንጀለኞች ሊሆኑ ለሚችሉ ሰዎች በጥንካሬ ለመግለጽ እንዲችል ቅጣቱም በዚሁ መጠን ከባድና ከወንጀሉ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት ። በሌላ አነጋገር የሚፈጸመው ቅጣት አግባብ ባልሆነ መንገድ መቀነስ ወይም ማሳነስ ነፍሰ ገዳዩና ሌሎች መሰሎቹ ኅብረተሰባችንን የሰው መግ ደልን ወንጀል አሰቃቂ ነው ብሎ አያምንበትም ወደሚል መንገድ ሊመራው ይች ላል[33]። ከዚህ ላይ ሳንጠቅሰው የማናልፈው ከላይ የተጠቀሰው የሞት ቅጣት ለምን መኖር እንዳለበት የሚያስረዳው ምክንያት በአንድ ወንጀል እርሱም በሰው መግ ደል ወንጀል ብቻ የተወሰነ ነው ። ከዚህ ለመረዳት የምንችለው የሞት ቅጣት ነፍስ ግድያ ባልሆኑ ወንጀሎች ላይ የሚፈጸምበትን አጥጋቢ ምክንያት ለመግለጽ ጨርሶ አይቻልም ባይባልም ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ነው ።

ስለሞት ቅጣት መቅረት ከሚሰነዘሩት ሃሳቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች ባለው ዘገባ ተመልክተዋል ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው

<u>አንደኛ</u> ፣ የመንግሥት ወኪሎች የሞት ቅጣትን በሚፈጽሙበት ጊዜ ሊያ ስወግዱት የማይችሉት ከፍተኛ አመጽ በተቀጭው ግለሰብ ላይ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ይፈጽማሉ ። የዚህ ዓይነቱ ተግባር ለኅብረተሰቡ ደህንነት ሲባል የሚወ ሰድ አስፈላጊ ዕርምጃ ነው ብሎ ማመን መቻሉና በሌላ ዘዴ መፍትሔ ሊገኝለት አይችልም ብሎ መወሰኑ አጠራጣሪ ነው ።

<u>ሁለተኛ</u> ፣ የሞት ቅጣት መኖር በወንጀል የፍትሕ አስተዳደር ላይ ጉጂ ተጽዕኖ ይኖረዋል ። ወንጀለኛው ተከሶ ለፍርድ በሚቀርብበት ጊዜ ሕይወቱ በአ ስጊ ሁኔታ ላይ መገኘት ብቻ በኅብረተሰቡ ዘንድ ጥፋተኛው የተከሰሰበትን ወን ጀል በመርሳት የርሕራሔ የድጋፍ ስሜት እንዲቀሰቀስ ያደርጋል ። ሕግንና የሕ ግን ተፈጻሚነት መደገፍ የሚገባው የሕዝብ ስሜት በዚህ የሞት ቅጣት እስከሚ ፈጸምበት ጊዜ ድረስ በሚከናወነው አስከፊ ሁኔታ የተነሳ ወደ ሌላ አቅጣጫ ያመራል ።

<u>ሶስተኛ</u> ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ለማስፈጸም በሚደረገው ጥረት አንዳ ንድ የተሳሳተ የጥፋተኝነት ውሳኔዎች መስጠታቸው አይቀርም ። አንዳንዴም ብዙ ጊዜ ካለፈ በኋላ ካልሆነ በቀር ስህተቱን ለማግኘት አይችልም ። እንደዚህ ያሉ ስህተቶች የሞት ቅጣቱ ከተፈጸመ በኋላ ሊታረሙ አይቻልም ። እንደዚህ ያለ ሁኔታም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተገነባበትን ዓላማና መልካም ምግባር ጨርሶ ያናጋዋል ።

<u>አራተኛ</u> ፣ ልምድ እንደሚያሳየው የሞት ቅጣት በጣም መጠነኛ በሆነ እኩ ልነት እንኳ አይፈጸምም ።

<u>አምስተኛ</u> ፡ የሞት ስጋት ከረጅም ጊዜ እስራት ስጋት የበለጠ የማስጠንቀቂያነት ፍቱንነት ይኑረው አይኑረው የዘረዘርናቸው አስተያየቶች የሞት ቅጣት መቅረትን እንድንመርጥ ያደርጉናል ። በእርግጥ የሞት ቅጣት በማስጠንቀቂያነት የጠቀመበት የተለዩ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ ። ሆኖም የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት ይህ ሁኔታ በመጠን በኩል ይህን ያህል ትኩረት የሚሰጠው አይደለም[34]።

እንግዲያውም ከላይ የገለጽነው ሁሉ የቅጣት ታሪክ በቅጣት ከባድነትና በወንጀል መፈጸም መካከል ያለውን ዝምድና አያሳይም በሚለው ስለሞት ቅጣት መቅረት በሚከራከሩ ሰዎች አባባል ሊደመደም ይችላል ፣ የተወሳሰበው የወንጀል መንስኤ ለሚመረምር ሰው ይህ አባባል ግልጽ ነው ። አንድ የእንግሊዝ የቅጣት ታሪክ እንደሚያስታውሰን ታይበርን በተባለ ቦታ ኪስ አውላቂዎች በአደባባይ በስቅላት ሲቀጡ ሕዝብ ተሰብስቦ ቅጣቱን በመመልከት ላይ እንዳለ ሌሎች ሰዎች ኪስ ሲያወልቁ ተይዘዋል[35]።

አንድ ሰው ኅብረተሰብ በሞት ቅጣት ምን ግብ ይመታል ብሎ ሊጠይቅ ይችላል ። ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት ከባድ አይደለም ። የሞት ቅጣትና እርሱን ተከትሎ የሚመጣው ጭካኔ ለኅብረተሰብ ከፍተኛ የበቀል ዕርምጃ ሆኖ አገልግሏል ። ይህ ሊካድ አይችልም ። ነገር ግን በቀል ኅብረተሰብ የሚያፍርበት እንጂ የሚያኮራው የቅጣት ግብ አይደለም ። በቀል የአውሬነት (የአለመሰልጠን) ምልክት በመሆኑ በበቀል አንጻር ብቻ የሞትን ቅጣት ብንመለከት መቅረቱ መደገፍ ያለበት ጉዳይ ሆኖ ይቀርባል ።

የሚቀጥለው የቅጣት ግብ ይኸውም እርማት ከዚህ ላይ ፈጽሞ ሊነሳ አይችልም።ምክንያቱም ኅብረተሰብ በሞት ቅጣት በመጠቀም እንዲህ ያለ ሰው ሊታረም አይችልም የሚል ውሳኔ በመስጠቱ ነው ። በትክክል ወይም ሳይገባው ኅብረተሰብ የማረም ችሎታው ዝቅተኛ እንደሆነ ተቀብሏል ። በተጨማሪ እንዲህ ያለ ወንጀለኛ ለኅብረተሰቡ ከእንግዲህ ወዲህ አይጠቅምም ከሚል ውሳኔ ላይ ደርሷል ። እነዚህም ለመወሰን አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታዎች ናቸው ። ያም ሆነ ይህ ኅብረሰብ በአንድ ግለሰብ ላይ የሞት ቅጣት ሲፈርድ የሚወስነው ይህንኑ ነው ።

ከሞት ቅጣት አኳያ በመጨረሻ የምንመለከተው የቅጣት ግብ ማስጠንቀቂያነት ነው ። የሞት ቅጣት በማስጠንቀቂያነት ምን ያህል ያገለግላል የሞት ቅጣት የተፈጸመበት ወንጀለኛ ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይደግም ወይም ሌላ ወንጀል እንዳይፈጽም <u>ፈጽሞ ችሎታ አጥቷል</u> ። ስለዚህም የሞት ቅጣት ከግለሰብ ማስጠንቀቂያነት አንጻር ምንም ዓይነት አስጠንቃቂ አይደለም ። የግለሰባዊ ማስጠንቀቅ ግብ የሚያተኩረው ወንጀለኛውን በሚጣልበት ማህበራዊ ቅጣት አማካይነት ወንጀልን እንደገና መፈጸም ጠቃሚ እንዳልሆነ በማስተማር ላይ ነው ። ይሁን እንጂ የሞት ቅጣት ወንጀለኛው ካለፈው ስህተቱ ተምሮ መልካም ዜጋ እንዲሆን ምንም የሚያበረክተው ትምህርት የለም ። የሞት ቅጣት ወንጀለኛው ለዘለቄታቸው በኅብረሰቡ ላይ ወንጀል እንዳይፈጸም ቢያደርገውም ኅብረተሰቡ ይህን ያደረገው ወንጀለኛው በቅጣት አማካይነት በማስተማር ሳይሆን እንዲሁ ወንጀለኛውን ለዘለዓለሙ በማስወገድ ነው ።

ታዲያ የሞት ቅጣት መቅረት እንዳለበትና እንደሌለበት የሚወስነው ባለው አጠቃላይ የማስጠንቀቂያነት ዋጋ ነው ። የሞት ቅጣት ለወደፊቱ ወንጀለኞች ሊሆኑ የሚችሉትንና ኅብረተሰቡን በጠቅላላው የወንጀል ውጤቱ መራራ መሆኑን

በማስታወቅ እነዚህ ለወደፊቱ ወንጀለኛ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ወንጀል እንዳይ ፈጽሙ የማስጠንቀቂያነት ትምህርት ይሰጣል ? ይህ እንዲሁ ልብ ወለድ መልስ የሚሰጠው ሳይሆን በሳይንሳዊ ጥናት ላይ የተመሰረተ መልስ የሚያስፈልገው ቁምነገር የተሞላው ጥያቄ ነው ።

አንድን የሞት ቅጣት ከነፍስ ግድያ ወንጀል ጋር አጣምሮ የመረመረ ጥናት ደራሲ ሲያጠቃልል «. የሞት ቅጣት ስጋት (ፍራት) ለወደፊቱ ወንጀል ከመ ሥራት እንዲቆጠብ በሰው ባሕርይ ላይ ተጽዕኖ ካለው ፍርሃት ከፍ ባለ ቁጥር በዚሁ መጠን ፍቱን ይሆናል ብለን መገመት እንችል ይሆናል ። የሞት ቅጣት የማስጠቃት ወይም የመከላከል ተጽዕኖ ካለው የሚከተሉት የመላ ምት አባባሎች ትክክል ይሆናሉ ብሎ መገመት ትክክለኛ ይመስላል ።

ሀ/ ሌሎች ሁኔታዎች ሁሉ እኩል ሆነው የነፍስ ግድያ ወንጀሎች የሞት ቅጣትን ካስቀሩ ሀገሮች ይልቅ የሞት ቅጣትን በሥራ ላይ ካዋሉ ሀገሮች ያነሱ መሆን አለባቸው ።

ለ/ የሞት ቅጣት ሲቀር የነፍስ ግድያ ወንጀለኛ መጨመር አለባቸው ። እንደ ገና ከሥራ ላይ ሲውል ደግሞ መቀነስ አለባቸው ።

ሐ/ የሞት ቅጣት በሚፈጸምባቸው ማኅበረሰቦች የማስጠንቀቂያነት ኃይሉ ከፍተኛ መሆን ይኖርበታል ፤ ከዚህም በላይ በነፍስ ግድያ ወንጀሎች ቁጥር ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይገባል ።

የተመረመሩት ማስረጃዎች የሚከተለውን ያሳያሉ ።

1. በነፍስ ግድያ ወንጀል ምክንያት የሚሞቱት ሰዎች ቁጥር በተለያዩ አገሮች ቡድን አንድ ዓይነት አይደለም ።
2. በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ የሚገኙ አገሮች ተመሳሳይ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት እያላቸው እኩል የሕዝብ ቁጥር እያላቸው የሞት ቅጣትን ያስቀሩ ትንና ያላስቀሩትን መለየት አይቻልም ።
3. በነፍስ ግድያ ወንጀል ምክንያት የሚሞቱት ሰዎች ቁጥር የሞት ቅጣትን ባስ ቀሩም ሆነ ባላስቀሩ አገሮች ተመሳሳይ ነው ።

ከዚህ ሊከተል የሚችለው ማስጠንቀቂያ እንዳየነው ሁሉ የሞት ቅጣት ለነፍስ ግድያ ወንጀል በሚሞቱት ሰዎች ቁጥር ላይ ጉልቶ የሚታይ ተጽዕኖ የለውም[36]።

ከዚህ በላይ ከፍ ብሎ የተመለከተው የተባበሩት መንግሥታት ዘገባ በሞት የሚያስቀጡ ወንጀሎች በአሁኑ ጊዜ በአንጻራዊ አስተያየት በርካታ እንደሆኑ የገለጸው የወንጀሎችን አይነትም በመተማመን እንደሚከተለው ያብራራል ።

ከነፍስ ግድያ ሌላ ሌሎች ወንጀሎችን በሞት የሚቀጡ አገሮች ቁጥር እየ ቀነሰ ነው በማለት ያጠቃልላል ። ይሁን እንጂ ዘገባው ያለፉት ሠላሳ ዓመታት ሶስዮሎጂካዊ የሕግ ዋና ዋና ባሕርያት ብሎ በሚጠራው ሁኔታ የታጀበ ነው ። ይኸውም የሞት ቅጣት ከፖለቲካ ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን እንደገና መታ የቱ ነው ። ዘገባው እንደሚሰነዝረው ኃሳብ ለዚህ ሁኔታ ኃላፊው ወይም መንስ ኤው ፈላጭ ቆራጭ የሆነ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ለማውጣት የሚደረገው አዝማ ሚያ ነው ። ይህ የፈላጭ ቆራጭነት አዝማሚያ ለመጀመሪያው የ20ኛ ምዕተ

ዓመት ግማሽ የሞት ቅጣትን ለማጥፋት ይደረግ የነበረውን ዓለማቀፋዊ አዝጋሚ ጉዞ ገታው ። እንዲሁም ይህ ሁኔታ የሞት ቅጣት በቀረባቸው ሀገሮች እንደገና እንዲታይ ከማድረጉም በላይ በሌሎች አገሮች ደግሞ ተፈጻሚነቱ በብዙ ወንጀሎች ላይ እንዲስፋፋ አድርጓል[37]።

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ የሞት ቅጣት ከፖለቲካ ወንጀሎች ጋር እየተያያዘ መጥቷል ። አንድ አፍሪካዊ ጸሐፊ ስለጉዳዩ ሲገልጽ የአፍሪካ አስከፊው የነጻነት ገጽታ የሞት ቅጣት ለብዙ የፖለቲካ ወንጀሎች በቀላሉና በሠፊው መልስ ሆኖ መቅረብ ነው ብሏል[38]። እንዳጋጣሚ ይህ በተለይ የአፍሪካ ባሕርይ ብቻ ሳይሆንም በመላው ዓለም የተለመደ ነው[39]።

ይህን ክፍል ለመደምደም የሞት ቅጣት በሁሉም ሕብረተሰቦች ዘንድ በሥራ ላይ ውሏል በማለት ለማጠቃለል ይቻላል ። ሆኖም ሀያኛው ምዕተ ዓመት ለሞት ቅጣት መፈጸም ገደብ ተደርጐበታል ። በእርግጥም ብዙ አገሮች በሕጐቻቸው የሞት ቅጣት እንዲቀር አድርገዋል ። ሌሎች ደግሞ የሞት ቅጣት በሕጐቻቸው ውስጥ እንዲቆይ ቢያደርጉም በግፍ አገዳደል ወንጀል ላይ ብቻ ተፈጻሚነት እንዲኖረው አድርገዋል ። በመሆኑም የሞት ቅጣት አግባብ ነው ከተባለ የሚፈጸመው በተለይ በነፍስ ግድያ ወንጀል ላይ ይሆናል ። የሚያስገርመው ግን በዚህ ምዕተ ዓመት ቅጣት ተፈጻሚነት በተለያዩ የፖለቲካ ወንጀሎች በርክቶ መታየት ነው ። የሞት ቅጣትን የነፍስ ግድያ ላልሆኑ ወንጀሎች በተለይም በፖለቲካ ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ገለልተኛ ከሆነ ምሁራዊ አመለካከት አንጻር ሲታይ አግባባዊነቱና ትክክለኛነቱ በሠፊው ጥናት የሚያስፈልግ ሆኖ ይገኛል ።

IV ወደ ሳይንሳዊ የቅጣት አቅጣጫ

በዚህ ሥራ በሶስተኛው ክፍል ሶስት ባሕላዊ የቅጣት ዓይነቶች ተወስደው ሲገመገሙ አጥጋቢ ሳይሆኑ ቀርተዋል ። ይህም የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ያስነሳል ። የጥቂት ባሕላዊ ቅጣቶችን አስፈላጊነት ስላቃለልን ታዲያ ሕብረተሰብ ቅጣትን ጽንሰ ሀሳብ ጨርሶ ማስወገድ አለበት ማለት ነው?

ኅብረተሰብ የተመሠረተበትን ወግ በሚጥሉ አፈንጋጮች ላይ ቅጣት ወይም አራሚ እርምጃ መውሰድ ለኅብረተሰቡ ዘላቂ ሕልውና አስፈላጊ ነው ። እንደዚህ ያሉ አራሚ እርምጃዎች ከሌሉ የኅብረተሰቡ አቋም ይናጋል ፤ ከአረመኔያዊነትና ከሕግ አልባነት ገደል ውስጥ እንወድቃለን የሚለው ፍራቻም አሳሳቢ ነው ። ነገር ግን ቁምነገረኛው ጥያቄ ታዲያ ቅጣት በምን ዓይነት መኖር አለበት? የሚለው ነው ። በዚህ ጥያቄ አኳያ ነው የባሕላዊ ቅጣቶች ዋጋ (ጉዳትና ጥቅም) የተነሳው ። አንድ ልንሰነዝረው የምንወደው ቀላል ሀሳብ ቅጣት መበቀያ መሆን እንደሌለበት ነው ። የበቀል ቅጣት ኅብረተሰብንም ሆነ አፈንጋጩን የማይጠቅም ጐጂ ኃይል በመሆኑ መሠረታዊውን የቅጣትን ዓላማ የሚጻረር ይሆናል ። ቅጣቱ አስጠንቃቂ ወይም አራሚ መሆን ነው ያለበት ። ይህን ለማድረግ ደግሞ ኅብረተሰብ በፈጠራ ችሎታው በመጠቀምና ምንጊዜም በመዳበር ላይ ባለው የሳይንሳዊ ሥነ ባሕርይ ጥበብ በመረዳት የተሻሉ የማረሚያ ቅጣቶች የመፍጠር ግዴታ አለበት ። ቅጣት ከታረሙና ወደ ኅብረተሰቡ ከተመለሱ ዜጐች አኳያ ሲታይ ፍጹም እንኳ ሳይሆን በመጠኑም ቢሆን የሚገኘው መልካም ውጤት ከፍ እንዲል የሚያደርግ ጥሩ ሙከራ (ኤክስፐርሚንት) ነው ። ይህን የወንጀልን ችግር ለመዋጋት ኅብረተሰቡ አስተዋይነትና ብልህነት የተሞላበት ውሳኔ ላይ መድረስ አለበት ። በዚህ አስፈላጊ ጉዳይ ላይ ሀሳብ የሚያመነጩ ሁሉ ለኅብረተሰቡ ጥቅም ሲባል መበረታታት ይኖርባቸዋል ።

በመሆኑም ኅብረተሰብ የትኛው ዓይነት ቅጣት ነው አስጠንቃቂና አራሚ ብሎም ተስፋ ሰጪ የሚሆነው የሚለውን ትክክለኛ ጥያቄ ሊያተኩርበትና መፍትሄ ሊፈልግለት ይገባል ። በቅጣት ጥያቄ ላይ ሥር ነቀል አመለካከት መልካም ተቀባይነት ሊኖረው ቢችልም ብዙ ሕብረተሰቦች ባሕላዊው የቅጣት ዓይነት ወደ ተሻለና ሳይንሳዊ የቅጣት ዓይነት ለመለወጥ አዝጋሚ የለውጥ መንገድ የሚከተሉ ነው የሚመስሉ ። የአዝጋሚ ለውጥን መንገድ እንዲከተሉ የሚያስገድዷቸው የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ ። ዋናው ምክንያት የሁሉም ኅብረተሰቦች ባሕርይ በአብነት ሊጠቀስና ሊታይ የሚችል የዘመናዊ ቅጣት ንድፍ (ዕቅድ) ያለመኖሩ ነው ። የእንደዚህ ዓይነቱ ዕቅድ ያለመኖር እንደዚህ ያለውን አሳሳቢና ቋሚ ማኅበራዊ ችግር ኅብረተሰብ በግድ የለሽነት እንደተመለከተው የሚያመለክት ነው ። በመጨረሻ ኅብረተሰብ በችግሩ ላይ እንዲያተኩር በሚገደድበት ጊዜ በየዕለቱ የሚያደርገውን ሙከራ መሠረት በማድረግ ብቻ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ እቅድ በማውጣት መሥራት ይኖርበታል ። እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት እንደዚህ ያለው ሙከራና እቅድ የሰው ኃይል ማሰማራትና ገንዘብ መመደብ ከመጠየቁም ሌላ ውጤት ለማግኘት ንቁ ጥረት ይጠይቃል ። የመጨረሻው ለውጥ ቀላልና የማይጨበጥ አይሆንም ነገር ግን እውነተኛው ለውጥ በአፈንጋጩና በኅብረተሰቡ አስተሳሰብ አድማስ ላይ ይሆናል ። እርግጥ የድሮዎቹ የአካል መቆራረጫ መሣሪያዎች ወደ ቤተመዘክር እንደገቡ ሁሉ የአሁኖቹ በሽቦ የታጠሩና የሚጠብቁ እሥር ቤቶችም ጊዜ ያልፍባቸዋል ። በቦታው ልዩ ዓይነት ከእሥር ቤት የተሻሉ የሕክምና ማዕከላት የሚመስሉ ተቋሞች ሊያብቡ እንደሚችሉ ይጠበቃል ።

በአንዳንድ አገሮች በአሁኑ ጊዜ በሙከራ ላይ ያለው እርግት ፍርድን ግለሰባዊ ማድረግ ነው ። በብዙ አገሮች ሕጋዊው የመንግሥት አካል ወንጀል ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ መስጠት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ወንጀሎች ቅጣቱን ይወስናል ። በብዙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጐች ቅጣት በመወሰን በኩል የሕጋዊው ሚና ለተለያዩ ወንጀሎች ከፍተኛና ዝቅተኛ የእሥራት ዘመን ማበጀት ነው ። ከዚህ በኋላ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘው ወንጀለኛ ላይ ፍርድ የመስጠቱ ጉዳይ ለዳኛው ከመተውም በላይ የሚሰጠው የፍርድ ውሳኔ በአጠቃላይ አነጋገር የመጨረሻ ነው ። ይሁን እንጂ አንድ ሌላ ሀሳብ ፤ ምናልባት «ያልተወሰነ ፍርድ» ሊባል የሚችል በመፍለቅ ላይ ነው[40]። ይህ ማለት ደግሞ በአጠቃላይ መንገድ በሐጋጊው የተደነገገው በመጀመሪያ በፍርድ ቤት በሚታይበት ጊዜ ግለሰባዊ ይሆናል በመሆኑም በአንድ ግለሰብ ወንጀለኛ ላይ ፍርዱን የመወሰን ኃላፊነት ለአይን ቁራኛው ቦርድ በመስጠት ዳኛው ከፍተኛውንና ዝቅተኛውን ፍርድ ብቻ ይወስናል ። እርግጥ የዚህ «ያልተወሰነ ፍርድ» ሌላው መልኩ በዳኛውና በዓይን ቁራኛው ቦርድ መካከል የሥራ ክፍፍል መፍጠር ነው ፤ ይኸውም ዳኛው ጥፋቱን የጥፋቱንም ደረጃ በመወሰን ወንጀለኛው ወደ ዓይን ቁራኛው ቦርድ ያስተላልፈዋል ፤ ቦርዱም ወንጀለኛውን በጥንቃቄ ከተከታተለ በኋላ እርግጠኛውን የቅጣት ጊዜ ይወሰናል ። ያልተወሰነ የፍርድ ኃሳብ ዋናው ባሕርይ ብቁ የሆኑ የዓይን ቁራኛ ቦርዶች ማቋቋምና የእስር ቤት አሠራርን ድጋፍ ሰጭ ከሆኑ ተቋሞች ጋር ማቆየት ነው ።

ሌላው ሥር በመሰደድ ላይ ያለው ሙከራ በቀላል ወንጀሎች ላይ የሚጣለውን የአጭር ጊዜ እሥራት በአንዳንድ አገሮች በሁለተኛ ደረጃ ቅጣቶች ተብለው የሚጠሩት የተለያዩ እርምጃዎች መተካት ነው ፤ ከእነሱም መካከል የገንዘብ ቅጣት ፤ ልዩ ሥራ ፤ ጊዜያዊ የመብት ገፈፋ ፤ ማስጠንቀቂያና በገደብ መልቀቅ ይገኙበታል[41] የአጭር ጊዜ እሥራትን በነዚህ እርምጃዎች መተካት ማኅበራዊም ሆነ ኢኮኖሚ

ያዊ ቁም ነገር አለው ። በመጀመሪያ ነገር ወንጀለኛው ከአምራችነት ተግባሩ ተነስቶ አይወሰድም ፤ ለእርሱ ዘበኛ ፤ምግብና መኝታ ሌሎችም ከእሥር ቤት ጋር የሚሄዱ ወጭዎችን በማቅረብ ኅብረተሰቡ አይቸገርም ። ሁለተኛ የቅርብ ወዳጆቹና ቤተሰቦቹ በእርሱ መታሰር በተዘዋዋሪ አይሰቃዩም ። ሶስተኛ የሕብረተሰብ የቅጣት ግቦች ማለትም ማስጠንቀቅና ማረም ያለምንም እንከን ከሥራ ላይ ይውላሉ ። የትኛው እርምጃ ለየትኛው ወንጀለኛ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ የሚወሰነው በእርግጥ ብዙ መለኪያዎችን በመውሰድ እያንዳንዱን ጉዳይ ለብቻው በመመልከት ነው ።

እንደገና ወደ እሥር ቤት አሠራር በመመለስ እንደ ስካንዲነቪያ አገሮች በመሳሰሉ ሥርዓቶች የተገኘው ልምድ መጥቀሱ ጥሩ ይመስለናል[42]። ስለወንጀል በሶሲዮሎጂካል ክሪሚኖሎጂ ዘዴ በማጤን የእሥር ቤቱን አሠራር በዘመናዊ መርሆዎች እንዲመሠረት ገፋፍቶታል ። ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ ፤

ሀ/ በፖሊሲ አወጣጥ ረገድ ፍጹም የሆነ ማዕከላዊነት

ለ/ የተቋሞች መለያየት

ሐ/ ሊታረሙ የሚገባቸውን ሰዎች ማዕከላዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ በየተቋሞች ማሠራጨት ። እንደዚህ ያለው የእሥር ቤቶች አሠራር በማዕከላዊ መንግሥት ደረጃ ፖሊሲ ማውጣት በጥንቃቄና በማስተዋል እቅድ መንደፍን በርካታ የሰለጠነ የሰው ኃይል በተለያየ ሥራና ሙያ የሚያተኩሩ ብዙ የእሥር ቤት ክፍሎችና ከፍተኛ ባጀት ማስፈለጉ አያጠራጥርም ። የእሥር ቤትን አሠራር ተከትሎ የሚመጣው የልማደኛ ወንጀለኛነት በከፍተኛ ሁኔታ ተደጋግሞ መታየት የመልካም ውጤት ሳይሆን የውድቀት ምልክት መሆኑ ግልጽ ነው ። ከጠቅላላው የውድቀት አዝማሚያ ለየት ባለ ሁኔታ ከዚያም የሚታዩት አንዳንድ የመልካም ውጤት ምልክቶችም የተሀድሶና የፈጠራ ውጤት መሆናቸውን መገንዘብ ያሻል ። በርካታና በደህና ሁኔታ ከታጠቁ ዘበኞች ይልቅ የአእምሮ ሐኪሞችን የሥነ አዕምሮ ሊቃውንትን የማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት ሠራተኞችን የማኅበራዊ ኑሮ ሊቃውንትን የሃይማኖት ሰዎችንና የሕግ ባለሙያዎችን በሥራ ማሠማራት ከጨለማና ጠባብ ቤቶች ይልቅ እሥረኞች አገልግሎት የሚያበረክቱባቸውን ሠፋፊ እርሻዎች ማስፋፋት ፤ ቀስ በቀስ እሥረኞችን ከሕብረተሰቡ ጋር ለማስተዋወቅ የተመላላሽ እሥር ቤቶችን ማቋቋም ፤ ሰብዓዊና አስተዋይ የሆኑ አመለካከቶች እንዲስፋፉ ማድረግ ፤ ለምሳሌ የፈጠራ ወይም ምርታማ የሆኑ ሥራዎች እንዲስፋፉ ማድረግ ፤ እንዲሁም ከቤተሰብ ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠንከርና በእሥር ቤት የትምህርት መስፋፋት ፤ እንዲሁም መሠረታዊ የሆኑ የኑሮ ሁኔታዎችን ማሻሻል ይህ ሁሉ እሥረኞችን ኅብረተሰብ እንደጭራቅ ሳይሆን እንደሰው ፤ ጥቅም እንደሌላቸው ሳይሆን ጥቅም እንደሚሰጡ አድርጎ እንዲመለከታቸው ያደርጋል ። እነዚህ ድጋፍ ሰጭ ተቋሞች ናቸው በእሥር ቤት አሠራር መልካም ውጤት እንዲታይ ሊያደርጉ የሚችሉ[43]። የእሥር ቤትን ቋሚ ሕልውና በሚቃወሙ ወይም አሁን ከምናውቀው ለየት ያለ የእሥር ቤት ዓይነት እንዲኖር በሚመርጡ ሰዎች ተደጋፊነት ሊኖረው የሚገባ ሀሳብ ይሠነዘራል ። ይኸውም እሥራት እንደ ሕክምና መታየት አለበት የሚል ነው ። እንደዚህ ያለው ሕክምና ፍቱን እንዲሆን ካስፈለገ በፈቃደኛነት ላይ መመሥረት ይኖርበት ይሆናል የሚሉም አሉ ፤ ምክንያቱም አለ ወንጀለኛው ትብብር ሊፈወስ አይችልምና ነው ። በመሆኑም እሥራት ወንጀለኛው ራሱ ሊመርጠው የሚችል አማራጭ የሕክምና ዓይነት ሆኖ ሊቀርብ ይችላል[44]።

የቅጣት አኳያ ከልማደኛ ወንጀለኛነትና ከወንጀል መስፋፋት አዘቅት ለመውጣት ያለው ብቸኛ መንገድ በሥነ ባሕርይ ሳይንሶች ውስጥ ከላይ የጠቀስናቸው ፍሬያማ ሀሳቦች ሥር እንዲሰዱ ማድረግ ይመስላል ። ይሁን እንጂ አብዛኛው ምርምርና ጥረት የሚያተኩረው አፈንጋጮችን በማረም በኩል ሳይሆን በመከላከል በኩል ነው ። ወንጀልን ለመዋጋት መጀመር ያለበት ከቅጣት ሳይሆን ዋና ዋና የወንጀል መንስኤዎችን ለይቶ በመረዳት ሕብረተሰብን እንደገና በመዋቅርና እንደአስፈላጊነቱ አቋሙን በማጠናከር መሆን አለበት[45]።

V ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ

ፍትሕ መሠረታዊ ብቻ አይደለም ፤ ሥነ ሥርዓታዊም ጭምር ነው ። ፍትሕ የሚመለከተው የገበሬውን ላም የሰረቀውን ሌባ ምን እንደምናደርገው ብቻ ሳይሆን የምናደርገውን ነገር እንዴት እንደምናደርገው ጭምር ነው ። በተጨማሪ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አስፈላጊነት በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ አይደለም ፤ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ሳይኖር መሠረታዊ ፍትሕ ሊሰጥ አይችልምና ።

አንድ ሕብረተሰብ የቱን ያህል ጨዋ የፈጠራ ችሎታ እንዳለውና ተራማጅ መሆኑና አለመሆኑ አንድን አፈንጋጭ ለመቅጣት በሚደረገው ሂደት ፍትሕን ለማግኘት ለነዚህ መሠረታዊ ሥነ ሥርዓቶች ባለው ታማኝነት በድጋሚ ይንጸባረቃል ። መሠረታዊ የሆኑት የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካሎች በቀላሉ ሊጠቃለሉ ይችላሉ ። ቀላል መስለው ሊታዩ ቢችሉም ለፍትሕ መገኘት የእነርሱ ተፈጻሚነት ፍጹም አስፈላጊ ነው[46]።

ከነዚህ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካሎች <u>የመጀመሪያው</u> «የሕግነት መሠረት» በመባል የሚታወቀው መርህ ነው[47]። ይህም ማለት መፈጸም የማይገባው ድርጊት ከመፈጸሙ መደረግ የሚገባው ነገር ካለመደረጉ አስቀድሞ ድርጊቱ ወንጀል እንደሆነ በሕግ መመልከት አለበት ። በሕግነት መሠረት መርህ አስቀድሞ መታወቅ ያለበት ሌላው ነገር ደግሞ የአንድ ወንጀል ክብደትና ክብደቱን የሚያንጸባርቀው በወንጀሉ ላይ የተጣለው ቅጣት ነው ። ከመፈጸሙ አስቀድሞ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው ባልተነገረ ድርጊት ላይ ተመስርቶ በአንድ ግለሰብ ላይ ክስ ማቅረብ ተገቢ አይሆንም ፤ በመሆኑም የሥነ ሥርዓታዊ ፍትህ ተቃራኒ ይሆናል ።

<u>ሁለተኛው</u> የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል«የንጽህና ግምት»የሚባለው ነው[48]። አንድ ወንጀል ተፈጽሞ አንድ ሰው በጥርጣሬ በሚያዝበት ጊዜ ጥፋተኛ ሆኖ እስከሚገኝ ድረስ ንጹሕ እንደሆነ መቆጠር አለበት ፤ ወንጀሉን የፈጸመው እርሱ ሊሆን ወይም ላይሆን ስለሚችል ነው ። አንድ ግለሰብ እንደወንጀለኛ ከመቆጠሩ በፊት ወንጀለኛው እርሱ ለመሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ ይኖርበታል ። አስቀድሞ አንድን ግለሰብ እንደወንጀለኛ መቁጠርና የወንጀለኛ አያያዝ እንዲደረግለት ማድረግ በኋላ ወንጀለኛ እንዳልሆነ በማስረጃ የተረጋገጠ እንደሆነ ተገቢ አይሆንም ። ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ከአንድ ወንጀል መፈጸም ወንጀለኛውን ለይቶ እስከ ማወቅና ቅጣቱን እስከመወሰን በሚደረገው ሂደት ትዕግሥትንና እርግጠኛነትን ይጠይቃል ግለሰቡ ወንጀለኛ ለመሆኑ የማረጋገጥ ግዴታ ያለበት አቃቤ ሕጉ ነው[49]። ግለሰቡ ወንጀለኛ ለመሆኑ አቃቤ ሕጉ ሸንጎውን ማሳመን አለበት ። ሁሉም ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የአንድ ግለሰብ ጥፋተኛነት በበቂ ማስረጃ ሳይረጋገጥ ሲቀር ግለሰቡ እንደንጹሕ ተቆጥሮ በነፃ መለቀቅ አለበት ። «የንጹሕና ግምት» የፍርድ ሥራው ሂደት እስከ ተፈጸመ ድረስ የሚቀጥልና ማስተባበያ እስካልቀረበበት ድረስ ሳይነካ የሚቆይ ነው ።

ሶስተኛው የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል ብቁና ገለልተኛ የሆነ ሸንጎ መኖርን ይጠይቃል ። ስለአንድ ግለሰብ ጥፋት ወይም ንጽሕናና ስለሚጣለው ቅጣት ውሳኔ የሚሰጡ ሰዎች በችሎታቸው ብቁ መሆን አለባቸው ። በቀረበው ማስረጃ ብቻ ላይ ከተመሠረተ ብይን ላይ ለመድረስ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ጉዳዩን በቅን ልቡና ማየት ይኖርባቸዋል ። ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት የሌላቸው ነገሮች ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸው አይገባም ። ሸንጎውን ገለልተኛ ለማድረግ በሚሰጠው ገለልተኛ ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ነገሮች ፤ ለምሳሌ ከተከሳሽ ጋር አስቀድሞ የነበረ ጠላትነት ፤ ወይም በጉሳና በቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ጥላቻ ፤ የሥልጣን ብልግና ወዘተ መጋለጥና መወገድ ይኖርባቸዋል ። በሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ መርሆዎች ውስጥ ያሉትን መብቶች ለመጠበቅ እንደዚህ ያለ ገለልተኛ ሸንጎ ብቻ ነው በቀረበው ማስረጃ ላይ ከተመሠረተ ውሳኔ ላይ ሊደርስ የሚችለው ። በዚህ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል ማለትም የገለልተኛ ሸንጎ መኖር ውስጥ አንድ ሰው የይግባኝን ሀሳብ ሊጨምር ይችላል[50]። ብቁና ገለልተኛ ሸንጎ ቢኖርም እንኳ ሰው ከሰብዓዊ ደካማነት የጠራ ሊሆን ስለማይችል ስህተት የመሥራቱ አደጋ ሊወገድ የማይችል ነው ።

አንድ በበታች ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከሳሽ ገለልተኛና ብቁ ወደሆነ የበላይ ፍርድ ጉዳዩን የመውሰድና ታች የተሠራውን ስህተት ለማሳረም መብት እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ስለዚህ በአንድ በአርአያነት ሊወሰድ በሚችል ሥርዓት ውስጥ ያለ የፍርድ ቤቶች መዋቅር ወይም የሥልጣን ተዋረድ አንድ ተከሳሽ ጉዳዩን በይግባኝ በሌላ ገለልተኛና ብቁ በሆነ ፍርድ ቤት እንደገና ለማስወሰን ሊኖረው የሚገባውን መብት መጨመር አለበት ።

አራተኛው የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል በአንድ የችሎት አዳራሽ ውስጥ የሚደረገው ተውኔታዊ ሂደትና ከዚህ ጋር የተያያዙትን ሌሎች ነገሮች ይመለከታል ። ተገቢ ምክንያቶች ከሌሉት በስተቀር (ለምሳሌ ፤ የሥነ ምግባር ፤ ንጹህ ለሆኑ ሶስተኛ ወገኖች አግባብ ያልሆነ ነገር ፤ የመንግሥት ጸጥታ ወዘተ) ችሎቱ ለማንኛውም ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ክፍት መሆን አለበት ። «ፍትህ መስጠት ብቻ ሳይሆን ፍትሕ ሲሠራም መታየት አለበት» የሚለው የእንግሊዝኛ አገነጋር ይህንን ያመለክታል ። የክሱ መስማት ያለአንዳች አስፈላጊ የሆነ መጓተት መፈጸም አለበት ፤ ፍትሕን ማዘግየት ፍትሕን መንሳት ነውና ። ተከሳሹ በምን ወንጀል እንደተከሰሰ እንዲሁም የቀረበበት ማስረጃና ማን እንደሚመሰክርበት በማያሻማ ቋንቋ ሊነገረው ይገባል ። ከዚያ በኋላ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ የሚያስችለው በቂ ጊዜና እርዳታም መስጠት አለበት ። ምስክሮች የመጠየቅና መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት ፤ እንዲሁም የቀረበበትን ማስረጃ የመቃወም መብት ፤ በመጨረሻም የራሱን ማስረጃ (ኤክስፐርትም ሆነ ሌላ) ካስፈለገ በሕብረተሰቡ ኪሳራ ማቅረብ ተከሳሹ ሊኖሩት የሚገቡ መብቶች ናቸው[51]። እነዚህ መብቶች የቱን ያህልና እንዴት መስጠት እንዳለባቸው ዝርዝር ደንብና ሥርዓት ሊያስፈልጋቸው ይችላል ። ይሁን እንጂ እንደዚህ ያሉ መብቶች መንፈግ ዞሮ ዞሮ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትህን ወደ መንፈግ ያመራል ፤ ይህም ጨርሶ ፍትሕን ወደ መንፈግ ያደርሳል ።

አምስተኛውና የመጨረሻው የሥነ ሥርዓታዊ ፍትህ አካል ከቅጣት ጋር የተያያዘ ነው ። ቅጣት ምንጊዜም ቢሆን ግለሰባዊ መሆን አለበት ፤ ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ብቻ ቅጣቱን መሸከም አለበት ። በወንጀለኛው ጥፋት ማሕበረሰቡን ፤ ዘመዶቹን ወይም ጐረቤቶች በመሆናቸው ብቻ መቅጣት ከፍትሕ መሠ

ረታዊ መርሆዎች ጋር አብሮ አይሄድም[52]። ከዚህም ሌላ ግለሰባዊ ቅጣት በቂ መሆን አለበት ፤ ሆኖም አስፈላጊ ባልሆነ መንገድ መደጋገም የለበትም ። ድጋሚ ቅጣት መወገድ ያለበት ተግባር ነው[53]።

አንድ ወንጀለኛ ቅጣቱን ከፈጸመና ወደ ሕብረተሰቡ ከተመለሰ ቅጣቱ ወንጀሉን ይፍቅለታል እንጂ ወንጀሉ በሄደበት ቦታ ሁሉ እንደ ጥላ አይከተለውም ። ወደ ሕብረተሰቡ የተመለሰው ወንጀለኛ በሕብረተሰብ አንድ ሌላ እድል ስለተሰጠው እንደማንኛውም የሕብረተሰቡ አባል ይታያል ። ቅጣቱ የበለጠ ሳይንሳዊ በሆነ ቁጥር አፈንጋጩም ፍጹም ወደ ሕብረተሰቡ ይመለሳል ፤ እንደዚህ በሙሆኑም ድጋሚ ወይም የማያቋርጥ ቅጣት ምንም ዓይነት ገንቢ አገልግሎት አይኖረውም

በዘመናዊ ሕጎች ውስጥ እነዚህ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካሎች አንድ በአንድ ተብራርተው ይገኛሉ ። በአፈጻጸማቸው ከአገር አገር (ከሥርዓት ሥርዓት) መለያየት ብቻ ሳይሆን የተለየ እውቀትንም ይጠይቃሉ ። ስለሆነም እነዚህን የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካሎች የሚነፈግና በእነርሱ የማይገዛ ሕብረተሰብ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕን ከመንፈጉም ሌላ የዚያኑ ያህል ፍትሕን ያጓድላል ።

የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

ሌል ሌል ቢ ፤ ሌል ሌል ኤም ፤ ጆይ ኤስ ዲ ዲግሪ ።
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤ የሕግ ፋኩልቲ - ጸሐፊው በዚህ ጽሑፍ ረቂቅ ላይ ለተደረገለት የተለያዩ ገንቢ ሀሳቦች ምስጋናውን ያቀርባል ።

1. ምንም እንኳን ቅጣት በሠፊው ማኅበራዊ ስሜት ኅብረተሰብ በአንድ አፈንጋጭ ላይ የሚወስደውን እርምጃ ሊያመለክት ቢችልም ፤ እዚህ ላይ የተጠቀምንበት ግን በጠባቡና በሕግ ትርጉሙ ፤ ከጥፋተኛነት ውሳኔ በኋላ የሚወሰደውን እርምጃ በሚመለከት ረገድ ነው ።
2. ይህ ጽሑፍ እንደዊበሪያን አመለካከት ዋጋ ካላቸው ወጎችና ልማዶች ተገንጥሎ ሳይሆን ችግር ቀመስ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ ዋጋ ያላቸው ወጎችና ልማዶች በተዋሐዱት መንገድ ምርምር ያደርጋል ። ጨዋነትንና ተራማጅነትን የመሳሰሉት ጽንሰ—ሀሳቦች ዋጋ ያላቸው ወጎችና ልማዶች የተዋሀዳቸው ናቸው ። ይህ ጽሑፍ የተጻፈበት ዓላማም ይህንኑ ለማሳየት ነው ፣ ጽሑፉ በሰው ልዕልና ላይ በተመሠረተ ሰብአዊና ትክክለኛ ሕብረተሰብ ላይ ያተኩራል ።
3. አንድ ሰው የሚጠቀምባቸው ምንጮች ፤ በምንጮቹ ብቁነትና መገኘት ይወሰናሉ ። የ1949ኙ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተጠቀሰበት ምክንያትም ጸሐፊው ከዚህ ሕግ ጋር ስለሚተዋወቅ ነው ። ሕብረተሰብን በአጠቃላይ ሁኔታ በሚያጠና እንደዚህ ባለ ጽሑፍ የአፍሪካና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ምንጮች አግባብነት ስላላቸው በተገቢው ቦታ ሁሉ ተጠቅሰዋል ።
4. ጂ.ኤ. ሆርኔት ፤ «ከለክ ፔይ ኤንድ ፕርዳክቲቢቲ ኢን ሳውዝ አፍሪካ» ፤ ሳውዝ አፍሪካን ሬስሪሌሽንስ ፤ ሴፕቴምበር 1972 ፤ የድኅነት ገደብ መስመር (ፖቨርቲ ዳተም ላይን) በመሠረቱ ለመኖር የሚያስችል ምንዳዕ አይደለም ፤ ነፍስና ሥጋ ሳይለያዩ ለማቆየት የሚችል ብቻ መሆኑን ማስታዎስ ያሻል ። ኤስ.ጂ ሮጀርስ ፤ «አፓርታይድ ኤንድ ዘ አፍሪካን ወርከር» ፤ የተ.መ.ድ ዶኩዩሜንት ፤ ሜይ 1975 ።
5. ፍትሕ በሕግ—ፍልስፍና ፤ የራሱ ተቀጽላ ከሚያደርገው የሰው—ሠራሽ ሕግ (ፖዘቲቭ ሎ) አንፃር ሊታይ ይችላል ፤ ወይም ፍትሕ የሚመነጨው ሙሉ በሙሉ ከሕብረተሰቡ ነው ፤ ግቡም የሕብረተሰቡን ደኅንነት ማሻሻል ነው - በማለት አጠንክሮ ከሚናገረው «የሕብረተሰብ ደኅንነት ነቢብ (ቲዮሪ) አኳያ ወይም ፍትሕ የሰው—ሠራሽ ሕግ ተቀጽላ ሳይሆን የተፈጥሮ መብት ነው ፤ በተፈጥሮ ያለውን ወይም የሚገባውን መስጠት ነው ከሚለው «ከተፈጥሮ መብት ነቢብ (ቲዮሪ)» አኳያ ሊታይ ይችላል ። ብዙ የሕግ—ፍልስፍና ሥራዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ ። አቶ ቦርድ ፤ «ዘ አይዲያ ኦፍ ጀስቲስ» ለአጠቃላይ አቀራረብ ፤ እና ቢ.ኤ. ተማኖቭ ኮንቴምፓራሪ ቡርዣ ሊጋል ቶዎት ፤ ሞስኮ ፤ 1974 ፤ ለማርክሳዊ አመለካከት ፤ ያ፡ዐዳድሯል ። ይሁን እንጂ ፍትሕ በፈለገው ዓይነት መንገድ ቢገለጽ በለውጥ መንገድ ላይ የሚጓዝ ሕብረተሰብ አንፃራዊ ጽንሰ—ሀሳብ ነው ። የሰው ልጅ በአዝጋሚ ለውጥ ወደፊትና ወደ ከፍተኛ ደረጃ በተጓዘ ቁጥር ፍትሕ አዲስና ሰፋ ያለ ትርጉም ይይዛል ።

6. አንድ ዋጋ ያለው ነገር (ቫልዩ) ለዘለዓለሙ በመጥፋቱ ፤ ድሮ የነበረውን ሥርዓት እንደነበረ ለመመለስ የማይችልባቸው ለየት ያለ ባሕርይ ያላቸው ወንጀሎች አሉ ፤ ለምሳሌ ነፍስ ግድያ ወይም የሆነ የግል ተበዳይ ሳይሆን ነገር ግን በደሉ በአጠቃላይ በመንግሥት ወይም በሕብረተሰብ ላይ ሲፈጸም ፤ ለምሳሌ ስለላ ።

7. ጀርሚ ቤንታም ፤ ቤንታም (የ) ወርክስ ገጽ 399—402 ፤ (ለንደን ፤ 1843 ፤ ለከፍተኛና ዝቅተኛ ቅጣት አወሳሰን የተለያዩ የፖሉሲ ሚናዎች ።

8. የሐሞራቢ ሕግ አንድ ጌታ በባሪያው ላይ የነበረውን መብት በተካረረ ሁኔታ ደንግጓል ፤ ባሪያው በጌታው ላይ ግን ምንም መብት አልነበረውም ። አንድ ግንበኛ የገነባው ቤት ተደርምሶ የቤቱን ባለንብረት ልጅ ስለገደለ ተመሳሳይ ሀዘን እንዲደርስበት በማለት የግንበኛው ልጅ ተገደለ ፤ ለንጹሑ የግንበኛ ልጅ መስጠት ስለነበረበት ፍትሕ ምንም ዓይነት ጭንቀት አልነበረም ። ሊረጋገጥ በማይችል እምነተ—ቢስነት የተከሳሾች ሚስት ለባሏ መልካም ስም ስትል እራሱን ባሕር ውስጥ ጨምራ መስጠም ነበረባት ፤ ከሴትዮዋ ሕይወት ይልቅ መልካም ስም ትልቅ ዋጋ ነበረውና ። ይሁን እንጂ የሐሞራቢ ሕግ ደካማውን ከብርቱው ለመጠበቅና ባሏ የሞተባትን ሴትንና የሙት ልጅን ጽኑንነት ለመጠበቅ የታለመ ነበር ብሎ መጥቀሱ ትክክለኛ ይመስላል ። እነዚህ ሕጐች በወጡበት ዘመን ለዚያ ሕብረተሰብ ተስማሚ ነበሩ ።

9. አንዳንድ የወንጀል ቅጣት ሊቃውንት ግለሰባዊውን ከአጠቃላዩ ለመለየትና የተለያዩ ዓላማዎች እንደሆኑ አድርገው ይቆጥሯቸዋል ።

10. እንደቀድሞ ሕጐች ሳይሆን ዘመናዊ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ለወንጀል በሙሉና በከፊል አላፊ አለመሆንን በአእምሮ አለመብሰልን ያሉትን የተለያዩ መከላከያዎችን በውስጡ ይዟል ። ይሁን እንጂ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኛነት የተፈጠረ ለወንጀል አላፊ አለመሆን ለመከላከያነት ሊቀርብ አይችልም ። አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ቁጥሮች ፤ 48 ፤ 49 እና 50

11. አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥሮች ፤ 58 ፤ እና 59
12. ቁጥር 105 እና 107 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ያወዳድሯል ።
13. የዕድሜ ልክ እሥራት ሌላው ዓይነት ጽኑ እሥራት መሆኑ መታወስ አለበት ።
14. ፍራንሲስኮ አልበሬዝ ፤ ናሬቲቭ ኦፍ ዘ ፖርቱጊዝ ኤምባሲ ቱ ኢትዮጵያ ዲዩሪግ ዘ ይርስ 1520—1527 ፤ ገጽ 335 ፤ ኒውዮርክ ፤ 1881 ።
15. ሪቻርድ በርተን ፤ ፈርስት ፉትስቴፕስ ኢን ኢስት አፍሪካ ፤ ገጽ 190 ፤ ለንደን ፤ 1886 ።
16. ማርጀሪ ፐርሐን ፤ ዘ ገቨርንመንት ኦፍ ኢትዮጵያ ፤ ገጽ 194 ፤ ለንደን 1969 ።
17. ሳሙኤል ጐባት ፤ ጆርናል ኦፍ ስሪ ይርስ ሪዚዳንስ ኢን አቢሲኒያ ፤ ገጽ 336 ኒውዮርክ ፤ 1851
18. ፐርሐም ከላይ የተጠቀሰ ፤ ገጽ 148
19. ፓውል ሐርተልሜር ጐልደን ላየን ፤ ገጽ 172 ፤ ለንደን 1965
20. ቁጥር 3 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1923 ።
21. ቁጥር 120—ሀ ። የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
22. ስቴቨን ሎዊንስተን ፤ ዘ ፒናል ሎ ኦፍ ኢትዮጵያ ገጽ 340 ፤ አዲስ አበባ 1965 ።
23. ዣን ግራቨን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ፤ ቅጽ 1 ፤ ቁጥር 2 ገጽ 248 ።
24. ቁጥር 635 እና 637 በተከታታይ ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
25. የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ቁጥር 256 ፤ 445 ፤ 474 እና 479—481 በድንጋጌ ቁጥር 45/1953 ተጨመሩ ። ሌሎች በአብዮታዊው የ1976 ዓ.ም. ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተጨምረዋል ።

26. ቁጥር 120—ሀ ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
27. በአካል ላይ ስለሚፈጸም ቅጣት በምንነጋገርበት ጊዜ ስለማሰቃየት (ቶርቸር) ለማውሳት መዘንጋት አይቀርም ። ምንም እንኳን ቶርቸር የራሱን የሰውን ልጅ ያክል እድሜ ቢኖረውም በአሁኑ ጊዜ በገቢር ላይ መዋሉ የጨመረ ይመስላል ። የተ.መ.ድ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ቶርቸር «የዘመናችን ክስተት» አድርጐ ይመለከተዋል ። አንድ ሰው በተብራራ ሁኔታ ስለቶርቸር ሲያትት «ቶርቸር በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ በ4ኛው ምዕተ— ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ በሠፊው ጥቅም ላይ መዋሉ ከአሳዛኝ ሐቆች አንዱ ነው ።» ይላል ።ይህን አባባል በአንድ ሰለሰብአዊ መብት ጉዳይ አግባብ ባለው ዓለምአቀፋዊ ድርጅት የታተመ ስታስቲክሳዊ መረጃ በመጥቀስ ያጠናክረዋል ። (ታይም)(የ) መጽሔት ፤ አገስት 16 ፤ 1976 (ከዚህም በላይ ቶርቸር ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር አብሮ ስላደገ የተራቀቀ መሣሪያ በመጠቀም በአንድ ግለሰብ አካል ላይ የጭካኔ ጠባሳ ወይም ምልክት ባለመተው ሕይወቱን እስኪሲት ድረስ ማሰቃየት ይቻላል ። ይሁን እንጂ ቶርቸር ከዚህ ጽሑፍ ዓላማ ውጭ ነው ። በመሠረቱ ቶርቸር የቱን ያህል በሠፊው በገቢር ላይ ቢውልም ከጥፋተኛነት ውሳኔ በኋላ የሚጣል ቅጣት ሆኖ በይፋ አይሠራበትም ፤ ነገር ግን ከፍርድ ውጭ ወይም ቅድመ—ፍርድ ላይ አስገድዶ ቃል ለመቀበል ይሠራበታል ። በሰው ልጅ ዕድገት ውስጥ እንደ ባርነትና እንደአብዛኛዎቹ በአካል ላይ የሚፈጸሙ ቅጣቶች ቶርቸርም በታሪክ ብቻ የሚታወስበት ጊዜ ይመጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

28. ሩሽ እና ኪርችሽሜር ፤ ፓንሽመንት ኤንድ ሶሻል ስትራክቸር ፤ ገጽ 21—22 ፤ ነው ዮርክ 1937 ።
29. ቁጥር 116 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1747 ።
30. አፍሪካ (የ) መጽሔት ገጽ 17 ፤ ማርች 1975 ።
31. የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጉዳይ መምሪያ ፤ የተ.መ.ድ ፤ ካፒታል ፓንሽመንት ፤ የተ.መ.ድ ጽሑፍ ኤስ ቲ (ኤስ ኦ ኤ) ኤስ ዲ) 9 ገጽ 28—30 ፤ ኒውዮርክ 1962 ዓ.ም
32. ግራሽን ፤ ከላይ የተጠቀሰ ገጽ 289 ፡
33. የውኒዮርክ ስቴት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ጊዜያዊ አሻሻይ ኮሚሽን ዘገባ (1965) በሉዊንስተን ውስጥ እንደተጠቀሰ ፤ ከላይ የተጠቀሰ ፤ ገጽ 337—38 ።
34. ሉዊንስተን ፤ ከላይ የተጠቀሰ ።
35. ሆልና ግላክ ፤ ክሪሚናል ሎ ኤንድ ኢንፎርስመንት ፤ ገጽ 17 ኒውዮርክ ፤ 1958 ።
36. ሴሊን ፤ ዘ ዴዝ ፒናሊቲ ገጽ 15—77 ፤ ኒውዮርክ ፤ 1959 ።
37. በተ.መ.ድ ዘገባ የተጠቀሰው «የፈላጭ ቆራጭነት አዝማሚያ» በዚህ ምዕተ—ዓመት ለአዲስ ዓለምአቀፋዊ ሥርዓት የሚደረገው ትንቅንቅና ትግል ያስከተለው ሁኔታ ሆኖ ነው መታየት ያለበት። የዓለም ጦርነቶች ፤ « የቆጡ » መንግሥታት ከሥልጣን ላይ መውጣት ፤ አዳዲስ ነፃ መንግሥታት በሶስተኛው ዓለም ብቅ ማለታቸውና የነዚሁ መንግሥታት የፖለቲካ ቁንጮ ሰዎች ለተቀዳጁት አዲስ ነፃነታቸው (ምናልባትም ለግል ሥልጣናቸው) ቀናኢ መሆን ፤ ይህንኑ «የፈላጭ ቆራጭነት አዝማሚያ» ገጽታ ይፋ አወጣው ፡ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ጉዳዮች መምሪያ ፤ ከላይ የተጠቀሰ ።
38. አፍሪካ (የ) መጽሔት ፤ ከላይ የተጠቀሰ ፤ ገጽ 16 ፤
39. ችግሩን ሰፋ አድርገን ስንመለከተው ደግሞ ብዙዎች የአፍሪካ መንግሥታት ይህንኑ የጥቂቱን ነጮች መንግሥት ለተቃዋሚዎቻቸው የላላ ሕግን እንዳያወጣ ለመጠየቅ እንዳይችሉ ከፍተኛ የሞራል ገደብ አለባቸው ፤ ምክንያቱም እነርሱም ቢሆኑ በተቃዋሚዎቻቸው ላይ ተመሳሳይ የጭካኔ ተግባር መፈጸማቸው ሊካድ የማይችል መራራ እውነት ስለሆነ ነው ። አፍሪካ መጋዚን ኤቢድ ገጽ 17
40. የተ.መ.ድ. ጽሑፍ ፤ ኤስ ቲ(ኤስ ኦ ኤ) ኤስ ዲ) 2 ፤ እና ኤን ሐይነር ፤ ሴንቴሲግ ባይ አን አድሚኒ ስትሬቲብ ቦርድ ኢን ሎ ኤንድ ኮንቴምፖራሪ ፕሮብሌምስ ፤ ቅጽ 23 (1958) ።
41. ቁጥር 88 ፤ 102 ፤ 122 እና 123 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
42. ኤን.ኤስ. ቲማሾፍ «ዘ ዳች ፕሪዝን ሲስተም» ኢን ጆርናል ኦፍ ክሪሚናል ሎ ፤ ክሪሚኖሎጂ ኤንድ ፖለቲካል ሳይንስ ቅጽ 48 (1958)
43. ኒውማን ፤ ሰርስ ቡክ አን ፕሮቤሽን ፤ ፓሮል ኤንድ ፓርደንስ ፤ ኒውዮርክ ፤ 1964 ፤ ሬክለስ ፤ ዘ ክራይም ፕሮብሌም ፤ ኒውዮርክ ፤ 1961 ፤ ኔሐራሶል ፤ ዘ ሶቪዬት ጁዲሽል ሲስተም ፤ ሞስኮ 1975 እና ሩሽ እና ኪርችሽሜር ፤ ከላይ የተጠቀሰ ያውዳድሯል ።
44. ኖርቢል ሞሪስ ፤ ዘ ፊውቸር ኦፍ ኢምሪዝንምንት ፤ ችካጐ ፤ 1957 ።
45. ወልተር ሬክለስ ፤ ዘ ክራይም ፕሮብሌም (3ኛ እትም 1961) ።
46. ይህ ጉዳይ ሰብአዊ መብትን የሚመለከት ከፍተኛ ቁም ነገር በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ በሕብረተ ሰብ መሠረታዊ ሕግ ውስጥ ይገኛል ፤ ሕገ መንግሥትም ውስጥም ቦታ ሊሰጠው ይችላል ። ዓለም አቀፋዊው የሰው ልጆች መብት ዲክለራሲዮን (1948) የተለያዩ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ጉዳዮችን ይዟል ።
47. ቁጥር 2(1) ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ 1949 ።
48. ይህ ግምት በከፊል በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ፤ 1754 ቁ. 42 ይገኛል ።
49. ቁጥር 136 (1) ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ፤ 1954 ።
50. ቁጥር 181—196 ፤ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት 1954 ።
51. እነዚህ መብቶች በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት 1954 ፤ በተለያዩ ቁጥሮች ሰፍረው ይገኛሉ ።
52. የተፈጥሮ ዕውቀት የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ አካል መስሎ ሊታይ ይችላል ፤ ይሁንና ይህ ሁልጊዜ ሥራ ላይ ውሎ አያውቅም ። ሌከስ ታሊዮኒ የአንድ ሰው ሚስትና ልጆች ላለበት ዕዳ ተከፋይ በመሆን ለባለገንዘቡ ባሪያ ሆነው እንዲያገለግሉ ለባለገንዘቡ እንዲሰጡ አጠቃላይ በሆነ መንገድ ይደነግጋል ። የታወቀው የሀሞራቢ ሕግ ግንበኛው የገነባው ቤት ተደርምሶ የቤቱን ባለንብረት ልጅ ሲገድል የግንበኛው ልጅ እንዲገደል ደንግጓል ። 4ኛውን ምዕተ— ዓመት በሚመለከት ረገድ በፋሲል ናሆም ውይይት የተደረገበትን የ1957 ዓ.ም. በኤርትራ ስለሽፍቶች የወጣ ሕግ ፤ የኤርትራ ሕግጋት እንቆቅልሽ ፤ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት ቅጽ 9 ቁ.2 ገጽ 258 ይመለከታል ።
53. ይህ ጉዳይ በ1947ኙ የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ 2 «በሕግነቱ መሠረት» ውስጥ ይገኛል ። ይሁን እንጂ በአንድ ጥፋት ሁለት ጊዜ መቅጣት ቢከለከልም ፤ የሕጉን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲባል የተለያዩ ቅጣቶች በአንድ ላይ ተደምረው ይጣላሉ ተብሎ በግልጽ በሕግ የተሰጠውን አያግድም ። ለአጠቃላይ ውይይት ፤ በሶቪዬት ሕብረት ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ ፤ ቢ ቴሬቢሎቭ ዘ. ሶቪዬት ኮርት፤ ፕሮግሬስ አታሚዎች ሞስኮ 1773 ይመለከታል ።

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግና በኢንሹራንስ ፖሊሲ መካከል ያለ አለመጣጣም ፤ በአካል አደጋና በሕይወት ፖሊሲዎች ላይ የተደረገ ልዩ ትኩረት

በበላይነህ ሰዩም *

መ ግ ቢ ያ

ኢንሹራንስ የተለያዩ ስልተ—ምርቶች ውጤት ሲሆን ዓላማውም የአደጋ
ሥጋትን ገንዘብ እየተከፈለው እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ሥጋቱን ከግለ—ሰቦች
ወደ ራሱ ለመቀበል ፈቃደኛ ወደሚሆን ኢንሹራንስ ሰጪ ማስተላለፍ ነው ።
የኢንሹራንስ ውል በአንድ ነገር መሆን ወይም አለመሆን ሁኔታ ላይ የሚመሠ
ረት ሲሆን ኢንሹራንስ ሰጪው በኢንሹራንስ ተቀባዩ ላይ አንድ የተወሰነ ድን
ገተኛ ጥፋት ፤ ጉዳት ወይም ኃላፊነት ሲደርስበት ያንን ለመካስ ይስማማል ።

ኢትዮጵያ ከውጪው ዓለም ጋር ግንኙነቷን ስታጠናክር ብዙ የውጪ የኢ
ንሹራንስ ኩባንያዎች በአገሪቱ ውስጥ ወኪሎቻቸውን በመመደብ እ.ኤ.አ.
1920 ዓ.ም. አካባቢ የአገር ውስጥ የኢንሹራንስ ንግዳቸውን ጀመሩ ። እነዚህም
ወኪሎች የውጪ ዜጎች ሲሆኑ ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ ወደኋላ የዋናዎቹ
ኩባንያዎች ቅርንጫፍ የሆኑ ጽ/ቤቶችን ከፍተዋል ። ቢሆንም እነዚህን የኢን
ሹራንስ ኩባንያዎች የሚመለከቱ ሕጐች የወጡት እ.ኤ.አ. በ1960 ዓ.ም. ነው ።
የኢንሹራንስ ሥራ በአገሪቱ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በሥራ ላይ ከዋሉት ፖሊ
ሲዎች ብዙዎቹ በእንግሊዝ አገር ከሚሠራባቸው ፖሊሲዎች የተገለበጡ በመ
ሆናቸው የእንግሊዝ ሕገ—ፍልስፍና ኢንሹራንስን በሚመለከቱ ሕጐች ላይ
ተጽዕኖ አድርጓል ለማለት ይቻላል ።

የማንኛውም ዘመናዊ የኢንሹራንስ ዓላማ በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ
አደጋ ሲደርስ የዚህን አደጋ ጠንቅ ማካካስ ነው ። በአጠቃላይ ሲታይ ያልታሰበ
ኪሣራን የማከፋፈያና የማቻቻያ ዘዴ ነው ። ኢንሹራንስ የሚገቡ ሰዎች ይደር
ስብናል ብለው የሚገምቱትን የአደጋ ጠንቅ ከራሳቸው ወደሌሎች ትከሻ ያስተ
ላልፋሉ ። ኢንሹራንስ ሰጪዎቹም ክፍያ ስለሚደረግላቸው ኃላፊነቱን በፈቃ
ደኝነት የሚቀበሉ ሲሆን በሕይወት ኢንሹራንስ ጊዜ ለጥገኞቻቸው መጠቀሚያ
የሚሆን ያዘጋጁላቸዋል ወይም እዳ መክፈል ለሚገባቸው ባለገንዘቦች ገንዘባ
ቸውን የሚያገኙበትን መንገድ ይፈጥሩላቸዋል[1] ።

በዘመናዊ የኢንሹራንስ አሠራር መሠረት ኃላፊነት የሚወሰድለት አደጋ
ተለይቶ የታወቀና ሁለቱ ወገኖች የተስማሙበት ሲሆን ኢንሹራንስ ሰጪውም
አደጋው በደረሰ ጊዜ ለሚከፍለው ካሣ ኃላፊነት በመውሰዱ አረቦን (ፒሪሚየም)
ተብሎ የሚጠራ ክፍያ ይደረግለታል ። በፖሊሲው ውስጥ አንዳንድ ሁኔታዎች ፤
መድኖችና ልዩነቶች አሉበት ። እነዚህም የኢንሹራንስ ሰጪውንና የኢንሹራንስ
ገቢውን ግዴታና ኃላፊነት የሚዘረዝሩ ናቸው ። ከዚህም በስተቀር የኢንሹራንስ
ሥራን የሚመለከቱና የኢንሹራንስ ገቢውን መብት በኢንሹራንስ ሰጪው እን
ዳይደፈሩበትና የኢንሹራንስ ሰጪውም ጥቅም አለአግባብ በኢንሹራንስ ገቢው
እንዳይነኩ የሚከላከሉለት ድንጋጌዎች በንግድ ሕግ ውስጥ ተጽፈዋል ።

በንግድ ሕጉ ውስጥ ኢንሹራንስን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች የተረቀቁት የኮንቲኔንታል የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ የሕግ ምሁር በመሆኑ የፈረንሳይና የጣልያን የኢንሹራንስ ሕግ በኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ሕግ ላይ ተጽዕኖ አድርገዋል ። ሆኖም የኢንሹራንስ ጽንሰ ሀሳብና ልምዱም በመሠረቱ የመነጨው በእንግሊዝ አገር በመሆኑ የኮንቲኔንታል የሕግ ባለሙያዎች አመለካከት ላይም እንኳን ቢሆን በዚህ በኩል የእንግሊዝ ሕገ—ፍልስፍና ትልቅ ተጽዕኖ ማድረጉ አልቀረም[2] ። ሌላው እውነታ ደግሞ የኢትዮጵያ የኢንሹራንስ ንግድ አብዛኛውን በሎይድስ (ግዙፉ የእንግሊዝ የኢንሹራንስ ንግድ ድርጅት) ቁጥጥር ሥር ስለነበር ከትንሽ ለውጥ በስተቀር ፖሊሲዎቹ በእንግሊዝ አገር ከሚሠራባቸው የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ ነው ። በነዚህ ፖሊሲዎች ላይ አልፎ አልፎ የተደረጉት ጥቂት ለውጦችም ቢሆኑ በፖሊሲዎቹና በኢንሹራንስ ሕግ መካከል ብዙም መስማማት አላስገኙም ። ይህ አለመጣጣም በተለይም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከዋሉ ወዲህ ከፊተኛውም ይበልጥ ጕልቶ ይታያል[3] ። ይህ ጽሑፍ ከሕጉ ጋር በማይጣጣሙ ስድስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው ። ይኸውም የአረቦን ክፍያን ፤ የይርጋ ጊዜን ፤ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ መደበቅን ፤ የአደጋ ሥጋት መጨመርን ፤ የሕይወት ኢንሹራንስንና ተደራራቢ ኢንሹራንስን የተለየ ትኩረት በመስጠት በሠፊው ይመለከታል ።

1. ስለ አረቦን ክፍያ

የአረቦን ክፍያን በሚመለከት ረገድ ለኢንሹራንስ ገቢው ጥቅም ሲባል ውሉ በድንገት እንዳይቋረጥበት የሚከላከልለት ድንጋጌ በንግድ ሕጉ ውስጥ ሠፍሯል ። በዚህም መሠረት ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን ሳያቋርጥ ክፍያው እስኪደረግ መጠበቅ ያለበት ጊዜ በሕጉ ተወስኗል ። ከዚህ ከተወሰነው ጊዜ በሚቀጥለው አንድ ወር ውስጥ የኢንሹራንሱ ውል እንዲታገድ ብቻ ይደረጋል ። ይህ አሠራር የመንግሥት ፖሊሲ በመሆኑ በሁለቱ ወገኖች ስምምነትም እንኳን ቢሆን ሊሻሻል አይችልም[4] ። በዚህ ፖሊሲ መሠረት የንግድ ሕግ ቁ. 666(2) እንዲህ ይላል ፤ «ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳ ተጠቃሚው ለኢንሹራንስ መግቢያ የሚከፈለውን ገንዘብ በተወሰነው ጊዜ ባለመክፈሉ ብቻ ውሉን ለማፍረስ አይቻልም ። ኢንሹራንስ ሰጪው ገንዘቡ እንዲከፈለው መጠየቅ አለበት ።»

ቢሆንም ቁ. 666 ይህ ድንጋጌ በእንዴት ያሉ ሁኔታዎች ሥራ ላይ እንደሚውል ግልጽ አድርጐ አይናገርም ። ቁ. 666 ተፈጻሚነት የሚኖረው በየጊዜው ለሚከፈል አረቦን ሆኖ የውሉ ጊዜ ከማለቁ በፊት ክፍያው ሲቋረጥ ነው ወይንስ ውሉ ከተቋረጠ በኋላ እድሳት ሲጠይቅ ?

ሀ. በየጊዜው የሚደረግ ክፍያ

ሁለቱ ወገኖች የአረቦን ክፍያ የሚደረገው በየጊዜው ሆኖ በየተወሰነ ቀን ነው ብለው ሊስማሙ ይችላሉ ። ኢንሹራንስ ገቢው ክፍያውን በወቅቱ ሳይከፍል ቢቀር የኢንሹራንሱ ውል ወዲያውኑ አይቋረጥም ፤ ምክንያቱም የውሉ መጨረሻ ጊዜ ባለመድረሱ ኢንሹራንስ ገቢው ክፍያውን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያጠናቅቅ እድል ይሰጠዋል ።

የንግድ ሕግ ቁ. 666 በሥራ ላይ ሊውል የሚችለው ኢንሹራንስ ገቢው በየጊዜው ሊከፍለው የተዋዋለውን ክፍያ የውሉ ጊዜ ከማለቁ በፊት ያቋረጠ

እንደሆነ ይመስላል ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ የአረቦን ክፍያው በየጊዜው በየተወሰነ ቀን የሚከፈል ሲሆን ፤ ክፍያው በዚያ በተወሰነ ቀን ባለመደረጉ ምክንያት ውሉ አይቋረጥም ። ኢንሹራንስ ሰጪው የአረቦን ክፍያው እንዲደረግ ይጠይቃል ፤ ውሉም የሚታገደው ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያውን እንዲፈጸም ከጠየቀ ከአንድ ወር በኋላ ነው ።

ሰ. ውሉን ለማሳደስ የሚደረግ ክፍያ

በልምድ እንደሚታየው ከሆነ የውሉ ማለቂያ ጊዜ ሲደርስ ኢንሹራንስ ሰጪው ለኢንሹራንስ ገቢው የውል ማሳደሻው ክፍያ ጊዜ መቃረቡን የሚያመለክት ማስጠንቀቂያ ይልክለታል ። ይህም በኢንሹራንስ ሰጪው በኩል ውሉ እንዲታደስ እንደቀረበ ሀሳብ ሊቆጠር የሚችል ሲሆን እድሳቱ ያው በፊተኛው ውል አኳኋን ወይም በማስጠንቀቂያው ውስጥ (ለምሳሌም የአረቦኑ ክፍ ማለት ወይም ሌሎች ግዴታዎች ተጨምረውበት ወይም ተቀንሰው) ተሻሽሎ በቀረበ አኳኋን ሊሆን ይችላል ።

በንግድ ሕጉ ውስጥ ኢንሹራንስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የኢንሹራንስ ፖሊሲ እንዴት እንደሚታደስና የእድሳቱም የሕግ ውጤት ምን እንደሆነ ለይተው አይናገሩም ። ታዲያ ሌሎቹን የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በተመሳሳይ ለኢንሹራንስ ውል እድሳትም ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ይቻል ይሆን ?

በንግድ ሕጉ ውስጥ ኢንሹራንስን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች የሚናገሩት የኢንሹራንስ ውል እንዴት ተፈጻሚነት እንደሚኖረው (ቁ. 659) ፤ በየጊዜው መከፈል የነበረበት አረቦን ሲቋረጥ ደግሞ እንዴት ውሉ እንደሚታገድ ፤ አረቦኑ ከተከፈለ በኋላ ደግሞ ታግዶ የነበረውን ውል እንዴት እንደገና ተፈጻሚነት እንደሚኖረውና (ቁ. 666) በተለየ ሁኔታ የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲንእንዴት መልሶ መግዛት እንደሚቻል ነው (ቁ. 710) ። እነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች ሁሉ የሚናገሩት ስለአረቦን ክፍያ እንጂ የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ምን መደረግ እንዳለበት ስላልሆነ ለውሉ እድሳትም ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው አድርጎ መውሰድ ትክክል አይደለም ።

አንድ ውል የሚፈጸመው በስምምነቱ መሠረት ሥራ ላይ ሲውል ወይንም ደግሞ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተፈጻሚነቱ ያበቃል የሚል ግልጽ ስምምነት ሲኖር ነው (ቁ. 1807 ፍትሐ ብሔር ሕግ)። አንዴ ውሉ ከቀረ በኋላ ግን ሁለተኛ ተፈጻሚነት ሊኖረው አይችልም ። ሁለቱ ወገኖች ውሉ የሚታደሰው አረቦን ሲከፈል ነው የሚል ስምምነት ላይ ደርሰው ከሆነ ፤ የአረቦኑ በውሉ መሠረት በተወሰነው ጊዜ ወይም በመጠበቂያው ጊዜ ውስጥ ያለመከፈል ውሉን እንዲፈርስ ያደርገዋል ። በቁ. 666 ኢንሹራንስ ገቢው አረቦኑን በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ባለመክፈሉ ብቻ ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን ሊያቋርጥበት አይችልም የሚለው ድንጋጌ እዚህ ላይ ተፈጻሚነት የለውም ፤ ምክንያቱም ውሉ ራሱ በክፍያው መቋረጥ ምክንያት ፈርሷልና ነው ።

ያም ሆኖ ቁ. 666 ብዙውን ጊዜ የተለያየ አተረጓጎም ተሰጥቶታል ። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እንደታየው ፍ/ቤቶች ግልጽ የሆነውን የሕግ ድንጋጌ በመቀበል ውሉ የሚያበቃው በስምምነት በተወሰነው ቀን ነው የሚለውን የሕጉን አነጋገር እንዳለ በሥራ ላይ አውለውታል ። በሌላ ጊዜ ደግሞ ቁ. 666/3/ንና/4/ን የፈረሰውን ውል እንደገና ተፈጻሚነት እንዲኖረው

በማድረግ ተጠቅመውበታል ። የዚህ ነጥብ አከራካሪነት ከዚህ በታች በተ
ገለጹት ጉዳዮች ውስጥ ጐልቶ ይታያል ። ዲንሳ ለጼሳና ጥቁር አባይ ኢን
ሹራንስ ኩባንያ[5] በተከራከሩበት ጉዳይ ውስጥ ፤ ከሳሽ እ.አ.አ. በኤፕሪል
1969 ዓ. ም. ለግል መኪናው የኢንሹራንስ ውል ከጥቁር ዓባይ የኢንሹራ
ንስ ኩባንያ ጋር ተዋውሎ እስከ ሜይ አንድ 1972 ዓ. ም. ድረስ ውሉን
እያሳደሰ ይቆያል ። የኢንሹራንስ ገቢው መኪና ሜይ 8/1972 ዓ. ም. ማለ
ትም የፊተኛው ውል ቀሪ በሆነ በሰባተኛው ቀን በአደጋ ምክንያት ጉዳት
ይደርስበታል ። ኢንሹራንስ ገቢው ይህንኑ ለኢንሹራንስ ኩባንያው አስ
ታውቆ ካሣ እንዲከፈለው ይጠይቃል ። ኩባንያውም አደጋው የደረሰው
የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ስለሆነ ኃላፊነት የለብኝም ብሎ ጥያቄውን ሳይቀ
በል ይቀራል ። ከሳሽም ጉዳዩን በግልግል ዳኞች ለመጨረስ ጥረት አድርጐ
ስላልተሳካለት በከፍ/ፍ/ቤት ኢንሹራንስ ሰጪውን ድርጅት ይከሰዋል ። ፍ/ቤቱም
አደጋው የደረሰው የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ ስለሆነ ተፈጻሚነት በሌለው
ውል ላይ ተመስርቶ ክስ ማቅረብ አይቻልም ብሎ በማተት ለተከሳሹ ኩባ
ንያ ይፈርዳል ። ጉዳዩ በይግባኝ ጠ/ፍ/ቤት ደርሶ ፍርዱ እንዲሻር ተደርጓል ።
ፍ/ቤቱ በዚሁ ጊዜ በሰጠው ሐተታ ላይ ምንም እንኳን በውሉ መሠረት የተወ
ሰነው ጊዜ ቢያልቅም ኢንሹራንስ ሰጪው በመጀመሪያ የኢንሹራንሱ ጊዜ ማለ
ቁን አስታውቆ ውሉን ቀሪ ከማድረጉ በፊት ሌላ አንድ ወር የመጠበቅ ሕጋዊ
ግዴታ ነበረበት ብሏል (ቁ. 666/3/ና/4) ። ፍ/ቤቱ ሐተታውን በመቀጠል
የመጀመሪያው ውል ካለቀ ገና አንደኛው ሳምንት ማለፉ ስለሆነና ክፍያ እንዲ
ደረግ ከተጠየቀበት ጊዜ አንስቶ አንድ ወር የመጠበቂያ ጊዜ ስለነበረ ከሳሽ የመ
ጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው ብሏል ።

ይህ ውሳኔ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ለዚህ ዓይነት አተረጓጐም መንገድ ይከፍ
ታል የሚለው ፍራቻ በኢንሹራንስ ሰጪዎችና በሕግ ባለሙያዎች ዘንድ ትልቅ
ሥጋት ፈጥሮ ነበር ። በነዚህ ሰዎች አስተያየት ውሳኔው የኢንሹራንስ ውሎችን
ዋጋ የሚያሳጣና ውሉ ካበቃም በኋላ ሊኖረው የሚገባውን ውጤት የሚለውጥ
ነው ።

በፍት/ሕ/ቁ. 1806 መሠረት አንድ የውል ግዴታ በውሉ መሠረት ከተፈ
ጸመ ቀሪ ይሆናል ። በኢንሹራንስ ውል ከሆነ ደግሞ ውሉ ተፈጻሚነት
የሚኖረው በስምምነት እስከተወሰነው ቀን ድረስ ብቻ እንጂ ከዚያ በኋላ
አይደለም ።

በዋኬኔ ፈልዳሶና በጥቊር ዓባይ ኢንሹራንስ[6] ክርክር አቶ ዋኬኔ ለሱቁ ጁን
13/1970 ዓ. ም. የእሳትና የመብረቅ ኢንሹራንስ ገባለት ። ሱቁ ባልታወቀ
ምክንያት ጁን 13/1971 ዓ. ም. በእሳት ይቃጠላል ። በውስጡም ከነበሩት
ዕቃዎች መካከል አብዛኞቹ ይጋያሉ ። በቃጠሎው ማግስት ኢንሹራንስ ሰጪው
የአደጋ ማስታወቂያ ይደርሰዋል ። ሆኖም ኢንሹራንስ ሰጪው አደጋው
የደረሰው ውሉ ቀሪ ከሆነ በኋላ ስለሆነ ኃላፊነቱ አይመለከተኝም ይላል ።

ለዚህም የኢንሹራንሱ ውል ተፈጻሚነት ሊኖረው ይችል የነበረው በኢን
ሹራንስ ፖሊሲ ውስጥ እንደተጠቀሰው ከጁን 13/1970 ዓ. ም. እስከ ጁን
13/1771 ዓ.ም. አስር ሰዓት ድረስ ሲሆን አደጋው ግን የደረሰው ጁን 13/1971
ዓ. ም. ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ነው ። በከፍ/ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት
ኢንሹራንስ ገቢው ከአደጋው ጥቂት ሰዓቶች ቀደም ብሎ ዕቃውን ከሱቁ

ውስጥ ማውጣቱ ስለተደረሰበት ቃጠሎው ካሣ ለማግኘት ሲባል ሆን ብሎ በከሳሹ የተደረገ ስለሆነ ካሣ መጠየቅ አይችልም ሲል ወሰነ ። ጠ/ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ሰሚነት ተመልክቶ ሁለቱን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በሌላ ምክንያት ለተከሳሹ ኩባንያ ፈረደ‚ል ። ፍ/ቤቱ ትኩረት የሰጠው ጭብጥ አንድ የኢንሹራንስ ውል የውሉ ጊዜ አልቆ ቀሪ ከሆነ በኋላ ካሣ ሊጠየቅ በት ይችላል ወይንስ አይችልም የሚለው ነበር ። አደጋው የደረሰው ጁን 13/1971 ዓ.ም. ከምሽቱ በአንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን በኢንሹራንስ ውል የተሸፈነው ጊዜ ደግሞ እስከ ጁን 13/1971 ዓ.ም. ከሰዓት በኋላ አስር ሰዓት ድረስ ብቻ ነው ። የኢንሹራንሱ ውል ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል[7] ። «በዚህ የኢንሹራስ ውል ውስጥ እንደራሱ እንደውሉ የሚቆጠሩ የተጻፉት ወይም ተጨምረው የገቡ ድንጋጌዎችና ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ውል ሠንጠረዥ ውስጥ የተጠቀሰው ንብረት ወይም ከፊሉ እረቦን ከተከፈለ በኋላ በሠንጠረዥ ውስጥ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ የመጨረሻ ዕለት ከቀኑ አስር ሰዓት በፊት ወይንም ከዚያ በኋላ ከሆነ ደግሞ ኢንሹራንስ ገቢው የውል ማሳደሻ አረቦን ከፍሎ ኮርፖሬሽኑም ተቀብሎት ከሆነ ይህ ንብረት በእሳት ወይንም በመብረቅ አደጋ ቢወድም ወይንም ጉዳት ቢደርስበት ኮርፖሬሽኑ ለኢንሹራንስ ገቢው አደጋው በደረሰ ዕለት ንብረቱ ያወጣው የነበረውን ዋጋ ወይንም በደረሰው ጉዳት መጠን ክፍያ ያደርጋል ወይንም በራሱ ምርጫ ንብረቱን በሙሉ ወይንም በከፊል መልሶ ያቋቁማል ወይንም ይተካል ።»

ከዚህ በላይ ባለው ሁኔታ መሠረት ጠቅላይ ፍ/ቤት ቃጠሎው የደረሰው በኢንሹራንስ ውል የተሸፈነው ጊዜ ካበቃ በኋላ ስለሆነ ኢንሹራንስ ገቢው በውሉ መሠረት ካሣ ሊጠይቅ አይችልም በማለት ወሰነ ።

2. ስለ ይርጋ

ሌላው ከዚሁ ጋር አግባብ ያለውና መመርመር ያለበት ጉዳይ የይርጋ ነገር ነው ። ይህን ድንጋጌ በንግድ ሕጉ ውስጥ መጨመር ያስፈለገበት ምክንያት በኢንሹራንስ ውል ውስጥ የሚጨመሩ የውል ቃሎች የኢንሹራንስ ገቢዎች መብት እንዳይገፉ ለመከላከል ነው ። የድንገተኛ አደጋ ኢንሹራንስ ውል ሁኔታ ቁ. 4 የሚከተለውን ይላል ፤

> « … … … ኮርፖሬሽኑ በዚህ ውል ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት ካሣ ሲጠየቅ ጥያቄውን ካልተቀበለና ይህ ጥያቄ ተቀባይነትን ባጣ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በዚህ ውል ውስጥ በተደነገገው መሠረት ጉዳዩ ለግልግል ካልቀረበ ጥያቄው እንደተተወ ተቆጥሮ ከዚያ በኋላ በዚህ ውል ላይ የተመሠረተ ማንኛውም ዓይነት የካሣ ጥያቄ አያነሳም[9] ።»

ይህ ሁኔታ (ኮንዲሽን) የኢትዮጵያን የሕግ ድንጋጌዎች እንዲከተሉ ምንም ጥረት ሳይደረግ በእንግሊዝ አገር ከሚሠራባቸው የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች በቀጥታ ለተገለበጡ ሁኔታዎች እንደ ጥሩ ምሳሌ ያገለግላል ።

በንግድ ሕግ ቁ. 674/1/[10] መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንሹራንስን የሚመለከት ክስ የማቅረቢያው የጊዜ ገደብ አደጋው ከደረሰበት ወይንም ተዋዋዮቹ ወገኖች የአደጋውን መድረስ ካወቁበት ጊዜ አንስቶ ሁለት ዓመት ነው ። እንዲህ ማለት ግን የይርጋው ጊዜ በመካከሉ ቢቋረጥም የጊዜ ገደቡ ሁለት ዓመት እንደሆነ ይቀራል ማለት አይደለም ። በፍት/ሕግ ቁ. 1852/1/ መሠረት የይርጋው

ጊዜ በተቋረጠ ቁጥር አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር ይጀምራል ። የኢንሹራንሱ ውል ስለይርጋው ጊዜ መቋረጥ ምንም ሳይናገር የጊዜ ገደቡን ብቻ ወደ ስድስት ወራት ዝቅ ያደርገዋል ። በድንገተኛ አደጋ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ.3 ውስጥ የአደጋው ማስታወቂያ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለኮርፖሬሽኑ ካልደረሰ ኮርፖሬሽኑ ለማንኛውም የካሣ ጥያቄ ኃላፊነት እንደሌለበት ይገልጻል ። ይህን ማለት አደጋው ስለመድረሱ ከሶስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የአደጋው ማስታወቂያ ለመድን ድርጅቱ መድረስ አለበት ፤ ያለዚያ ድርጅቱ በኃላፊነት አልጠየቅም ይላል ።

በንግድ ሕግ ቁ. 670 መሠረት የኢንሹራንስ ገቢው ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ኢንሹራንስ ሰጪውን በኃላፊነት ሊያስጠይቅ የሚችል አደጋ ሲደርስ ወዲያውኑ አደጋው መድረሱን እንዳወቀ ወይንም በአምስት ቀናት ውስጥ ለኢንሹራንስ ሰጪው ያስታውቃል ይላል ። የንግድ ሕግ ቁ. 670 የአደጋ ማስታወቂያውን ጊዜ በኢንሹራንስ ውል ውስጥ ከተሰጠው ጊዜ ይልቅ ያሳንሰዋል ። በሌላ በኩል ደግሞ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ድንጋጌና የንግድ ሕግ ቁ. 670 በንግድ ሕግ ቁ. 674 ከተሰጠው የይርጋ ጊዜ ጋር ይቃረናሉ ።

በቁ. 674/1/ መሠረት ኢንሹራንስ ሰጪውን ለአደጋው ተጠያቂ ማድረግ የሚቻለው አደጋው በደረሰ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው ። ከዚህም ይልቅ በቁ. 674/3/ ሥር እንደተጻፈው ተዋዋይ ወገኖች በፈቃዳቸው ይህንን የጊዜ ገደብ ከዚህ አሳንሰው መስማማት እንደማይችሉ በግልጽ የተደነገገ ሲሆን ይህም ሕግ አውጪው ለዚህ ጉዳይ ምን ያህል ክብደት እንደሰጠው ያመለክታል ። ይህን የይርጋንና የአደጋ ማስታወቂያ ጊዜን የሚመለከት አንድ ፍ/ቤት ደርሶ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ አለ ። ይኸውም ወ/ሮ ቅድስት ሚቸል ኮትስ ኩባንያን የከሰሱበት ነው ። አቶ ጌታሁን የተባሉ የወ/ሮ ቅድስት ባል ከኩባንያው የኢን ሹራንስ ክፍል የአደጋ ኢንሹራንስ ፖሊሲ ይገዛሉ ። በውሉ ስምምነት መሠረት ኢንሹራንስ ገቢው ቢሞቱ ወይንም አደጋ ቢደርስባቸው 40'000 ብር ካሣ ይከፍላቸዋል ። አቶ ጌታሁን መኪና እየነዱ ወደ ጂማ ሲሄዱ ጃንዋሪ 5/1967 ዓ.ም. ከባድ አደጋ ስላጋጠማቸው በዚሁ ጠንቅ ጃንዋሪ 23/1967 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ይለያሉ ። ስለአደጋው መድረስና ሟችም የሞቱት በዚሁ የመኪና አደጋ ጠንቅ መሆኑን የሚያመለክት ማስረጃ ጨምሮ የአደጋ ማስታወቂያው ጃንዋሪ 26/1967 ዓ.ም. ለኩባንያው ይደርሳል ። ኩባንያው ግን በፖሊሲው ሁኔታ ቁ.2 መሠረት የጽሑፍ ማስታወቂያው አደጋው በደረሰ ወይንም ሕመሙ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በ14 ቀናት ውስጥ ለኩባንያው መድረስ ስለሚኖርበትና ይህ ደግሞ ባለ መደረጉ ኃላፊነቱን እንደማይቀበል ገለጸ ። ባሁኑ ጉዳይ ውስጥ የአደጋው ማስ ታወቂያ የደረሰው በ21ኛው ቀን ላይ ነበር ። ይህም ማለት ከጃንዋሪ 5 ቀን 1967 ዓ.ም. እስከ ጃንዋሪ 26 ቀን 1967 ዓ.ም. ድረስ የነበረው ጊዜ ማለት ነው ። ከፍተኛው ፍ/ቤት ማስታወቂያው በ14 ቀናት ውስጥ መድረስ አለበት ተብሎ በፖሊሲው ላይ የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ሁኔታ ላይ ትኩረት በማድረግ ለተከሳሹ ፈረደ ። ጉዳዩ በይግባኝ ጠ/ፍ/ቤት ደርሶ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ይህ ሁኔታ የተደነገገው በአደጋ ምክንያት ለቆሰሉ ወይንም ለታመሙ ሰዎች እንጂ በአደ ጋው ለሞቱ ሰዎች አይሠራም በማለት ወሰናል ። ሆኖም ሁለቱም ፍ/ቤቶች ቢሆኑ ውሳኔያቸውን የሰጡት በትክክለኛው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት አይደለም ። ሌላው ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያለውና በሕጉና በተለያዩ ፖሊ ሲዎች መካከል ያሉትን ግልጽ ልዩነቶች የሚያመለክተው በመካነ እየሱስ ቤተ

ክርስቲያንና በኢት/መድን ድርጅት መካከል የተነሳው ክርክር ነበር[110] ። በሞ ራኒ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያና (ውል ተቀባይ) በአፍሪካ አንድነት ኢን ሹራንስ መካከል ዲሴምበር 16/74 ውል ተፈረመ ። ይኸውም ውል የሥራ ክን ውን ዋስትና (ፐርፎርማንስ ቦንድ) ሲሆን የኢንሹራንስ ድርጅቱ ለኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ውል ተቀባዩ በውሉ መሠረት ግዴታውን ባይወጣ እስከ 200,000 ብር ለመክፈል ዋስትና የገባበት ነው ።

ውል ተቀባይ የሕንጻውን ሥራ ከጀመረ በኋላ በድንገት ኢትዮጵያን ለቅቆ በመሄዱ የሕንጻው ሥራ እንደተቋረጠ ለጥቂት ወራት ቆየ ። ውል ተቀባዩ የጀ መረውን ሥራ ተመልሶ እንደማያጠናቅቅ አሠሪው አንዳንድ ፍንጮችን ካገኘ በኋላ ይህንኑ ለኢንሹራንስ ኩባንያው አስታውቆ በሥራው መቋረጥ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት እንዲካስ ጠየቀ ። የመድን ድርጅቱም በሚከተሉት ምክን ያቶች ኃላፊነቱን እንደማይቀበል ለግልግል ኮሚቴው አስታወቀ ፤

ሀ. ውል ሰጪው በፖሊሲ ቁ. 1 መሠረት በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለሁኔታው ለኢ ንሹራንስ ድርጅቱ ማስታወቂያ አልላከም ። ከዚህም ሌላ ውል ተቀባዩ አገ ሪቱን ለቅቆ የወጣው ከጁን 1975 ዓ.ም. በፊት ሲሆን ማስታወቂያው ግን ለኢንሹራንስ ኩባንያው የደረሰው በኖቬምበር 1976 ዓ.ም. መሆኑን አን ስቶ ኩባንያው ተከራከረ ።

ለ. ውል ሰጪ በፖሊሲው ቁ.4 መሠረት የጉዳዩ የይርጋ ጊዜ ውል ተቀባይ በውሉ መሠረት ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረበት ጊዜ አንስቶ እስከ 12ኛው ወር ብቻ በመሆኑና ግን አሁን ይህ ክስ የቀረበው ከሳሽ ስለሁኔታው ባወቀ በ16ኛው ወር በመሆኑ ልጠየቅ አይገባም አለ ።
እዚህ ላይ ሁለት ሊታረቁ የማይችሉ ሀሳቦች ይነሳሉ ።

1. በሥራ ክንውን ዋስትና ፖሊሲ ድንጋጌ ቁ. 1 መሠረት ማንኛውም የኢን ሹራንስ ገቢ ጉዳት የሚያስከትል ሁኔታ መድረሱን ሲያውቅ ወዲያውኑ ለድርጅቱ ማሳወቅ አለበት ። የአደጋ ፖሊሲ ቁ.2 (በወ/ሮ ቅድስትና በሚ ቸል ኮትስ ክርክር ውስጥ እንዳየነው) የካሣ ጥያቄ ሊነሳ የሚችልበትን ጊዜ በግ ልጽ ይናገራል ። ይኸውም አደጋው በደረሰ ወይንም ሕመሙ በጀመረ በ14 ቀናት ውስጥ ማስታወቂያው በጽሑፍ ለኢንሹራንስ ድርጅት መድረስ አለበት የሚለው ነው ። አንዱ የኢንሹራንስ ውል ድንጋጌ ማስታወቂያው በአጭር ጊዜ ውስጥ መድረስ አለበት ሲል ፤ ሌላው ደግሞ ማስታወቂያው በስንት ጊዜ ውስጥ መድረስ እንደሚገባው ቁርጥ አድርጐ ይደነግጋል ። በፊተኛው ሁኔታ «በአጭር ጊዜ ውስጥ» የሚለው አነጋገር የተለያየ አተ ረጓጐም ሊያስነሳ የሚችል ነው ። ይህ እንግዲህ በተለያዩ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች መካከል እንኳን የማይጣጣሙ ድንጋጌዎች መኖራቸውን ለማ ሳየት የቀረበ ነው ። ይህም ማለት አንዳንዶቹ ፖሊሲዎች የሚሰጡት የጊዜ ገደብ አሻሚ ሲሆን የአንዳንዶቹ ደግሞ ቁርጥ ያለ ነው ።

2. በሥራ ክንውን ዋስትና ፖሊሲ ሁኔታ ቁ.4 ውስጥ እንደተጻፈው በውሉ ላይ የተመሠረተ የክፍያ ክስ ለክሱ ምክንያት የሆነው ሁኔታ መኖሩ በታወቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ካልተጀመረ በስተቀር በድርጅቱ ላይ ሊቀርብ አይችልም ።

ይህ ድንጋጌ በኢንሹራንስ ውል ላይ የተመሠረተ ክስ ሊቀርብ የሚችለው ፤ ለክሱ መነሻ የሆነው ነገር በተፈጠረ በሁለት ዓመታት ውስጥ ነው ተብሎ

በንግድ ሕግ ቁ. 674/1/ የተወሰነውን የይርጋ ጊዜ የሚጻረር ነው ። ይህ ደግሞ ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር እንዲስማሙ ለማድረግ ምንም የማሻሻያ ጥረት ሳይደረግባቸው በእንግሊዝ አገር የሚሠራባቸው ፖሊሲዎች እዚህ በሥራ ላይ የመዋላቸው አንዱ ሌላ ምሳሌ ነው ።

3. እውነተኛ ነገሮችን ስለመሸሸግ

የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አስፈላጊ ነገሮች ኢንሹራንስ በገባው ሰው ስለሚሸሸጉበትም ሁኔታ መጠነኛ ድንጋጌዎች ይዟል[11] ። የኢትዮጵያ ሕግ ምን ጊዜም ቢሆን «ከፍተኛ ቅን ልቦና» የሚለውን መርህ ይከተላል ። ይህ ከፍተኛ ቅን ልቦና መኖር ያለበት አደጋው ከመድረሱ ቦፊት ብቻ ሳይሆን ከደረሰም በኋላ ነው ። በመሠረቱ አደጋ በመድረሱ ጉዳት የደረሰበት አንድ ኢንሹራንስ ገቢ በውሉ መሠረት እንዲፈጸምለት ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ውሉ በተፈጸመ በት (ፖሊሲው በተጻፈበት) ጊዜ የአደጋውን ባሕርይ ወይም መጠን የሚያሳየ ውን ወይም ውሉን ከመፈጸም ያግደው የነበረውን ወይም መክፈል ይገባው የነበ ረውን የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መጠን ያፋልስ የነበረውን ማንኛውንም ነገር በትክክልና በሙሉ አልገለጽክም የሚል መከላከያ ሊቀርብበት እንደሚችል መገንዘብ አለበት ።

በአጠቃላይ አነጋገር በኢትዮጵያ ሕግ ቅን ልቡናን መጣስ በውሉ መጽናት ላይ በሚያስከትለው የተለያየ ውጤት መሠረት በሶስት ተመድቧል ። እነርሱም ፤

ሀ. <u>መሸሸግ፡</u>— ይህ እያወቁ እውነቱን ነገር በመሸሸግ የሚፈጸመውን የቅን ልቡና መጣስ ይመለከታል ።

ለ. <u>በቅን ልቡና ትክክል ያልሆነ ነገር መናገር፡</u>— ይህ ሆን ተብሎ ሳይሆን ወይም ያለአንዳች አጭበርባሪነት የሚነገረውን ትክክለኛ ያልሆነ አባባል ይመለከታል ።

ሐ. <u>አታላይነት</u> ፤ ይህ አንድ ነገር ሀሰት መሆኑን እያወቁ ሀሰቱን እውነት አስ መስሎ ማቅረብን ይመለከታል ። ነገር ግን ጉዳዩን ለመመርመር ሲባል ባለመጠንቀቅ የተነገረው ሀሰት ነገር አይደለም[12]

በንግድ ሕግ ቁጥር 668/1/ መሠረት ኢንሹራንስ የገባው ሰው እያወቀ እውነቱን ነገር የሸሸገ ወይም የሀሰት መግለጫ የሰጠ እንደሆነ ፤ እውነተኛው ነገር ተገልጾለት ቢሆን ኖሮ ኢንሹራንስ ሰጪው ይህን ውል አይዋዋልም ፤ ወይም ተጠቃሚው ከፍ ያለ ገንዘብ እንዲከፍል የሚያደርግበት ውል ይዋዋል ነበር እስከሚያሰኝ ድረስ እነዚህ የተሸሸጉ ነገሮች ወይም በሀሰት የተሰጡ መግ ለጫዎች የኢንሹራንስ ሰጪውን የአደጋውን አስተያየት ለውጠውበት እንደሆነ ፤ ውሉ ፍርስ ይሆናል ። ነገር ግን ሕጉ የሀሰት መግለጫው ሆን ተብሎ የማይደረ ግበትን ሁኔታም ይደነግጋል ። መሸሸጉ ወይም የሀሰት መግለጫው በቅን ልቡና የተደረገ እንደሆነና የታወቀውም አደጋው ከመድረሱ በፊት የሆነ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው ሁለት ምርጫ ተሰጥቶታል ፤ ይኸውም ለኢንሹራንስ ገቢው ማስታወቂያ ከሰጠ ከአንድ ወር በኋላ ውሉን የማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያው ገንዘብ ተጨምሮ ውሉ እንዲቀጥል የማድረግ[13]። ነገር ግን የተሸሸ ገው ነገር የታወቀው አደጋው ከደረሰ በኋላ የሆነ እንደሆነ ለኢንሹራንስ ገቢው

የሚከፈለው ገንዘብ መጠን ይቀነሳል በማለት ሕጉ ይደነግጋል[14] ። ሆኖም በፖሊሲው ላይ የተገለጸው ሁኔታ በሕጉ ከተደነገገው ለየት ያለ አዝማሚያ ይታይበታል ። በአጠቃላይ አደጋ ፖሊሲ ቁጥር 8 የተጠቀሰው ሁኔታ እንዲህ ይላል ፤ « ... ... ኢንሹራንስ ገቢው አስቀድሞ በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም ይህን ኢንሹራንስ በሚያድስበት ጊዜ በሰጠው ቃል ወይም ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ ጉዳይ በሚቀርብ ክርክር ሀሰቱን እውነት አስመስሎ ያቀረበ እን ደሆነ ወይም ሆነ ብሎ ሁኔታውን አጋንኖ ያቀረበ እንደሆነ ወይም ሆነ ብሎ መግለጽ ይገባው የነበረውን ነገር ሳይገልጽ የቀረ እንደሆነ ፖሊሲው ዋጋ ከማ ጣቱም በላይ የተከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ አይመለስም[15]። » በመሆኑም እንደ ፖሊሲው አባባል በኢንሹራንስ ገቢው ሊገለጽ የሚገባው ነገር የተሸሸገ ወይም የሀሰት መግለጫ የተደረገ እንደሆነ ፖሊሲውን ዋጋ ያሳጣዋል ፤ ኢንሹራንስ ገቢው የከፈለውን የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብም ያጣል ። በአ ጠቃላይ አነጋገር ፖሊሲውና የሕጉ ድንጋጌዎች ኢንሹራንስ ገቢው ሊደርስ የሚ ችለውን አደጋ ባሕርይና መጠን የሚያሳየውን ውል ከመዋዋል ሊያግድ የሚ ችለውን ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ተመን ሊለውጥ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር በትክክል መግለጽ እንዳለበት በኢንሹራንስ ገቢው ላይ ግዴታ ይጥልበታል።ይሁን እንጂ ይህ የመሸሸግ ወይም አንድን ነገር አለመግለጽ በሚያ ስከትለው ውጤት ረገድ በንግድ ሕግና በፖሊሲው መካከል የሚታዩትን ዋና ዋና ልዩነቶች ሊሰውራቸው አይችልም ። ባጭሩ እንደሚከተለው ማሳየት ይቻ ላል ።

<u>በኢንሹራንስ ገቢው እውነተኛ የሆነው ነገር ሲሸሸግ በሕጉና በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት</u>

ሀ. 1. መሸሸጉ ሆነ ተብሎ በሚደረግበት ጊዜ	<u>በንግድ ሕግ የሚያስከትለው ውጤት</u> ፤ ውሉ በኢንሹራንስ ሰጪው ይቋ ረጣል ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው የኢንሹራንስ መግቢያውን ገን ዘብ ያስቀራል ።
2. መሸሸጉ በቅን ልቡና በሚሆ ንበት ጊዜ	
ሀ/ መሸሸጉ ከአደጋው በፊት በኢንሹራንስ ሰጪው ሲታ ወቅ	ከአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በኋላ ውሉን ማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገን ዘብ መጨመርና ውሉን መቀ ጠል ።
ለ/ መሸሸጉ ከአደጋው በኋላ ሲታወቅ	ሊደርስ የሚችለውን አደጋ በሙሉና በትክክል ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ለኢንሹራንስ ሊከ ፈል ይገባ የነበረውን በማመ ዛዘን ኪሣራውን በዚሁ መጠን መቀነስ ።

ለ.	በጥያቄ የሀሰት መግለጫ ማቅረብ ፤ ሆነ ተብሎ የተጋነነ ነገር ማቅረብ ወይም ሆነ ብሎ መተው (አለማድረግ)	<u>በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት</u> ፖሊሲው ዋጋ ያጣል ፤ የኢንሹራንስ መግቢያው ገንዘብ ለኢንሹራንስ ሰጪው ይቀራል ።

በሕጉና በፖሊሲው መካከል ያለውን የውጤት ልዩነት ማስተዋል ይቻላል ። እንደ ፖሊሲው አባባል ማናቸውም ሆነ ተብሎ የተደረገ ወይም ሆነ ተብሎ ያል ተደረገ የሀሰት መግለጫ ፖሊሲውን ዋጋ ያሳጣዋል ፤ በሌላ በኩል ሕጉ ሆነ ተብሎ የተደረገ መሸሸግና ሆነ ተብሎ ያልተደረገ የሀሰት መግለጫ በማለት ውጤቱን በሁለት ይከፍለዋል። መሸሸጉ ሆነ ተብሎ የተደረገ እንደሆነ ውሉ ይፈርሳል ፤ መሸሸጉ የተደረገው በቅንልቡና ከሆነና ይኸው የተገለጸው አደጋው ከመድረሱ በፊት ከሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ሁለት ምርጫ አለው ፤ ይኸውም ከአንድ ወር ማስ ታወቂያ በኋላ ውሉን ማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ጨምሮ ውሉ እንዲቀጥል ማድረግ በማለት ሕጉ ይደነግጋል ። ነገር ግን መሸሸጉ የታወቀው አደጋው ከደረሰ በኋላ ከሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ለኪሳራው የሚከፍለውን ገንዘብ በዚያው መጠን ሊቀንስ ይችላል ። የፍትአብሔር ሕግ ቁጥር 1678 ሁለት ወገኖች የሚዋዋሉት ውል ከሕጉ ዓላማ እስካልራቀና የሕጉን አስገዳጅ ድንጋጌዎች እስካልጣሰ ድረስ ማናቸውንም ውል ለመዋዋል ነፃነት አላቸው በማለት ይደነግጋል ። ይህን ከዚህ ላይ ያነሳነው ፤ ምንም እንኳን ኢንሹራንስ ገቢውና ኢንሹራንስ ሰጪው በማናቸውም ዓይነት ሁኔታ ለመዋዋል ነፃነት ቢኖራቸውም ውላቸው ከሕጉ መንፈስ ሊርቅ ወይም ከሕጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች ውጪ ሊሆን የማይችል መሆኑን ለማሳየት ነው ።

ማክጊልቭሬይ[16] እንዲህ ይላል ፤ «አንድ ነገር አስፈላጊ ነገር ነው ፤ መገለጽ ነበረበት ፤ ብሎ ለመወሰን ኢንሹራንስ ሰጪዎች እውነተኛው ነገር ተገልጾ ቢሆን ይህ የአደጋውን እስተያየት ይለውጥባቸው እንደነበረ ማረጋገጥ አያስፈልጋቸውም ፤ እውነተኛው ነገር ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ልምድ ያላቸው ኢንሹራንስ ሰጪዎች ጉዳዩን ላለመቀበል ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ለመጨመር ይገፋፋቸው ነበር ብሎ ማረጋገጥ በቂነው። « ኢንሹራንስ ገቢው ኪሣራ እንዲከፈለው በሚጠይቅበት ጊዜና ኢንሹራንስ ሰጪው መሸሸግን በማንሳት በሚቃወምበት ጊዜ ኢንሹራንስ ሰጪው የሚከተሉትን ሁኔታዎች የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት ፤

ሀ/ እውነተኛው ነገር ተሸሽጐ እንደነበር ወይም የሀሰት መግለጫ ተሰጥቶ እንደነበር ፤

ለ/ የተባለው እውነተኛ ነገር አስፈላጊ እንደነበር ፤

3. የተባለው እውነተኛ ነገር አስፈላጊ ለመሆኑና የሐሰት መግለጫ ተሰጥቶ እንደነበር ፍርድ ቤቱ እንዴት እርግጠኛ ሊሆን ይችላል? የኢትዮጵያን የንግድ ሕግ ሕገ—ፍልስፍና አመጣጥ ስንመረምር ከሚከተሉት አንዱ እውነተኛ ነገር (አስፈላጊ ነገር) ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን[17] ።

ሀ. የአደጋውን ባሕርይ ወይም መጠን ሊያሳይ የሚችል ነገር ፤ ወይም

ለ. ውሉን ከመዋዋል ሊያግድ የሚችል ነገር ፤ ወይም

ሐ· የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ መጠን ሊያቃውስ የሚችል ነገር ። በአጠቃላይ የአንድ ነገር አስፈላጊ መሆን የፍሬ ነገር ጥያቄ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ ከሆነ ውሳኔ ላይ ይደርስ ዘንድ መረጋገጥ ያለበት ልዩ ሙያ ባላቸው ሰዎች ከመሆኑም በላይ ፤ ልምድ ያለው ኢንሹራንስ ሰጪ በሀሰት በተሰጠው መግለጫ ወይም በተሸሸገው እውነተኛ ነገር ምክንያት ስለአደጋው ይኖረው የነበረው አስተያየት ልዩ ይሆን እንደነበር ማረጋገጥ አለበት[18] ። በከሳሽ በወይዘሮ ቅድስት እና በተከሳሽ በሚቸል ኮትስ ኩባንያ ጉዳይ ላይ ፤ ተከሳሽ ያነሰው መከላከያ ኢንሹራንስ ገቢዋ የፖሊሲውን ፎርም በሚሞሉበት ጊዜ እውነተኛውን ነገር ሸሽገዋል ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው እውነተኛው ነገር ቢገለጽለት ኖሮ ውሉን ያፈርሰው ነበር ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ መጠን ያሳድገው ነበር የሚል ነበር ። ይሁን እንጂ ከሳሽ ሳይገልጽ የቀረው ነገር አስፈላጊ ነገር አልነበረም ፤ የውሉን መሠረት ሊያናጋው አይችልም ነበር ፤ ብለው ከመከራከራቸው በቀር ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ እንደ ጭብጥ አንስቶ ውሳኔ አልሰጠበትም ። በመሆኑም የፍርድ ቤቱን አቋም ከዚህ ላይ መናገር አይቻልም[19] ።

4. የአደጋው እየከበደ መሄድ

የንግድ ሕግ ቁ. 669 ስለ አደጋ እየከበደ መሄድ ይደነግጋል ። እንዲህ ይላል ፤ «ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄድ ውሉ በተደረገ ጊዜ አደጋው በዚህ ሁኔታ እየከበደ የሚሄድ መሆኑ ቢታወቅ ኖሮ ኢንሹራንስ ሰጪው የማይዋዋል መሆኑ ወይም ቢዋዋልም ኢንሹራንስ ገቢውን ከፍ ያለ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ አስከፍሎ ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ሆኖ ሲገኝ ፤ ኢንሹራንስ በገባው ሰው ምክንያት ሲሆን አደጋው እየጨመረ እንዲሄድ ያደረገው ሁኔታ በተደረገ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ወይም ይህን ድርጊት ኢንሹራንስ ገቢው ካወቀበት ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ኢንሹራንስ ገቢው ለኢንሹራንስ ሰጪው ማስታወቅ አለበት » ። ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን ለማፍረስ ወይም ለኢንሹራንስ የሚከፈለው ገንዘብ ከፍ እንዲልና ውሉ እንደጸና እንዲቆይ ለማድረግ ይችላል ። ይሁን እንጂ በፖሊሲው የተሰጠው የአደጋን መክበድ ያለማስታወቅ ውጤት በሕጉ ከተደነገገው በጭራሽ የተለየ ነው ። የአካል ጉዳት አደጋ ፖሊሲ ፤ ንዑስ ክፍል 3 እንዲህ ይላል ፤ «ኢንሹራንስ ገቢው ድርጅቱን ሳያስታውቅ ፤ ፈቃድ ሳያስገኝና በድርጅቱ ሲጠየቅ ተጨማሪ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ሳይከፍል ከፍ ያለ አደጋ ሊያስከትል በሚችል ተግባር ላይ የተሰማራ እንደሆነ ይህ ፖሊሲ ፍጹም ዋጋ አይኖረውም ፤ ይህን በሚመለከት ረገድ ማናቸውንም የመብት ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም ። » እንደዚህ በመሆኑም ምክንያት የአደጋ መክበድ ያለማስታወቅ ውጤትን በሚመለከት ረገድ በሕጉና በፖሊሲው መካከል ልዩነት እናያለን ። ሊደርስ የሚችል አደጋ እየከበደ የሄደ እንደሆነና ኢንሹራንስ ሰጪው አደጋው እየጨመረ እንዲሄድ ያደረገውን ሁኔታ በተደረገ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ ወይም ይህንን ድርጊት ኢንሹራንስ ገቢው ካወቀበት ከአሥራ አምስት ቀን በማይበልጥበት ጊዜ ውስጥ እንዲያውቅ የተደረገ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው ውሉን ለማፍረስ ወይም ለኢንሹራንስ የሚከፈለውን ገንዘብ ጨምሮ ውሉ እንዲጸና ለማድረግ ይችላል ። ነገር ግን ማስታወቂያ ያልተሰጠ እንደሆነ፣ ውጤቱ በቁጥር 668 ድንጋጌ መሠረት ይሆናል።

ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን በኢንሹራንስ ገቢው ያለማስታወቅ (ማለትም በተወሰነው ጊዜ ያለማስታወቅ) በሕጉና በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት

		በንግድ ሕግ ውስጥ ያለው ውጤት[20]
1.	ሊደርስ የሚችለውን አደጋ እየከበደ መሄዱን ያለማስታወቅ ሆን ተብሎ የተደረገ ሲሆን	ውሉ በኢንሹራንስ ሰጪው ይፈርሳል ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው ለኢንሹራንስ መግቢያ የተከፈለውን ገንዘብ ያስቀራል ።
2.	ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን ያለማስታወቅ በቅን ልቡና የተደረገ ቢሆን	
ሀ.	አደጋው ከመድረሱ በፊት የተገለጸ እንደሆን	ከአንድ ወር ማስታወቂያ በኋላ ውሉን ማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ በመጨመር ውሉ እንዲቀጥል ማድረግ ።
ለ.	አደጋው ከደረሰ በኋላ የተገለጸ እንደሆነ	ሊደርስ የሚችለው አደጋ በሙሉና በትክክል ተገልጾ ቢሆን ኖሮ ለኢንሹራንስ ሊከፈል ይገባ የነበረውና በአሁኑ ጊዜ በተከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መካከል ልዩነት ታይቶ ኢንሹራንስ ገቢው የሚከፈለው ገንዘብ በዚሁ ልክ ተቀናሽ ይሆናል ።
		በፖሊሲው ውስጥ ያለው ውጤት
3.	ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን ለድርጅቱ ያለማስታወቅ	ፖሊሲው ፍጹም ዋጋ ያጣል ፤ ይህን በሚመለከት ረገድ የመብት ጥያቄ ማቅረብ አይቻልም ።

ስለዚህ ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን ያለማስታወቅ በሕጉና በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት የተለያየ እንደሆነ መመልከት ይቻላል ። ፖሊሲው ሊደርስ የሚችለው አደጋ እየከበደ መሄዱን ባለማስታወቅ በአጠቃላይ ውሉን ፈራሽ ሲያደርገው ፤ ሕጉ ሆን ተብሎ የተደረገና ሆን ተብሎ ያልተደረገ ያለማስታወቅ ብሎ ከሁለት ከመክፈሉም በላይ የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤትም እንደዚሁ ለያይቶ ይገልጸዋል ።

5. የሕይወት ኢንሹራንስ (ፖሊሲ)

የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ደንበኞችን ለመሳብ የሚረዱ የውል ቃሎችን በፖሊሲው ውስጥ ያስገባሉ ። የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ቁጥር 9 ጠቅላላ ድንጋጌ እንዲህ ይላል ፤ «ኢንሹራንስ ገቢው ፖሊሲው ከተፈረመበት ወይም

ከታደሰበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት አእምሮው ጉደሎ ሆኖ ወይም ጤነኛ ሆኖ ራሱን የገደለ እንደሆነ የሚከፈለው የኢንሹራንስ ገንዘብ መጠን ከተከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መጠን ጋር እኩል ይሆናል ፤ በምንም ዓይነት ከዚህ አይበልጥም ።» ከዚህ ላይ ፖሊሲው የተከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ በሙሉ ለኢንሹራንስ ገቢው እንደሚመለስለት ይናገራል ፤ በሌላ በኩል ፤ ሕጉ ይህን ጉዳይ ከፋፍሎ ይመለከተዋል ። ቁጥር 699/1/ «ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳ ለሕይወት የሚደረግ ኢንሹራንስ ፤ ኢንሹራንስ የገባው ሰው ሆን ብሎ ራሱን የገደለ እንደሆነ ኢንሹራንሱ ዋጋ የለውም … … … » ይላል ። በተጨማሪ «ሆን ብሎ ራሱን ያልገደለ መሆኑን ተጠቃሚው ማስረዳት የቻለ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ውል ዋጋ ያለው ይሆናል ።» ይላል ። ከዚህ ላይ ራስን መግደል በሕጉና በፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት የተለያየ እንደሆነ እንመለከታለን ። በሕጉ ፤ ራስን መግደል ሆን ተብሎ ያልተደረገ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ውል ዋጋ ያለው ይሆናል ። ነገር ግን ራስን መግደሉ ሆን ተብሎ የተደረገ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ውል ፍርስ ይሆናል ፤ ካሣም አይከፈልም ። የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ጠቅላላ ድንጋጌ የኢንሹራንስ መግቢያን ገንዘብ በሚመለከት ረገድም ከሕጉ ጋር የማይታረቅ አቋም አለው ። የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ቁጥር 2 እንዲህ ይላል ፤ «የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ እና በየጊዜው የሚከፈለውን የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ክፍያ ለመክፈል የተፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ 30 ቀን ነው ። በኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ብድር ፤ ወይም ውሉ እንዲቀር በሚያደርገው የውሉ ቃል መሠረት ጸንቶ እንዲቀጥል ካልሆነ በቀር የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ወይም በየጊዜው የሚከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መከፈል በነበረበት ቀን ወይም በተጨማሪው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ እንደሆነ ፤ መጥሪያ መስጠት ወይም ሌላ ዓይነት ሥነ ሥርዓት መከተል ሳያስፈልግ ይህ ፖሊሲ ዋጋ ያጣል » ይህ የፖሊሲ ድንጋጌ ትንታኔ የሚፈልጉ ሁለት አግባብ ያላቸው ነጥቦች ይዟል ። ይኸውም ፤

ሀ. የኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብ ለመክፈል ባለኢንሹራንሱ 30 ቀን ተጨማሪ ጊዜ ይሰጣል ።

ለ. የኢንሹራንስ ውል ማደሻው ገንዘብ መክፈያ ቀን ሲደርስ ባለኢንሹራንሱ ክፍያ አይጠይቅም ፤ ነገር ግን ሕጉ የኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብ ክፍያ መጠየቅን የባለኢንሹራንሱ ግዴታ አድርጎታል ።

ሕጉ ፤ የኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብ ያለመክፈልን ውጤት ፖሊሲው ጸንቶ የቆየበትን ጊዜ ግምት ውስጥ በማስገባት ይከፋፍለዋል ። ይኸውም ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል የተመደቡ ገንዘቦች ያነሰ የተከፈለበትና ቢያንስ ለሶስት ዓመት አከፋፈል የተመደቡ ገንዘቦች የተከፈለበት በማለት ነው ። ይሁንና በነዚህ ሁለት ጊዜያት ሕጉ በባለኢንሹራንሱ ላይ ክፍያ የመጠየቅን ግዴታ ይጭንበታል ። ቁጥር 709/2/ እንዲህ ይላል ፤ «ስለሆነም በየዓመቱ ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል የተመደቡ ገንዘቦች ያነሰ የተከፈለ ሆኖ በየዓመቱ የሚከፈለው ገንዘብ በተወሰነው ጊዜ ያልተከፈለ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው እንዲከፈለው መጠየቅና ጠይቆም ለማግኘት ያልቻለ እንደሆነ ፤ ጥያቄ ካደረገ ከአንድ ወር በኋላ ውሉን ማፍረስ ይችላል ።» ቁጥር 709/3/ ደግሞ ፤ « በየዓመቱ ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል የተመደቡ የኢንሹራንስ ገንዘቦች ከተከፈሉና በየዓመቱ የሚከፈለው ገንዘብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ እንደሆነ ፤ ኢንሹራንስ ሰጪው እንዲከፈለው ከጠየቀበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ያልተከፈለ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ውል ውድቅ አይሆንም ። ባለኢንሹራንሱ ማድረግ የሚችለው ለተከፈለው ገን

ዘብ[21] የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ መስጠት ወይም በውል የተስማሙበትን ዋና ገንዘብ ወይም በየጊዜው በሕይወት እስካለ ድረስ የሚከፈለውን ገንዘብ በቁጥር 656 በተመለከተው መሠረት መቀነስ ብቻ ነው ፡፡» ይላል ፡፡ በመሆኑም ፣ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ የመጠየቅ ግዴታ እንዳለበት ሕጉ ሲደነግግ ፖሊሲው ደግሞ የኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብ መክፈያ ዕለት ሲደርስ ፣ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ አይጠይቅም ይላል ፡፡ ይህ ኢንሹራንስ ሰጪው ወይም ሕግ አዋቂው በአፋጣኝ መፍትሔ ሊሹለት የሚገባ ጉዳይ ነው ፡፡

<u>የፕሪሚየም ክፍያ መቋረጥ በሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ፣</u>

<u>የሕይወት ኢንሹራንስ ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

ለኢንሹራንስ ውል ማደሻ ገንዘብና በየጊዜው ለሚከፈለው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መክፈያ 30 ቀን ተጨማሪ ጊዜ ይፈቀዳል ፡፡

የኢንሹራንስ ገንዘብ በተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ያልተከፈለ እንደሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ አይጠይቅም ፣ ፖሊሲው ያለምንም ማስታወቂያ ውድቅ ይሆናል ፡፡

<u>የንግድ ሕግ ድንጋጌ</u>

1. ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል ከተመደበው ገንዘብ ያነሰ የተከፈለ እንደሆነ ፣
   - ሀ/ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ ይጠይቃል ፡፡
   - ለ/ ጥያቄ ከቀረበበት ከአንድ ወር በኋላ ውሉን ማፍረስ ይችላል ፡፡
2. ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል ከተመደበው ገንዘብ የበለጠ የተከፈለ እንደሆነ ፣
   - ሀ/ ኢንሹራንስ ሰጪው ክፍያ ይጠይቃል ፡፡
   - ለ/ ጥያቄ ከቀረበ ከአንድ ወር በኋላ ክፍያ ያልተደረገ እንደሆነ ፣ ኢንሹራንስ ሰጪው (1) ለተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ ይሰጣል ወይም (2) በየጊዜው በሕይወት እስካለ ድረስ የሚከፈለውን ገንዘብ በቁ. 656 (1) መሠረት ይቀንሳል ፡፡

ስለአታላይነት[22] የሚናገረው የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ጠቅላላ ድንጋጌ እንዲህ ይላል ፣« የኢንሹራንስ ውል ፖሊሲ ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ውል ለመዋዋል ሀሳብ ባቀረበው ሰው ወይም በኢንሹራንስ ገቢው ሆነ ተብሎ የተደረገ አታላይነት መኖሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ፣ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ከተገለጸው ከማናቸውም ግዴታ ድርጅቱ ነፃ ነው ፡፡ በመሆኑም ኢንሹራንስ ገቢው የከ

ፈለውን ወይም ከኢንሹራንስ ሰጪው ይከፈለው የነበረውን ማናቸውንም ገንዘብ ያጣል ።» ይሁን እንጂ ፖሊሲው በመቀጠል እንዲህ ይላል «፤የኢንሹራንሱ ውል ፖሊሲ ከጸና ከሁለት ዓመት በኋላ ኢንሹራንስ ገቢው ባልተገለጸው ነገር ምክንያት የሞተ እንደሆነ ድርጅቱ ውሉ በተመሠረተበት እለት የሚከፈለውን የኢንሹራንስ ዋጋ ወይም የተከፈለውን ጠቅላላ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ፤ ከሁለቱ ብዛት ያለውን ፤ ማናቸውንም ተጨማሪ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ሳይጨምር በመክፈል ብቻ ይወሰናል ።«<u>ኢንሹራንስ ገቢው በሕይወት ባለበት በማናቸውም ጊዜ የተደበቀው ነገር የተገለጸ እንደሆነ ድርጅቱ ባለው የኢንሹራንስ ውል ደንብ መሠረት የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ያስተካክለዋል ።</u>

የዚህን ድንጋጌ የመጨረሻ ክፍል በሚመለከት ረገድ ልዩነቱን ማስተዋል ይቻላል ። ሕጉ ፤ መሸሸጉ አደጋ[23] ከመድረሱ በፊት የተገለጸ እንደሆነ ኢንሹራንስ ሰጪው ከአንድ ወር ማስታወቂያ በኋላ ውሉን ማፍረስ ወይም የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ተጨምሮ ውሉ እንዲቀጥል ለማድረግ ይችላል ሲል ይደነግጋል ። ነገር ግን ፖሊሲው የተደበቀው ነገር ፤ ኢንሹራንስ ገቢው በሕይወት እያለ የተገለጸ እንደሆነ የኢንሹራንስ ሰጪውን ከአንድ ወር ማስታወቂያ በኋላ የማፍረስ መብት ወደ ጐን የተወው ይመስላል ።ለኢንሹራንስ ሰጪው የተሰጠው መብት ባለው የኢንሹራንስ ውል ደንብ መሠረት የኢንሹራንስ መግቢያውን ገንዘብ ማስተካከል ብቻ ነው ።

6. ተደራራቢ ኢንሹራንስ

ሕጉና ፖሊሲው የማይጣጣሙበትና ትክክለኛውን ሁኔታ የማያንጸባርቁበት ሌላም ክፍል አለ ። ይኸውም ስለ ተደራራቢ ኢንሹራንስ የሚናገረው ክፍል ነው ። የአካል አደጋ ኢንሹራንስ ፖሊሲ ክፍል 3 እንደሚከተለው ይደነግጋል ፤ « ... ... ኢንሹራንስ ገቢው ይህን የኢንሹራንስ ፖሊሲ ከተቀበለ ወይም እንዲጸና ካደረገ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ድርጅቱ በጽሑፍ ሳይስማማ ከሌላ ኢንሹራንስ ሰጪ ጋር በአካል አደጋ ችሎታ ማጣት ወይም የሞት ኢንሹራንስ ውል የተዋዋለ እንደሆነ ይህ ፖሊሲ ፍጹም ዋጋ ያጣል ፤ ይህን በሚመለከት ረገድ ምንም ዓይነት የመብት ጥያቄ አይኖርም[24]። » አያሌ ኢንሹራንስ ሰጪዎች አንዱን ዕቃ ለአንዱ ዓይነት ጉዳት ኢንሹራንስ በመስጠታቸው ኢንሹራንስ የገባው ዕቃ ዋጋ ኢንሹራንስ ከተደረገበት ዋጋ የበለጠ ሲሆን እያንዳንዱ የኢንሹራንስ ሰጪ በኢንሹራንስ ገቢው በኩል ማታለል ከተደረገ ውሉ እንዲፈርስና ኪሣራም እንዲከፈለው መጠየቅ ይቻላል ። ኢንሹራንስ የገባው ሰው በቅን ልቦና ያደረገው እንደሆነ በአደጋ ጊዜ እያንዳንዱ ኢንሹራንስ ሰጪ ስለኢንሹራንሱ በተዋዋለበት ሂሳብ መጠን ካሣ ከፋይ ይሆናል[25]። ፖሊሲው በአጠቃላይ ያለድርጅቱ የጽሑፍ ስምምነት ከሌላ ኢንሹራንስ ሰጪ ጋር ስለመዋዋልና ስለውጤቱ ሲናገር ሕጉ ግን በማታለል የተደረገና በቅን ልቡና የተደረገ በማለት ከሁለት ይከፍለዋል ። በሚከተለው ማጠቃለያ መግለጫ በቀላሉ ቀርቧል።

ተደራራቢ ኢንሹራንስ በሕጉና በኢንሹራንስ ፖሊሲው የሚያስከትለው ውጤት	
	በፖሊሲው ያለው ውጤት
ኢንሹራንስ ገቢው አንድ ፖሊሲ ከጸና በኋላ ያለድርጅቱ የጽሑፍ ፈቃድ አንድ ዕቃ ለአንዱ ዓይነት ጉዳት ፤ ከሌላ ኢንሹራንስ ሰጪ ጋር የተዋዋለ እንደ ሆነ ፤	ፖሊሲው ፍጹም ዋጋ ያጣል ፤ ይህን በሚመለከት ረገድ ምንም ዓይነት የመብት ጥያቄ አይኖርም።

	በሕጉ ያለው ውጤት
ስለ አንዱ ዕቃ ለአንዱ ዓይነት ጉዳት ከአያሌ ኢንሹራንስ ሰጪዎች በማታለል መዋዋል ።	እያንዳንዱ ኢንሹራንስ ሰጪ ውሉ እንዲፈርስና ኪሣራም እንዲከፈለው ይጠይቃል ።
ተደራራቢው ኢንሹራንስ የተደረገው በቅን ልቦና ሲሆን ፤	እያንዳንዱ ኢንሹራንስ ሰጪ አደጋ በደረሰ ጊዜ ስለኢንሹራንሱ በተዋዋለ በት ሂሳብ መጠን ካሣ ይከፍላል ።

ከዚህ በላይ ከሰፈረው መግለጫ ማየት እንደምንችለው በሕጉና በፖሊሲው መካከል አለመጣጣም ከመኖሩም በላይ በሕጉም ሆነ በፖሊሲው ስለተደራራቢ ኢንሹራንስ የተነገረው ጊዜው ያለፈበት ነው ። ሁለቱም ከአዋጅ ቁጥር 26/1967 መንፈስና ዓላማ ጋር አብረው አይሄዱም ። ኢኮኖሚውን ማኅበራዊ ለማድረግ በተደረገው ሙከራ ፤ መሠረታዊ የሆኑት የምርት መገልገያዎች ሁሉ እንደ መሬት ፤ ፋብሪ ካዎች ፤ ማዕድናት ወዘተ ያሉት የሕዝብ ንብረት ሆነዋል ። በአዋጅ ቁጥር 26/1967 ክፍል 2(ፐ) መሠረት ሙሉ በሙሉ የመንግሥት ከሆኑት ድርጅቶች አንዱ ኢንሹራንስ ነበር ። ይህ ወደ አንድ ዓቢይ ማጠቃለያ ይመራናል ፤ ይኸውም ሁሉም የኢንሹራንስ ድርጅቶች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ከመሆናቸውም በላይ ሁሉም ቅርንጫፎች በብሔራዊ ኢንሹራንስ ድርጅት ሥር ተደራጅተዋል። በመሆኑም አንድን ዕቃ ለአንድ ዓይነት ጉዳት ኢንሹራንስ ያስገባ ማንኛውም ሰው ይህንኑ ዕቃ ለተመሳሳይ ጉዳት ከሌላ ኢንሹራንስ ሰጪ ዘንድ ኢንሹራንስ ሊያስገባው አይችልም ፤ ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ኢን ሹራንስ ሰጪ ብቻ ነው ያለው ። ይኸውም ብሔራዊ የመድን ድርጅት ነው ። ለሥራ ቅልጥፍናና የደንበኞችን መጨናነቅ ለማስወገድ ሲባል ይህ ድርጅት አያሌ ቅርንጫፎች ፤ ለምሳሌ አፍሶል ቅርንጫፍ ፤ አንበሳ ቅርንጫፍ ፤ ናይል ቅርንጫፍ ፤ የመሳሰሉትን በውስጡ ይዟል ።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

ኢትዮጵያ የሶሻሊስት የዕድገት መንገድ ለመከተል ስለአወጀች ለድሮው ሁኔታ ተስማሚ የነበሩ ተቋሞችና ሕጐች ጊዜው ያለፈባቸው ይመስላሉ ። ምንም እንኳ በሁለቱ መካከል በይነ—ግብር መኖሩ የማይዘነጋ ቢሆንም ላዕላይ—መዋ ቅሩ ታሕታይ—መዋቅሩን ማንጸባረቅ አለበት ። የቀድሞዎቹ ሕጐችና ተቋሞች ከአዲሱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር መስማማት አለባቸው ስንል የቀድሞዎቹ ሕጐችና ተቋሞች በሙሉ ይቅሩ ማለታችን አይደለም ። አጠናክረን ለመናገር የምንሞክረው ከአዲሱ ማኅበራዊ ሁኔታ ጋር የሚስማሙትንና አግባብ ያላቸውን ነገሮች ማቆየት ፤ ከአዲሱ ሥርዓተ ማኅበር ዓላማና መንፈስ ጋር አብረው የማይ ሄዱትንና የድሮውን ማኅበራዊ ግንኙነት ዕድሜ ለማራዘም አስተዋጽኦ የሚያ ደርጉትን ነገሮች መተው እንዳለብን ነው ። እርግጥ ፤ በፖሊሲውና በሕጉ ውስጥ ያሉትን አግባብነት የሌላቸውን ነገሮች መተው ቀላል አይደለም ። በብዙ አቅ ጣጫ ጥናትና ምርምር ማድረግን የሚጠይቅ ነው ።

የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ በንግድ ሕግ የኢንሹራንስ ድንጋጌዎችና በኢንሹራንስ ፖሊሲ መካከል ያለውን አለመጣጣም መጠቆም ነው ። እንዲህ ያለው ችግር እንዴት መቃለል አለበት? ሕጉን መለወጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፤ የኢንሹራንስ ንግድን እንደሚስማማና የኢንሹራንስ ገቢውን ሕጋዊ ጥቅሞች እንደሚጠብቅ ሆኖ መለወጥ አለበት ። በእርግጥ ሕጉ መለወጥ አለበት ፤ ለምን ቢባል ፤ በአንድ በኩል የሕግ ድንጋጌዎች በሌላ በኩል ደግሞ መሠረታዊ የሆኑትን የሕጉን ድንጋጌዎች የሚሽሩ የውል ቃሎችና የውል ሁኔታዎች በአንድነት መኖር የለባቸውም ።

መቸም በአንድ በኩል የሁለቱን ወገኖች ግንኙነትና ሕጋዊ ግዴታ የሚመለከቱ የፖሊሲ ድንጋጌዎች እርስ በርስ ሳይጣጣሙ ሁለቱም ጐን ለጐን አብረው መቆየት እንደማይችሉ ግልጽ ነው ። ለዚህ መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ፤

ሀ. ፖሊሲዎቹም ሆኑ ሕጉ የንግድን ተጨባጭ ሁኔታ እንዲያንጸባርቁ አድርጐ ማስተካከል ነው ። ይህም ሲሆን በሕጉና በፖሊሲው ውስጥ ያሉትን ድንጋጌዎች እንዲጣጣሙ ማድረግን ይጠይቃል ።

ለ. የተለያዩ የፖሊሲ ድንጋጌዎችን በመለወጥ ከሕጉ ጋር እንዲስማሙ ማድረግ ፤ ይህ ካልሆነ ግን ለወደፊት አብረው መሄድ የማይችሉና አቅጣጫቸው የተለያየ የፖሊሲና የሕግ ድንጋጌዎች ሳይስማሙ እንዳሉ እንዲቆዩ ያደርጋል ።

የግርጌ ማስታወሻዎች

* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ ሕግ ፋኩልቲ ሌክቸረር (ለጥናት በሚጊል ዩኒቨርሲቲ ይገኛሉ ።)

1. ፕሬስተንና ኮሊንሾ ፣ ሎውስ ኦፍ ኢንሹራንስ ፣ ገጽ 1
2. ብርሃኑ ኪዳኔ ፣ ኢንሹራንስ ዳሜጅስ ኢን ኢትዮጵያ ፣ ኮምፐንሴሽን ኦር ሚትስ ፡ ገጽ 11.
3. አዋጅ ቁ. 26 ማርች 11/1975
4. ፒተር ዊንሺፕ ፣ ባክግራውንድ ዶኩመንትስ ኦፍ ዘ ኢትዮጵያን ኮመርሻል ኮድ ፤ እ. አ. አ. 1960 ገጽ 80
5. የፍ/መዝገብ ቁ. 1099(1965/እ. ኤ. አ)
6. የፍት/ይግባኝ መዝገብ ቁ. 1184/1965(እ. ኤ. አ)
7. የእሳትና የመብረቅ ውል አንቀጽ (11)
9. ፒተር ዊንሺፕ ፣ ባክግራውንድ ዶኩመንትስ ኦፍ ዘ ኢትዮጵያን ኮመርሻል ኮድ 1960 ገጽ 86
10. ለሁሉም ዓይነት አደጋ ፖሊሲ ፣ የማይወሰድ ሁኔታ ቁ.9 ፣ ኮንስኮንሻል ኪሣራ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 11 ፣ 15 ፣ የሠራተኛ ካሣ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 10 ፣ የቤት ሥርሠራና ቤት ሰብሮ የመግባት ፖሊሲ ቁ. 8

11ሀ. የፍት/መዝ/ ቁ. 1166/ 1974 (እ.ኤ.አ.)

11. የንግድ ሕግ ቁ. 668 ን ይመለከቷል ።
12. ዲስዳሌ እና ማክሙርዶ ፣ ኤለመንትስ ኦፍ ኢንሹራንስ ገጽ 84
13. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁ. 668(2)
14. ከዚያው ቁ. 668(2) (ለ)
15. ኮንስኮንሻል ሎስ ፖሊሲ ኮንዲሽን ቁ. 1 ፤ መኒ ፖሊሲ ኮንዲሽን ቁ. 3. 6 ፤ ፓብሊክ ላያቢሊቲ ፖሊሲ ኮንዲሽን ቁ. 12 ፣ በርግለሪ ፖሊሲ ኮንዲሽን ቁ. 2.
16. ማክጊልብሬይ ፡ ኢንሹራንስ ሎው ፣ ቮልዩም 1 — ቁ. 893
17. የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ቁጥር 668 እና 669 ይመለከቷል ።
18. አሰገደች እንዳይላሉ ፣ ከሳሽ ፣ የኢምፔሪያል ኢንሹራንስ ኩባንያ መልስ ሰጭ ፤ የፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 1055/59
19. ወ/ሮ ቅድስት ከሳሽ ሚቸል ኮትስ ተከሳሽ የፍትሐብሔር መዝገብ ቁ. 1001/61
20. የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ፤ 1960 ቁ. 669 (3)
21. ሉተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንስ ውል መስጠት ፣ የኢንሹራንሱ ውል እንደጸና ቢቀጥልኖሮ ውሉ በሚፈጸምበት ዕለት ወይም ኢንሹራንስ ገቢው ከተጠቃሚው አስቀድሞ የሞተ እንደሆን የሚከፈል ከነበረው ያነሰ የገንዘብ መጠን ነው ። ለተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንስ ውል የሚሰጠው ፣ ቢያንስ ለሶስት ዓመት ጊዜ አከፋፈል የተመደቡ ገንዘቦች ተከፍለው ፣ ኢንሹራንስ ገቢው በተለያዩ ምክንያቶች የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ ለመክፈል ያልፈለገ ወይም ያልቻለ እንደሆን ነው ። ስለ ዚህም ፣ ኢንሹራንስ ገቢው ውል በሚፈጸምበት ዕለት ወይም ከተጠቃሚዎቹ አስቀድሞ የሞተ እንደሆነ ይከፈለዋል ።

    የተከፈለው ገንዘብ ዋጋ የተከፈለበት ዓመት ብዛት ፖሊሲው ጸንቶ የቆየበት ጊዜ መድን የተሰጠበት ገንዘብ መጠን የተከፈለ ገንዘብ ዋጋ ፖሊሲው በተሰረዘበት ዕለት ከሚከፈል ጥሬ ገንዘብ የተለየ ነው ። ውሉ በተሰረዘበት ዕለት የሚከፈል የኢንሹራንስ ዋጋ ማለት የኢንሹራንሱ ውል እንደጸና ቢቀጥል ኖሮ ይከፈል ከነበረው ያነሰ ፖሊሲው በሚሰረዝበት ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ መጠን ነው ። በአጠቃላይ ግን አነስተኛ መጠን ያለው የተከፈለ ገንዘብ ዋጋ እየተባለ ይጠራል ፤ ምክንያቱም የክፍያው ጊዜ እስከ ውሉ መፈጸሚያ ዕለት ስለሚቆይ ነው ። ኢንሹራንስ ገቢው የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ መክፈል ካቋረጠበትና ስለዚሁ ማስታወቂያ ከደረሰው እስከ ሶስት ወር ድረስ ለተከፈለው ገንዘብ የኢንሹራንሱ ውል በተሰረዘበት ዕለት ጥሬ ገንዘብ የመጠየቅ መብት አለው (የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ቁጥር 4 ፣ ጠቅላላ ድንጋጌ ይመለከቷል ።)

22. የሕይወት ኢንሹራንስ ፖሊሲ ጠቅላላ ድንጋጌ ቁ. 10
23. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁጥር 668 ፤
24. የግል መኪና አጠቃላይ ፖሊሲ ፣ ሁኔታ ቁ. 6 ፤ የሁሉም ዓይነት አደጋ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 7 ፣ ኮንስስኮንሻል ኪሣራ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 2 ፣ 12 ፣ የሠራተኛ ካሣ ፖሊሲ ሁኔታ ቁ. 11 ፤ የንግድ ተሽከርካሪ ፖሊሲ ፤ ሁኔታ ቁ. 6 ፣ የቤት ሥርሠራና ቤት ሰብሮ የመግባት ፖሊሲ ፤ ሁኔታ ቁ. 8 ፤
25. የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁ. 681

በ1969 ዓ. ም. የወጣው የገንዘብና የባንክ አዋጅ ለውጦች ውጤቶች

በበፈቃዱ ደግፌ*

መ ግ ቢ ያ

የገንዘብ ታሪክ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የረጅም ጊዜ ዕድሜ ያለው ቢሆንም በአንፃሩ[1] አጠቃላይ ገንዘብ ነክ ሕጎችና ተቋሞች መታወቅ የጀመሩት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው ። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባንክ የአበሻ ባንክ በመባል የሚታወቀው የግብጽ ብሔራዊ ባንክ ቅርንጫፍ ነበር ። ይህ ባንክ እ.ኤ.አ. ከየካቲት 16/1905 ዓ.ም. ጀምሮ ለአገሪቱ የንግድ እንቅስቃሴ በሩን ክፍት በማድረግ በአምስት መቶ ሺህ (500,000) ፓውንድ ካፒታል ሥራውን ጀመረ ። በጥቅምት ወር 1931 ዓ.ም. እ.ኤ.አ በኢትዮጵያ መንግሥት ተገዝቶ የኢትዮጵያ ባንክ (ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) በሚል አዲስ ስያሜ ተግባሩን ሲቀጥል በዚህም ባንኩ ፤ አገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቸኛ ባለ ንብረትነቱን የያዘችበት ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ አህጉር የመጀመሪያው ከባዕድ እጅ ነፃ የሆነ ብሔራዊ ማዕከላዊ ባንክ ሊሆን ቻለ ።

የኢትዮጵያ ባንክ እ.ኤ.አ. በ1936 ዓ.ም. ሲፈርስ እስከ 1942 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) በቦታው የተተካ ምንም ዓይነት ኢትዮጵያዊ ባንክ ያልነበረ ቢሆንም በዚህ ጊዜ የባንክ አገልግሎቶች አልተቋረጡም ። ባንኮ ዲ. ኢታሊያ ፤ ባንኮ ናሲዮናል ዴል ላቦሮ ፤ ባንኮ ዲ. ሮማና ባንኮ ዲ. ናፖሊ የተባሉት አራት የኢጣሊያ ባንኮች ቅርንጫፎች አገልግሎት ሲሰጡ ነበር ። ከነዚህም ሁለቱ አገልግሎታቸውን ሲያቋርጡ ባንኮ ዲ. ሮማና ባንኮ ዲ. ናፖሊ እ.ኢ.አ. በጥር ወር 1975 ዓ. ም. እስከ ተወረሱበት ጊዜ ድረስ ተግባራቸውን ቀጠሉ ። በ1941 ዓ.ም. (እ.አ.አ.) ጣሊያኖች ወጥተው እንግሊዞች ወደ አገራችን ሲገቡ የእንግሊዙ ባርክሌይስ ባንክ (ባርክሌይስ ባንክ ኦፍ ብሪተን) የተሰኘው ባንክ የእንግሊዝ ወታደሮችን ዱካ ተከትሎ በመግባት ቅርንጫፍ ከፍቶ እስከ 1942 ዓ.ም. ድረስ ሲሠራ ቆየ ። በድህረ ሁለተኛ ዓለም ጦርነት ፤ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ባንክ በ1942 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በአዋጅ የተቋቋመው (አዋጅ ቁ. 21/42) የኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ (ስቴት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ) ነበር ። ይህም ባንክ እስከ 1963 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ድረስ የንግድና የማዕከላዊ ባንኮችን ተግባራት በማዋሃድ ሲሠራ ቆየ ።

በ1963 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) የወጣው የገንዘብና የባንክ አዋጅ ከዚህ በታች ገባአ 1 ብለን የምንጠራው አዋጅ ቁ. 206/63 የንግድና የማዕከላዊ አገልግሎቶችን በመለየት ፤ የኋለኛው ማለትም የማዕከላዊ ባንኩን ዘርፍ በዚሁ ዓመት በትዕዛዝ በተመሠረተው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኃላፊነት ሥር አዋለው ። ምንም እንኳ ከ1963 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) በፊት ገንዘብና ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሕጎች ቢኖሩም የአገሪቱ የገንዘብ ፖሊሲ በግልጽ የተብራራውና አመራሩም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሥር ሆኖ የተደላደለ ሥርዓት ሊይዝ የቻለው እላይ በተጠቀሰው በገባአ 1 መሠረት ነው ።

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በታኅሣሥ ወር 1975 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) የሚከተለው የኅብረተሰባዊነት ፍልስፍና መሆኑን በማወጅ ለዚህም ግብ መምታት የሚያስችል የኤኮኖሚ ፖሊሲ ቀየሰ ። ከብዙ በጥቂቱ የዚህ ኤኮኖሚ ፖሊሲ ዓላማ ለኢኮኖሚ ግንባታ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ከፍተኛ የማምረቻ መሣሪያዎች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚውሉበት ዘዴ የታቀደበት ነበር ። ከላይ የተጠቀሰውን ተግባራዊ ለማድረግ ጊ.ወ.መ. በጥር 1 ፤ 1975 (እ.አ.አ.) ዓ.ም. ሶስት የንግድ ባንኰችን ፤ አሥራ አንድ የሚሆኑ የመድን ድርጅቶችንና ሁለት ሁለገብ የገንዘብ ድርጅቶችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በማድረግ የኅብረተሰቡን ፍላጐት ሙሉ በሙሉ ለማርካት በሚቻልበት መንገድ እንዲያዙ ወሰነ ። የተወረሱት የመድን ድርጅቶች ቀድሞውኑ የመንግሥት ከሆኑት የመድን ድርጅቶች ጋር በመዋሃድ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሚል መጠሪያ ታወቁ ። ሁለቱ ሁለገብ የገንዘብ ድርጅቶችም ተዋህደው የቤትና የቁጠባ ባንክ ተቋቋመ ። የመንግሥት የሆኑ የእርሻና እንዱስትሪ ባንኮችም እንደገና ተቋቁመው ለእርሻውና ለእንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊውን ብድር የመስጠቱን ሥራ ተያያዙት ። ንግድ ባንኮችን እንደገና የማቋቋሙ ተግባር በሁለት የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ አልፎአል ። የመጀመሪያው የተወረሱት ሶስት ባንኮች መዋሀድና አዲስ ባንክ መባል ሲሆን የመጨረሻው ደረጃ ደግሞ ንብረትነቱ የመንግሥት የሆነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚል መተካቱ ነው ። የገንዘቡ ክፍለ ኤኮኖሚ ያሳየው የመጨረሻ ዕድገት በ1963ቱ (እ.አ.አ.) የገንዘብና የባንክ አዋጅ (ገባአ1) በ1976 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. የገንዘብና የባንክ አዋጅ ከዚህ በታች ገባአ2 ብለን በምንጠራው መተካት ነው ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በገባአ 1 ፤ 1963ቱ ቻርተርና በዚሁ ዓመት አዋጅ ቁ. 211/63 እና በገባአ 2 መካከል ያሉትን ልዩነቶች ጨምቆ ለማሳየት ሙከራ ሲደረግ በአዋጆቹ የተፈጠሩ አዳዲስ ሁኔታዎች በኢኮኖሚው የተንጸባረቁትን ገፅታዎች አብሮ ለማየት ጥረት ተደርጓል ። በክፍል አንድ ውስጥ የ1963ቱንና የ1976ቱን አዋጆች በማነጻጸር አጠቃላይ ግምገማ ሲደረግ ትኩረት የተደረገው በልዩነቶች ላይ ነው ። በዚህም ውስጥ ለአቀራረብ እንዲያመች የ1976ቱን አዋጅ መዋቅር ተከትለናል ። ክፍል ሁለት ደግሞ በአዋጆቹ ሳቢያ የተከሰቱት ዋንኞቹ ለውጦች ያስከተሉአቸውን ሁኔታዎች ያጠናል ።

1. በ1976 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በወጣው የገንዘብ አዋጅ የተደረጉ ዋና ዋና ለውጦች

(እ.ኤ.አ.) ከ1963 ዓ.ም. ወደዚህ ያለው የገንዘብ ፖሊሲና አመራሩ በሁለት አዋጆች[2] ሥር በተጠቃለሉ 78 አንቀጾችና በአንድ ትዕዛዝ[3] ሥር ተዘርዝሯል ።

እነዚህም አዋጆች ገንዘብና ባንክን እንዲሁም የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪን የሚመለከቱ ሲሆኑ ትእዛዙ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተቋቋመበት ቻርተር ነው[4]። ሁለቱም አዋጆች ማለትም የ1963ቱና የ1976ቱ አንቀጾች ብሔራዊ ባንኩን ያቋቁማሉ ፤ የሕግ ሰውነትም ያጐናጽፉታል ፤ እንዲሁም ሥልጣኑንና ተግባሩን ያብራራሉ ። በሁለቱም አዋጆች መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገሪቱን የገንዘብና የባንክ ሥርዓት ይቆጣጠራል ። ሆኖም ግን የባንኩን ተግባርና ሥልጣን በሚመለከት ረገድ ገባአ 2 ከገባአ 1 የበለጠ ግልጽ ነው ። የ1963ቱ ድንጋጌዎች ባንኩን የገንዘብ ኖቶችና ሳንቲሞች ብቸኛ አመንጪ ሲያደርጉት[5] በተጨማሪም ደግሞ ለሚከተሉት ተግባራት ሥልጣን ያሰጡታል[6]። እነዚህም በአገልግሎት ላይ የሚውለን የገንዘብ መጠን የመቆጣጠር ፤ የወለድ መጠንን የመወሰን ፤ የአገሪቱን ዓለም አቀፋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ የመምራት ፤ የገንዘብን ዋጋ መረጋጋት በሚያግዝ ዓላማ ለባንኮች የሥራ ፈቃድ የመስጠትና ተግባራ

ቸውን የመቆጣጠር[6]፤ ለተመዛዘነ የምጣኔ ሀብት ዕድገት ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር በሚችል አኳኋን የክሬዲትና የገንዘብ ምንዛሪ ሁኔታዎች የመቆጣጠር ናቸው[7]። በዚሁ ረገድ ገባእ 2 ከዚህ ይልቅ ጠለቅ ባለ ሁኔታ ባንኩ ከላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎችንም የተሰጡትን ሥልጣኖች በተግባር ለመተርጐም የሚከተላቸውን ዓላማዎች ይገልጻል ። ይህም በብሔራዊ ደረጃ ከተነደፈው ፕላን ጋር በሚጣጣም ዓይነት ከፍተኛ ዕድገት ፤ የሥራ ዕድልና የተረጋጋ የዋጋ ሁኔታን ለመፍጠር ይሆናል[8]። የብሔራዊ ባንኩ ሥልጣን በአዋጁ አንቀጽ ዘጠኝ ሥር በተዘረዘሩ አሥራ ስድስት ንዑስ አንቀጾች የተገለጸ ሲሆን በነዚህም አንቀጾች ባንኩ የኀብረት ይዞታ ባላቸው የሥራ ክፍሎች[9] ውስጥ ለባንኩ ክፍት የሆነ ሂሳቦችን የመቆጣጠር[10]፤ በቁጥጥራቸው ሥር ያለን ሀብት አግባብ ባልሆነ መንገድ ለሚያውሉ ድርጅቶች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ብድር የመከልከል[11] መብት የተሰጠው ሲሆን ዓላማውም የአገሪቱን ሀብት ጠቃሚ ለሆነ ጉዳይ በተቀላጠፈ ሁኔታ ተግባር ላይ ለማዋል ታቅዶ ነው[12]። በዚህም ረገድ ገባእ 2 የባንኩን ተግባራት ይበልጥ በማያሻማ መንገድ ሲያብራራው ሥልጣኑን ግልጽ በሆነ መንገድ ያስቀምጠዋል ።

የአዋጁ ምዕራፍ ሶስት በ1963ቱ ቻርተር[13] ውስጥ የተጠቀሱትን የካፒታል ፤ የመጠባበቂያና የሂሳብ ማስታወቂያዎችን ይመለከታል[14]። በመሠረቱ የሚለየው ግን በካፒታሉ መጠን መጨመርና በትርፍ ስርጭት አያያዝ[15] ላይ ነው ።

የምዕራፍ አራት ይዘት የባንኩን ድርጅታዊ መዋቅርና አስተዳደር የሚመለከት ሲሆን ይህም ጉዳይ በቻርተሩ ውስጥ በቅድሚያ ተጠቅሷል[16] ። በሁለቱም አወቃቀር መሠረት ባንኩ የሚተዳደረው በዲሬክተሮች ቦርድ ሲሆን የተቀሩት አንቀጾች አስተዳደርና ባጠቃላይ በድርጅታዊ መዋቅሩ ላይ ያተኩራሉ ።

ምዕራፍ አምስት በባንኩና በመንግሥት መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ያብራራል ። ይህም በገባእ 1 ውስጥ በምዕራፍ ሶስት የተገለጸ ሲሆን ከፊሉ በ1969 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ማሻሻያ የተደረገላቸው ናቸው[17]። በዚህም መሠረት ባንኩ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በሚመለከት የመንግሥት ወኪልና ባንክ ሆኖ ያገለግላል ። በአንጻሩም በመንግሥት ስም ገንዘብ ያበድራል ፤ ገንዘብ ይቀበላል እንዲሁም አስፈላጊ ክፍያዎችን ያከናውናል ።

የብድርን አሰጣጥ በሚመለከት በገባእ 1 (እንደተሻሻለው) ባንኩ ለመንግሥት የሚሰጠው ብድር በሚከተሉት መንገዶች ይሆናል ።

ሀ/ ቀጥታ በማበደር ለ/ የግምጃ ቤት ሰነዶችን በመግዛትና ሐ/ የመንግሥት ዕዳ ሰነዶችን (ቦንዶችን) በመግዛት ነው[18]።

ሁለተኛ የብድሩ መጠን ገባእ 1 (እንደተሻሻለው) ለመንግሥት የሚሰጠውን ቀጥታ ብድር ካለፈው የበጀት ዓመት መደበኛ የመንግሥት ገቢ ከመቶ ሃያው እጅ (20 %) ሊበልጥ እንደማይችል ይወስናል ። ይህም በዓመት ከመቶ ሶስት (3 %) ሊያንስ የማይችል ወለድ የሚታሰብበት ሆኖ የወለዱም መጠን በባንኩና በገንዘብ ሚኒስቴር መካከል በሚደረግ ስምምነት ይወሰናል ። በዚህ አዋጅ መሠረት ማለትም ገባእ 1 (እንደተሻሻለው) መንግሥት ተጨማሪ ብድር ለማግኘት የሚችለው ያለበትን ዕዳ በቅድሚያ አጠናቅቆ ሲከፍል ብቻ ነው[19]።

ገባእ 2 ግን የብድሩን መጠን ከመደበኛ የመንግሥት ገቢ አንጻር ያለውን ሚዛን ከሃያ በመቶ (20 %) ወደ ሃያ አምስት በመቶ ከፍ ሲያደርገው በመቶ ሶስት የተባለውንም ወለድ ጣሪያው አድርጐታል ። እንደዚሁም የቀድሞውን ዕዳ ማጠናቀቅን ለተጨማሪ ብድር መስጠት እንደ ቅድመ ሁኔታ አይቆጥረውም[20]።

እንዲሁም በገባአ 1 ((እንደተሻሻለው) መንግሥት በግምጃ ቤት ሰነዶች ሽያጭ ከባንኩ ወይም በባንኩ በኩል ብድር ሊያገኝ ይችላል[21]። የሰነዱም ዋጋ መጠን ካለፈው የበጀት ዓመት መንግሥት ከሰበሰበው መደበኛ ገቢ ከአሥራ ሁለት ተኩል በመቶ (12½%) እንደማይበልጥ ሲወሰን ገባአ 2 ግን ይህንን ሚዛን ወደ ሃያ በመቶ (20%)ከፍ አድርጐታል[22]።

መንግሥት ብድር ሊያገኝበት የሚችለው ሶስተኛው መንገድ ደግሞ የዕዳ ሰነዶች ሽያጭ ነው ። መጠኑም የባንኩን ካፒታል ሶስት እጅ የጠቅላላ መጠባበቂያ ሂሳብና ሰማኒያ ሁለት ሚሊዮን ብር[23] ያህል ነበር ። በገባአ 2 ግን ብድሩ የሚተመነው ባለፈው የበጀት ዓመት መንግሥት የሰበሰበው መደበኛ ገቢ መሠረት ሆኖ ሚዛኑም በመቶ ሃምሳ (50%) እንዲሆን ተደርጓል[24]።

ምዕራፍ ስድስት ባንኩ ከሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን እርሱም ሶስት ክፍሎች አሉት ።

ሀ/ የክሬዲት ሥራን ማስተባበርና መቆጣጠር

ለ/ የክሬዲት ትራንዛክሽን ፤ በአደራ የሚቀመጡ ንብረቶችና ከዚህ ጋር ዝም ድና ያላቸውን ተግባሮች ማከናወን የሚመለከቱና

ሐ/ ከኢንተርናሲዮናል የመጠባበቂያ ንብረቶች ጋር የተያያዙ ንብረቶች ሲሆን ይህ በመጨረሻ የተጠቀሰው ከቀደመው አዋጅ[25] የሚለይበት ምንም ስለሌለው ብዙም ትኩረት አይሰጠውም ። ይህም የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሬን ሥራ ለማካሄድና ይህንንም ተግባር በወኪል አማካይነት በማስፈጸም ረገድ ባንኩን ብቸኛ ባለሥልጣን ከሚያደርጉት አንቀጾች አንጻር ማለት ነው ።

ሀ/ የክሬዲት ሥራን ማስተባበርና መቆጣጠር

በዚህ ረገድ ሁለቱም ሕጐች[26] ተመሳሳይነት ሲኖራቸው ባንኩ የራሱንም ሆነ የሌሎች ገንዘብ ድርጅቶችን ክሬዲት የመምራት ፤ ሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ከባንኩ የሚበደሩበትን የወለድ ተመን የመወሰን ፤ እንደዚሁም ራሳቸው በሚይዙት የማጠራቀሚያ ሂሳቦች ላይ የሚታሰበውን ወለድ የመተመን የሂሳቦቹንም መጠን ተግባርና ወቅት የመቆጣጠር ሥልጣኖች አሉት ።

እዚህ ላይ ሁለቱ ሕጐች የሚለዩባቸው ሁለት ጉልህ ነጥቦች ጥሬ ገንዘብና የመጠባበቂያ ሂሳቦችን የማኖርን አስፈላጊነት የሚመለከቱ ናቸው ። በሁለቱም ሕጐች መሠረት[27] ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ለተቀማጭነት ከተቀበሉት ገንዘብ ውስጥ የተወሰነ መጠን በጥሬ ገንዘብ ወይም በግምጃ ቤት ሰነዶችና በመሳሰሉት ገንዘብ መሰል ንብረቶች[28] መልክ በባንኩ የማስቀመጥ ግዴታ አለባቸው ። ትልቁ ልዩነት ግን በገባአ 1 የሚጠራቀመው ሂሳብ መጠን ከጠቅላላው ከመቶ ሃያ (20%) መብለጥ የማይገባው መሆኑን ሲገልጽ ገባአ 2 ግን መጠኑን ለባንኩ ይተውዋል ። በተጨማሪም ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች በአጭር ጊዜ ከሚከፈለው ዕዳቸው የተወሰነ መጠን በገንዘብ መሰል ንብረቶች መልክ በባንኩ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል ። የማጠራቀሚያው ሂሳብ ጣሪያ ከጠቅላላው እዳ በመቶ ሰላሳ (30%) እንዲሆን ገባአ 1 ሲወስን በገባአ 2 ግን ውሳኔው የባንኩ ፋንታ ነው[29]

ለ/ ስለክሬዲት ሥራና በአደራ ስለሚቀመጡ ንብረቶች

በዚህ በኩል ሁለቱም አዋጆች ማለትም ገባአ 1 ና ገባአ 2 ባንኮችና ሌሎችም የገንዘብ ድርጅቶች ከብሔራዊ ባንክ ገንዘብ ሊበደሩ የሚችሉበትን ሁኔታዎች

ይተነትናሉ[30]። በዚሁ ውስጥ እንደተጠቀሰው ብሔራዊ ባንኩ የሐዋላ ሰነዶችን የግምጃ ቤት ሰነድ ደብተሮችንና የመሳሰሉትን ቅናሽ ወይም የቅናሽ ቅናሽ በማድረግ ሊሸጥ ወይም ሊለውጥ ይችላል ።

ምዕራፍ ሶስት ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችን ስለመቆጣጠር የሚመለከት ነው ። በገባአ 2 ውስጥ በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ብሔራዊ ባንኩ ሌሎችን ባንኮችን የማቋቋም የማዋሃድና የመቆጣጠር ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው ስለሆነ[31] በገባአ 1 ምዕራፍ አምስት የተጠቀሰው የቁጥጥርና የፈቃድ መስጠት ተግባር በዚህኛው አዋጅ ውስጥ አልተጨመረም ። ከዚህም ሌላ በዚህ ምዕራፍ ሥር የተደነገጉት የቁጥጥርና ምርመራ የማድረጉ ተግባር በገባአ 1 ባንኮችን ብቻ ሲመለከት በገባአ 2 ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችንም ያጠቃልላል ። እዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ነጥብ አለ ። ይኸውም በገባአ 1 መሠረት በባንኮች የገንዘብ አመራር ውስጥ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮች ሲከሰቱ እንደሁኔታው ቅለትና ክብደት ባንኩ ፤

ሀ/ የተመረመረው ባንክ ሥራውን የሚያቃናበት እርምጃ እንዲወስድ ማስደረግ

ለ/ የተመረመረው ባንክ ተጨማሪ ተቀማጭ ሂሳቦች እንዳይቀበል ወይም ብድር እንዳይሰጥ መከልከል

ሐ/ የተመረመረው ባንክ ሥራውን ለጊዜው በከፊል ወይም በሙሉ እንዲያቆም ማድረግ እና

መ ከነጭራሹ ማፍረስ[32] ሲችል ፤ በገባአ 2 ግን አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ ይወስዳል[33]።

በምዕራፍ ስምንት ውስጥ የተገለጹት ስለገንዘብ መደብ ልክ ስለ ሕጋዊ ገንዘብና ስለውጭ አገር ገንዘብ አስተዳደር ሲሆን ገባአ 1 ይህንኑ በአንደኛው ምዕራፍ ይዟል ። ገባአ 2 የኢትዮጵያን የገንዘብ መደብ ልክ ከዶላር[34] ወደ ብር[35] ሲለውጠው ክብደቱና ጥራቱ ሳይለወጥ ዋጋው በተጣራ የወርቅ ዴስማል 0.355468 ግራም ሆኖ እንዲጸና አድርጓል ። በገባአ 1 መሠረት የኢትዮጵያን ዶላር የወርቅ ዋጋ ይዘት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ የሚቻለው በሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅራቢነቱ በንጉሠ ነገሥቱ ሲጸድቅ ነበር[36]። በገባአ 2 ግን ባንኩ ለመንግሥት ሲያቀርብ ተፈጻሚነት ያገኛል[37]።

ስለብሔራዊ ባንኩ የንብረት ሥርጭት ጉዳይ የተደረገ አንድ ጉልህ ማሻሻያ አለ ። ሁለቱም ሕጎች ባንኩ ከጠቅላላው ንብረቱ ከፊሉን በወርቅ ፣ በውጭ አገር ገንዘብና በግዴታ ሰነዶች ወዘተ በኢንተርናሲዮናል የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያኖር ይደነግጋሉ[38]። በገባአ 1 ውስጥ በግልጽ የተመለከተው ባንኩ ከላይ በተጠቀሰው ሂሳብ ሊያኖር የሚገባው ከሚያወጣቸው የገንዘብ ኖቶች (ሳንቲሞችን ሳይጨምር) በተጠየቀ ጊዜ ወዲያውኑ ሊከፈል የሚችል ቢያንስ ሀያ አምስት በመቶ መሆን ይገባዋል[39]።

በገባአ 2 መሠረት ግን ባንኩ በኢንተርናሲዮናል የመጠባበቂያ ሂሳብ የሚኖረው ንብረት ፣

ሀ/ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡት አስፈላጊ ዕቃዎች

ለ/ የውጭ አገር ግዴታዎችንና ዕዳዎችን ለመክፈል የሚያስችል

ሐ/ ወደ አገሪቱ የሚገቡትን የአስፈላጊ አገልግሎቶችን የሚመጣጠን እንዲሆን ያስፈልጋል[40]።

ምዕራፍ ዘጠኝ ስለ ውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ደምብ ሲሆን በዚሁ አዋጅና የተሻረው አዋጅ በተመሳሳይ ምዕራፍ ሥር የያዘውን የውጭ አገር ገንዘብ ምን ዛሪ የሚፈጸምበትን ሁኔታዎች ያብራራል ፡፡ በተለይም ከባንኩ ወይም ሌላ ለመ ንዛሪነቱ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት በስተቀር ማንም የውጭ አገር ገንዘብ ለመያዝም ሆነ የምንዛሬ ሥራ ለማካሄድ የማይችል መሆኑን እና በእጃቸው የሚገኘውን የውጭ አገር ገንዘብ ለባንኩ የማስረከብ ግዴታ እንዳለ ባቸው ይገልጻል[41]፡፡

የገባአ 2 ምዕራፍ አሥር ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ፤ ስለተሻሩና በሥራ ላይ ስላሉ ድንጋጌዎች (ፈዚህና በሌሎች ሕጎች መካከል የትርጉም ግጭት ሲኖር የፊተኛው የሚጸና ስለመሆኑና ባንኩ ልዩ ልዩ ደምቦችን ማውጣት ስለ መቻሉ ፣ አዋጁን የሚተላለፍ በወንጀል የሚቀጣ ስለመሆኑ ፣ አዋጁ ስለሚጸ ናበት ጊዜ ወዘተ በዚህ ክፍል ተዘርዝሯል፡፡[42] በተጨማሪም ባንኩ አሠራሩን በምስጢር ለመያዝ የሚያስችለው አንቀጽም ገብቷል[43]፡፡ ምሥጢራዊነት በባንክ እንዱስትሪ አሠራር የተለመደ ነገር ቢሆንም ቅሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ግን ሕግ ካልፈቀደው በቀር የባንክ ምስጢራዊ አሠራር ከ1963 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ) በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ግዴታ ተገልጿል[44]፡፡

2. በገባአ2 የታዩ ዋና ዋና ለውጦችና ውጤቶች

የገንዘብና የባንክ አዋጅ (ገባአ2) የአብዮቱ ሂደት ያፈለቀው አዲስ የፍልስፍናና የኢኮኖሚ ግምባታ ውጤት ሲሆን የታቀደበትም ምክንያት የአገሪቱ የገንዘብና የባንክ ሥራ ፖሊሲ ከአዲሱ ሥርዓት ጋር እንዲጣጣም ለማ ድረግና ለዚህም ዓላማ ግብ መምታት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት ነው ፡፡ በገባአ2 እና በርሱ በተሻሩ ሕጎች መካከል ያለው ልዩነት በመሠረቱ ሕጎች በወጣባቸው ሥርዓቶች ሁኔታዎች ፣ እንዲሁም በታቀዱላቸው ዓላማዎች መካከል ያሉ ልዩነቶች ነጸብራቅ ሁነው መታየት ይገባቸዋል[45]፡፡

ገባአ2 መሠረት አድርጐት የተነሳው ነፃ ኢኮኖሚን የመገንባት ብሔራዊ ዓላማ ሲሆን የዚህም ጽንሰ ሀሳብ ራስን የመቻል መርሆ ነው ፡፡ በዕድገት ጐዳና ላይ ለመንደርደሪያነት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማግኘት አገሪቷ የምትተማ መነው ከውጪ በሚመጡ ሳይሆን በራስ ሀብት ላይ ይሆናል ፡፡ ይህ ዓላማ በአዋጁ ውስጥ ፣ ሀ/ የገንዘብ ኖቶች ማውጣት ለ/ የገንዘብ አወጣጥንና የክሬዲት ሥራ መቆጣጠርንና ፣ ሐ/ የኢት.ብ.ባ. ለመንግሥት የሚሰጠውን ብድር በሚመለከቱ አንቀጾች ተንጸባርቋል ፡፡

ሀ/ የኢት.ብ.ባ. የገንዘብ ኖቶችን ማውጣት ስለመቻሉ

በአገሪቱ የገንዘብ ፖሊሲ ዕድገት ውስጥ መሠረታዊ ሆኖ ሊጠቀስ የሚ ገባው አንድ ለውጥ በገባአ2 በአንቀጽ ስድሳ ሥር የተደነገገው ነው ፡፡ ይህ አን ቀጽ የኢት.ብ.ባንክን የንብረት ስርጭት የሚመለከት ሲሆን በአገሪቱ የገንዘብ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በአገር ውስጥ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች አወጣጥ ተግባርና በባንኩ የውጪ ሀብቱ መካከል የነበረውን መተሳሰር በመስበሩ ታሪ ካዊ ነው ፡፡ የዚህን ድንጋጌ ጉልህነት ለመገንዘብ ከ1976 ዓ.ም. በፊት የአገሪቱ የገንዘብ ኖቶች ሲወጡ የነበሩባቸውን ሁኔታዎችና እነዚህም በኢኮኖሚው ላይ የነበራቸውን ተጽዕኖ መለስ ብሎ መቃኘት አስፈላጊ ይሆናል ፡፡

ምንም እንኳ የገንዘብ ኖቶችና ሳንቲሞችን ለማውጣት በ1945 ዓ.ም. መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት ባንክ ብቸኛ ሥልጣን የሰጠው ቢሆንም[46] በዚያውም ደግሞ ታትመው ከሚወጡት ኖቶች (ሳንቲሞችን አይጨምርም) ቢያንስ ቢያንስ ከመቶ ሰባ አምስት (75%) ያህል የሚገመት በወርቅ ፥ በብር ፤ (ሲልቨር) በውጭ አገር ገንዘብ ፥ በውጭ አገር ባንክ ሂሳብ ወይም ወዲያውኑ በውጭ አገር ገንዘብ ወይም በውጭ አገር ባንክ ሂሳብ ሊለወጡ በሚችሉ የዋስትና ገንዘቦች መልክ በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ ፥ እንዲሁም ደግሞ ቀሪው ከመቶ ሃያ አምስት (25%) ግምት ያህል በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የግምጃ ቤት ግዴታ ሰነዶች መደገፍ ይኖርበታል[47] ። በዚሁ ጊዜ በአገሩቱ ነፃ የምንዛሬ ሥርዓት ይካሄድ ነበር[48]። በዚህ ዓይነቱ አሠራር መሠረት ታትሞ የሚወጣውን የገንዘብ ኖት ልክና ብሎም በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወር ገንዘብ ልክ የሚወሰነው በአገሪቱ ኢኮኖሚ ፍላጐት ሳይሆን ከውጪ ጋር በሚደረገው የንግድ ሚዛን (በትክክለኛው አገጋገር በክፍያ ሚዛን) ይሆናል። የንጉሠ ነገሥቱን የመንግሥት ግምጃ ቤት ግዴታ ለጊዜው ተወት አድርገን በውጭ አገር ቡናውን በአንድ ሺህ ብር የሸጠ አንድ የቡና ላኪ እናስተውል ፥ የኢት. መንግሥት ባንክ ይህን አንድ ሺህ ብር ሊከፍል የሚችለው የዚህኑ ያህል የውጭ አገር ምንዛሬ በጁ ሲያስገባ ነው ። ይኸው ላኪ(ወይም ሌላ ነጋዴ) በውጭ አገር ምንዛሬ ዋጋው አንድ ሺህ ብር የሚሆን ሸቀጥ ወደ አገር ያስገባ እንደሆነ ይህንኑ ያህል ገንዘብ ለኢት መ. ባንክ ማስረከብ አለበት ። እንደገና ለአገላለጽ እንዲቀል ከዚሁ ከመቶ ሃያ አምስት (25%) ግምጃ ቤት ግዴታ ድጋፍ ከሚለው ብንነሳ በመንግሥት ባንክ የሚወጣው የገንዘብ ኖት ልክና ብሎም በኢኮኖሚው ውስጥ በዝውውር ያለ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ይኸውም ከባንኮች ውጪ ያለ ገንዘብ ፥ የተጣራ ተንቀሳቃሽ ማጠራቀሚያ ሂሳብ ጠቅላላ ድምር ወደ ውጪ የሚወጡት ዕቃዎች ሸቀጦች ዋጋ ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡት (ዕቃዎች) ሸቀጦች ዋጋ የሚያሳየውን ብልጫ ያህል ይሆናል ። የገቢና የወጪ የንግድ ዕቃዎች ዋጋ ተስተካክሎ ሲገኝ ለውጪ ዕቃዎች ንግድ የሚወጣው የገቢ የንግድ ዕቃዎችን ሥራ ለማካሄድ ባንኩ በሚያወጣው ኖት የሚጣጣ ስለሆነ ተጨማሪ ኖቶች አይወጡም ።

ይህም ማለት የአገር ውስጥ የገንዘብ አወጣጥ በመሠረቱ የሚፈጸመው የአገር ውስጥን ፍላጐት ሳይመለከት በባንኩ የተያዘው የኢንተርናሲዮናል መጠባበቂያ ሂሳብ መሠረት ነው ። የአገር ውስጥ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንደፈለገው ቢሆን ባንኩ ለማንኛውም ዓይነት ተግባር ቢያንስ በመቶ ሰባ አምስት (75%) ያህል በሆነ የውጭ ሀብት ያልተደገፈ የገንዘብ ኖቶች ሊያወጣ አይችልም ።

ይህ አሠራር የአገሪቱን የገንዘብ ቦርሳ በውጭ ኃይሎች ቁጥጥር ሥር በማድረጉ ብቻ አገሪቱ ነፃ ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚያስፈልጋትን ጉልበት የመስለብና የማዳከም ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ ነበረው ። ስለዚህም የብሔራዊ ኢኮኖሚው እንቅስቃሴ አቅጣጫና ፍጥነት በአገሪቱ ውስጥ በሚዘጋጁ ፖሊሲዎች ሳይሆን በዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የሚገዛና የሚታዘዝ ነበር። በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረው ገንዘብ መጠን በክፍያ ሚዛን የሚወሰኑ እውነታና ፤ የወደፊቱ ወደ ውጭ የሚላኩና የማይላኩ ዕቃዎች ምርት ቀደም ብለው የተፈጸሙትና ወደፊትም የሚጠበቁት ተግባሮች ክንውን ስለሆነ ፥ የምርትና ለሥራ ዕድል እድገት እንዲሁም የአገሪቱ የገቢ ንግድ ዕቃዎች ፍላጐት የውጭው ዓለም ከአገሪቱ በሚፈልገው ውጤት ጥብቅ ቁጥጥር ስር ዋሉ ።

የንግድ ሚዛንን መዛነፍ ሁኔታ እንኳ ወደ ጐን ብንተው ይህን የመሰለው የኖቶች አወጣጥ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ መረጋጋትም አደገኛ ነው ። የንግድ ሚዛን ወደ አገሪቱ አድልቶ ሲገኝ ወይም ጥሩ አዝማሚያ ሲኖረው የገንዘብ አወጣጥና ፍላጐትም ይጨምራል ። ይህም ፍላጐትን ለመምራት የሚያስፈልጉ የአሠራር መዋቅሮች በሌሉበት የገንዘብ ኃይል መድከምና የዋጋ ሙናርን ያስከትላል ። በአንጻሩ ደግሞ የንግዱ ሚዛን ለአገሪቱ ተስማሚ ባልሆነ ሁኔታ ላይ ሲሆን የአ ገር ውስጥ የገንዘብ አወጣጥንና ፍላጐትን እንዲሁም የዋጋ መውደቅን ብሎም የምርት ውጤት መቀነስን ያስከትላል ። በአጠቃላይ አመለካከት ይህ አሠራር የውጭ እንቅስቃሴ በቅድሚያነት ተወስዶ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በተቀጥላነት ከርሱ ጋር እንዲገናዘብ የሚጠይቅ በመሆኑ ባጭሩ ሊሳካ የማይችል ሁኔታ ነው እንላለን ።

በቡና ዋጋ መውደቅና ከዚሁ ጋር በተያያዙ እላይ ጠባያቸው በተጠቀሰው ችግሮች ሳቢያ በ1949 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) መንግሥቱ የአገር ውስጥ የገንዘብ ኖቶች የሚወጡበትን መሠረት መለወጥና በዚያውም የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ መቆጣጠሪያ ሥርዓትን የማቋቋም አስፈላጊነት ሊገነዘብ ቻለ ። ከ1949 እስከ 1950 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ባለው ጊዜ ሁለት ዋና ዋና ሕጐች ወጥተው ነበር ። አን ደኛው የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ሥራን ለመቆጣጠር ያስቻለ ሲሆን[49] ሌላ ኛው ደግሞ በአገር ውስጥ የሚወጡ ኖቶች በትንሹ በመቶ ሰባ አምስት (75%) በሚ ገመት የውጪ ሀብት መደገፍ የነበረባቸውን ቢበዛ ወደ ከመቶ ሠላሳ (30%) ዝቅ እንዲልና ቀሪው ሂሳብ በን.ነ.መ. የግምጃ ቤት ግዴታዎች እንዲሟላ ያደ ረገው ነው[50]። ይህ በአገር ውስጥ ሕጋዊ ገንዘብና በውጪ ሀብት መካከል ላለው ግንኙነት የተሻሻለ ማብራሪያ የሆነው ሕግ አንደኛው የገንዘብና የባንክ አዋጅ (ገባአ 1) ወጥቶ ሚዛኑን ቢበዛ በመቶ ሃያ አምስት (25%) እንዲሆን እስካደረገው ጉስከ 1963 እ.ኤ.አ. ዓ.ም. ድረስ ሲሠራ ቆይቷል[51]። ስለዚህም ከ1950 እስከ 1963 ዓ.ም. ድረስ የአገር ውስጥ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች እትመትና የዚሁ ውጤት የሆነው የአገር ውስጥ የገንዘብ አወጣጥ በአገሪቱ የውጪ ሀብት የመወሰኑ ሁኔታ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ለመምጣት ችሏል ።

በገባአ2 መሠረት ንንደቀድሞው ለኢት.ብ.ባ. የገንዘብ ኖቶችን የማውጣት ብቸኛ ሥልጣን ሲሰጠው በዚያው ደግሞ ካለው ሀብት በከፊል በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲያኖር ይጠበቅበታል[25]። ይሁንና ትልቁ ነገር በሚወጡት ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች መጠንና በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ ውስጥ በሚኖረው ንብረት መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዲኖር አለመ ደረጉ ነው ። በአንፃሩም በአዋጁ መንፈስ በቀጥታም ባይሆን የምንረዳው የሚ ወጡት የኖቶች ብዛት በአገሪቱ ኢኮኖሚ ፍላጐት መሠረት መሆኑንና በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ የሚኖረው ንብረት ግምት ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋ ፤ እንዲሁም ለዕዳ መክፈያ የሚወጣውን መሸፈን መቻል አለበት ። በዚህም መሠረት ገባአ2 በአገር ውስጥ ሕጋዊ ገንዘብ እትመትና ብሎም በአገሪቱ የገንዘብ አወጣጥና በዓለም አቀፍ የመጠባበቂያ ሂሳብ መካከል የነበረውን መተሳሰር በማስቀረት ፣ ለአንድ አገር ነፃ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ምንም አማራጭ የሌለውን ከውጪ ተጽዕኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ በብሔራዊ አመራር የሚ ካሄድ የኢኮኖሚ ፖሊሲን ለማጠናከር ለሃያ አምስት ዓመታት ያህል ሲካሄድ የቆየውን ሂደት ከፍጻሜ አድርሶታል ።

ለ/ የገንዘብ አወጣጥና የክሬዲት ሥራ በኢ.ብ.ባ. ቁጥጥር ሥር መዋሉ

የአገር ውስጥ ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች እትመት (እና ስለዚህም የአገሪቱ የገንዘብ አወጣጥ) ከአገሪቱ ቁጥጥር ውጪ ከሆኑና ከብሔራዊ ጥቅም ጋር ሊጋጩ ከሚችሉ ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች መሪር ተጽዕኖ የማላቀቁ እርምጃ መልካም አዝማሚያ የሚታይበት ሲሆን (አዋጁ) ገባአ2 የኢ.ት.ብ.ባ.ን ኃላፊነት በበለጠ ሰፋ ብሎ የሚከተሉትን እንዲጨምር አድርጓል ፤ እነዚህም ፥ (1) የተመዛዘነና የተፋፋመ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲሠፍን የመርዳት ፥ (2) ከፍተኛ ምርት ፤ ሥራና ገቢን የማራመድን የማጠናከር ፥ (3) በገንዘባዊ ተቋሞች አማካኝነት የገንዘብን መጠን ከፍላጐት ጋር በማጣጣም የኢትዮጵያን የምርት ኃይሎች ዕድገት ማበረታታትና ማራመድ ናቸው ። የገንዘብ አወጣጥ መሠረቱ በመጀመሪያ ደረጃ የሚወጡት ሕጋዊ የገንዘብ ኖቶች ቀጥሎም በሌሎች ዋና ዋና ተቋሞች ማለትም በመንግሥት ፥ በሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች እንዲሁም የባንክ ሥራ ባልሆነው የግል ክፍለ ኢኮኖሚ የገንዘብ አጠቃቀም ስለሆነ ከውጪ ኃይሎች ተጽዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ በኢኮኖሚ ውስጥ የሚዘዋወረውን የገንዘብ ልክ ከፍላጐት ጋር በትክክል አጣጥሞ በ ተግባር የመተርጐሙ ጉዳይ የሚወሰነው ባንኩ በራሱ ላይ ባለው ቁጥጥርና ከነዚህም ሶስት ተቋሞች ጋር በሚፈጸሙ የሥራ ግንኙነት ዓይነት ይሆናል ። ከነዚህም ሁለት ዓይነት ችግሮችን በቀላሉ ለመወጣት ይቻላል ። አንደኛ ባንኩ በራሱ ላይ የሚኖረውን ቁጥጥር በሚመለከት ረገድ በዕድሜም የጠና በመሆኑ በሚፈጽማቸው ማናቸውም ተግባሮች በጥንቃቄ የተጠኑና የበሰሉ እርምጃዎችንም የመውሰድ ኃላፊነት በሚገባ ሊሸከም ችሏል በሚል ግምት ላይ የተመሠረተ ነው ። ሁለተኛ የባንክ ሥራን በማይጨምረውና ከባንኩ ቀጥታ ቁጥጥር ውጪ የሆነውን (እና እስከ መስከረም 1979 ዓ.ም. እንደ ኤ.አ.አ. (በመቶ ሰባ ስድስት (76 %) ያህል የሚሆነው ከባንኮች ውጪ የሆነ ገንዘብ የያዘ [53]) የግል ክፍለ ኢኮኖሚ በሚመለከት ፥ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች የሚጠይቁትን ወይም የሚከፍሉትን (እንደሁኔታው) የወለድ ደረጃ በመወሰንና ደምበኞቻቸውም ካሁኑ በበለጠ ሁኔታ የገንዘብ ድርጅቶቹ በሚሰጡት አገልግሎት እንዲጠቀሙ በመገፋፋት በገንዘብ ሀብታቸው አመራር ባንኮችን እንዲጠቀሙ በማድረግ የቁጥጥር ኃይሉን ሊያጐለብት ይችላል ። በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች በኩል ገንዘብ ነክ ሥራዎችን መቆጣጠርና ባንኩ ከመንግሥት ጋር ያለው ግንኙነት ይበልጥ ውስብስብ በመሆናቸው ባጭሩ ለመግለጽ እንሞክራለን ።

1/ ባንኮች ፥ ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችና የኢ.ት.ብ. ባንክ

ከውጪ ሁኔታዎች ጋር በቀጥታ ያልተሳሰረ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማካሄድ ብርቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር በመሆኑ በትጋትና በብልሃት መያዝ ይኖርበታል ። በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረው የገንዘብ ልክ ከሚፈለገው በላይ ወይም በታች ከሆነ የአገሪቱ የውስጥ ኢኮኖሚ ሚዛን ተቃውሶ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መዳከምን ወይም የገንዘብ ኃይል መዳከምና የዕቃዎች ዋጋ መናርን ወይም ሁለቱንም ሊያስከትል ይችላል ። ስለዚህም የጊዜው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ፍላጐትና የገንዘብ አወጣጡ ሁልጊዜ ተመዛዛኝነት እንዲኖራቸው ማድረጉ የማያቋርጥ የቅርብ ክትትል የሚያስፈልገው ወሳኝ ተግባር ይሆናል ።

በሁለቱም አዋጆች ማለትም በገባአ 1ና በገባአ2 መሠረት [54] ለኢ.ት.ብ.ባ. የገንዘብ አወጣጥን የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቶታል ። በኢትዮጵያ ሁኔታ ገንዘብ

ማለት ከባንክ ውጪ ያለ ገንዘብንና የተጣራ የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ነው ። እንደ ሁለቱም ሕጎች የመቆጣጠሪያ ዘዴዎቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም ባንኮችንና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችን የሚመለከት አንድ በጣም ጠቃሚ የሆነ ድንጋጌ በገባአ2 ውስጥ በመጨመሩ የኢ.ት.ብ.ባንክ ከገባአ1 ይበልጥ በዚህ አዋጅ ሥር ጠንከር ያለ ሥፍራ አለው ። የገንዘብ አወጣጥን ለመቆጣጠር የኢ.ት.ብ.ባ. ሊጠቀምባቸው ከሚችለው መንገዶች ውስጥ ዋንኞቹ ባጭሩ፣ ሀ/በቀጥታ የግዥና የሽያጭ አሠራር፣ ለ/ ቅናሽ በማድረግና ሐ/ በመጠባበቂያ ሂሳብ ግዴታ ናቸው ። የኢ.ት.ብ.ባ. በነዚህ መንገዶች (በነጠላ ወይም በማዋሀድ) እንዴት እንደሚጠቀም በምሳሌ ለመግለጽ ከላይ በተብራራው መልክ ያለው የገንዘብ ልክ ለኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ከሚፈለገው በላይ ነው እንበል ። በዚህን ጊዜ የፖሊሲው ዓላማ በኢኮኖሚው ውስጥ በዝውውር ያለውን ገንዘብ መጠን መቀነስ ይሆናል ማለት ነው ። ቀጥታ የግዥና የሽያጭ አሠራር ለመጠቀም የወሰኑ እንደሆነ የመንግሥት የዋስትና ሠነዶችን (የግዴታ ሠነዶችን፣ የግምጃ ቤት ሠነዶችን፣ የውል ሠነዶችን፣ ወዘተ.) ለባንኮች ፤ ለሌሎች የገንዘብ ድርጅቶችና ለሌሎች ሰዎች ለመሸጥ [55] በሚያስችለው ሥልጣኑ ይጠቀማል[56]። የኢ.ት.ብ. ባንክ በግዴታ ሠነዶች ሽያጭ ጊዜ የመንግሥት ዕዳ የምስክር ወረቀቶችን በማውጣት ገንዘብ ይሰበስብበታል ። በኢ.ት.ብ.ባ. ውስጥ ያለ ገንዘብ እንደ ውጪ ገንዘብ ስለማይቆጠር ይህ እርምጃ በባንክ ወጪ ካለ ገንዘብና ከማጠራቀሚያ ፍላጎት ውስጥ ለጊዜው የወጣውን ያህል ውጪ ከሚሆነው ገንዘብ ወዲያው ለማጉደል ይችላል ። የኢኮኖሚው ፍላጎት በዝውውር ላይ ካለው ገንዘብ ከፍ ብሎ ሲያገኘው ባንኩ ከላይ የተጠቀሰውን ሂደት መቀልበስ ይኖርበታል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢ.ት.ብ.ባ. የገንዘብ አወጣጥን ለመቆጣጠር የቅናሽ ፖሊሲን ሊከተል ይችላል ። [57] ይህ መንገድ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ከባንኩ እንዲበደሩ በማበረታታት ወይም እንዳይበደሩ ተስፋ በማስቆረጥ ሊሠራበት ሲችል የሚያገኙትም ብድር የክሬዲት ሥራ የመፍጠር ችሎታቸውን ያሰፋል ፤ ይህም በበኩሉ የገንዘብ አወጣጥን ከፍ ለማድረግ የሚችል ነው ። የኢ.ት.ብ.ባ. በአንድ ወቅት በዝውውር ላይ ያለው ገንዘብ ከኢኮኖሚው ፍላጎት ጋር የሚመጣጠን ወይም ከፍላጎት በላይ ሆኖ ሲያገኘውና፣ በዚያው ወቅት ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ደግሞ የደምበኞቻቸውን ፍላጎት ለማርካት ከባንኩ ለመበደር ቢፈልጉ፣ ለነርሱ የሚያበድርበትን ወለድ ተስፋ ሊያስቆርጥ በሚችል ደረጃ ከፍ ያደርጋል ። የገንዘብ አወጣጥ መጨመር አለበት ብሎ በሚያምንበት ጊዜ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ግን የጥሬ ገንዘብ እጥረት ያለባቸው መሆኑን ሲገነዘብ የወለድ ደረጃውን ዝቅ በማድረግ ከርሱ እንዲበደሩ ይገፋፋቸዋል ።

የቀጥታ ግዥና ሽያጭ አሠራርና የቅናሽ ደረጃው አሠራር አስፈላጊ ቢሆኑም የገንዘብ አወጣጥ ከኢኮኖሚ ፍላጎት ጋር ብቻቸውን ፍሬያማ ሊያደርጉት አይችሉም ። ይህ የሚሆነው በባንክ ሥራ ኢንዱስትሪ ሁለት መሠረታዊ ጠባዮች ምክንያት ነው ። የመጀመሪያው እነዚህ ሁለት መንገዶች ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች የመንግሥት ዋስትና ሠነዶችን ለመግዛት (ወይም ለመሸጥ) ወይም ለመበደር ፈቃደኛ ፍላጎት ሲኖራቸው ብቻ በመሆኑ ነው ፤ አለበለዚያ ባንኩ ከፍላጎቱ ጋር እንዲስማሙ የሚያደርግበት ምንም መንገድ የለውም ፤ ሁለተኛ በኢ.ት.ብ.ባ. በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች መካከል የፍላጎት ልዩነት ወይም የጥቅም መጋጨት ሊኖር ይችላል ። የመጀመሪያው ፍላጎት የገንዘብ አቀራረብን ከፍላጎት ጋር ማስተካከል ሲሆን

የኋለኞቹ ግን ትርፍን ማካበት ነው ። በዚህ የተነሳም የኢ.ት.ብ.ባ. የዋስትና ሠነዶችን በመሸጥና ወይም የቅናሽ ደረጃን ከፍ በማድረግ የገንዘብ አወጣጥን መጠን ለመቀነስ ቢፈልግ ፣ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ትርፍ በማካበት ዓላማቸው በመገፋፋት በደምበኞቻቸው የተጠራቀመውን የገንዘብ ሀብት እንደገና በማዘዋወር የገንዘብ አወጣጥ መጠን እንዲያሽቅብ ሊያደርጉ ይችላሉ ። የመጠባበቂያ ሂሳብ መኖር ግዴታና የገንዘብና ገንዘብ አከል ሀብቶች ሚዛን (የክሬዲት ሥራን የመጠንና የዓይነት ቁጥጥር አክሎ)[58] የኢ.ት.ብ.ባ. ፣ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ሊያበድሩ የሚችሏቸውን ሂሳቦች የሚቆጣጠርባቸው መንገዶች ስለሆኑ በጣም አስፈላጊ ሆነው እናገኛቸዋለን[59]። የኢ.ት.ብ.ባ. የመጠባበቂያ ሂሳብ ግዴታን ለመጠቀም ይችላል[60]። ይህን መሣሪያ መጠቀም ማለት ባንኩ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ከእዳቸው ውስጥ በመቶ የተወሰነውን ያህል በራሱ ሂሳብ እንዲያጠራቅሙ ሲያስገድድ ይህን ገንዘብ ለማበደርም ሆነ ለማንኛውም ነገር እንዳይጠቀሙ ያደርጋሉ ማለት ነው ። በዚሁ ዓይነት እንዲጠራቀም የተወሰነውን የገንዘብና የገንዘብ አከል ንብረቶች ሚዛን ለመሸፈን የተቀመጡት ሀብቶች ለሌላ ምንም ዓይነት ተግባር ሊውሉ አይችሉም[61]።

የቀጥታ ሽያጭ ግዥ የቅናሽ ደረጃ አሠራር ድንጋጌዎች ያለምንም ለውጥ ከገባአ 1 ወደ ገባአ2 በቀጥታ የተላለፉ ሲሆን[62] የመጠባበቂያ ሂሳብ ግዴታንና የገንዘብና ገንዘብ አከል ንብረቶች ሚዛንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች የማይናቁ ማሻሻያዎች ተደርገውላቸዋል ። በገባአ1 ይኸው ሥልጣን ለኢ.ት.ብ.ባ. የተሰጠው ቢሆንም የመጠባበቂያ ሂሳብ ግዴታው ከፍተኛ ጣሪያ ከእዳው በመቶ ሀያ (20 %) እንዲሆን ሲደነገግ ፣ ከአጭር ጊዜ ክፍያ እዳው የሚጠራቀመው የገንዘብና ገንዘብ አከል ንብረቶች ሚዛንም እንደዚሁ ከመቶ ሰላሳ (30 %) እንዲሆን ወስኗል[63]። ይህም ማለት ገንዘብ በገፍ በዝውውር ላይ በሚሆንበት ጊዜ እንኳን ባንኮቹና ሌሎቹ የገንዘብ ድርጅቶቹ ከሚጠራቀመው እዳቸው ውስጥ በመቶ ሰማኒያውን(80 %) ከአጭር ጊዜ ክፍያ እዳቸው ደግሞ ከመቶ ሰባ (70 %) ያህሉን እንደልባቸው ለማበደር ስለሚችሉ በጊዜው የኢኮኖሚው ፍላጐት የሚጠይቀውን የገንዘብን ቅነሳ ፖሊሲ ሊያጨናግፉ ይችላሉ ። ይህንን ችግር በመገንዘብ ይመስላል የገባአ2 አዘጋጆች ከተጠራቃሚና ከአጭር ጊዜ ክፍያ እዳው መያዝ ያለበት የመጠባበቂያ ሂሳብ መጠን የመወሰን ሥልጣን ለባንኩ በመተው ባንኮቹና ሌሎቹ የገንዘብ ድርጅቶች ሊያበድሩ በሚችሉት ሂሳብ ላይ የመቶ በመቶ (100 %) የቁጥጥር ችሎታ እንዲኖረው ያደረጉት[64]። ይህም ባንኩን ከቀድሞ በተሻለ ሁኔታ ላይ ያደርገዋል ። በነዚህ ድንጋጌዎች አማካኝነት የኢ.ት.ብ.ብ. ተፈላጊውን ውጤት እንደሚያስገኝ አድርጐ የመጠባበቂያና የጥሬ ገንዘብ ሚዛኑን በፈለገው አቅጣጫ ሊለዋ ውጠው ይችላል ።

2/ የክሬዲት ሥራ ቁጥጥር

በገባአ1 ሥር የኢ.ት.ብ.ባ.[65] በሚያወጣቸው ደምቦች አማካኝነት ለባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች ክሬዲት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማስታወቅ ፣ ሁሉም ፤ ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ለደምበኞቻቸው በሚሰጡት ልዩ ልዩ ዓይነት ብድሮች ላይ የሚያስከፍሉትን ወለድ ደረጃና እንዲሁም ፣ የብድሩን ሁኔታ ፤ ጊዜ ፣ ተግባርና ወሰን ሊቀይስ ይችላል ። እነዚህ በቀጥታ ወደ ገባአ2 የተላለፉ ሲሆን[67] የኢ.ት.ብ.ባ. በሕዝብ ባለቤትነት ሥር ያሉ ድርጅቶች በቁጥጥራቸው

ሥር የሌሎችን ሀብቶች ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ በሆነ ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማረጋገጥ የሂሳብ መዝገባቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችለውን[67] ሥልጣን ተግባራዊ የሚያደርግበት ድንጋጌ በገባአ2 ተጨምሯል ። ባንኩ በሕዝብ ባለመብትነት ሥር ያሉ ድርጅቶች ሀብቶቻቸውን ያለአግባብ የሚጠቀሙበት መሆኑን ሲያምን ባንኮቹና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ምንም ዓይነት ብድር እንዳይሰጣቸው ሊያዝ ይችላል[68] ስለዚህ የኢ.ት.ብ.ባ. ለአገሪቱ እድገት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ሥራዎች አስፈላጊውን ብድር እንዲያገኙና ለኢኮኖሚው ጠቅላላ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የብድሩን መጠን የመወሰን ብቻም ሳይሆን የአገሪቱ ሀብቶች በትክክል ጥቅም ላይ መዋላቸውንም ለማረጋገጥ ይችላል ።

ሐ/ የመንግሥትና የኢ.ት.ብ.ባ. ግንኙነት

በመንግሥትና በኢ.ት.ብ.ባ. መካከል ያለው ግንኙነት በገባአ2 ሥር የበለጠ የተጠናከረ ነው ። በገባአ1 ሥር በኢ.ት.ብ.ባ.ና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት በባንክና በአንድ ደምበኛ መካከል የሚኖር ዓይነት ሲሆን በገባአ2 ሥር ፤ ሀ/ የገንዘብ መረጋጋትንና የክፍያ ሚዛንን ለመጠበቅ ለ/ ኪሲራውን ለመሸፈን ለመንግሥት የፊናንስ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በመንግሥቱ የፊናንስ ፕላን ዝግጅት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል[69]

ሁለተኛም አዋጁ መንግሥት ከኢ.ት.ብ.ባ. በሶስቱም የቀጥታ ብድር ፣ የግምጃ ቤት ሠነዶች ፡ የመንግሥት ዕዳ ሠነዶች መንገድ የሚያገኘው ብድር የሚታሰብበትን መደብ ቋሚ እንዲሆን አድርጎታል ። ካሁን ወዲያ መደቡ በአለፈው የበጀት ዓመት የተሰበሰበው መደበኛ ገቢ ይሆናል ። በተጨማሪም መደበኛውን ገቢ ከብድሩ መጠን ጋር ያለውን ሚዛን ከፍ በማድረግ የቀጥታ ብድሩ ሩብ ፣ የግምጃ ቤት ሠነዶች ሲሶና የመንግሥት እቃ ሠነዶች ግማሽ ያህል እንዲሆን አድርጓል ። የመደቡ ለውጥ ፤ የሚዛኖቹ ከፍ ማለትና የወለዱ ጣሪያ በመቶ ሶስት (3%) እንዲሆን መወሰን ሁሉ መንግሥት ለሚያከናውናቸው ተግባሮች ለሚያስፈልጉት የፊናንስ አገልግሎቶች በቂ ገንዘብ እንዲያገኝ ለማስቻል ነው[70]።

ከኢ.ት.ብ.ባ. ወደ መንግሥት የሚተላለፈው ገንዘብ መጠን ከፍ ማለትም መንግሥቱ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ የሚጫወተውን ግንባር ቀደምሚናና ፣ ኃላፊነቱም ቢያንስ ቢያንስ ካሁኑ ሁኔታ ለመገመት እስከምንችልበት ጊዜ ድረስ ከገቢው በጣም የላቀ ወጪ እንዲደረግ የሚጠይቅ ከመሆኑ አንፃር ስናየው ተገቢ ይሆናል ።

አዋጁና የኅብረተሰቡ ግብ አለመጣጣም

የኢትዮጵያ አብዮት ዓላማ ኅብረተሰባዊነትን መገንባት መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ የተገለጸ ሲሆን ለዚህም ማናቸውም ገንዘብ ነክ ድርጅቶች በአመቺ ሁኔታ በታለመው ግብ አቅጣጫ አገልግሎታቸውን ማበርከት እንዳለባቸው አሌ የማይባል ሐቅ ነው ። ዳሩ ግን 1976ቱ አዋጅ ይህንን መሠረታዊ ዓላማ የሚቃረኑ አንዳንድ ሀሳቦች ያዘለ ሲሆን ዋና የሆኑት ሁለቱ ከዚህ በታች ተገልጸዋል ።

ሀ/ <u>ነፃ ውድድር ስለመፍቀድ</u>

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና በሌሎች ባንኮች የገንዘብ ድርጅቶች በተለይም በንግድ ባንኮች ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ከአንድ በላይ በመሆናቸው በማይቃረን ውድድር ተግባራቸውን ያከናውናሉ በሚል ግምት ላይ የተመሠረተ ነው ። ሆኖም ግን በሶሻሊስት አገሮችና በሌሎችም የኅብረተሰባዊነት መርሖ የሚከተሉ አገሮች የባንኮች ይዞታ ልምድ አንድ ማዕከላዊ የሆነ ባንክና በርሱ ቁጥጥር ሥር ዘመናዊ የአሠራር ስልትን የሚከተሉ ሌሎች ባንኮች መኖራቸውን ሲያስተምረን በመካከላቸው ምንም ዓይነት ውድድር አለመኖሩን ያስረዳል ። በኢትዮጵያ የባንኮች ዕድገት ሁኔታ ባለው አንድ የንግድ ባንክ አንፃር ከላይ የተጠቀሰውን ግምት የመከተሉ አዝማሚያ ተስፋ አነስተኛ ይሆናል ። ይህ አባባል በዚህ በኩል ያለውን ዕድገት ይቃወማል ማለት ሣይሆን ሕጉ በዝምታ ነፃ ውድድርን የመፍቀዱ ጉዳይ ከተያዘው ዓላማ ጋር የማይጣጣም አለመሆኑን ለማሳየት ነው ።

ለ/ ሁለተኛውና ከፍተኛ አለመጣጣም መኖሩን የሚያሳየው በብሔራዊ ባንኩና በመንግሥት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ነው ። የሶሻሊስት ኢኮኖሚ በማዕከላዊ ፕላን ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ያለው አከራካሪ ጉዳይ የታቀደው ፕላን ተግባሩን በሥራ ላይ ለማዋል የገንዘብ ምንጮች ለዚህ ዓላማ ተገዥ መሆን አለባቸው ወይስ ፕላኑን በሥራ ላይ ለማዋል በቅድሚያ ወሳኙ የገንዘቡ መገኘት ጉዳይ ነው የሚለው ጭብጥ ነው ።

በኢትዮጵያ ሁኔታ የንግድ ባንኩ ሌሎች ባንኮችና የገንዘብ ድርጅቶች በማዕከላዊ ባንክ ቁጥጥር ሥር በመሆናቸው የተነሳ የመንግሥት የገንዘብ ምንጭ ከነዚሁ ብቻ በሚቀርብለት ላይ የተወሰነ ስለሆነ ከላይ ከተነሳው ጭብጥ ሁለተኛው አቀራረብ የሚያዋጣ አይመስልም ።

<u>መ ደ ም ደ ሚ ያ</u>

ገባአ2 ምንም እንኳ ከአንቀጾቹ ብዙዎቹን ከቀደሙት ሕጎች የወረሰ ቢሆንም በአገሪቱ የገንዘብ ፖሊሲና በአመራሩ ከፍተኛ ለውጦች አድርጓል ።

የአገሪቱን የውስጥ የገንዘብ ፖሊሲ ለመጀመሪያ ጊዜ ከውጭ ኃይሎች ሸክምነት ወጥቶ ራሱን ችሎ እንዲቆም ፣ መንግሥት ሊጠቀምባቸው የሚችለውን የገንዘብ ሀብት መጠን ለመጨመርና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገሪቱን የገንዘብ ሥርዓት የመቆጣጠር ሥልጣን ከፍ ለማድረግ ችሏል ። ሆኖም ግን እነዚህ የታዩት መሻሻሎች የሚያኮሩ ቢሆኑም ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች በወለድ ደረጃዎችና በውስን በብድር አሰጣጡም በኩል በደምበኞቻቸው አካባቢ ብቻ የተወሰኑ ናቸው ። እነዚህ ሥልጣኖች ከጠቅላላው የገንዘብ አወጣጥ ጋር ሲመዛዘኑ ከባንክ ውጭ ያለው ገንዘብ ዝቅተኛ ሆኖ ለሚታይባቸው አገሮች በቂ ሲሆኑ ሶስት አራተኛው የሚወጣው ገንዘብ ከባንኮች ውጪ በሆነበት ኢትዮጵያ ውስጥ ግን አጥጋቢ አይደሉም ። ይህንን ግዙፍ የተበተነ ሀብት ሰብስብ አድርጎ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ መንገዶችን የሚፈጥር ጠበቅ ያለ የገንዘብ ፖሊሲ አስፈላጊ ነው ። ይህ እስኪሆን ግን የኢት.(ብ)ባንክ የገንዘብ አወጣጥን የመቆጣጠር ችሎታ ያልተሟላ ሆኖ ይቆያል ።

የግርጌ ማስታወሻ

* ረዳት ፕሮፌሰርና የምርምር ተባባሪ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

1. ስለባንክና ስለባንክ አገልግሎት ታሪክ ኢትዮጵያ ኦብዘርቨር ቅጽ 8 ቁ. 4 ይመልከቱ ፡
2. የገንዘብና የባንክ አዋጅ 1963 ዓ. ም. (እ. ኤ. አ) ?.ዋጅ ቁ. 206 ና የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ አዋጅ 1963 ዓ.ም. (እ. ኤ. አ.) አዋጅ ቁ. 211
3. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቻርተር 1963 ዓ.ም. (እ. ኤ. አ.) ትዕዛዝ ቁ. 30
4. ቻርተሩና አዋጅ ቁ. 206 በየጊዜው የተሻሻሉ ስለሆነ በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀምነው ለመ ጨረሻ ጊዜ በተሻሻሉት መሠረት ነው ።
5. ቻርተር አንቀጽ 8
6. ገባአ1 አንቀጽ 2
7. ቻርተር አንቀጽ 3
8. አንቀጽ 6
9. በአንቀጽ 2(5) (ሀ) ና (ለ) ሥር የተብራራ
10. አንቀጽ 9 (8)
11. አንቀጽ 9(7)
12. አንቀጽ 9(6)
13. ምዕራፍ 3 ከአንቀጽ 9— 14
14. ቻርተር አንቀጽ 9 እና ገባአ2 አንቀጽ 10 በቅደም ተከተሉ
15. ገባአ2 አንቀጽ 12(1) እና የቻርተሩን አንቀጽ 11(1) ፡ ገበአ2 አንቀፅ 12(2) እና የቻርተሩን አንቀጽ 12(2) ፤ ገባአ2 አንቀጽ 12 (3) (ሀ) እና (ለ) እና የቻርተሩን አንቀፅ 11 (3) (ሀ) እና (ለ) ን በቅደም ተከተል ይመለከቷል
16. የቻርተሩ ምዕራፍ አራት ከአንቀጽ 15—21
17. የገንዘብና የባንክ አዋጅ ማሻሻያ ድንጋጌ ቁ. 54/1969 (እ.ኤ.አ) (ከዚህ በታች ድንጋጌ ብለን የም ንጠራው)
18. አንቀጽ 13(3) ፤ (4) ፤ 7
19. ድንጋጌ አንቀጽ 2(ሀ) ና ገባአ ፤ አንቀጽ 29 እና 26(3)(ሀ)
21. ድንጋጌ አንቀጽ 2 (6)
22. አንቀጽ 26(3) (ለ) (3)
23. ድንጋጌ አንቀጽ 2(ሐ)
20. አንቀጽ 26(3)(ሀ)
24. አንቀጽ 26(3)(ሐ)
25. በምዕራፍ አራት ክፍል ሶስት ውስጥ የሚገኙትን አንቀጾች ያገናዝቡ
26. ገባአ 2 አንቀጽ 20—35 እና ገባአ 1 አንቀጽ 15—20
27. ገባአ 1 አንቀጽ 18ና ገባአ 2 አንቀጽ 33
28. ገባአ 1 አንቀጽ 13(5) እና ገባአ 2 አንቀጽ 26(3) (ለ) (2)
29. ገባአ 1 አንቀጽ 38(1) እና ገባአ 2 አንቀጽ 50
30. ገባአ 1 አንቀጽ 21—23 እና ገባአ 2 አንቀጽ 36—38
31. አንቀጽ 9(3)
32. አንቀጽ 37
33. አንቀጽ 49
34. ገባአ 1 አንቀጽ 3(1)
35. አንቀጽ 51
36. አንቀጽ 3(3)
37. አንቀጽ 52
38. ገባአ 1 አንቀጽ 8(1) ና ገባአ 2 አንቀጽ 60(1)
39. ገባአ 1 አንቀጽ 8(2)
40. አንቀጽ 60(1) ና (2)
41. አንቀጽ 61—67
42. አንቀጽ 69—74
43. አንቀጽ 68
44. ምንም እንኳ የባንክ ደብተሮችን በግል በምስጢር መያዝ ስለመቻሉ በ1943ቱ (እ. ኤ. አ.) የኢትዮ ጵያ ባንክ ቻርተር የተደነገገ ቢሆንም በገባአ 1 ግን ይህ አንቀጽ አልተጨመረም ነበር ።
45. የገባአ 2 ን (ችግሮች) እንከኖችና የገንዘብ ፖሊሲውን ውጤታማነት በሚመለከት በሌላ ሥራ ውስጥ የታተተበት ጉዳይ ስለሆነ እዚህ እንመለስበትም ፤ ለዚህም ከበፊቃዱ ደግፌ ሞነታሪ ፖሊሲ ፎር ዘ ሞብላይዝሽን ኤንድ ኢፊክቲቭ ዩቲሊዜሽን ኦፍ ፋይናንሻል ሪሶርስስ ገጽ 80—158 ያለውን ይመልከቱ

46. በ1945(እ. ኤ. አ) የወጣ የገንዘቦችና የሕግ ገንዘቦች አዋጅ አንቀጽ 3 (አዋጅ ቁ. 76)
47. አንቀጽ 4
48. እስከ 1949 ዓ. ም. (እ. ኤ. አ.) የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ቁጥጥር አልነበረም ። የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ማሻሻያ አዋጅ (የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ. 127) ፤ 1949 (እ.ኤ.አ.) የወጣውን ይመልከቱ
49. የ1949(እ. ኤ.አ.) የገንዘብ ምንዛሬ አዋጅ ማሻሻያ) የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 127/1949
50. የ1950(እ.ኤ.አ) የገንዘቦችና የሕግ ገንዘቦች አዋጅ ማሻሻያ (አዋጅ 112/1950)
51. የገባእ 1 አንቀጽ 8(1)
52. አንቀጽ ሰባትና ስድሳን በተከታታይ ይመለከቷል ።
53. የኢት. ብ. ባ. በየሶስት ወሩ የሚወጣ መጽሔት (ኳርተር ሊቡለቲን) ቅጽ 6 ቁጥር 1 ፤ መጋቢት 1960 ።
54. አንቀጽ 2(9) እና 9(1) በተከታታይ
55. አንቀጽ 26(1) (ለ) ና አንቀጽ 26(3) (ሐ)
56. አንቀጽ 26(3(ለ) (4) ከላይ ከተጻፈው ሌላ
57. አንቀጽ 31
58. አንቀጽ 50 እና አንቀጽ 9(2) እንዲሁም የገባእ 2 አንቀጽ 34 በተከታታይ
59. የመጠባበቂያ ኃብት ግዴታና የገንዘብና ገንዘብ አከል ንብረቶች ሚዛን ሌላ መለስተኛ ዓላማቸው ባንኮችና ሌሎች የገንዘብ ድርጅቶች ኪሳራ ሲደርስባቸው ለደንበኞች የተጠራቀመ ሂሳብ ዋስትና በከፊል እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው ።
60. አንቀጽ 33
61. ባሁኑ ጊዜ ለመጠባበቂያ የሚያስፈልገው ገንዘብ በተጠየቀ ጊዜ ለሚከፈሉ ሂሳቦች በመቶ አሥር (10)%፤ ለቁጠባ ሂሳቦችና ለተወሰነ ጊዜ ለሚቀመጡ ሂሳቦች በመቶ አምስት (5%) ነው ።
62. አንቀጽ 13(2) (ለ) ፣ 13(4) ፣ 13(5) 13(6) እና የገባእ 1 ን አንቀፅ 16 ከላይ ከተጠቀሱት የገባእ 2 አንቀፆች ጋራ ያስተያዩ
63. የገባእ 1 አንቀጽ 18(1) እና አንቀፅ 38 (1) በተከታታይ
64. አንቀጽ 33 ና 50
65. አንቀጽ 15—23
66. አንቀጽ 30—35
67. አንቀጽ 9(8)
68. አንቀጽ 9(7)
69. አንቀጽ 9(15) እና 26(2)
70. ከታህሣሥ ወር 1979 (እ. ኤ. አ.) የመንግሥት የአገር ውስጥ ዕዳ ብድር በጠቅላላው 1.2 ቢሊዮን ብር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 26%ቀጥታ ብድር ፣ 24% የግምጃ ቤት ሰነዶች (የተሰፋ ሰነዶችን ጨምሮ) እና ቀሪው 50%በመንግሥት ዕዳ ሰነዶች መልክ ነው ። ለዚህም በየሶስት ወሩ ታትሞ የሚወጣውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ (ኳርተርሊ ቡለቲን) ቅጽ 6 ቁ. 1 መጋቢት 1980 (እ.ኤ.አ)ይመለ ከቷል

የተመረቱ ዕቃዎች ለሚያስከትሉት ጉዳት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ያለው ኃላፊት*

በጆርጅ ክሽቺኖቪች**

መ ግ ቢ ያ

በሞያው የተለየ ዕውቀት ላላቸው የጉባኤው ተሳታፊዎች የቀረበው የዚህ ዘገባ ውስብስብነት ለነገሩ እንግዳ ለሆኑ አንባቢዎች ግር ሳይላቸው አይቀርም ። ለነዚሀ ሰዎች ጥቅም ሲባል ይህ መግቢያ ቀለል ባለ መንገድ የጽሑፉን ፍሬ ሀሳብ ለማቅረብ ይሞክራል ።

«የተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት» ኢትዮጵያ አሁን ከተሰማራችበት ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተያያዘ አዲስና አወዛጋቢ የሕግ ጽንሰ —ሀሳብ ነው ። የኢንዱስትሪ መስፋፋት ብዙ ጥቅም ያስገኛል ፤ ሆኖም ጠቃሚ የሆኑት ውጤቶች (ለምሳሌ ሞተር ተሽከርካሪ ወይም መድኃኒቶችን የመሳሰሉት) ከሚያስከትሉት አደጋ ተነጥለው አይታዩም ። በአስተዳደር ሕግ ከሚወሰኑት ሁኔታዎች አንዱ የዕቃዎችን አሠራር የንግድ ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታን አስቀድሞ በመቆጣጠር ለሕዝብ ገበያ ላይ የሚውሉ ዕቃዎች ተገቢውን ደረጃ ያሚሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው ። በአንፃሩ ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ከሚወሰኑት ሁኔታዎች አንዱ (ዋናው ጉዳያችን) እነዚህ የአስተዳደር ጥንቃቄዎች ቢኖሩም አንድ ሰው ዕቃውን በተገቢው መንገድ ሲጠቀምበት ጉዳት ቢደርስበት በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ዘግየት ብለው የተገለጹት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ፤ የተጐዳው ሰው በዕቃ ሠሪው መካሱን ማረጋገጥ ነው ። ይህን በሚመለከት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2085 ለዕቃዎች አላፊነት የተደነገገው ሕግ እንዲኖረው የታለመው ከፍተኛ ሚና እንደሚከተለው ሊብራራ ይችላል ።

1. በተበላሸ የቆርቆሮ ምግብ ጉዳት የደረሰበት ተጠቃሚ ባልተለመደው አሠራር የቆርቆሮውን ምግብ በቀጥታ ከሠሪው የገዛው ሲሆን ሠሪውን በውል (ቁ.2287 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች) ሊከሰው ይችላል ።

2. የዚሀ ዓይነቱ ቀጥተኛ መገበያየት ከሌለ ተጠቃሚው ሠሪውን ከውል ውጭ በሚደርስ አላፊነት ሊከሰው ይችላል ። ይኸውም ፤

   ሀ. እቃ ሠሪው በዕቃው አሠራር ላይ ጥፋት መፈጸሙን ሊያስረዳ ከቻለ (ቁ.2028 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች) ባልተለመደው ሁኔታ ፤ ወይም

   ለ. ጉዳቱ የደረሰበት የተበላሸውን ዕቃ (የቆርቆሮ ምግብ) በተገቢው መንገድ ሲጠቀምበት (ሲመገበው) መሆኑን ሲያስረዳ ብቻ በተለመደው ሁኔታ ። ይህ ዘገባ የሚመለከተው በቁጥር 2085 የተደነገገውን (አንዳንድ ሁኔታዎች ታክለውበት) መፍትሔ ነው ። ይህም መፍትሄ በዘገባው መደምደሚያ ላይ ተተችቷል ።

በዚህ መጽሔት ውስጥ ዘገባው አንዳንድ ለውጦች ተደርገውበት ቀርቧል ። ክፍል1 መግቢያ ሲሆን በቅድሚያ ለተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት የተደነገገውን ድን ጋጌ እንዳለ ካስቀመጠ በኋላ ጽንሰ ኃሳቡን በማስተዋወቅ ላይ ያተኩራል ። ከዚህ ቀጥሎ በተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት ላይ ለሚቀርብ ክስ መሟላት ስለአለባቸው መሠረታዊ (የአዎንታና የአሉታ) ሁኔታዎች በክፍል 2 ተተንትነዋል ። ክፍል 3 ተዘሏል ። በፊት ክፍል 4 የነበረውና አሁን ክፍል 3 የተባለው የጽሑፉን መደምደሚያ የያዘ ሆኖ የተመረቱ ዕቃዎች ኃላፊነትን በሚመለከት በውጭ አገር ስላለው አዝማሚያና በኢትዮጵያም ይዘቱ ምን መሆን እንዳለበት የሚጠ ቁም ሀሳብ ተጨምሮበታል ።

በአሜሪካ የፍርድ ውሳኔ ሕግ ላይ የተመሠረተው የአካዳሚው ቃለ ጉባኤ ተቀባይ (የፕሮፌሰር ደብልዩ ግሬይ) ንድፈ—መጠይቅ ከኢትዮጵያ የሕግ ሥር ዓት ጋር አይጣጣምም ፤ ሆኖም ምንም እንኳ ንድፈ መጠይቁን አጥብቄ ባልከ ተለውም በዘገባው ውስጥ አንዳንድ ድግግሞች ሊወገዱ አልቻሉም ። ይህ መግ ቢያ ፤ ማከያውና ተቀጽላው የተጨመሩት በ1980 ዓ.ም. ነው ።

ክፍል 1

መ ግ ቢ ያ

(1) በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2085 መሠረት የተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት የተሠሩ ዕቃዎች ፤

(1) ትርፍ ለማግኘት ሲል ዕቃዎችን የሚሠራና እነዚሁኑ ለሕዝብ (በተ ዘዋዋሪ)[1] የሚያቀርብ ሰው በዕቃዎቹ በሚገባ ሲጠቀምባቸው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሱ እንደሆን አላፊ ነው ።

(2) ቢሆንም ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው የዕቃው ጉድለት በልማዳዊ ምር መራ ሊታወቅ ይችል የነበረ ከሆነ አላፊነት የለም ።

(2) መንደርደሪያ መመሪያዎች[2]

በቁጥር 2085 የተሰጠው አጥፊ ሳይከን አላፊ ስለመሆን (የጉዳት) መመዘኛ «ድብልቅ» እንለዋለን ፤ ምክንያቱም መገምገሚያው ሁለቱንም የመመዘኛ ዘዴዎች ማለትም የ «ዕቃውን ዓይነት» እና የ «ሥራውን ዓይነት» የሚመለከት በመሆኑ ነው ።

ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ነገር የተሠራ ማለትም ሰው ሠራሽ መሆን አለበት (ተፈጥሮ የለገሰውና በሰው የተሰበሰበ ብቻ መሆን የለበትም) ።

ተከሳሹ በማምረት ሥራው የሚሠማራው ትርፍ[3] ለማግኘት ዕቃውን እየ ሠራ ለሕዝብ[4] ማቅረብ ሲኖርበት ከሳሹ ደግሞ ዕቃውን የሚገዛው በተገቢው መንገድ በዕቃው ለመጠቀም መሆን ይኖርበታል ። ስለዚህ ቀደም ሲል በተጠቀ ሱት (አጥፊ ሳይኮን አላፊ ስለመሆን) ጉዳዮች አላፊነት የሚኖርበት የተመረተው ዕቃ «ባለቤት» ወይም «ጠባቂ» ሳይሆን የተመረተውን ዕቃ ሠርቶ «ባለቤትነቱን» ወይም «ጠባቂነቱን» ያስተላለፈው አምራቹ ነው ። ይህ ጐጂ ነገር የተፈጥሮ ውጤት የሆነው እንስሳ ሊሆን አይችልም ፤ ነገር ግን በሰው የሚሠራው ሕንፃ[5]

ወይም መኪና ሊሆን ይችላል ። በርግጥ በተገቢው መንገድ ግልጋሎት ላይ የዋለ ሞተር ተሽከርካሪ ሊታይ ከማይችል ከመሪው የአሠራር ጉድለት የተነሳ በሰው ላይ ለደረሰው ጉዳት አላፊ የተደረገ ባለቤት ፤ በተራው ከሞተር ተሽከርካሪው ሠሪ ካሳ ሊጠይቅ ይችላል ።

የሠሪው ዕቃውን በመጨረሻ ለሚገለገሉበት (ማለትም ለተጠቃሚዎች) «ጥብቅ» አላፊነት በሮማውያን የሕግ ሥርዓቶች የታወቀ አይመስልም ። በኮመን ሎው ደግሞ ሩቅ ከሆነውና አሁንም ሥሩ «ንዝህላልነትን ከሚጨምረው» የእንግሊዙ «የደኖግና የስቴቨንስን» ጉዳይ (1932 ዓ.ም.)[6] ላይ ከተሰጠው ውሳኔ ጋር የተያያዘ ይመስላል ። ምንም እንኳን ክልሉ (ምንና ምን ዕቃዎች ?) እና ሕጋዊ መሠረቱ አሁንም አከራካሪ ቢሆንም ፤ የሠሪው ለዕቃው የመጨረሻ ተጠቃሚዎች አላፊነት «ጥብቅ» መሆን ግልጽ እየሆነ የሄደው በአሜሪካ ብቻ ነው ። የተለመደው «መከራከሪያ» ለመጨረሻው ተጠቃሚ «ከዕቃው ጋር አብሮ የሚሄድ» (በጠመዝማዛ የሕግ አተረጓጐም) የሥሩ ውላዊ «የሽያጭ መድን» ነው የሚለው ነው[7]።

ይኸንን አመለካከት ፕሮሰር የተባሉ ምሁር «የተድበሰበሰ የውል ሽፋን ሳያስፈልግ መጀመሪያውኑ የተደነገገ ከውል ውጭ አላፊነት አለ ቢባል በጣም ይቀል ነበር»[8] በማለት ያወግዙታል ። ይህ በትክክል የኢትዮጵያው ሕግ አውጭ የተከተለው አቋም ነው ። («የክልል» መለኪያውም እንደዚሁ ቀላል ነው) ።

(1) ምንም እንኳ ... ... ቁጥር 2085 (2) ከቁጥር 2293 (2) ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም (የጉድለቶች «መገኘት መቻል») በቁጥር 2085 ሥር የተጻፈው የኛ የውል ውጭ ግዴታ ድንጋጌ ራሱን የቻለና ከውል ውጭ መፍትሔዎች ጋርም የማይጣጣም ነው[9]። ልብ—ወለድ ምክንያቶች አያሹንም ።

(2) የቁጥር 2085 ክልል እስከምን ድረስ ነው? በዚህ ቁጥር ሥር ይሸፈናሉ ተብለው የታሰቡት የትኞቹ ሰው—ሠራሽ ዕቃዎች ናቸው? መልሱ ግልጽ ነው ። በቁጥር 2085 ውስጥ ሁሉም ተሸፍነዋል ። በዚህ ረገድ[10] ማናቸውም በአሜሪካ የተደረጉ አከራካሪና ግልጽ ያልሆኑ ልዩነቶች በኛ ሕግ ውስጥ የሉም ። ሰው ሠራሽ ዕቃ (የተሠራ ዕቃ) የሚባለው ማንኛውም በሰው የተሠራ ፤ የተለወጠ ፤ ወይም የተዘጋጀ (ለምሳሌ የተቀቀሉ ወይም ሳይበላሹ እንዲቆዩ ተደርገው የተሠሩ ምግቦች)ነው ።

3. የርዕሱ ክልል

«ለተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት» የሚለው ጽንሰ—ሀሳብ የተጀመረው በአሜሪካ ነው ። ይህ የመጀመሪያው ሐረግ ራሱ በቅጡ ሳይተረጐምና ወሰኑ ሳይታወቅ እቻ የኢትዮጵያ ቃል ሊፈለግለት አይችልም ። የሚከተለው ዐረፍተ ነገር ተገቢ ከሆነ ይህም ደግሞ በተራው የማይቻል ነው ።

> «ለተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት» የሚለው የአሜሪካን አነጋገር የውል ውጭን ወይም የውልን አንድ ክፍል ይመልከት ወይም ራሱን የቻለ ልዩ አስተሳሰብ ይሁን ወይም ምናልባትም ሰስቱንም ያጠቃል ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ አይደለሁም[11]።

ስለዚህም እቻ የውጭ ቃል ካለ መፈለጉን ለሌሎች ትተን በቀላሉ ሊረጋገጥ ከሚችለው ከኢትዮጵያ ለተሠሩ ዕቃዎች (ማለትም የተመረቱ) አላፊነት[12] ትርጉም መጀመር ይኖርብናል ። በኢትዮጵያ ሕግ ሥርዓት ለተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት በውልም ሆነ በጥፋት ላይ አይመሠረትም ።

ሀ. ለተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት ከውል ውጭ የሚመነጭ ግዴታ ነው ። ሊነሳም የሚችለው ከውል ውጭ አላፊነት ሕግ ብቻ ነው (ቁ.2088) ። ውላዊ «የጥራት ዋስትናን ያለማክበር» አላፊነቶች ፤

1. በተለዩ የውል ሕግ ደንቦች ይተዳደራሉ (ቁ.2287 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች) ፤

2. ሰው ሠራሽ ዕቃዎችን ሳይሆን በሰው ያልተሠሩትንም ዕቃዎች ይመለከታሉ (ከዚህ በኋላ ዕቃዎች «የተሠሩ» (ሰው—ሠራሽ) ዕቃዎች በሚለው ጠባብ ስሚታቸው ይወሰዳሉ) ።

ለ. በውል ውጭ አላፊነት ሕግ ውስጥ ለዕቃዎች አላፊነት የተጻፈው ድን ጋጌ በጥፋት ላይ ያልተመሠረተ አላፊነትን በሚመለከተው ክፍል እንደመሆኑ የጥብቅ አላፊነት አካል ነው ። በሥሪው «ጥፋት» ላይ የተመሠረተ አላፊነት ለ «ዕቃዎች (የተሠሩ ዕቃዎች) አላፊነት» ሊባል አይቻልም[13]። በነገራችን ላይ ፤ የእኛ የዕቃዎች አላፊነት ድን ጋጌ (ቁ. 2085)[14] የሚመጣው ጥብቅ አላፊነትን በሚመለከተው ክፍል ውስጥ አደገኛ ሥራዎችን ፤ እንስሶችን ፤ ሕንጻዎችን ፤ መኪና ዎችን ፤ ሞተር ተሽከርካሪዎችን (ከቁጥር 2069 እስከ ቁጥር 2084) ከሚመለከቱት ድንጋጌዎች ቀጥሎ ሲሆን በሁሉም ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚነት ካላቸው ድንጋጌዎች ግን ይቀድማል ። እነዚህ በሁሉም ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው ድነጋጌዎች «የተጐጅውን ጥፋ ተኝነት» (ቁ. 2086) ፤ ወይም «ውላዊ ግንኙነትን» (ቁ.2088) ፤ ወይም «ጥቅም የሌለው ግንኙነትን» (ቁ. 2089)[15,16] ከሚመለከቱት መከላከያዎች በስተቀር ማናቸውም ለጥብቅ አላፊነት አጠቃላይ መከ ላከያ ይሆናሉ ተብለው የሚቀርቡት መከላከያዎች የላይኞቹን ድንጋ ጌዎች ተፈጻሚነት እንዳያቃውሱ ያግዳቸዋል ።

4. ክሳ የሚጠይቅ ማነው? ከማን ላይ?

በዕቃዎች አላፊነት የክሳ ጥያቄዎች ሊነሱ የሚችሉት በዕቃው ተጠቃሚ (ከሳሽ) እና በዕቃ ሠሪው (ተከሳሽ)[17] መካከል ብቻ ነው ።
«ተጠቃሚ» የሚለው ቃል «ተገልጋይን» ማለትም በዕቃው «የሚገለገለውን» ሰው (ለምሳሌ የተዘጋጀውን ምግብ የሚበላን) ይጨምራል ። ለተመረቱ ዕቃዎች አላፊነትን ከሠሪው ጋራ ባደረጉት ውል ምክንያት «ከዕቃው ጋር ተገናኝተው» የዕቃው ተጠቃሚ የሆኑት ሰዎች « ሊያነሱት አይችሉም » (ቁ. 2088)[18]። ሌሎች ተጠቃሚዎች) ግን (ለምሳሌ የገዥ ገዥዎች ፤ የተከራይ ተከራዮች ባለፈቃዶች ፤ ተጋባዦች ለተመረቱ ዕቃዎች አላፊነት ድንጋጌን ሊያነሱ ይችላሉ ። ነገር ግን በዕቃው እንዲጠቀም ያልተፈቀደለት ተጠቃሚ

በዕቃ ሠሪው ላይ የሚያቀርበው ክስ «የተጐጂው ጥፋት» በሚለው መከላከያ (ቁ.2086) ውድቅ ሊሆን ይችላል ።

5. ካሳ የሚያስገኙት ምን ዓይነት ጉዳቶች ናቸው?

በቁ. 2085 መሠረት ለዕቃዎች አላፊነት ሲመጣ ከዕቃው የተለመደ አጠቃቀም ለመጣ ለማንኛውም ጉዳት (በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ለሚደርስ) ተገቢው ካሳ ይኖራል ።
እንግዲህ በዕቃዎች አላፊነት ላይ የሚቀርብ ክስን ሊደግፍም ሆነ ሊያስቀር የሚችል የጉዳቱ ዓይነት ሳይሆን መነሾው (ከዕቃው የተለመደ አጠቃቀም የመጣ መሆኑና አለመሆኑ) ነው[19]።

6. የዕቃዎች አላፊነት አከፋፈል

በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ፤ ለዕቃዎች አላፊነት ፤

(ሀ) የ1960ው የፍትሐ ብሔር ሕግ ስለግዴታዎች የሚደነግገው መጸሐፍ ክፍል ነው ፤

(ለ) በግዴታዎች ሕግም ውስጥ ከውል ውጭ አላፊነት ላይ የተመሠረተ ነው ፤

(ሐ) ከውል ውጭ አላፊነት ሕግም ውስጥ በጥብቅ አላፊነት ላይ የተመሠረተ ነው ፤

(መ) በጥብቅ አላፊነት ክፍልም ውስጥ በልዩ ለዕቃዎች አላፊነት ድንጋጌ ውስጥ (ቁ. 2085) ተገልጿል ።

ለዕቃዎች አላፊነትን በሚመለከት (ለ) ፤ (ሐ) እና (መ) ክፍሎች በቅደም ተከተል ከሌሎች ሁኔታዎች መካከል — የሚከተሉትን ውጤቶች ያስከትላሉ ።

(ለ) የውል ሕግ «የጥራት ዋስትና» ጽንሰ—ሀሳብ ለዕቃዎች አላፊነት አግባብ የለውም ። በሌላ በኩል ደግሞ ስለ ካሳ[20] እና ስለካሳ ክስ አቀራረብ የሚያወሱት የውል ውጭ ሕጐች በሁሉም ዓይነት የውል ውጭ ግዴታዎች ላይ ተፈጻሚነት አላቸው ፤ እና ስለዚህም ለዕቃዎች አላፊነትም ያገለግላሉ ፤

(ሐ) ለዕቃዎች አላፊነት የተከሳሹ «ጥፋት» አግባብ የለውም ፤

(መ) ከላይ በ3. ሉ. ሥር የተጠቀሱት ለሁሉም ጥብቅ አላፊነት ክፍሎች ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጐች (መከላከያዎችን በሚመለከት) ለዕቃዎች አላፊነትም ያገለግላሉ (ቢሆንም የግርጌ ማስታወሻ 15ን ይመለከቷል) ።

ክ ፍ ል 2[21]

በዕቃዎች አላፊነት ላይ ክስ ለማቅረብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

(ሀ) የአዎንታ አስፈላጊ ሁኔታዎች

ስለዕቃዎች አላፊነት የተጻፈው የቁ.2085 ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (1) የሚከተለው ነው ፤

> «ትርፍ ለማግኘት ሲል ዕቃዎችን የሚሠራና እነዚሁኑ ዕቃዎች ለሕዝብ (በተዘዋዋሪ) የሚያቀርብ ሰው በዕቃዎቹ በሚገባ ሲጠቀምባቸው በሌላው ላይ ጉዳት ያደረሱ እንደሆነ አላፊ ነው»[22]

ከዚህ ንዑስ ቁጥር እና ቀደም ሲል ከተሰጡት ትንታኔዎች አንጻር ሲታዩ ለዕቃዎች አላፊነት የሚቀርብ ክስ የአዎንታ አስፈላጊ ሁኔታዎች (ለአሉታ አስፈላጊ ሁኔታዎች እታች ለ ን ይመልከቱ) እንደሚከተለው ይብራራሉ ፤

(1) ይገባኛል ባዩ ጉዳት ደርሶበት መሆን አለበት ፤

(2) ጉዳቱ ከዕቃ (ከ «ተሠራ» ዕቃ ፤ ማለትም በሰው የተሠራ ፤ የተለወጠ ወይም የተዘጋጀ) ተገቢ አጠቃቀም የመጣ መሆን አለበት ፤

(3) ለዕቃዎች አላፊነትን ማንሳት የሚችል የዕቃው ተጠቃሚ ብቻ ነው «ተጠቃሚ ያልሆነ» ሰው ክስ በዕቃዎች አላፊነት ላይ ሊመሠርት አይችልም ፤ ነገር ግን የፈጸመው «ጥፋት» ካለ በሠሪው ላይ ሊመሠርት ይችላል[23]።

(4) ክሱ መቅረብ ያለበት በዕቃ ሠሪው (ሠሪ ፤ ለዋጭ ፤ አዘጋጅ) ላይ መሆን አለበት ፤

(5) የዕቃ ሠሪው ሥራም ዕቃውን ለሕዝብ አቅርቦ ትርፍ ለማግኘት መሆን አለበት ።

(1) ፤ (3)፤ (4) እና (5) ነጥቦችን በሚመለከት በመጠኑም ቢሆን አሳማኝ ማብራሪያ ሊቀርብባቸው ሲችል ፤ አስፈላጊ በሆነው በነጥብ (2) ጉዳዩ የተለየ ነው ። ይህ ነጥብ በውስጠ ታዋቂ (ከ ... የመጣ) አስቸጋሪ የሆነውን ምክንያታዊ ግንኙነትን ይመለከታል ። ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ምንድን ነው? የተፈለገው የዕቃ ተገቢ አጠቃቀም በሌላ ዕቃ ምክንያትነት ጉዳት አድርሶ ሊሆን ይችላል ። ትርጉም የለሽ ውጤት ላይ ከመድረስ ይልቅ ራሱ በጥቅም ላይ የዋለው ዕቃ የጉዳቱ ዋነኛ ምክንያት መሆን አለበት ማለቱ የሚሻል ይመስላል ።

ይህ እንዲህ ከሆነ ፤ ዕቃው ነው ወይስ በዕቃው ያለ «ጉድለት»? ለመሆኑ በንዑስ ቁጥር (2) ሥር (እታች በ ለ.1 ሥር እንደተተነተነው) የጉድለቱ ምክንያት ሊደረስበት አለመቻሉ «የአሉታ»አስፈላጊ ሁኔታን ይመሠርታል ከሚለው እውነታ በመነሳት የ«ጉድለት» የ«አዎንታ» አስፈላጊ ሁኔታ አለ ለማለት ያስችላል ወይ? መልሱ አዎን ከሆነ (ግን ያጠራጥራል) «ጉድለት» ምንድነው? መልሱ አይደለም ከሆነ (በግልጽ) «ተገቢ» አጠቃቀም እንዴት መተርጐም ይገባዋል?

በርግጥ « ... በዕቃዎቹ በሚገባ ሲጠቀምባቸው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሱ እንደሆነ አላፊ ነው» የሚለው ቀላል መሳይ ምንባብ ከሚፈታው ይልቅ የበለጠ ችግ

ር ይፈጥራል ። ዳኞቻችን ፣ ከነዚሁም ጥቂቶች አሁንም መደበኛ የሕግ ትምህርት የሌላቸው ፣ እነዚህን ችግሮች በማይለዋወጥ መንገድ መፍታት ያዳግታቸዋል ። ከዚህ ምንባብ የሚመነጩት አጠራጣሪ ሁኔታዎች ምናልባት ቢኖሩም በግልግል ወይም በፍርድ ውሳኔዎች ፣ (የኋለኞቹ ሪፖርትም አልቀረበባቸው አልተመዘገቡምም) ግልጽ በሆነ አተረጓጎም አልተወገዱም ። በወሬ ወሬ በመስማት የተወሰነ ዕውቀት ካለን አልፎ አልፎ ከሚያጋጥሙ ጉዳዮች እንደምንረዳው የዕቃዎች አላፊነትን በማስመርኮዝ የይገባናል ጥያቄ አቅራቢዎች ምንም እንኳን እላይ በተጠቀሰው ምንባብ የማይገደዱ ቢሆንም በዕቃዎቹ ውስጥ ያሉትን «ጉድለቶች» ለምሳሌ የሞተር ተሽከርካሪን የተንቀሳቃሽ መሣሪያን «የአሠራር» ጉድለት («ከአካሉ» ይልቅ)[24] ለማሳየት የሚጣጣሩ ይመስላል ። በሌላ በኩል ደግሞ ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ዕቃውን «በተገቢው» መንገድ መጠቀማቸው እንዲገመትላቸው በስህተት ያስባሉ ። ውጤቱም የተዘበራረቀና ዋጋ ቢስ መሆኑ የማይቀር ነው ። ምክንያቱም

(ሀ) በፍርድ ቤቶች ላይ እምነት ስላልሰፈነ (ምክንያቶቹን እላይ ይመለከቷል) ፤

(ለ) በዕቃዎች አላፊነት ላይ የይገባናል ጥያቄ ለማቅረብ አግባብ ይኖራቸዋል የሚባሉ ሰዎች ያልነቁና መብታቸውን የማያውቁ ስለሆኑ ፤

(ሐ) በአገር ውስጥ በጥቅም ላይ የሚውሉት ብዙዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ዘመናዊ ዕቃዎች የሚሠሩት ፣ በመሠረቱ የልዩ ልዩ አገሮች ሕጎችን ተፈጻሚነት የሚያስተዳድር (ኮንፍሊክት ኦፍ ሎውስ) ሕግ ከሌላት ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ስለ ፍርድ አፈጻጸም ስምምነት በሌላቸው የውጭ አገሮች ስለሆነ ።

ለዕቃዎች አላፊነትን በሚመለከት ረገድ የሚቀርቡ ክሶች እጅግ ጥቂት ከመሆናቸውም በላይ ቢቀርቡም እንኳ ከፍርድ ቤት ውጭ «በርትዓዊ» ስምምነት ፍጻሜ የማግኘትን አዝማሚያ የሚያሳዩ ናቸው ። በዕቃዎች አላፊነት ላይ የሚቀርበውን ክስ ለመወሰን የሚያስችሉትን መገምገሚያዎች ለማዳበር በፍርድ ቤቶች ላይ ግፊት የለም ። በመሆኑም እነዚህ ግልጽ ያልሆኑ መገምገሚያዎች በጨቅላነት ደረጃ ቀርተዋል ።

ለ. የአሉታ አስፈላጊ ሁኔታዎች

ለዕቃዎች አላፊነት ክስ ለማቅረብ ፤ የአዎንታ አስፈላጊ ሁኔታዎች ከተሟሉም በኋላ ፤ ተፈጻሚነት የሚኖራቸውን አንዳንድ ለመከላከያ የሚጠቅሙ የሕግ ድንጋጌዎችን በማንሳት የቀረበውን ክስ ውድቅ ማድረግ ይቻላል ። የነዚህ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ማጣት ለዕቃዎች አላፊነት ለሚቀርበው ክስ የአሉታ አስፈላጊ ሁኔታዎችን ይመሠርታል ።
እነዚህ ድንጋጌዎች እታች (1 ፤ 2 ፤ 3) ተጠኑዋል ።

1. ለዕቃዎች አላፊነት ተፈፃሚነት ካላቸው ከሶስቱ የመከላከያ ድንጋጌዎች[25] መካከል አንደኛው ብቻ ልዩ ነው ፤ እሱም በቁ. 2085 ንዑስ ቁጥር (2) ውስጥ ይገኛል ። ይህ ንዑስ ቁጥር እንደሚከተለው ይነበባል ፤ «እጥቅም ላይ የዋለው ዕቃ በልማድ እንደሚደረገው ተመርምሮ

ቢሆን ኖሮ ጉዳቱን ያመጣው ጉድለት ሊታወቅ ይችል ከነበረ አላፊነት የለም ። »

እንግዲህ

(ሀ) ግልጽ የሆነ የዕቃውን የውስጥ ወይም የአካል «ጉድለት» የማመልከት ፤
(ለ) ለጉዳቱ «ምክንያት» የሆነውም ይኸው ጉድለት መሆኑን የማሳየት ፤ እና
(ሐ) አጥቅም ላይ የዋለው ዕቃ በልማድ እንደሚደረገው ተመርምሮ ቢሆን ኖሮ ሊታወቅ ይችል እንደነበረ የማስረዳት ግዴታ የተከሳሹ ነው ።

እነዚህ ለመከላከያ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች በክስ የተሞከሩ አይመስልም ። ሶስተኛው ተፈላጊ ነገር (የጉድለቱ ለመገኘት መቻል) በሽያጭ መድን ውስጥ ተፈጻሚነት ካለው የውል ሕግ ከሆነው ከቁ. 2293 (2) የተወሰደ ነው ።

2. የቁ. 2088 የመከላከያ ድንጋጌ የሚያገለግለው ለዕቃዎች አላፊነት ብቻ ሳይሆን ለሌሎቹ ጥብቅ የውል ውጭ አላፊነቶችም ስለሆነ አጠቃላይ ነው ። ይገባኛል ባዩ[27] ከተከሳሹ ጋራ በተደረገ ውል (ለምሳሌ የሽያጭ)[28] ምክንያት ከዕቃው ጋራ ግንኙነት አለው ብሎ ለማሳየት ፤ ግዴታው የተከሳሹ ነው ።

3. የቁ. 2086 የመከላከያ ድንጋጌ የሚያገለግለው ለዕቃዎች አላፊነት ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የጥብቅ አላፊነቶችም ስለሆነ አጠቃላይ ነው[29]።

ይገባኛል ባዩ በራሱ ጥፋት ብቻ መጐዳቱን የማስረዳት ግዴታው የተከሳሹ ነው(እታች ለ ን ይመለከቷል ።) ይህን በሚመለከት የሚቀጥሉት ገለፃዎች አግባብ አላቸው

ሀ. በቁ. 2086 ንዑስ ቀጥር (1) መሠረት ለዕቃዎች አላፊነትንም ለሚጨምሩት ለጥብቅ የውል ውጭ አላፊነቶች ፤ ተከሳሹ ጥፋተኛ ያለመሆኑን ፤ ወይምየሶስተኛ ወገን ጥፋት መሆኑን ፤ ወይም ከአቅሙ በላይ የሆነ ኃይል [30]መኖሩን ፤ ወይም «የጉዳቱ ምክንያት አለመታወቁን» ለማስረዳት ማናቸውንም መከላከያዎች ከማንሳት በግልጽ ተከልክሏል ። እነኝህ ክልከላዎች የሚከተሉትን አስተያየቶች ይጠይቃሉ ፤

(1) ራሱ የጥብቅ አላፊነት ክፍል ርዕስ «ያለጥፋት አላፊነት» ማለትም በጥፋት ላይ ያልተመሠረተ ስለሚል «ጥፋት የለብኝም» በሚለው መከላከያ ላይ የተደረገው ክልከላ ትርፍ ነው ።

(2) «የጉዳቱ ምክንያት አይታወቅም» በሚለው መከላከያ ላይ የተደረገው ክልከላ ትርጉም የለውም[31]። ለሁሉም ጥብቅ ከውል ውጭ አላፊነት ክሶች የአዎንታ አስፈላጊ ሁኔታዎች ምክንያትን[32] ስለሚጨምሩ የጉዳቱ ምክንያት አይታወቅም የሚል ክርክር «በመከላከያ» ደረጃ ፈጽሞ እንዳይነሳ ያግዱታል ። ይህ እንግዲህ የተጠቀሰው ከተፈላጊው «የዕቃው ተገቢ አጠቃቀም» ይልቅ ራቅ ያለ[33] ምክንያት አለማግኘት ማለቱ ይሆናል ተብሎ በዘፈቀደ ካልተወሰደ ነው ።

(3) በኢትዮጵያ የጥብቅ ከውል ውጭ አላፊነት ሕግ ውስጥ የሶስተኛ ወገን ጥፋት እና «ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል» በሚሉት መከላከያዎች ላይ

የተደረገው ክልከላ ለአሠራር አመቺ ነው ። የኢንሹራንስን የክፍያ ዋጋ እጅግም ሳይጨምር ክርክርን ያቀላል ።
በተለይም ደግሞ ዕቃውን የሠራው ተከሳሽ ኢትዮጵያዊ ሲሆን ወይም «ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል» የሚሉትን መከላከያዎች በይገባኛል ባይ ላይ በመቃወሚያነት ማንሳት አይችልም ።

ለ. በቁ 2086 ንዑስ ቀጥር (2) መሠረት በይገባኛል ባዩ ላይ የደረሰው ጉዳት በይገባኛል ባዩ ጥፋት[34] «ብቻ» መሆኑን ካስረዳ ሙሉ በሙሉ ከጥብቅ አላፊነት ነፃ ነው ። በነገራችን ላይ ፤ እላይ በ(2) ሥር በተሰጡት መሰል ምክንያቶች መሠረት «ብቻ» የሚለው ተውሳከ ግሥ የሚያመለክተው የሌሎችን ምክንያቶች አለመኖር ሳይሆን ሌሎች የጥፋት ግንኙነቶችን[35] ካልሆነ ትርጉም አይኖረውም ። በዕቃዎች አላፊነት ላይ ባለው ተፈጻሚነት «የይገባኛል ባዩ ጥፋት» መከላከያ እታች እንደተገለጸው ምናልባትም በአብዛኞቹ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ አይደለም ።

በመሠረቱ በዕቃዎች አላፊነት ይገባናል ባዮች የሚፈጽሙአቸው ጥፋቶች ፤ ዕቃውን «በተገቢው» መንገድ ይጠቀሙ ፤ የሚለውን የአዎንታ አስፈላጊ ሁኔታ መጓረርን ይጨምራሉ ። ዕቃውን «በተገቢው» (ጥፋት በሌለበት) መንገድ መጠቀም ለክሱ አስፈላጊ ቅድመ—ሁኔታ እንደመሆኑ መጠን[36]፤ የይገባኛል ባዩን ጥፋተኛ (ተገቢ ያልሆነ) አጠቃቀም የማስረዳት ግዴታ የተከሳሹ ሳይሆን ዕቃውን ጥፋት በሌለበት (በተገቢ) መንገድ የተጠቀመበት መሆኑን ማስረዳት የይገባኛል ባዩ ግዴታ ነው ። ለምሳሌ ዕቃ ሠሪው ከሰጠው ተቀባይነት ካለው የአጠቃቀም ዘዴ መመሪያ ወይም በዕቃው ላይ ከተለጠፉ ማስጠንቀቂያዎች ጋራ በማይጣጣም መንገድ በጥቅም ላይ ውሎ ከሆነ ይገባኛል ባዩ እንዲህ ያለው አጠቃቀም «በተገቢው» መንገድ እንደነበረ ማስረዳት ሊያዳግተው ይችላል[37]።

ክ ፍ ል 3

መደምደሚያ[38]

1. ከ1960 ዓመተ ምሕረት የፍትሐ ብሔር ሕግ ጋር አብሮ የታወጀው የኢትዮጵያው ለዕቃዎች አላፊነት ድንጋጌ ቁጥር 2085 ንዑስ ቁጥር (1)[39] የ1950ዎቹ አንዳንድ አሜሪካውያን የሕግ ጸሐፊዎች[40] ሀብታምና ኃያል ለሆነው አገራቸው «ተጠቃሚ» ሕዝብ[41] ከፍተኛ ጥበቃ ለመስጠት ያቀረቧቸው ጊዜውን ቀድመው የተሰነዘሩትን የአንዳንድ መፍትሔዎችን ፍሬ—ሀሳብ ተቀብሎ በአንድ ነጠላ ሐረግ አጠቃሎታል ። ይህ ድንጋጌ ከታወጀ ከብዙ ጊዜ በኋላም ፤ በማደግ ላይ ባለች ድኃ ኢትዮጵያ ፤ ዋጋ አጥቶ መቅረቱ አያስደንቅም ። የቁ. 2085 ንዑስ ቁ. (1) አሽብራቂ መፍትሔ «ከውበት» በስተቀር ሌላ ግቦች ከነበሩት፤ ግቦቹን አልመታም ። ሌሎቹ ጉዳቶቹ ይቅሩና እራሱን በተግባር ላይ ማዋሉ እንኳ በርካታ የሆነ የተወሳሰበ ክርክር ያስከትል ነበር ። ደግነቱ የዚህን መፍትሄ ሥር—ነቀልነት ቀድሞም ሆነ አሁን የተገነዘበው አልተገኘም[42]። ከ1974 ዓ.ም ቱ እብዮት ወዲህ እንደዚህ ዓይነት የአሉታ አመለካከት በአዳዲስ ምክንያቶች ሊደገፍ ይችላል ።

(ሀ) ብዙዎቹ በኢንዱስትሪ ምርት ተግባር ላይ የተሠማሩ ድርጅቶች በ1975 ዓ.ም. በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ በታወጀው መሠረት የመንግሥት ንብረት ሆነዋል ።

(ለ) ይህቺ ድሀ አገር እየጨመሩ የሚሄዱትን ለኅብረተሰብአዊነት ግንባታ የሚደረጉ ወጪዎችን መደገፍ አለባት ፤ አምራቹ መንግሥትና የእሱ የሆኑት የማምረቻ ድርጅቶች ዕቃዎቻቸውን «በተገቢው መንገድ በመጠቀም» ለሚያደርሱባቸው ለሁሉም ጉዳቶች አላፊዎች ይሁኑ ከተባለ ችግር የበዛበት ባጀቷ የባሰውን ይቃወሳል[43]።

(ሐ) በኢኮኖሚ እድገት የመጀመሪያዎቹ ደረጃዎች ውስጥ ምርትን የማሳደጉ ዓላማ ፤ እጥቅም ላይ በዋለው ዕቃ ጉልህ ጉድለት ምክንያት ከደረሰ ከፍተኛ ጉዳት በስተቀር ተጠቃሚዎቹን ለጉዳት ከመካስ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ።

2. በቁ. 2085 ላይ የተመሠረተ ለዕቃዎች አላፊነት ክስ አለመኖሩ ፤ እጥቅም ላይ በዋለው ዕቃ ጉልህ ጉድለት ምክንያት ለደረሱ ከፍተኛ ጉዳቶች እንኳ በአምራቹ (በሠሪው) ላይ ከውል ውጭ የሆኑ ክሶችን በእርግጥ እንደሚያስነሱ የሚያመለክት ይመስላል ። ለምሳሌ ከአንድ ቆርቆሮ ምግብ መመረዝ የደረሰ የሶስት ሰዎች ሞት በወሬ ወሬ እንደሰማሁት በሕይወት ባሉት የሚቾቹ ጥገኞች ወደ ፍርድ ቤት አልቀረበም ነበር ። ሠሪው ድርጅት ራቅ ባለ የውጭ አገር ውስጥ ይገኝ ነበር (ክፍል 2 ፤ ሀ. (ሐ)ን ይመለከቷል) ። በሌላ በኩል ደግሞ በሕይወት ያሉት የሟቾቹ ጥገኞች መብታቸውን ያወቁ አይመስልም፤እና ያም ሆነ ይህ እውጭ አገርም ለመክሰስ አቅም አልነበራቸውም።

3. ለተጠቃሚው በሚደረግለት የቲኦሪ ከፍተኛ ጥበቃ መርሕ እና ተጠቃሚው በሚገኝበት እውነተኛ ሁኔታ መካከል ያለው ልዩነት እጅግ የተራራቀ ነው ። ይህ ሁኔታ ፤ እላይ ከ (ለ) እስከ (ሐ) ሥር የገለጽናቸው የሶሻል እና የኢኮኖሚ መሠረተ ሀሳቦች መስዋዕት ሳይሆኑ ፤ መፍትሔ ማግኘት የሚገባው ጉዳይ ነው ። ይኸን ግብ ለመምታት ፤ በጣም አጠቃላይ የሆነው (ግን ተከታይ ያጣው) የቁ. 2085 ንዑስ ቁ. (1) መገምገሚያ ክልሉን በማጥበብ ተለይቶ መጻፍ አለበት እንላለን ። በይገባኛል ባዩ ላይ የደረሰበት ጉዳት ከሌሎች ነገሮች መካከል እጥቅም ላይ በዋለው ዕቃ «ጉድለት» ምክንያት መሆን አለበት የሚል ግልጽ ቅድመ—ሁኔታ ማስቀመጥና የጉድለትን ትርጉም ማስከተል ይገባል ። የሆነ ሆኖ በተግባር የሚገለጽ ገደብ ያለው ጥበቃ ለተጠቃሚው ለመስጠት በሚሻሻለው ሕግ ላይ መግለጫዊ አስተያየት ቢጨመርበት ጠቃሚ ይሆናል ። (ተጨማሪ ሀሳቦች በመዝጊያው ጽሑፍ ውስጥ ቀርበዋል) ።

ስለውጭ አገር ሁኔታዎች በ1980 ዓ.ም. የተዘጋጀ ማከያ

የውጭ አገር ሕጐችን ወይም ረቂቅ ሕጐችን እና ሀሳቦችን የራስ ከሆኑት ጋር ማወዳደር የኋለኛውን ጥሩ ነገሮች እና ጉድለቶች አጣርቶ ለማየት ይረዳል ። ስለዚህም ዘገባችን ለዕቃዎች አላፊነትን በሚመለከት በውጭ አገር ስላሉ አንዳንድ መሠረታዊ ሁኔታዎች በተሰጡት አስተያየቶች በጥቂቱ ቢታከልበት ተገቢ

ይመስላል[44]። የሚከተሉት አስተያየቶች የሚመሠረቱት (1) የጉባኤው ተሳታፊ የነበሩ አንዳንዶቹ ጓዶቻችን ለጉባኤው ባቀረቧቸው ብሔራዊ ዘገባዎች[45]፤ (2)በፕሮፌሰር ደብልዩ ግሬይ (ሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ) የማጠቃለያ ዘገባ ፤ እና (3) በሌሎቹም ምንጮች ላይ ነው ።

እስካሁን ያሉ (እና ምናልባትም ያልተሟሉት) መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ለዕቃዎች አላፊነት በላይኛው ስሜቱ አሁንም በአንዳንድ በተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት ግዛቶች[46] ብቻ የሚሠራበት መሆኑንና ከሃያ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በዚህ ጉዳይ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው አመለካከት አርአያ መሆኑን ይጠቁማሉ (እላይ ሙደምደሚያውን ይመለከቷል) ።

እነዚህ ጥብቅ ከውል ውጭ አላፊነት አመለካከትን የሚከተሉ በተባበሩት የአሜሪካ መንግሥታት ለዕቃዎች አላፊነት የተሰጡ ውሳኔዎች ፤ ብዙዎቹ የተመሠረቱት የአሜሪካ የሕግ ተቋም በሚያሳትመው እና ተቀባይነት ባለው ሪስቴትመንት አፍ ቶርትስ ሰከንድ[47] ክፍል 402—ሀ ላይ ነው ። ሆኖም በዚህ ጉዳይ ላይ የፌደራል ሕግ የለም ።

በኢንዱስትሪ በበለጸጉት አገሮች ውስጥ ጥብቅ ከውል ውጭ ለዕቃዎች አላፊነት ድንጋጌ ባለመኖሩ ፤ ከሠሪው ጋራ ውል የሌላቸው ወይም ጥፋቱን ለማረጋገጥ የተሳናቸው የተጐዱ የዕቃ ተጠቃሚዎችን ለመጠበቅ ያለው የፍርድ ቤቶች ዝን ባሉ ሕጉ እነሱን እንዲደግፍ <u>ሀሳብ—ወለድ</u> ዘዴ ወደ መቀየሱ ሊያመራ ይችላል ወይም ያመራል ። የሚሠራባቸው የቴክኒክ ዘዴዎች ይለያያሉ ። በሁሉም አገሮች የሚሠራበት ዘዴ የእሱ ዕቃ ጉድለት አለው ከሚለው እውነታ ብቻ የሠሪውን <u>ጥፋት</u> መገመት ነው ። ግምቱ ፈራሽ አይደለም ተብሎ በሕጉ ውስጥ ካልተገለጸ (ወይም በማስረጃ ለማስተባበል አስቸጋሪ ካልተደረገ[48]) በቀር ፤ ይህ ማለት ደግሞ ውጤቶቹ ያው እንደጥብቅ አላፊነቶቹ አንድ ናቸው ፤ ይህ ዘዴ እንከን—የለሽ አይደለም ። በፈረንሳይ ፤ ሠሪው በዕቃዎቹ ውስጥ ያሉትን ጉድለቶች «ያውቃል» ፤ እና ስለዚህም እነሱን ገበያ ላይ ካወጣቸው ጥፋተኛ ነው የሚል ለማስተባበልም የማይፈቀድ በፍርድ ውሳኔ የተመሠረተ ዓይነት በዘገባችን ክፍል 1 ፤ 2 ውስጥ ተገልጾ ተተችቷል ። እሱም ጉዳት ለደረሰበት የመጨረሻ ተጠቃሚ ፈጽሞ የሌለውን ውላዊ የሽያጭ መድን ለጉድለቶች መፍትሄ ለመስጠት ሲል <u>የውል ግንኙነት</u> አለ የሚል ሽፋን ይሰጣል ። በጥፋቱ ወይም በውል ግምት ላይ ተመሠረቱም አልተመሠረቱም እንደዚህ ያሉ የተወሳሰቡ ሀሳብ—ወለዶች መጠቀምን የፈረንሳይ ዘገባ አቅራቢ ያወግዙአቸዋል ። እነሱን አደናጋሪና የማያጠግቡ ብለው ይሠይሙአቸዋል[49]።

ባሁኑ ጊዜ የብዙ አገሮች የምሁራን አስተሳሰብ ጥብቅ ከውል ውጭ ለዕቃዎች አላፊነት መጠቀምን ይደግፋል ። ከዚህም በላይ በብዙ አገሮች <u>የሕግ አሻሻይ</u> ድርጅቶችና በዓለም አቀፍ ደረጃም ጉድለት ካለባቸው ዕቃዎች ለሚደርስ ጉዳት አላፊነትን ግልጽ በሆነ ሕግ የመወሰን አዝማሚያ እየታየ ነው ። እነዚህ አዝማሚያዎች በዚህ የማከያ በቀሪው ክፍል ውስጥ በተለያየ ትኩረት የተተነተኑ ሲሆን ፤ በአንዳንድ የቅርብ ጊዜ ሠነዶችም[50] ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የተሰጣቸው መሆኑ ግልጽ ነው ።

ሀ. ስለግዴታዎችና ስለውሎች የተዘጋጀው <u>የዩጎዝላቪያ</u> የ1976 ዓ.ም. ረቂቅ ሕግ[51] ። የዚህ ረቂቅ ቁ. 151 ትርጉም እንደሚ

ከተለው ይነበባል ፤

«ማንም በሱ የተሠራን ዕቃ ለገበያ የሚያቀርብ ሰው ዕቃዎች በጉድለት ወይም ሊያውቃቸው ባልቻለው ጠባያቸው ምክንያት በሰው ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ለማስከተል የሚችሉ ሲሆን ፤ በዚሁ ጉድለት ወይም ጠባይ ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት አላፊ ነው» ። (በዚህ ትርጉም ውስጥ ጉድለት የሚለውን ቃል እንጠራጠራለን)

ይህ ሕግ በጥፋትም ሆነ በውል ላይ ያልተመሠረተ ጥብቅ ከውል—ውጭ አላፊነት ድንጋጌ በመሆኑ የኢትዮጵያውን ለዕቃዎች አላፊነት ድንጋጌ ይመስላል ። ነገር ግን በቀድሞው ጽሑፋችን[52] በገጽ 41—ኤፍ በተገለጹት ምክንያቶች መሠረት በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ ከማይሠራበት «አደገኛ ዕቃ» ከሚለው አጠቃላይ ጽንሰ—ሀሳብ የመነጨ በመሆኑ ልዩ ነው ። እላይ የተጠቀሰው ረቂቅ ሕግ ሲታወጅ ሠሪው ወይም ጠባቂው ዕቃውን ለገበያ ካቀረበም በኋላ በዕቃው ለሚደርስ ጉዳት አላፊ እንደሆነ ይቀራል ።

ለ. «ጉድለት ስላለባቸው ዕቃዎች አላፊነት» (ጥብቅ ከውል ውጭ አላፊነትን በመደገፍ) የእንግሊዝ የሕግ ኮሚሽንና የስኮትላንድ የሕግ ኮሚሽን[53] በጋራ ያቀረቡት እጅግ በጣም ጥሩ ዘገባ በእንግሊዝ አገር እስካሁን ወደረቂቅ ሕግነት ባይለወጥም ፤ ከሌሎች ነገሮች መካከል በአውሮፓው ረቂቅ ስምምነትም ስለዕቃዎች አላፊነት በሚል ርዕስ (እታች ያተትነው) ስለተጠኑት እና ተቀባይነትንም እንዲያገኙ በሕግ ኮሚሽኑ ማሳሰቢያ ስላቀረበባቸው መሠረታዊ ችግሮች ጥልቅ ዕውቀት ይሰጣል ።

ሐ. አሁን የተጠቀሰው ረቂቅ ስምምነት ፤ ከዚህ በኋላ ስምምነት ተብሎ የሚጠራው ሙሉ ርዕስ «የአካል ጉዳትና ሞትን በሚመለከት ስለዕቃዎች አላፊነት የአውሮፓ ስምምነት »[54] የሚል ነው ።
ስምምነቱ በኢንዱስትሪ በጣም በዳበሩ የአውሮፓ አገሮች እንዲሠራበት የታቀደ ቢሆንም የያዘው ዋና ፍሬ ነገር—ጥብቅ ከውል ውጭ አላፊነት-ከኢትዮጵያ ሕግ ጋራ አንድ ነው ። በተጨማሪም ለኢትዮጵያ እንግዳ የሆኑት አንዳንድ ፍሬ ነገሮቹ በኋለኛው ተቀባይነትን ካገኙ[55] ካሁን በኋላ ቀመሮች (ፖስቹሌትስ) እየተባሉ የሚጠቀሱትን የዘገባችንን የመደምደሚያ ቀመሮች(ክፍል 3) በተግባር ላይ ያውላሉ ። ስለዚህም እንደሚከተለው የሚነበበውን የስምምነቱን መሠረታዊ ድንጋጌ (ቁ.3/1) እንዳለ ካስቀመጥን በኋላ እነኝህን ፍሬ ነገሮች (ፊቸርስ) እናቀርባለን ፤

ሠሪው በሠራው ዕቃ ውስጥ ባለ ጉድለት ምክንያት ለሚደርስ ሞት ወይም የአካል ጉዳት ካሣ የመክፈል አላፊነት አለበት[56]።

ፍሬ—ነገር 1

በስምምነቱ (ቁ.2 (ሀ)) ሥር « ዕቃ» የሚለው ቃል የሚያጠቃልለው ተንቀሳቃሽ ዕቃዎችን ብቻ ነው ።ይህ የማይንቀሳቀሱ ዕቃዎች ሠሪዎች በዕ

ቃዎች አላፊነት ሕግ እንዳይነኩ ይከላከልላቸዋል ። ይህ ገደብ (ቆየት ብሎ የሚተነተን) ከእኛ ቀመር 3 ጋራ ይስማማል ።

ፍሬ—ነገር 2

ስምምነቱ (ቁ.3 (1)) ጉዳቱ ዕቃው ውስጥ ባለ ጉድለት ምክንያት መድረሱን አስፈላጊ ቅድመ—ሁኔታ ያደርገዋል ። ይህም እንደገና ከእኛ ቀመር 3 ጋራ ይስማማል ። አሁን የሚሠራበት ሕጋችን ጉዳት «ከተገቢ አጠቃቀም» ብቻ የደረሰ መሆን እንዳለበት ይጠይቃል[57]።

ፍሬ—ነገር 3

ስምምነቱ (ቁ.2(ሐ)) (ቆየት ብሎ የሚተነተነው) የዕቃ «ጉድለት» ትርጉምን ይጨምራል ። ይህም ከእኛ ቀመር 3 ጋራ ይስማማል ።

ፍሬ—ነገር 4

ስምምነቱ (ቁ. 3 (1)) በዕቃዎች የሚደርስ ጉዳት አላፊነትን ለ«ሞት» ወይም ለ«አካል ጉዳት» ብቻ ይወስነዋል (በዕቃዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት የተደረገው እገዳ ኋላ ይተነተናል)[58]። ይኸ ፤ ከቀመር 1 (ለ) እና 3 ጋራ ይስማማል ።

ፍሬ—ነገር 5

በስምምነቱ (ቁ. 3 (2-3)) «ሠሪ» የሚለው ቃል ፤ በስምምነቱ ለተገለጸው ለአላፊነት ጉዳይ ሲባል ፤ አንዳንድ እንደአምራች የሚቆጠሩ ሰዎችን ይጨምራል ። እነዚህ ሰዎች የሚከተሉት ሳይሆኑ አይቀሩም ።

ሀ/ ከውጭ የመጡ ዕቃዎችን በሚመለከት ፤ የዕቃው አስመጪ ። ይህ ከእኛ ውስጠ—ታዋቂ ቀመር 2 ጋራ ይስማማል ።

ለ/ የራሱን የንግድ ስም ወይም የንግድ ምልክት ወዘተ በመለጠፍ («የራስ ምልክት» የተለጠፈበት ዕቃ) «ዕቃውን እንደራሱ ዕቃ አድርጎ ያቀረበው» ሰው ።

ሐ/ የዕቃ አምራቹን ወይም አቅራቢውን ማንነት ካልገለጸ በምትክነት ፤ የሠሪውን ወይም እንደሠሪ የሚቆጠሩትን ሰዎች ማንነት የማይገልጹ ዕቃዎች የሚያቀርብ ።

ፍሬ—ነገር 6

ስምምነቱ (ቁ.5(1)) ፤ ሠሪውን ሚዛናዊ በሆኑትና የእኛን ቀመር 1 (ለ) በሚስማሙ ልዩ መከላከያዎች እንዲከላከል ያስችለዋል ። ሠሪው[59]

ሀ/ ዕቃው በእሱ አልተሰራጨ እንደሆነ (ነገር ግን ፤ ለምሳሌ ፤ ከመሞከሩ በፊት ተሠርቆ ተሸጦ ከሆነ) ፤ ወይም

ለ/ የአካባቢው ሁኔታዎች ሁሉ ተገምግመው (ለምሳሌ በኤክስፐርቶች አስተያየት) ዕቃውን ባሠራጨ ጊዜ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ጉድለት ካልነበረ ወይም ይኸ ጉድለት ዘግይቶ ከተፈጠረ (ለምሳሌ በግዴለሽ ተጠቃሚ ወይም በሶስተኛ ሰው) ፤ ወይም

ሐ/ ዕቃው የተሠራው እና (ወይም የተሠራጨው ለሠሪው የኤኮኖሚ ጥቅም ወይም ንግዱን በሚያንቀሳቅስበት ጊዜ ካልነበረ ፤ አላፊነት የለበትም ።

በነገራችን ላይ ፤ የስምምነቱን ዓለም—ዓቀፋዊ ገጽታዎችም[60] ሆነ በእኛ ጠቅላላ የውል ውጭ ሕግ[61] በሚዛናዊ መንገድ የተቀየሱትን የችግሮች መፍቻዎቹን ፤ እንዲሁም እምብዛም የማያስፈልጉንን ድንጋጌዎቹን[62] አላጤንናቸውም ።

መ/ ከሁን በኋላ መመሪያው እየተባለ የሚጠራ (የአውሮፓ ማኅበረሰቦች ደርግ) ጉድለት ላለባቸው ዕቃዎች አላፊነትን በሚመለከት ተመሳሳይ ሕጐች እንዲኖሩ መመሪያ እንዲሰጥበት የቀረበ ሀሳብ[63] ከሌሎች ነገሮች መካከል ፤ ለኛ ቀጥተኛ አግባብ ስለሌላቸው ስለሠሪው የአላፊነት መጠን ገደቦች ሀሳብ ያቀርባል ። ቢሆንም በማብራሪያው ሀሳብ በአንቀጽ 22 ውስጥ ለሚገኘው (ለእኛ አግባብ ላላቸው) ለእነኝህ ገደቦች አጠቃላይ ሀሳብ ለሚሰጠው ቁም ነገራዊ ምክንያት ስንል እዚህ እንጠቅሰዋለን ።
«ምንም ገደብ ያልተደረገለት ያለጥፋት አላፊነት በሠሪው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ይጥልበታል» በተጨማሪም «ማንኛውም (የአላፊነት) ኢንሹራንስ ውል ደግሞ ለሚሸፍነው አላፊነት የተወሰነ የገንዘብ መጠን ገደብ ያደርግበታል»(ወዘተርፈ እታች በተቀጽላው ውስጥ መመሪያውን ይመለከቷል) ።

ተ ቀ ጽ ላ

ስለዕቃዎች አላፊነት ጉዳይ በውጭ አገር ስላሉት አዝማሚያዎች የቀረበው የላይኛው ማከያ የዚች አገር ለዕቃዎች አላፊነት ሕግ ያለውን ጥቅም (ጥብቅ ከውል ውጭ አላፊነት) እና ጉድለቱን ፤ በተለይም ከአውሮፓው ረቂቅ ስምምነት አንፃር ሲታይ ፤ የአንባቢውን ዕውቀት ከፍ ያደርገዋል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል ። የስምምነቱ ከ1—6 ያሉት ፍሬ ነገሮች (እላይ ይመለከቷል) አስፈላጊው መስተካከል ተደርጐላቸው ተቀባይነትን ቢያገኙ ፈቃዳችን ነው ። እስካሁን ከዘገባችን የመደምደሚያ ሀሳብ ቀመሮች ጋራ አብረው መሄዳቸውን ብቻ ጠቁመናል ። በዚች አገር ውስጥ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ተጨማሪ ምክንያቶች እታች ተሰጥተዋል ።

ፍሬ—ነገር 1

የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ፤ «ዕቃ» በሚለው ቃል እንዳይሸፈኑ መደረጉ ፤ በቁ. 2077 (1) ሥር በማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለቤት ላይ ክስ አቅርቦ እሱም ደግሞ በተራው በቁ. 2077 (2) መሠረት «ከገንቢው (ሠሪው) ላይ እንዲጠይቅ »[64] ማድረግ ከዕቃዎች አላፊነት መፍትሔ ጋራ የሚኖረውን ጊዜ አጥፊ መደራረብ ያስወግዳል ።

ፍሬ—ነገሮች 2—3

ጉዳቱ ዕቃው ውስጥ ባለ ጉድለት የደረሰ መሆን አለበት የሚለው አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ትክክለኛ አመለካከትን የያዘ የጉድለት ትርጉም ሲታከልበት ፤ ሠሪዎችን ተገቢ ካልሆነ ክስ ይጠብቃቸዋል ። በስምምነቱ የቀረበው ትርጉም በውል ሕግ ውስጥ የሚሠራበትን እን

ደማስወገድ ይቆጠራል ። ከውል ውጭ ሕግ ውስጥ የዕቃ ጉድለት የሚ ባለው የዕቃው አገልግሎት አለመስጠት ወይም የንግድ ጥራት ማጣት ሳይሆን የደኅንነት ዋስትና የሌለው መሆኑ ነው ።

አንድ ዕቃ ፤ ያካባቢው ሁኔታዎች ሁሉ ታይተው (የዕቃውንም አቀራረብ ጨምሮ) አንድ ሰው ሊጠብቀው የሚገባውን (ተገቢ)[65] የደኅንነት ዋስትና የማይሰጥ ከሆነ «ጉድለት» አለው (የስምምነቱ ቁ.2 (ሐ) ። ብዙውን ጊዜ «የደኅንነት» ጉድለት ከዕቃው አካላዊ አቋም (ለምሳሌ የአደገኛ መድኃኒት ወይም ፍሬን) ላይ ብቻ ይገኛል ። በሌሎች ጉዳዮች ደግሞ ፤ የአካባቢው ሁኔታዎች ሲታዩ ፤ አንድ ዕቃ ጉድለት ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል ። ለምሳሌ ጉድለቱ ከአደ ገኛ አስተሻሸግ የመነጨ ሊሆን ይችላል ። የስምምነቱ የመግለጫ ዘገባ ፤ አንቀጽ 36 ፤ ዕቃው ከሞላ ጎደል በትክክል (በተገቢ ሁኔታ) አገልግሎት ላይ መዋሉን ፤ ወይም ከሞላ ጎደል ለመገንዘብ በሚቻል መንገድ እጥቅም ላይ መዋሉን ማጤን እንደሚገባ ይጠቅሳል ። የዕ ቃው አቀራረብ ሁኔታ መጤን ካለባቸው የአካባቢ ሁኔታዎች መካከል አንዱ እንዲሆን በግልጽ መነገሩ «ጉድለት» ፤ ለምሳሌ «ያልተሟሉ ያጠቃቀም መመሪያዎችን ወይም ማስጠንቀቂያዎችን» ወይም «የአ ጠቃቀም መመሪያ ወይም ማስጠንቀቂያ ያለመኖር» ሁኔታን (ለደኅ ንነት ሲባል አስፈላጊ ሲሆኑ) ይጨምራል ማለት ነው ። «የአቀራረብ» ጉድለቶች የጉዳት አደጋ የሚፈጥሩ ትክክል ያልሆኑ ምልክቶች ማድ ረግን ወይም ትክክል ያልሆነ አገላለጥን ሊጨምሩ ይችላሉ ።

ፍሬ—ነገር 4

በንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት በጥብቅ ከውል ውጭ አላፊነት እን ዳይሸፈን እላይ በግርጌ ማስታወሻ 53 በተጠቀሰው የእንግሊዙ ሠነድ በአንቀጾች 117—121 ብዙ የተብራሩ ምክንያቶች ተሰጥተዋል ። የሚከተለውን ብቻ እዚህ እንጠቅሳለን ፤

> በዕቃዎች ላይ የሚደርስ ጉዳትን በሠሪዎች ላይ ጥብቅ አላ ፊነትን በሚጭነው የአላፊነት ክልል ውስጥ ማግባት በሠ ሪው (ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ መንግሥት ወይም የመንግሥት የማምረቻ ድርጅት) ላይ ከፍተኛ የኢንሹራንስ ዋጋ እንደመጨመር ይቆጠራል ። በሠሪው ላይ የተጫነው ተጨማሪ ወጪም በዕቃው ዋጋ ላይ ተጨምሮ ሕዝቡ ላይ ይወድቃል ።

ከፍተኛ ዋጋ ባለው ንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት እንደተለመደው በባ ለንብረቱ የአንደኛ ወገን ኢንሹራንስ መሸፈን ይኖርበታል ። ስለዚህም ለዕቃዎች አላፊነት ለአካል ጉዳትና ለሞት ጉዳዮች ብቻ እንዲወሰን እናሳስባለን ። በነገራችን ላይ ፤ ይኸ በሌሎች የጥብቅ አላፊነት ድን ጋጌዎች (ለምሳሌ በቁ. 2082 ፤ 2077 ፤ 2069) ወይም በ «ጥፋት» ድንጋጌዎች (ለምሳሌ ቁ. 2031) ለንብረት ጉዳት መካስን በምንም ዓይነት አይከለክልም ።

ፍሬ—ነገር 5

እላይ በፍሬ—ነገሮች 1—4 እና እታች በ6 የተደረገበትን የጥበቃ ክልል መቀነስ ለማካካስ ፤ ጉዳት የደረሰበት ተጠቃሚ በቀላሉ ሊገኙ

በሚችሉ ተከሳሾች[66] ላይ ክስ የማቅረብ መብት ሊሰጠው ይገባል ። ስለዚህም የስምምነቱን ፍሬ—ነገር 5 ነጥብ ለ/ን በመተው ፤ ነጥቦች ሀ/እና ሐ/እንዲገቡ እናሳስባለን[67]። በነገራችን ላይ አስመጪው ወደ አገር ውስጥ በገባው ዕቃ ውስጥ «የጉድለት መድን» ባለመከበሩ ለደረሰበት ጉዳት ካሣ መጠየቅ ስለሚችል (ቁ. 2287 ፤ 2289 ፤ 2300 (3) ፣ 2361 (1) የሚጣልበት ካሣ መክፈል አስቸጋሪ ሊሆንበት አይ ችልም ። ሌሎች ዕቃዎች አቅራቢ ነጋዴዎችን በሚመለከት ፤ እነሱ «መግለጽ» በሚለው ጽንሰ—ሀሳብ ተጠብቀዋል ።

ፍሬ—ነገር 6

የዚህን ፍሬ ነገር ተቀባይነት ማግኘት እንደግፋለን ። በሀ/ እና በለ/ የተገለጹት መከላከያዎች ሠሪውን (ኢትዮጵያ ውስጥ በመሠረቱ መንግሥት ወይም የእሱ የማምረቻ ድርጅት ነው) ተገቢ ካልሆነ ክስ ይጠብቁታል ። በሐ/ የተገለጸው መከላከያ ሚዛናዊና ባሁኑ ሕግም ውስጥ (ቁ. 2085) ውስጠ—ታዋቂ ነው ። በነገራችን ላይ ፤ ስምምነቱ «የጉድለት መገኘት መቻል» መከላከያ እንደሚሆን አይደነ ግግም ። ይህ ለሸያጭ የጥራት ዋስትና ዓይነተኛ የሆነው መከላከያ (ቁ. 2293 (2)) የተጠቃሚውን ደኅንነት ከሚመለከቱት (ፍሬ—ነገሮች 2—3ን ይመለከቷል) ከዕቃዎች አላፊነት ሕግ ጋራ የማይገጥም ነው ።

መመሪያው

በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት የመመሪያው የአላፊነት ገደብ ቁም ነገራዊ ጽንሰ—ሀሳብ (ማከያ መ ን ይመለከቷል) ጠባብ በሆነው በዕቃዎች አላፊነት አስተሳሰብ አንፃር ሊተነተን አይችልም ። በኢትዮጵያ ሕግ ውስጥ የሀላፊነቱ ሕጋዊ መሠረት ምንም ይሁን ምንም[68]

1. ሞትን በሚመለከት ፤ ለንዋይ ጉዳት ያለው አላፊነት «መተዳደሪያን በመስጠት እንደሚደረገው ጡረታ መልክና ዓይነት» ካሣ በመስጠት ላይ የተወሰነ (ቁ. 2095) (2)[69]፤
2. ሞትን ወይም የሰውነት ጉዳትን («የአካል ጉዳት» ን) በሚመለከት የጉዳቶች አካል የሆነው የ «ሕሊና» ጉዳት ካሣ በጣም አነስተኛ በሆነው 1000 ብር የተወሰነ ነው (ቁ. 2116) (3)[70]፤
3. ሞት የማያስከትል ጉዳትን በሚመለከት በመሠረቱ[71] ለንዋይ ካሣ[72] አላፊነቱ ወሰን የለውም ።

ረቂቅ ሕግ

እላይ በተጤኑት በሁሉም ግምገማዎች አንፃር የፍት. ሕግ ቁጥር 2085ን በመጨረሻ ይተካሉ ተብለው የታሰቡትን የሚከተሉትን ረቂቅ ድንጋጌዎች በአክብሮት እናቀርባለን ።

ለዕቃዎች አላፊነት—1. መሠረቱ

ዕቃው ውስጥ ባለ ጉድለት ምክንያት በዕቃው ተጠቃሚ ላይ ለደረሰ የሞት ወይም የአካል ጉዳት ሠሪው አላፊ ነው ።

ለዕቃዎች ኣላፊነት—2. ትርጉም

(1) «ዕቃ» ማለት በሰው የተሠራ ፤ የተለወጠ ወይም የተዘጋጀ ተንቀሳቃሽ ነገር ነው ።

(2) አንድ ዕቃ ፤ የዕቃውን አቀራረብ ጨምሮ ያካባቢው ሁኔታዎች ሁሉ ከተጤኑ በኋላ ፤ አንድ ሰው ሊጠብቀው የሚገባውን ተገቢ የደኅንነት ዋስትና የማይሰጥ ከሆነ «ጉድለት» አለው ።

3) «ሠሪ» ማለት፡—

ሀ/ የዕቃው አምራች ፤

ለ/ የውጭ አገሩን ዕቃ አስመጪ ፤ እና

ሐ/ የአቅራቢውን ማንነት ለይገባኛል ባዩ ለመግለጽ ፈቃደኛ ካል ሆነ የዕቃው አቅራቢ ነው ።

ለዕቃዎች ኣላፊነት—3. መከላከያዎች

ሠሪው

ሀ/ ዕቃው በእሱ አለመሠራጨቱን ፤ ወይም

ለ/ የነገሩ አካባቢ ሁኔታ በሙሉ ከተጤነ በኋላ ዕቃውን ባሠራጨ ጊዜ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ጉድለት አለመኖሩን ወይም ይህ ጉድለት በኋላ መፈጠሩን ፤ ወይም

ሐ/ ዕቃው የተሠራ አለመሆኑን እና/ ወይም የተሠራጨው ሠሪው ንግዱን በሚያከናውንበት ጊዜ ትርፍ ለማግኘት እንዳልነበረ ካስረዳ ኣላፊ አይሆንም ።

በነገራችን ላይ ፤ ቁ. 2086 (2) የተሰጠው በጥብቅ—ኣላፊነቶች ላይ የሚቀር በው «የተጐጂው ጥፋት» የሚለው መከላከያ ለዕቃዎች ኣላፊነትን በሚመለከት ክስም መከላከያ ነው ።

የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

*ለ10ኛው ኢንተርናሽናል ኮምፓራቲቭ ሎው አካዳሚ የቀረበ ሪፖርር (1978 ዓ.ም. እ.ኤ.አ.)

** በሕግ ፋኩልቲ ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር የነበሩ ፡

1. « በተዘዋዋሪ » ምክንያቱም «በቀጥታ » ለትርፍ ማቅረብ የውል ግንኙነት ስለሚፈጥርና ይህ ደግሞ ከውል ውጭ መፍትሔዎች ውጭ ስለሆነ ። ቁ. 2088 እና 2037 ን ይመለከቷል ።
2. እንዲሁም ጂ ክሽቺኖቪች ዘ. ኢትዮጵያን ሎው ኦፍ ኤክስትራ ኮንትራክቸዋል ሊያቢሊቲ (አዲስ አበባ 1970 ዓ. ም.) « ምሁራዊ ማስተዋወቂያ » ይመለከቷል ።
3. የ « ትርፍ » መመዘኛ ለምሳሌ መራመድ ለማይችሉ ያለትርፍ በሚያቀርበው ማንከሻ ውስጥ ላለው ጉድለት የኢትዮጵያ መልሶ ማቋቋም ማዕከልን ጥብቅ አላፊነት ያስቀረዋል ፡
4. « ለሕዝብ የማቅረቡ » መመዘኛ ለመጨረሻ ተጠቃሚዎች ሳይሆን ከሌላ ሥራ ለተጨማሪ ለውጥ ለቀረቡ ዕቃዎች (ለምሳሌ ብረትን ወደሞተር ተሽከርካሪነት ለሚለውጥ) « ጥብቅ » የውል ውጭ አላፊነትን ያስቀራል ።
5. ነገር ግን በቁጥር 3039 ሥር የውል መፍትሔ መኖር በገንቢው ላይ ቁጥር 208 5 ን የመጠቀሙን ሁኔታ ሊያስቀረው ይችላል ።
6. ከኤች ስትሪት (ዘ ሎው ኦፍ ቶርትስ ፤ ለንደን 1963) ከገጽ 172 እና ተከታዮቹ ገጾች ውስጥ የተጠቀሰ ።
7. ደብልዩ ኤል ፕሮሰር (ሃንድቡክ ኦፍ ዘ ሎው ኦፍ ቶርትስ ሴንት ፖውል ሚን 1964) ገጽ 543 እና ገጽ 678 ን ይመለከቷል ።
8. በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ገጽ 681
9. ተፈጻሚነት ሲኖረው በዚያው ተከሳሽ ለምሳሌ ለከሳሹ ዕቃውን በሸጠው ሥራ ላይ የውል ውጭ ሕግን ተፈጻሚነት ያስቀረዋል ። ቁጥር 2088 ን ይመለከቷል ።
10. እንደገና ፕሮሰርን ይመለከቷል ።
11. ቲ. ቢ. ስሚዝ ፣ « ሎው ሪፎርም ኢን ኤ ሚክስድ . . ጁሪስዲክሽን » ቱዚያና ሎው ሪቪው (ቅጽ 35 1975 ልዩ እትም) ፣ ገጽ 956.
12. የዚህን ትንታኔ እላይ በ2 ሥር ይመለከቷል ።
13. ይህ አገላለጽ እራሱ ለሁሉም በጥፋት ላይ ለተመሠረተ አላፊነት ድንጋጌዎች ክፍል (ቁ. 2028 እስከ 2065) ባዕድ ነው ።
14. በሌላ ሁኔታ ካልተገለጹ በስተቀር « ክፍል » ወይም « ቁጥር » (እና « ክ » ወይም « ቁ ») በቅደም ተከተል የሚያመለክቱት በኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ ውስጥ ያሉትን ክፍሎችና ቁጥሮች ነው።
15. ነገር ግን ይህ የመጨረሻው መከላከያ ተፈጻሚነቱ በቁ. 2071—2084 ሥር በተገለጹት ዕቃዎች « ባለቤቶች ወይም ጠባቂዎች » ላይ ብቻ ስለሆነ ለዕቃዎች አላፊነት አግባብ የለውም ።
16. የኢትዮጵያ የውል ውጭ ድንጋጌዎች (ምዕራፍ 13 ፍት. ሕ. ቁ. 2027—2161) በፍትሐ ብሔር ሕጉ የእንግሊዝኛ ቅጅ ውስጥ በትክክል አልተተረጎሙም ። በዚህም ምክንያት አንባቢው ተሻሽሎ የቀረበውን ትርጉማቸውን ከጂ ክሽቺኖቪች ዘ ኢትዮጵያን ሎው ኦፍ ኤክስትራኮንትራክቸዋል ሊያቢሊቲ (አዲስ አበባ 1970) ተቀጥላ ዲ ወይም ዘ ኢትዮጵያን ሎው ኦፍ ኮምፕንሴሽን ፎር ዳሚጅ (አዲስ አበባ 1977) ገጽ 316—354 ውስጥ እንዲመለከት እንመራዋለን ።
17. የውል ሕግን ያነጻጽሯል ፣ « በጥራት መድን » ክስ ውስጥ ከሳሾቹ የግድ « ተጠቃሚዎች » መሆን የለባቸውም ፣ ተከሳሾቹም የግድ የዕቃው « ሠሪዎች » መሆን የለባቸውም ። ቁም ነገሩ የውል ግንኙነት መኖሩ ብቻ ነው ።
18. ለምሳሌ በፈታሽነታቸው ወይም የሠሪው ተቀጣሪዎች በመሆናቸው በአሠራሩ ውስጥ በመሳተፋቸው ከእቃው ጋር ግንኙነት ያላቸው ተጠቃሚዎች « በዕቃዎች አላፊነት » ፈንታ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 2549 እና ተከታዮቻቸውን ቁጥሮች እና ሌላ አግባብ ያለው የሠራተኛ ሕግ መጥቀስ አለባቸው ።

19. በከሳሹ የመጠቀም ያለመጠቀም ሁኔታ ባይኖርም ፣ በእሱ የተገዛውን ዕቃ ጥቅም ብቻ የሚነካ ጉድለት በሻጩ ላይ ለካሳ ያቀረበውን ክስ ሊደግፍለት ስለሚችል ፣ በውል ሕግ ሥር በጥራት ዋስትና ጉዳዮች ውስጥ ሁኔታው በርግጥ የተለየ ነው ።

20. ካሳን በሚመለከት የውል ውጭ አላፊነት ድንጋጌ ቁ. 2091 ን ከውል ሕግ ድንጋጌ ቁ. 1799 ጋር ያወዳድሯል ።

21. ይኸኛው ክፍል አንዳንድ ጊዜ ተደጋጋሚ ነው ፣ ሆኖም ከክፍል 1. ይልቅ ችግሮችን ከተለያዩ አቅጣጫና በከፍተኛ ጥልቀት ይመለከታል ።

22. « በተዘዋዋሪ » የገባው በክፍል 1. 1 ውስጥ በተሰጡት ምክንያቶች ነው ።

23. ተጠቃሚዎች ያልሆኑ ከሥሪው ሌላ ጉዳት አድራሹን ዕቃ በባለቤትነት ከያዙት ፣ ከሚጠቀሙበት ወይም ከሚቆጣጠሩት ሰዎች — ባለቤቱ (የመኪናው ፣ የሞተር ተሽከርካሪው ፣ የሕንጻው — ቁ. 2081 እና 2077 እና ተከታዮቹ ቁጥሮች) ፤ ጠባቂው(ቁ. 2082) ፤ የአደገኛ ሁኔታዎች ፈጣሪው (ቁ. 2069) በበቂ ሁኔታ በጥብቅ አላፊነት መፍትሔዎች ተጠብቀዋል ። የተዘጋጁ ምግቦችና አብዛኛዎቹ መድኃኒቶች ግን ተጠቃሚ ያልሆኑትን አይጐዱም ።

24. እስካሁን የንድፍ (የዲዛይን) ጉድለትን ብቻ የሚመለከቱ ለዕቃዎች አላፊነት ክርክሮች አናውቅም። ራሱ የቁ. 2085 አጻጻፍ የ « ንድፍ » ጉድለት አስተሳሰብን ለዕቃዎች አላፊነት ክስ አግባብ እንዳይኖረው ያደርገዋል ። ቢሆንም በንድፍ ውስጥ የሚገኝ ጉድለት በዕቃው ውስጥ ለሚገኝ ሌላ ጉድለት እንደማጠናከሪያ ማስረጃ ሊያገለግል የሚችል መሆኑ እርግጥ ነው ።

25. ሌሎቹ ሁለት የመከላከያ ድንጋጌዎች (እታች ከ2—3 ይመለከቷል) ይበልጥ አጠቃላይ ናቸው ፤ እነሱ ከዕቃዎች አላፊነት ሌላም ለጥብቅ አላፊነት ጉዳዮችም ሊነሱ ይችላሉ ።

26. ይገባኛል ባዩ ማስረዳት ያለበት ጉዳት የደረሰበት ዕቃውን በአግባቡ ሲጠቀምበት መሆኑን ብቻ ሲሆን ፣ ምናልባትም ደግሞ ቢበዛ ጉዳቱ የደረሰው በዕቃው ልክ ያልሆነ « ጠባይ » መሆኑን (እላይ ሀ. ንጥብ (2) ንና ስለሱ የተሰጠውን ትንተና ይመለከቷል) ጭምር ነው ።

27. ወይም በሌሎቹ የጥብቅ አላፊነት ጉዳዮች ውስጥ ከአደገኛው እንቅስቃሴ ፣ ወይም ከእንስሳው ፣ ሕንጻ ፣ መኪና ፣ ሞተር ተሽከርካሪ (ቁ.2069 ፣ 2077 ፣ 2081) ።

28. እንደዚሁም የግርጌ ማስታወሻ 18 ንና ማብራሪያውን ይመለከቷል ።

29. በአደገኛ ሥራዎች ፣ ወይም በእንስሳ ፣ በሕንጻ ፣ በመኪና ፣ በሞተር ተሽከርካሪ (ቁ. 2069 ፣ 2071 2077 ፣ 2081) ለደረሰ ጉዳት አላፊነቶች ።

30. በአጭሩ ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ፣ እቫን ፕሮዤ ደ ኮድ ሲቪል ለኢምፓየር ዲ ኢትዮፒ የፍትሕግ ሠነዶች (አዲስ አበባ 1955) ገጽ 21 ውስጥ በተገለጸው በሕጉ አርቃቂ ሬኔ ዳቪድ የቁ. 2085 ንዑስ ቁጥር (1) አጻጻፍ መሠረት ። በጥብቅ ከውል ውጭ አላፊነት ውስጥ እንዳያገለግል ቢደረግም « ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል » የሚለው መከላከያ በኢትዮጵያ የውል ሕግ ውስጥ ተቀባይነት አለው።

31. በፈረንሳይ የፍርድ ውሳኔዎች ውስጥ ከሚገኙ በቂ ካልሆኑ ቅንብሮች የተወሰደ ነው ።

32. በዕቃዎች አላፊነት ውስጥ « በዕቃው ተገቢ አጠቃቀም » ምክንያት የደረሰ (እላይ በሀ. ንጥብ (2) ሥር ተወስቷል) ።

33. ዕቃው በተሰራጨበት ነገር ውስጥ ወይም በአካሉ ላይ ያለ ትክክለኛ የጉድለት ምክንያት የመሳሰሉ። ጉድለቱ « ሊታወቅ የመቻሉ ሁኔታ » እላይ በ1 ሥር የተመረመረውን መከላከያ ያጠናክራል ።

34. ተከሳሹም ጥፋተኛ ከሆነ ፣ በከፊል ብቻ ነጻ ይሆናል ፣ ቁ. 2098 ን ይመለከቷል ።

35. ለበለጠ ማብራሪያ ጂ ክሽኖቪች ፣ ዘ ኢትዮጵያን ሎው ኦፍ ኮምፐንሴሽን ፎር ዳሜጅ (አዲስ አበባ 1977) ፤ ገጽ 124 ይመለከቷል ።

36. እላይ በሀ. ንጥብ (2) ሥር ያለውን ገለጻ ይመለከቷል ።

37. በነገራችን ላይ ፣ « ውላዊ » ማስጠንቀቂያዎች እና (ወይም አላፊነትን የሚያወርዱ ጽሑፎች ለዕቃዎች አላፊነት (የሶስተኛ ወገን) የካሳ ጠያቂዎችን መብት አይነኩም ።

38. የሚከተለው ጽሑፍ የዚህን ዘገባ ክፍል 4 የፈረንሳይኛ ቅጂ መሠረት በማድረግ እንደገና የተስተካከለ ነው ።

39. ክፍል 1 ፣ 1 ን ይመለከቷል ። ይህ ጸሐፊ ትዝ እንደሚለው ይህ ድንጋጌ ሕጉ በሚወጣበት ጊዜ በችኮላ የተረቀቀ ነው ።

40. ለምሳሌ እክፍል 1 ውስጥ በግርጌ ማስታወሻ 7 የተጠቀሰውን ደብልዩ ኤልፕሮስርን ይመለከቷል ።

41. አሁን አብዛኛውን ጊዜ የተባበረው የአሜሪካ መንግሥት የፍርድ ውሳኔ ሕግ ይህንን ፖሊሲ ያንጸባርቃል (በፕሮፌሰር ሲ ሽሮት ለጉባኤው የቀረበ ዘገባ እንደሚያመለክተው) ፣

42. ክፍል 2 ፣ ንጥብ (2) እና የሚከተለውን ይመለከቷል ።

43. እዚሁ አሁን የተጠቀሰው ውስጥ ይመለከቷል ።

44. የተሟላ ዘገባ ለማቅረብ ሠፊ የሆነና ብዙ ቦታ የሚፈጅ ምርምራዊ ጽሑፍ ይጠይቃል ።
45. በቡዳፔስቱ ጉባኤ በቂ ያልሆነ ዝግጅት ምክንያት ብዙ ብሔራዊ ዘገባዎች በእቅዱ መሠረት ለመ ሰል ዘገበኞች ከመድረሳቸው በፊት ጠፍተዋል ።
46. ፕሮፌሰር ደብልዩ ግሬይ ጠቅላላ ዘገባ ።
47. ፕሮፌሰር ፒ ሽሮት ፣ የተባበረው የአሜሪካ መንግሥት ዘገባ ።
48. በንግሊዝ አገር እንደሚደረገው ሁኔታው እራሱ ይናገር የሚለው ዝነኛ ምሑራዊ ዘገባ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ።
49. ፕሮፌሰር ፒ ማሊንቨ ፣ የፈረንሳይ ዘገባ ።
50. እታች በሀ ሥር ያለውን ትርጉም ከሚጨምረው ከፕሮፌሰር ግሬይ ጠቅላላ ዘገባ ውስጥ የተራባ ወይም የተጠቀሰ ።
51. ይህ ረቂቅ ሕግ በሥራ ላይ መዋል አለመዋሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የለንም ። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ በዶክተር ጂ ራዲሲክ እና በፕሮፌሰር ሚትሮቢች የተዘጋጀው የዩጐዝላቢያ ዘገባ ለጉባኤው ባለመ ሰጠቱ (የግርጌ ማስታወሻ 45 ን ይመለከቷል) ቅር ተሰኝተናል ። እታች የቀረበውን የትችቱን ትክ ክለኛነት ምናልባት የሚነካው ቢሆን ይቅርታ እንጠይቃለን ።
52. እላይ በመጀመሪያ በግርጌ ማስታወሻ 16 የተጠቀሰው መጽሐፍ ።
53. የንግሥቷ የጽሕፈት ዕቃዎች ጽሕፈት ቤት ፣ ሎንደን 1977 ዓ. ም
54. አይ—15.341 የሮፒያን ትሪቲስ ሲሪስ ፣ ቁ. 91(1977) ፤ እስካሁን በኦስትሪያ ፣ በቤልጅግ ፣ በፈረ ንሳይ ፣ በሉክሰምበርግ የተፈረመ ።
55. በስምምነቱ የተገለጹት የማብራሪያ ዘገባዎች በተለያዩ ምክንያቶች ተቀባይነትን ሊያገኙ ይችላሉ።
56. በቀዳሚው ቁጥር 2 ውስጥ « ዕቃ » ፣ « ሠሪ » እና « ጉድለት » ትርጉም ተሰጥቷቸዋል ።
57. በዘገባችን ክፍል 2 ፣ ሀ (2) ውስጥ የተሰጠውን ትችት ይመለከቷል ።
58. በተቀጥላው ጽሑፍ ውስጥ ፍሬ ነገር 4 ን ይመለከቷል ።
59. ማስታወሻ « ሠሪ » እንደሠሪ የሚቆጠርንም ይጨምራል (እላይ ይመለከቷል) ።
60. የስምምነቱ ቁጥሮች 1 እና 10—19 ።
61. የስምምነቱ ቁጥሮች 3 (5) ፤ 4(1) ፣ 5 (2) 6 ፣ 7 ፣ 8 ፣ የኢትዮጵያን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 2086 (1) ፣ 2086(2) ፤ 2143 ፣ 2147 (3) ፣ 2155 (1) ፤ 2156 ን ያወዳድሯል ።
62. ለምሳሌ የስምምነቱ ቁጥሮች 2(ለ) ተቀባይነት ያጣ ፣ 2 (መ) እና 9(ሀ) (የማያስፈልግ) ፤ 9(ለ) (ጊዜው ያልደረሰ)
63. ኦፊሻል ጆርናል ኦፍ ዘ ዩሮፒያን ኮሙኒቲስ (1976) ቁ. ሲ 24179
64. እላይ በግርጌ ማስታወሻ 16 በመጀመሪያ የተጠቀሰውን ሥራችንን ገጽ 44 ይመለከቷል ።
65. ተገቢ የሚለው ቃል በስምምነቱ ተትቷል(የስምምነቱን የማብራሪያ ዘገባ አንቀጽ 35 ይመለከቷል) ምክንያቱም በፈረንሳይኛው ቅጂ ውስጥ ያልተፈለገ ትርጉም ስለሚሰጥ ፣ እኛ ተጨባጭ « ተገቢ ነት » ቢጠበቅ ትክክል ይመስለናል ።
66. ለተጨማሪ ማብራሪያ በግርጌ ማስታወሻ 53 የተጠቀሰውን የእንግሊዙን ሠነድ አንቀጽ 102 ይመ ለከቷል ። እንዲያውም ለበለጠ ምክንያት መብታቸውን የማያውቁ ይገባናል ባዮች ለሞሉባት ኢትዮጵያ ይስማማሉ ።
67. « የራስ ምልክት » የተለጠፈባቸው ዕቃዎች በዚች አገር ውስጥ እጅግም ስለማይታወቁ አንዳንድ ልዩ የሆኑ ጉዳዮች ሲገጥሙ በምትክነት በ ሐ/ የተሰጠው መፍትሔ ተፈጻሚነት እንዲኖረው በማድረግ ችግሩን መፍታት ይቻላል ።
68. ለምሳሌ በፍት/ሕግ አንቀጽ 13 የምዕራፍ 1 ፣ 1—2 ክፍሎች ሥር ።
69. ስለዚህ አደናጋሪ መመዘኛ የተሰጠውን ትችትና መደምደሚያ እላይ በግርጌ ማስታወሻ 35 በተጠ ቀሰው መጽሐፋችን ውስጥ ከገጽ 146—153 ይመለከቷል ።
70. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠውን ትችትና የቀረበውን ሃሳብ በገጽ 287 እና 291(መ) እናት ላይ ይመለከቷል ።
71. ለልዩነቶች በዚህ መጸሐፍ ውስጥ ምዕራፍ 3 ክፍል 2 ን ይመለቷል ።
72. በነገራችን ላይ ፣ ከሰውነት መጐዳት የተነሳ (ሞትን ቢያስከትልም ባያስከትልም) የንዋይ ጉዳት አካል የሆነው « የገቢን ማጣት » በሚመለከት የዴንማርክን አሠራር ካጤንን በኋላ በዚሁ መጽሐፍ (ገጽ 153) ውስጥ ገቢ በመቅረቱ (የመተዳደሪያ ገቢ) ለሚፈጠረው አላፊነት ገደብ እንዲደረግበት ከፍተኛው መጠን ለምሳሌ በአንድ መካከለኛ የመንግሥት ሠራተኛ ገቢ ላይ የተወሰነ እንዲሆን ሃሳብ አቅርበናል ። ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች እራሳቸው ከፍተኛ የኢንሹራንስ ሽፋን መግዛት ይኖርባቸዋል ።

በሕብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ፤
ጠቅላይ ፍርድ ቤት
አዲስ አበባ ።

የወንጀል ይግባኝ መ.ቁ. 4/71
ኅዳር 7 ቀን 1772 ዓ. ም.

ዳኞች :— 1.
2.
3.
4.
5.

ይግባኝ ባዮች :—
1/ አለቃ ወ. ሃ. ሰ.
2/ ቢ. ተ.

መልስ ሰጭ :— ዓቃቤ ሕግ

ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል ።

ው ሳ ኔ

ለዚህ ይግባኝ መነሻ የሆነው አንደኛው ይግባኝ ባይ በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 20 የተጻፈውን ድንጋጌ ተላልፎ አቶ ኃ. ፀ.ን በማስገደሉ ለምር መራ ታስሮ በነበረበት ጊዜና ከወጣም በኋላ ጥፋቱ እንዳይደረስበትና በፍርድ እንዳይቀጣ ዳኞችና መርማሪዎች በሥራ ግዴታቸው ማድረግ የማይገባቸውን እን ዳያደርጉ ወይም እንዲያደርጉ በማሰብ ከአምስት ሺህ ብር በላይ ጉቦ ሰጥቷል ፤ እንዲሁም ሁለተኛው ይግባኝ ባይ እላይ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ተላልፎ የአንደ ኛው ይግባኝ ባይ አባሪ በመሆን እሥር ቤት አብሮ በነበረበት ጊዜ ከአንደኛው ይግባኝ ባይ ሁለት ሺህ ብር ተቀብሎ ጉዳዩን ለያዘው መርማሪ ለሻምበል ባሻ ገ.ሥ ሰጥቷል ፣ ከእሥር ቤት ከወጣም በኋላ ጉቦ ለመስጠት የወሰደውን ሌላ ሁለት ሺህ ብር ለራሱ ጥቅም አውሏል ተብለው በከፍተኛው ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ክስ ፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው ፍርድ ቤት ተከሣሾቹን በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኞች አድርጐ አንደኛው ተከሣሽ በአስር ዓመት ጽኑ እሥራት ፣ ሁለተኛ ተከሣሽ ደግሞ በስድስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ መስከረም 7 ቀን 1972 ዓ. ም. በዋለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 203/71 የሰጠውን ፍርድ በመ ቃወም ነው ።

የይግባኝ ባዮቹ ጠበቃ ደንበኞቹ የተነገረባቸውን ወንጀል ለመፈጸማቸው አስተማማኝ በሆነ የሶስተኛ ሰው አስረጂነት አልተረጋገጠባቸውም ፣ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በድምጽ ብልጫ የሰጠው ፍርድ መሠረት ያደረገው ተከሣሾቹ ለፖሊስ ሰጥተዋል የተባለውን የእምነት ቃል ነው ፣ የእምነቱ ቃል ግን በፈቃደኛነት ሳይ ሆን በማስገደድ በድብደባ የተገኘ ነው ፤ ተከሣሾቹ በምርመራ በነበሩበት ጊዜ ከ ባድ ድብደባና ከፍተኛ ስቃይ የደረሰባቸው መሆኑን በቆጠሯቸው መከላከያ ምስ ክሮች በሚገባ አስረድተዋል ፣ ከፍተኛው ፍ/ቤት ተከሣሾቹ በፖሊስ ጣቢያ ሰጥ ተውታል ተብሎ የቀረበለትን የእምነት ቃል በፈቃደኛነት ሳይሆን በማስገደድ የተገኘ መሆኑን በተቃራኒ ማስረጃ እያረጋገጥን ትክክል ነው ብሎ የተቀበለው በማይገባው ነው ፣ ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በድምጽ ብልጫ የተሰጠውን

ፍርድ ሸሮ በአንስተኛ ድምጽ የተሰጠውን የውሳኔ አስተያየት በመደገፍ ይግባኝ ባዮቹን በነጻ ያሰናብትልኝ ሲል ጠይቋል ።

ክርክሩን በዚህ ፍርድ ቤት በመልስ ሰጭነት የሚመራው ዐቃቤ ሕግም በበኩሉ ጥቅምት 29 ቀን 1972 ዓ. ም. በተጻፈ ሶስት ገጽ የመልስ ማመልከቻ ፡ ይግባኝ ባዮች በተከሰሱበት ወንጀል በጣቢያ ከሰጡት የእምነት ቃል ሌላ የቀረበባቸው ግዙፍ ማስረጃ የለም፣ በምርመራ ላይ በነበሩበት ጊዜ ከሰብአዊ ርህራሄ ውጭ አ ራት ቀን በተከታታይ እንደተደበደቡና ቆስለውም እንደነበረ የመከላከያ ምስክሮ ቻቸው አረጋግጠውላቸዋል ፡ በዚህም ምክንያት በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠው የእ ምነት ቃል ያላንዳች ማስገደድ በፈቃደኛነት የተገኘ ነው ለማለት አይቻልም ፡ ይግባኝ ባዮቹ ወንጀሉን ለመፈጸማቸው በአጥጋቢ ማስረጃ አልተረጋገጠባቸውም ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በአነስተኛ ድምጽ የተሰጠውን የውሳኔ አስተ ያየት ደግፎ ይግባኝ ባዮቹ በነፃ ቢለቀቁ አንቃወምም ሲል አሳስቧል ።

ይግባኝ ባዮቹ አስቀድመው በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተከራከሩት፣ አሁንም በይግባኝ ደረጃ በዚህ ፍርድ ቤት አጥብቀው የሚከራከሩት በክስ አቤቱታው ላይ የተነገረባቸውን ወንጀል መፈጸማቸውን በመካድ ነው ። ዐቃቤ ሕጉ ክሱን ለማ ስረዳት ያቀረበው ማስረጃ ተከሣሾቹ በፖሊስ ጣቢያ ሰጡ የተባሉትን የእምነት ቃልና የእምነት ቃሉን ሲሰጡ ነበሩ የተባሉ አስረጂዎችን ብቻ ነው ።

ተከሣሾቹ የእምነቱን ቃል በፖሊስ ጣቢያ መስጠታቸውን ያልካዱትና የማይክዱት ነገር ነው ። የእነርሱ ክርክር ወንጀሉን መፈጸማችንን ያመንነው በተከታታይ ለአራት ቀናት ስለተደበደብን የደረሰብንን ስቃይ መቋቋም ባለ መቻላችን ነው የሚል ነው ። በምርመራ በነበሩበት ጊዜ ተከሣሾቹ የድብ ደባ ተግባር የተፈጸመባቸው ለመሆኑ መከላከያ አስረጂዎች አቅርበው አረጋ ግጠዋል ። ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተከሣሾቹን በድምጽ ብልጫ ጥፋተኞች ያደረጋ ቸው በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የተገኘውን የተከሣሾቹን የእምነት ቃል ሐቀኛና ብቁ ነው በማለት ነው ። በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠው የእምነት ቃል ብቁና ሐቀኛ መሆኑን ለማሳመንም የድምጽ ብልጫው ውሳኔ በብዙ አንጻሮች አጠያያቂ የሆኑ የትችት ነጥቦች ሠፍሮበት ይታያል ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ « በድብደባ ለነ ፍስ አድን የሚሠነዘር የፈጠራ ቃል እንደመኖሩ መጠን በድብደባም አማካኝነት የሚወጣ ሐቅ እንዳለም መዘንጋት አይገባም » ይላል ። ይህ አስተያየት በምር መራ ደረጃ የሚፈጸም ማባበልን ፤ ማስፈራራትንና የኃይል ተግባርን ተገቢ ነው ብሎ የሚያጸድቅ ነው ። በምርመራ ጊዜ አንድ መግለጫ ለማግኘት ወይም ጥፋ ትን ለማሳመን የሚፈጸም የኃይል ተግባር በሕግ የሚያስጠይቅና የሚያስቀጣ (ወ. መ. ሕ. ቁጥር 417 እና ልዩ ወ. መ. ሐ ቁጥር21) መሆኑ ቀረና፣ የእምነት ቃልም አጠራጣሪነቱ ተረሳና፣ ፍርድ ቤት የሚሠራው በሕግ፣ ሕግም የተደነገገው የኃይል ተግባርን ለመቋቋም መሆኑ ተረሳና ድብደባ መልካም ነው ፣ ሐቁን ያወጣል የሚል ትችት ሰብአዊ መብት ይከበርበታል ፣ የተበደለም ይካስበታል ፣ የበደለም ይቀጣበ ብታል ተብሎ አደራ ከተጣለበት የፍትሕና ርትዕ አደባባይ መሠንዘሩ እጅግ አሳ ዛኝ ነው ። እርግጥ በማባበል፣ በማስፈራራትና የኃይል ተግባር በመጠቀም አንዳንድ ጊዜ የተዳፈነ ሐቅ ይፋ ሊወጣ ይችላል ። መታወቅ ያለበት ቁም ነገር ግን የወንጀል ተግባር ፈጽሞ ይሆናል ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው ሁሉ ወንጀለኛ አለመሆኑ ነው ። ሐቅን ለማግኘት ተብሎ ተጠርጥሮ የተያዘው ሁሉ የኃይል ተግባር የሚፈ ጸምበት ከሆነ ደግሞ ንጹኃን ጭምር መበደላቸውና መጎዳታቸው አይቀርም ። ተጠርጣሪው በእርግጥ ወንጀለኛ ቢሆን እንኳ ፣ የኃይል ተግባር ከተፈጸመበት ሽብ

ርና ጭንቀት ስለሚያድርበት የሚሰጠው የእምነት ቃል ሁልጊዜ ሙሉ በሙሉ
ትክክለኛ ፣ ሐቀኛና አስተማማኝ ሊሆን አይችልም ። ሕግም ሆነ ትክክለኛ የዳኝ
ነት አስተያየት እንዲህ ዓይነቱን እርምጃ የሚያወግዙት ንጹኃን አላግባብ እንዳይ
በደሉና ሕይወታቸውን ለማትረፍ ሲሉ ባልፈጸሙት ተግባር ራሳቸውን እንዳይወ
ነጅሉ ነው ። የሕጉ ምርጫ ንጹኃን አላግባብ ከሚበደሉ አጥፊው ቢያመልጥ ይሻ
ላል ነው ። ድብደባ ሕገወጥ አድራጐት በመሆኑ ፣ በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ የእ
ምነት ቃልም ሕጋዊ ሊሆን አይችልም ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ ትችቱን በመ
ቀጠል « የዓለም ሕዝብ በሥልጣኔ እየተራመደ እንደመሄዱ መጠን የወንጀል አፈ
ጻጸሙ ዘዴም ያን ያህል የረቀቀ ስለሆነ ፣ እውነቱን ለማግኘት ብዙ ብልሃት የማድ
ድረጉ ጉዳይ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል » ይላል ። እርግጥ የዕድገት ደረጃ ከፍ እያለ ፣
ሥልጣኔም እየገፋ ሲሄድ የወንጀል ተግባራትም በረቀቀ ዘዴ እንደሚፈጸሙ አያ
ከራክርም ። በአንጻሩ ሕግን ፣ ሰላምንና ጸጥታን በሚያስከብረው ክፍል በኩልም
ለመፈጸም የታቀደ ወንጀልን ለማክሸፍ ወይም የተፈጸመ ወንጀልን ፈልፍሎ ይፋ
ለማውጣትና አጥፊውንም ይዞ ለፍርድ ለማቅረብ የተራቀቀ ዘዴና ብልሃት ያስፈ
ልጋል ። እስከዚህ ድረስ በድምጽ ብልጫ ከተሰጠው ውሳኔ የተለየ አስተያየት የለ
ንም ። መችም ቢሆን ግን ድብደባ ሥልጣኔ ያስገኘው የወንጀል ተግባር ማክሸፊያ
ወይም ማጋለጫ ልዩ ጥበብ ፣ የተራቀቀ ዘዴና ብልሃት ነው አንልም ። ድብደባ አሪ
ታዊ እንጂ ሥልጣኔ ያስገኘው ዘመናዊ የምርመራ ሥልት አለመሆኑ ለማንም የታ
ወቀና መታወቅም ያለበት ነገር ነው ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ ግን ሊያሳምነን
የሞከረው ድብደባ ሐቁን ለማውጣት ሥልጣኔ ያስገኘው የተራቀቀ ዘዴና ብልሃት
መሆኑን ነው ። ትችቱ ድብደባ የተፈቀደ ዘዴና ብልሃት መሆኑን ለማሳመን ባደረ
ገው ሙከራ ብቻ ተወስኖ አልቀረም ። በድብደባ የተገኘ የእምነት ቃል በሚቀር
ብበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች በተለይም በሶሺያሊስት አገር ያሉ ፍርድ ቤቶች ምን ማድ
ረግ እንዳለበባቸው ተግባራዊ መሠረት ይጥልላቸዋል ። ይህንንም አሳብ « የሶሻያሊ
ስት አገር ፍርድ ቤቶች ዓይነተኛ ዓላማም የመንግሥት አካል እንደመሆናቸው መ
ጠን ሐቁ የሚወጣበትን መንገድ መሻት ስለሆነ በፖሊስ በኩል የሚቀርበውን
ቃለ ምርመራ በጥሞና አጥንተው በጉዳዩ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ነው እንጂ
ያለባቸው ፣ አንዳንድ ጥቃቅን የሥርዓተ ሕግ ፎርማሊቲ አልተሟላም ተብሎ ብዙ
ድካም የተወሰደበትን ቃለ ምርመራ ውድቅ ማድረግ ተገቢ አሠራር ነው ብለን
እናምንበትም » በማለት ገልጦታል ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ በአንድ በኩል
ፍርድ ቤቶች ሐቁ የሚወጣበትን መንገድ መሻት ነው ይልና በሌላ በኩል ደግሞ
ብዙ የተደከመበትን የምርመራ ውጤት ውድቅ ማድረግ የለባቸውም ይላል ። በፖ
ሊስ ምርመራ « ተጣርቶ » የቀረበላቸውን ሁሉ ውድቅ ሳያደርጉ እንዳለ መቀበል
ካለባቸው ፍርድ ቤቶች ሐቁ የሚወጣበትን መንገድ እንዴት አድርገው መሻት
እንደሚችሉ በፍጹም ሊገባን አልቻለም ። በምርመራ ተገኘ የተባለውን ውጤት
የሕግን ፎርማሊቲ ሳይከተሉ ራሳቸው ሳይመራመሩና ሳያመዛዝኑ እንዳለ ይቀበ
ሉት ከተባለ በጥሞና የሚያጤኑት ምኑን እንደሆነ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው ። የድብ
ደባ ተግባር በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑ ተዘንግቶ የአንድ ተጠርጣሪ የእም
ነት ቃል በድብደባም ቢገኝ ድብደባ ክብደት የማይሰጠው የሕግ ፎርማሊቲ ስለሆ
ነና ብዙ ድካምም ስለተወሰደበት ሀቅነቱን አትጠራጠሩ ከተባለ የሕግ አውታር
መዘርጋትና የፍርድ ቤቶች መኖር በፍጹም አያስፈልግም ማለት ነው ። አንድ ተከ
ሳሽ ፍርድ ቤት የሚቀርበው ተመሳክሮና ተነጣጥሮ ፣ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩንና የቀ
ረበለትን ማስረጃ በገለልተኛነት አይቶለትና መዝኖለት ሐቀኛው ፍሬ ነገር ነጥሮ
እንዲወጣና ተገቢውን ዳኝነት እንዲያገኝ ነው ። በድምጽ ብልጫ እንደተሰጠው
ውሳኔ ከሆነ ግን የፍርድ ቤት ተግባር ጉዳዩን ማበጠርና እውነቱን ማንጠር ሳይሆን

በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበለትን ማስረጃ ሐቀኛነቱን ሳይጠራጠር አሜን ብሎ መቀበል ነው ። የፍርድ ቤት ተግባር ለዐቃቤ ሕጉ ማስረጃ ቡራኬ መስጠት ብቻ ከሆነ ደግሞ የፍርድ ቤት መኖርና የተከሰሰም ሰው ፍርድ ቤት መቅረቡ ባላስፈለገም ነበር ። በድምጽ ብልጫ የተሰጠው ውሳኔም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያጸድቀው ይህንኑ አስተያየት ይመስላል ።

አንደኛው ይግባኝ ባይ ኃ. ፀ.ን አስገድሏል ተብሎ በከፍተኛው ፍ/ቤት ክስ ቀርቦበት ጉዳዩ ከተመረበረ በኋላ ኅዳር 21 ቀን 1971 ዓ. ም. በዋለው ችሎት በነጻ ተለቋል ። ይህን ሁኔታ በአሁኑ ጉዳይ ውሳኔ የሰጠው ችሎትም በሚገባ ያውቀዋል ። ነገሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ በድምጽ ብልጫ የተሰጠው ውሳኔ « እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንጹሕ ነኝ የሚል ሰው ይህን ወንጀል እስከመሥራትና እስከማሠራት ያደረሰው ምንድነው ? የሚል ጥያቄ እስካሁን መልስ ያልተገኘለት ቢሆንምቅሉ ፣ በበኩላችን ግን ያሳዛኙ የኃ. ፀ. የግፍ አገዳደል ወንጀል እንቅ ቆቅልሽ ሆኖ እንዲቀር ለማድረግ የታቀደ ዘዴ ሳይሆን አይቀርም የሚል እምነት እንድናሳድር የነገሩ አካባቢ ያስገደደን መሆኑን ሳንገልጽ እናልፍም » የሚል ትችት ሠንዝሯል ። ይህ ትችት የተሠነዘረው አንደኛው ይግባኝ ባይ በተከሰሰበት የሰው መግደል ወንጀል በነጻ ከተለቀቀ ከአሥራ አንድ ወራት በኋላ ነው ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ በአንድ በኩል አንደኛው ይግባኝ ባይ የአሁኑን ወንጀል ለምን እንደፈጸመው በውል ተለይቶ አለመታወቁን ይገልጥና በሌላ በኩል ደግሞ ነጻነቱ በአደባባይ የተረጋገጠለትን ሰው ተከሶ ነጻ የወጣበትን ወንጀል ለማዳፈን ነው የሚል መልስ ይሰጠናል ። እዚህም መደምደሚያ የደረሰው በግዙፍ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ሳይሆን በግል ያሳደረውን ጥርጣሬና እምነት መሠረት በማድረግ ነው ። ዳኛ ደግሞ ይህ ያደርግ ዘንድ አይገባውም ። « እንደ ጲላጦስ ንጹሕ ነኝ» ፤ «ያሳዛኙ የኃ. የግፍ አገዳደል » የሚሉት ስሜታዊ ቃላት ጉዳዩ በገለልተኛኛነት እንዳልታየ በጉልህ የሚያረጋግጡ ናቸው ። የድምጽ ብልጫው ውሳኔ በዚህ አድራጐቱ ግዙፍ በሆነው ፍሬ ነገር ሳይሆን በስሜት ተመርቷል ። ገለልተኛነቱን ሠርዞታል ። የዳኝነትን መሠረታዊ አቋም ንዶታል ። በመጨረሻም የድምጽ ብልጫው ውሳኔ« ያም ሆነ ይህ የቀረበልን የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የማያሻማና አጥጋቢ ስለሆነ » ተከሳሹቹ ጥፋተኞች ናቸው ሲል አስተያየቱን ይደመድማል ። የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የማያሻማና አጥጋቢ ከሆነ የታወቀ የሕግ ተመራማሪዎች የነደፉትን አሳብ ቦታ ሳይሰጡ በመጠቀስ ብቻ በድብደባ የተገኘ የአንድ ተጠርጣሪ የእምነት ቃል ብቁና ሐቀኛ ነው በማለት የማይታመነውን ለማሳመን ያ ሁሉ መከራ ለምን አስፈለገ ? የታወቁት ሊቃውንት እነ እርችቦልድና ሾው አንድ የእምነት ቃል በሌላ የእምነት ቃልና አካባቢ ማስረጃ ተደግፎ ሲገኝ ሙሉ እምነት ሊጣልበት ይገባል ያሉትን የድምጽ ብልጫው ውሳኔ ደጋፊ አሳብ ነው ብሎ ጠቅሶታል ። ነገር ግን ንድፈ አሳቡን ለውርደበጅ ያህል ጠቀሰው እንጂ ከቀረበለት ጉዳይ ጋር አላዛመደውም ፣ አላዋሃደውም ። ይህን ቢያደርግ ኖሮ የጠቀሳቸው የሕግ ምሁራን የነደፉት አሳብ እርሱ ከደረሰበት መደምደሚያ ጋር ሆድና ጀርባ መሆኑን ይረዳው ነበር ። የተጠቀሱት ሊቃውንት የእምነት ቃል ብቻውን ብቁና አስተማማኝ ነው አላሉም ። እነርሱ ያሉት አንድ የእምነት ቃል በሌላ የእምነት ቃልና የአካባቢ ማስረጃ ከተደገፈ ሊታመን ይገባል ነው ። እኛም በዚህ አሳብ እንስማማበታለን ። በያዝነው ጉዳይ ግን የቀረበው ተከሳሾቹ በፖሊስ ጣቢያ ሰጡ የተባለው የእምነት ቃል ብቻ ነው ። ይህን የእምነት ቃል የሚያጠነክር አንዳችም የአካባቢ ማስረጃ አልቀረበም ። ይህ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ የሊቃውንቱ ንድፈ አሳብ ምን ለማሳመን እንደተጠቀሰ አልገባንም ።

እንግዲህ ነገሩን ስናጠቃልለው ይግባኝ ባዮቹ ፈጸሙ ለተባሉት ወንጀል የቀረበባቸው በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት የእምነት ቃል ብቻ ነው። ተከሳሾቹ ግን ጉዳዩ ፍርድ ቤት ሲቀርብ የተነገረባቸውን ድርጊት መፈጸማቸውን ክደውታል ። በፖሊስ ጣቢያ ማመናቸውን ባይክዱም ፣ ይህን የእምነት ቃል የሰጡት ወደውና ፈቅደው ሳይሆን ከባድ የድብደባ ተግባር ስለተፈጸመባቸው ሥቃዩን መቋቋም ስላቃታቸው መሆኑን ገልጠው ማስረጃነቱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል ። ለምርመራ ፖሊስ ጣቢያ በነበሩበት ጊዜ በተከታታይ ለአራት ቀናት ተደብድበውና ቆስለውም እንደነበረ የቆጠሯቸው የመከላከያ ምስክሮች በሚገባ አስረድተውላቸዋል ። በፖሊስ ጣቢያ የተሰጠ የእምነት ቃል በአንድ ተከሣሽ ተጨማሪ አስረጂ ሊሆንበት ይችላል ። ነገር ግን የእምነቱ ቃል ተጨማሪ አስረጂ የሚሆነው ተከሳሹ ያላንዳች ተጽእኖ ፡ ማስፈራራትና ማግባባት በንጹህ ኅሊና በራሱ ፈቃድ የሰጠው ከሆነ ነው ። በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ ባዮቹ ለምርመራ ፖሊስ ጣቢያ በነበሩበት ጊዜ በከባድ ሁኔታ ተደብድበው እንደነበረ በመከላከያ አስረጂዎች ተረጋግጧል ። የተደበደቡ መሆናቸው ከተረጋገጠ ደግሞ የእምነቱን ቃል ወደውና ፈቅደው ሰጥተውታል ለማለት አይቻልም ። ይግባኝ ባዮቹ ድርጊቱን መፈጸማቸውን ያላንዳች ማስገደድ በራሳቸው ፈቃድ በፖሊስ ጣቢያ ካመኑ ፣ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ የሚክዱበት ምክንያት አይታየንም ። አስቀድመው ለማመን ፈልገው በኋላ አሳባቸውን ለውጠው ክደውታል እንጂ በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት የእምነት ቃል ትክክል ነው እንዳይባል ፣ ይህን መደምደሚያ የሚያጠናክር ተጨማሪ ግዙፍ ማስረጃ አልቀረበም ። ይግባኝ ባዮቹ ወንጀሉን ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩት ምን ፍንጭ ተገኝቶ ወይም በማን ተጠቁሞ እንደሆነ በጭራሽ የሚታወቅ ነገር የለም ። በፖሊስ ጣቢያ የሰጡት የእምነት ቃል የኃይል ተግባር ተፈጽሞባቸው የተገኘ መሆኑ እየተረጋገጠና የኃይል ተግባር ቢፈጸምባቸውም የሰጡት የእምነት ቃል ትክክል ነው ለማለት የሚያስችል ምንም ዓይነት ተጨማሪ ግዙፍ ማስረጃ ሳይቀርብ ይግባኝ ባዮቹ ጥፋተኞች ሊሆኑና ሊቀጡ አይገባቸውም ። ስለዚህ ከፍተኛው ፍ/ቤት በድምጽ ብልጫ የሰጠውን ፍርድ ሠርዘንና አነስተኛውን ድምጽ ደግፈን ይግባኝ ባዮቹን በነፃ አሰናብተናቸዋል ። ፍርዱ መሻሩን እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይተላለፍለት ፡ እንዲሁም ይግባኝ ባዮቹን እንዲለቃቸው ታስረው ለሚገኙበት ወህኒ ቤት ይጻፍለት ብለናል ።

ተገዶ ክስን ስለማመን—በወንጀል ይግባኝ

መ. ቁ. 4/71 የፍርድ ጉዳይ ትችት ።

በዮሴፍ ገብረ እግዚአብሔር*

በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ የመረመረው ጭብጥ ተገዶ ክስን ማመንን የሚመለከት ነው ። በዚህ ጉዳይ የተነሱ ጭብጦች ፤

ሀ/ በማስገደድ የሚገኝ የእምነት ቃልን በማስረጃነት ለመቀበል አስተማማኝና የማያስተማምን በማለት ልዩነት መፍጠር ይገባል ? ወይስ

ለ/ በማስረጃነት የቀረበው የእምነት ቃል በማስገደድ የተገኘ መሆኑን በመ መልከት ብቻ አስተማማኝ ቢሆንም ባይሆንም ተቀባይነት ማጣት አለበት ? የሚሉት ናቸው ።

አንድ ሰው ወንጀል ስለመሥራቱ በፍርድ ቤት ተቀባይነት ባለው በማያጠራጥር ማስረጃ መረጋገጥ አለበት[1] የሚለው ሕጋዊ አቋም ተቀባይነት ያገኘው ከብዙ የታሪክ ሂደት በኋላ ነው ።

በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች ንጹህነታቸውን ለማረጋገጥ ከወነጀሏቸው ሰዎች ጋር ፍልሚያ ገጥመው ማሸነፍ አለባቸው ይባል የነበረበት ዘመን ነበር ።[2]

አሁን ባለንበት ዘመን ምንም እንኳን በኃይል በማስፈራራት ወይም በሌላ ሕገ ወጥ ዘዴ መጠቀም በሕግ መከልከሉ ተገቢ ነው ብሎ በማለት የተለያዩ መርሆዎችን መጥቀስ ቢቻልም ፣[3] ከማስረጃ ሕግ አንጻር ስናየው ግን ማንም ሰው ጥፋተኛነቱ እስካልተረጋገጠበት ድረስ እንደ ንጹህ ይቆጠራል ከሚለው መርህ ጋር የተሳሰረ ሆኖ እናገኘዋለን ።

አንድ ሰው ጥፋተኛነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ ንጹሕ ነው ብሎ መገመት በሁሉም አገር ተቀባይነት ያገኘ መርህ ለመሆኑ ከተለያዩ ጽሁፎች ፣ ስምምነቶችና የሕግ ቅንጅቶች ማየት ይቻላል ። በዚሁም መሠረት በዲሴምበር 16/1966 ዓ. ም. በወጣው ዓለም አቀፍ የፍትሐብሔርና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት በአንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ 2 « ማንም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በሕጉ መሠረት ወንጀለኛነቱ እስኪረጋገጥበት ድረስ እንደንጹህ የመገመት መብት ይኖረዋል »[4] ተብሎ ተደንግጓል ። ሩዶልፍ ሄርማን የተባለው ምሁር « በምንም ዓይነት መንገድ ጥርጣሬ ብቻውን እንደበቂ ምክንያት ተወስዶ ማንኛውም ሰው ሕግ አክባሪ ዜጋ ነው የሚለውን መሠረታዊ እምነት ሊያስለውጥ አይገባም » በማለት ጽፏል ።[5] በሶቭየት ሕብረትና በዩንየን ሪፓብሊኮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረታዊ መርህ በክፍል 14 በፓራግፍ ሁለትና ሶስት የሚከተለው ተደንግጎ ይገኛል ፣ « ፍ/ቤቱ ፣ ዐቃቤ ሕጉ ፣ መርማሪውና ቃል ተቀባዩ ምን ጊዜም ቢሆን የማስረዳቱን ሸክም ወደ ተከሳሽ ሊያዞሩ አይችሉም ። በኃይል በመጠቀም ፣ በማስፈራራት ፣ ወይም በሌላ ሕገወጥ ዘዴ በመጠቀም ከተከሳሹ ማስረጃ ማግኘት የተከለከለ ነው ። »[6]

እነዚህ ስምምነቶችና ድንጋጌዎች « ከወንጀል ምርመራ ጋር አግባብ ያላ ቸው ተቋሞች ሁሉ አንድን ሰው በቅድሚያ እንደጥፋተኛ መገመት እንደሌላባቸ ውና ምን ጊዜም ፍርድ መስጠት የሚገባቸው በግልጽ በሚታይና በማይታብል ማስ ረጃ መሠረት መሆን እንዳለለበት ያስገነዝባሉ ። »[7]

ከላይ ከተገለጸው መገንዘብ እንደሚቻለው እንደ ንጹህ መገመት የሚለው መር ህ የተከሳሹ ጥፋተኛነት በሚገባ የሚያስጠረጥር ማስረጃ ከመገኘቱ በፊት ጥፋቱን የማስረዳት ሕግን ማስፈጸም ተግባራቸው ከሆነው ተቋሞች ወደ ተከሳሹ መዞር እንደሌለበት ይደነግጋል ። በሶቭየት ሕብረትና በዩጎየን ሪፓብሊኮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረታዊ መርሆዎች የአንድ ተከሳሽ እንደ ንጹህ የመገመቱ መብት በተግባር መተርጐም የሚጀምረው ገና ምርመራው ከሚጀምር በት ጊዜ አንስቶ ለመሆኑም ከላይ ከተጠቀሰው መረዳት ይቻላል ። ይህ እንግዲህ በተጨባጭ በተግባር ሲተረጐም ማንም መርማሪ ባለሥልጣን አንድን ሰው ተጠር ጣሪ ነው ብሎ በቁጥጥሩ ሥር በማዋል እስጨናቂ በሆነው ምርመራ እንዲጠመድ ከማድረጉ በፊት ያንን ሰው በበቂ ምክንያት ለመጠርጠር የሚያስችሉ ማስረጃዎች በተጠርጣሪው አማካይነት ሳይሆን በቴክኒካዊ ምርመራ በቅድሚያ መሰብሰብ አለበት ማለት ነው ።

ቢሆንም ወንጀለኞችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ሕብረተሰቡን ከወንጀል ድር ጊቶች የመከላከል ከባድ ኃላፊነት የተጣለባቸው ፖሊሶች በሶቭየት ሕብረትና በዩጎየን ሪፓብሊኮች የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረታዊ መርሆዎች ክፍል 14 አንቀጽ ሁለትና ሶስት አገላለጽ መሠረት « ማስረጃውን ወደ ተከሳሽ የማዞሩን » ክልከላ እና « ማስረጃ ለማግኘት በኃይል ፥ በማስፈራራትና በሌላም ሕገወጥ ዘዴ » ያለመጠቀምን ተግባራዊ ለማድረግ ከባድ ሆኖ ያገኙታል ።

ይህንኑ ችግር በመረዳት ፖሊሶች በስልጣናቸው ያላግባብ በመጠቀም ወንጀ ለኛነቱ ያልተረጋገጠበትን ተከሳሽ እንደ ንጹህ ሰው የመገመት መብቱን እንዳይ ገፉት ለመከላከል የተለያዩ አገሮች የተለያዩ ዘዴዎችን በመቀየስ በሕጋቸው አሥፍረው ይታያሉ ።

ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር ይህ « ያለአግባብ » በስልጣን መጠቀም « ተከሳሹ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር በነበረበት ጊዜ የተጠረጠረበትን ጥፋት በማስመልከት የሚ ደረገውን ጥያቄ ሁሉ በማስረጃነት እንዳይቀርብ በመከልከል ችግሩ ይቃለላል ተብሎ ይታመናል ። »[8] ከዚህም በላይ ፍርድ ቤቶች ተከሳሹ የሰጠው የእምነት ቃል ራሱን ከወንጀል ነጻ ከሚያደርገው መብት ጋር ተጻራሪ በሆነ መንገድ የተገኘ ከመ ሰላቸው ማስረጃው ዋጋ እንዳይኖረው ሊያደርጉት ይችላሉ ።[9]

በአሜሪካን አገር ይህ ያለአግባብ በሥልጣን የመጠቀም አዝማሚያ ተጠር ጣሪው በፖሊስ ጣቢያ በሚቆይበት ጊዜ ከሕግ አማካሪው ጋር እንዲገናኝ ዕድል በመስጠት ይወገዳል ተብሎ ይገመታል ። ተጠርጣሪው ይህን መብት ከተነፈገ ሰ ጠው የተባለው የእምነት ቃል ሁሉ የሚታመን ቢሆንም እንኳን በግዴታ እንደተ ገኘ ተቆጥሮ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም ።[10]

በህንድ አገር ግን አሠራሩ ለየት ያለ ነው ። በተከሳሽ የተሰጠ የእምነት ቃል በማስረጃነት ተቀባይነት እንዲኖረው ከተፈለገ በመርማሪ ዳኛ (ማጅስትሬት) ፊት መሰጠት አለበት ። ይህ አሠራር የእምነቱ ቃል የተሰጠው በፈቃደኛነት ነው ብሎ ለማመን ያስችላል ተብሎ ይገመታል ። [11]

በዩጎዝላቪያ ደግሞ ከነዚህ የተለየ አሠራር ይታያል ። ከሜይ 11 ፣1967 ዓ. ም. በፊት በዩጎዝላቪያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት የመመርመር ሥልጣን የተሰጣቸው ሁለት ተቋሞች ነበሩ ። እነርሱም ፖሊስ እና ፍርድ ቤት ነበሩ ። ሆኖም ሜይ 11 ፣ 1967 ዓ. ም. በወጣው ሕግ መሠረት ሙሉ በሙሉ በፖሊስ ይካሄድ የነበረው ምርመራ እንዲቀር ተደርጓል ። አሁን የሚሠራበት የምርመራ ዓይነት ራሱ « ዋናው ምርመራ » ሲሆን ይህም ሙሉ በሙሉ በዳኛ ይካሄዳል ።[12] በተሻሻለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት አዲሱ የፖሊስ ተግባር « ለዐቃቤ ሕጉ መነሻ የሚሆን ማስረጃ ማጠናቀር ሲሆን ይህም ዐቃቤ ሕግ በምርመራው ይገፋበት ወይም ይተወው እንደሆን ለመወሰን ያስችለዋል እንግዲህ የሕግ አውጪው ዓላማ ፖሊስ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ቢሆን ተጠርጣሪው የተጠረጠረበትን ወንጀል በማስመልከት ጥያቄ በማድረግ ማስረጃ እንዳያቀርብ መሆኑ ግልጽ ነው።»[13] ለዚህ ዓይነቱ አሠራር መፈጠር ዋና ምክንያት የሆነው በፖሊሶች በኩል የሚታየው የሰዎችን በንጹህነት የመገመትን መርህ በትክክል ሥራ ላይ ያለማዋል ይመስላል ።[14]

እንደ ንጹህ የመገመት መርህ በኛም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ከመጀመሪያው የምርመራ ደረጃ ጀምሮ ይገኛል ። አንድን ግለሰብ ከሌሎች ሁሉ ነጥሎ ወንጀሉን የፈጸመው እርሱ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ዓይን ሳይጣልበት በፊት መርማሪው ፖሊስ ለጥርጣሬው መነሻ የሚሆነው በቂ ምክንያት ሊኖረው ይገባል ።[15] ከዚህም በላይ ፣ « ፖሊሱ የምስክርነት ቃል ሲቀበል ተጠያቂውን መደለል የተስፋ ቃል መስጠት ፣ የማስፈራራት ፣ የኃይል ሥራ ወይም ሌሎች ከሕግ ውጪ የሆኑ ዘዴዎች መፈጸም አይችልም »[16] ተብሎ ተደንግጓል ።

አንድን ወንጀል መመርመር ተግባሩ የሆነ ፖሊስ ይህን ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜ ተመርማሪውን በመደለል ፣ በማስፈራራት ፣ የተስፋ ቃል በመስጠት ወይንም በሌላ ተገቢ ባልሆነ ዘዴ በመጠቀም ተመርማሪው ቃል እንዲሰጠው ያደረገ እንደሆነ ቅጣት እንደሚያገኘው በሕጋችን በግልጽ ተደንግጓል ። የተሻሻለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 214/1974 ዓ. ም. አንቀጽ 22 እንደሚከተለው ይደነግጋል ፤

« 1. ወደ ፍ/ቤት እንዲቀርብ የታዘዘውን ፣ ተይዞ በማረፊያ ቤት ወይም በእሥራት የተቀመጠውን ወይም በተለየ ቦታ እንዲቀመጥ የተወሰነበትን ሰው የሚጠብቅ የመንግሥት ሹም ወይም ሠራተኛ ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ወይም የሕብረት ሥራ ማሕበር ተመራጭ ወይም የጥበቃ ጓድ አባል ፤ የተሰጠውን ሥራ በሚያከናውንበት ጊዜ ፤ በዚህ ሰው ላይ ከሰብዓዊ ርህራሄ ውጪ የሆነ ወይም ለሰው ልጅ ክብር ተቃራኒ የሆነ ተግባር የፈጸመበት እንደሆነ ፣ ይህ አድራጎቱ ሊያስከትልበት የሚችለው የከባድ ቅጣት ኢወሳሰን ደንብ ከሌለ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል ።

« 2. ወንጀሉ የተፈጸመው በመንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ባለሥልጣን ትዕዛዝ ከሆነ ፣ ይኸው ባለሥልጣንም ከአምስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል[17] ። »

ነገር ግን ፖሊስ በሕግ ከተደነገገው መንገድ ተጻራሪ በሆነ ዘዴ ከተከሳሹ የእምነት ቃል አግኝቶ በማስረጃነት ሲያቀርብ ፣ በዚህ ዘዴ የተገኘ ማስረጃ በሕግ ምን ያህል ክብደት እንደሚሰጠው በሕጉ አልተደነገገም[18]።

በሌላ በኩል ግን ፍርድ ቤቶች የዚህ ዓይነት በግዴታ የተገኘ ማስረጃ ሲያጋጥማቸው ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ሕጉ ሥልጣን ባይሰጣቸውም ፣ በልምድና በሥራቸው ጠባይ ምክንያት ውሳኔ መስጠት ስላለባቸው ማስረጃው ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ወይም አይገባም ብለው መወሰን አለባቸው ። በዚህ ጉዳይም ከሞላ ጎደል የተደረገው ይኸው ነበር ።

ጉዳዩ ሲመረመር እንደሚያረጋግጠው እንደ ንጹህ የመገመት መርህና ይህንኑ በተግባር ለመተርጐም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት በቁ25 የተደነገገውን በመከተል ፖሊሶቹ ይግባኝ ባዮቹ ከሰጡት ቃል ሌላ ማስረጃ ለማግኘት ጥረት አላደረጉም። ፖሊሶች ይግባኝ ባዮችን በቁጥጥራቸው ሥር ከማዋላቸው በፊት ይግባኝ ባዮቹን በሚገባ የሚያስጠረጥር በይግባኝ ባዮች ቃል ያልተመሠረተ ማስረጃ ለማግኘት ተገቢውን ጥረት በማድረግ ፈንታ በስሜታዊ ግፊት ብቻ ቀን ሳስተው ፣ ይግባኝ ባዮቹን በቁጥጥራቸው ሥር በማዋልና የእምነት ቃላቸውን እንዲሰጡ በማስገደድ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ. 31 ን ከመጣሳቸውም በላይ የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ አዋጅ ቁ. 21 ንም በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል ። ከዚህም በስተቀር የይግባኝ ባዮቹን የእምነት ቃል እንኳን የሚያጠናክር ተጨማሪ ማስረጃ አላገኙም ።

ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ባዮቹ ተሰጠ የተባለው የእምነት ቃል በፈቃደኝነት የተገኘ ካለመሆኑም ሌላ በአካባቢ ማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ሳይቀበለው ቀርቷል ። የእምነት ቃሉ በሌላ ተጨማሪ ማስረጃ የተደገፈ ቢሆን ኖሮ ይቀበለው ወይስ አይቀበለውም ነበር ? ስለሚለው ጥያቄ ግን ግምት ከመውሰድ በስተቀር ፍርድ ቤቱ የወሰደው ግልጽ የሆነ አቋም አለ ለማለት ያስቸግራል ።

መ ደ ም ደ ሚ ያ ።

1. ፍርድ ቤቱ በመሠረቱ የሰጠው ውሳኔ በዚህ ጉዳይ የተገኘው የእምነት ቃል በድብደባ የተገኘ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም የሚል ነው ። ሆኖም በፈቃደኝነት ያልተገኘ የእምነት ቃል ተቀባይነት የሚያጣው እምነት የማይ ይጣልበት ሲሆን ነው የሚል ተጨማሪ አስተያየትም ከፍርዱ መውሰድ ይቻላል ።

2. የተሰጠው የእምነት ቃል አስተማማኝ ቢሆንም እንኳ በማስገደድ የተገኘ እስከ ሆነ ድረስ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም ብሎ መወሰን ፖሊሶች በዚህ ዓይነቱ አሠራር እንዳይቀጥሉ ለማድረግ ይረዳል የሚለውን አመለካከት ፍርድ ቤቱ መፍትሂ ይሆናል ብሎ ያመነበት አይመስልም ። የፍርድ ቤቱ አቋም በምርመራ ጊዜ አስገድዶ የእምነት ቃል መቀበል የሚያስቀጣ አሠራር እንደመሆኑ መጠን ማስረጃው አስተማማኝ ከሆነ ይህን በማስረጃነት ተቀብሎ የእምነት ቃሉን በማስገደድ ያገኘውን ፖሊስ መቅጣት የተሻለ መፍትሔ ነው የሚል ይመስላል ።

3. የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተመሰረተው ፍርድ ቤት በሚነሱት ክርክሮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ባለው ሥልጣን እንጂ በሕግ በተደነገገ ሥልጣን አይደለም ። ሆ

ኖም የዳኛ ሥልጣን መመንጨት ያለበት ከተደነገገ ሕግ ነው የሚለውን አመለካከት በመቀበል ሕጐች ሁሉ ተደንግገው በሚወጡበት አገራችን ራሱን የቻለና የተሟላ የማስረጃ ሕግ[19] ያለመኖር ብዙ ችግርን የሚያስከትል ስለሆነ ፥ ይህ በቶሎ መፍትሄ ሊደረግለት የሚገባ ጉዳይ ነው ።

4. የዚህ ዓይነቱ ሥልጣንን የመተላለፍ አዝማሚያ በፖሊስ በኩል የሚታየው ፖሊሶች በኃይል ተጠቅመው አንድን ተጠርጣሪ ማሳመን ልዩ ጥቅምን ያስገኝልናል ብለው ስለሚያምኑ አይደለም ፤ በሕጉ ላይ ንቀት አድሮባቸው ነው ለማለትም አይቻልም ። ምክንያት ሊሆን የሚችለው ተጠርጣሪ ወንጀለኞችን በቁጥጥራቸው ሥር ማዋል ተግባራቸው ስለሆነ ማንም ሰው ወንጀለኛነቱ ካልተረጋገጠበት በስተቀር እንደ ንጹሕ ይቆጠራል የሚለውን መርህ የሚተላለፉት በተጠርጣሪ ወንጀለኞች ላይ ባላቸው ከምያ ግዴታቸው በሚመነጭ ስሜታዊ አመለካከት ነው ።[20] ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ከሕግ ውጪ መሥራት የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑ ብቻ ተፈላጊውን ውጤት ሊያስገኝ አይችልም ። በሌላ በኩል ደግሞ በዩጐዝላቪያ እንደሚደረገው የወንጀል ምርመራን ተግባር ከፖሊስ ክፍል ወስዶ ወደ ዳኝነቱ ክፍል ማስተላለፍ ከጊዜው በጣም የቀደመ አሠራር ሊሆን ይችላል ።
ቢሆንም አሁን ያለውን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ. 27 ን በማሻሻል ፖሊስ የተከሳሽን ቃል እንዳይቀበል ማድረግና ቀድሞም እንደተባለው[21] ቁ. 35 ን እንዳለ እንዲቀይ ማድረግ ይበጃል ። ይህም ሲሆን በፍርድ ቤቱም ቢሆን የሚሰጠው የእምነት ቃል « ስውር » ተጽዕኖ ወይም ተጠሪጣሪው ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በፖሊስ የተፈጸመበት የኃይለ ሥራ ያለመኖሩን የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ደንቦች መታከል ይኖርባቸዋል ። ይህ ከተሟላ በዚህ ፀሐፊ እምነት ከሥልጣን በማለፍ በሕገወጥ መንገድ የእምነት ቃል የማግኘቱን አሠራር ጨርሶም ባያጠፋው በጣም ይቀንሰዋል ።

የ ግ ር ጌ ማ ስ ታ ወ ሻ

* ረዳት ፕሮፌሰር ፥ ሕግ ፋኩልቲ ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ።

1. የወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 141 ይመለከቷል ።

2. ፕሉስኮው ሞሪስ ፥ ዘ ዲቨሎፕመንት ኦፍ ፕረዘንት ዳይ ክሪሚናል ፕሮሲጀርስ ኢን ኢሮፕ ኤንድ አሜሪካ ፥ ሀርባርድ ሉው ረቪው (ቅጽ 48 ፥ 1934—35) ፤ ገጽ 440 ።

3. ለምሳሌ የፌዴራሊስት ዩጐዝላቪያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 176 ን ብንመለከት እንዲህ ይላል "በሰው ልጅ ክብረ — ሀሊና ፥ የግለሰብም ሆነ የቤተ ሰብ ሕይወት (አኗኗር) እንዲሁም ሌሎችም፤ ሰብአዊ መብቶች ሁሉ የተጠበቁ ናቸው ።

"በኃይል በመጠቀም የእምነት ቃልም ሆነ ምስክርነት ማግኘት የተከለከለ እና የሚያስቀጣ ነው ።" እንግዲህ ከዚህ የምንረዳው በኃይል በመጠቀም የእምነት ቃል ማግኘት በሰብአዊ ክብረ—ሀሊና ላይ ወንጀል መፈጸም መሆኑን ነው ። እንዲሁም ዊግሞር ፥ ኤቪደንስ ኢን ትራያልስ አት ኮመን ሎው (ሊትል ብራውንና ኩባንያው እ.ኤ.አ. 1970) ቅጽ 3 ፥ ገጽ 329—344 ይመለከቷል ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በኃይል የተገኘ የእምነት ቃል ማስረጃነቱ የማያስተማምን ከመሆኑም በላይ በራስ ላይ ምስክር ከመሆን ነጻ የሚያደርገውን መብት ይጻረራል ተብሏል ። ቢሆንም የኋለኛው ቲኦሪ አንድ ሰው ወንጀለኛነቱ ካልተረጋገጠበት በስተቀር እንደ ንጹህ ሰው ይቆጠራል ከሚለው መርህ ጋር አንድ አካል ነው ። ምክንያቱም ይህ አባባል ራሱ አንድ ሰው በወንጀለኛነት ተጠርጥሮ ከሌሎች ሕግ አክባሪ ሰዎች መካከል ተነጥሎ ከመውጣቱ በፊት ያለእርሱ እርዳታ በቅድሚያ ወንጀለኛነቱን የሚያመለክት ማስረጃ መሰብሰብ እንደሚገባው ስለሚያሳይ ነው ።

4. ሄርማን ጂ. ዲ. አር ክሪሚናል ፕሮሲጀር ሎው ጎቨርንድ ባይ ሶሻሊስት ፕራንስፐልስ፡ ሎው ኤንድ ሌጂስሌሽን ኢን ዘ ጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ (እ.ኤ.አ. 1974፤ሁለተኛ እትም) ገጽ 29።

እንዲሁም ፣ « ማንኛውም በወንጀል የተከሰሰ ሰው በግልጽ ችሎት ራሱን የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ጥፋተኛነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥበት ድረስ እንደ ንጹህ ይገመታል » የሚለውን በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ማረጋገጫ አንቀጽ 11/ 1 የተደነገገውን በብራውንሊ ፤ ቤዚክ ዶኩመንትስ ኦን ሂዮማን ራይትስ (ክላሬንደን ፕሬስ ኦክስፎርድ ፣ እ. ኤ. አ. 1971) ገጽ 109 ይመለከቷል ። በተለያዩ አገሮች ሕጐች ውስጥ ስለሚገኙ ተመሳሳይ ድንጋጌዎች ይህንኑ መጽሐፍ ፣ ገጽ 3—89 ይመለከቷል ።

5. ሄርማን ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 4 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 29 ።

6. ሎው ኢን ኢስተርን ኢሮፕ (ቅጽ 3) ገጽ 119 ላይ የሚገኘውን የሶቪየት ህብረትና የዩንየን ሪፑብሊኮች የወ. መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረታዊ መርሆች ክፍል 14 ፤ ፓራግራፎች 2 እና 3 ን ይመለከቷል ።

7. ሄርማን ፣ በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 4 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 19—30

8. ፊሸር ፣ ያለ ነጻ ፈቃድ የሚሰጡ የእምነት ቃላትና የወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 35 የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት (ቅጽ 3 ቁ. 1) ገጽ 317 ።

9. ከላይ እንደተጠቀሰው ።

10. ከላይ እንደተጠቀሰው ነገር ግን በድህነት ውስጥ በሚገኙ ሰዎችና በተለይም በከበርቴው ህብረተሰብ « በታችኛው መደብ » አባል ላይ ባለው ዝቅተኛ አመለካከት ምክንያት ይህ መብት ምን ያህል በተግባር ላይ ሊውል እንደሚችል ያጠራጥራል ።

11. ከላይ እንደተጠቀሰው ፣ ገጽ 332 ።

12. ኮሌክሽን ኦፍ ዩጐዝላቫ ሎውስ ፣ ኮድ ኦፍ ክሪሚናል ፕሮሲጀር (ቢዎግራድ ፤ እ ኤ አ 1969) ቅጽ 19 ፣ ገጽ 9 ።

13. ከላይ እንደተጠቀሰው ። ዳኛ በመጀመሪያው የወንጀል ምርመራ ደረጃ ውስጥ ስለወንጀሉ አፈጻጸም ምርመራ የማካሄድ ሚና እንዲኖረው የተደረገው አሠራር ከሲቢል ሎው የሕግ ቅንጅት የተገኘ ለመሆኑ ፣ ከላይ በግርግ ማስታወሻ 2 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 433—467 ይመለከቷል ።

14. ከላይ እንደተጠቀሰው ፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 ገጽ 8 ይመለከቷል ።

15. የወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 25

16. የወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 31

17. ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 41ኛ ዓመት ቁ. 2 ። እንዲሁም የወ. መቅጫ ሕግ ቁ. 417ትን ይመለከቷል ።

18. በወ.መ. ሕግ ሥነ ፡ ሥርዓት አዋ ፕሮገፎ ድጋሚ ቁ. 462 ንዑስ ቁ. 2 ሥር በፊሸር፡ ኢትዮጵያን ክሪሚናል ፕሮሲጀር ኮድ ፣ ኤ ሶርስ ቡክ (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ ጋር በመተባበር ያሳተመው ፣ እ.ኤ.አ. 1969) በገጽ 458 እንደሚገኘው ሕገ ወጥ በሆነው መንገድ የተገኘ የእምነት ቃል ውጤት እንደማይኖረው ይደነግጋል ። ቢሆንም ይህ ረቂቅ በአሁኑ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓታችን ቁ. 31 ተተክቷል ። እንደፊሸር አባባል (ከላይ በግ. ማስታወሻ ቁ. 8 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 333—34) በወ. መ. ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁ. 31. ስር የእምነት ቃሉ ሊኖረው ስለሚችለው የማስረጃነት ጠባይ ያልተጠቀሰበት ምክንያት ምናልባት ሕግ አውጪው ይህ በማስረጃ ሕግ ይደነገጋል የሚል እምነት ስለነበረው ይመስላል ።

19. ይህም ሲባል በሕጋችን ውስጥ ማስረጃን የሚመለከት ሕግ የለም ማለት አይደለም ። ለምሳሌ የፍትሐብሔር ሕግ (ነጋሪት ጋዜጣ ፣ 19ኛ ዓመት ቁ. 8 አዋጅ ቁ. 165/52) ቁ. 2001—2026 ይመለከቷል ።

20. ፊሸር ፣ ስለ ኢትዮጵያ መያዝ ሕግ አንዳንድ ጉዳዮች ፣ በማጠናቀር ሕግን የማሰናዳት ዘዴ ፣ የኢትዮጵያ የሕግ መጽሔት (ቅጽ 3 ቁ. 2) ገጽ 438 — 439 ።

21. ፊሸር ፣ ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 የተጠቀሰው ፣ ገጽ 320—329 ይመለከቷል ።

በኅብረተ ሰብአዊት ኢትዮጵያ
ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ፣
ጠቅላይ ፍርድ ቤት
አዲስ አበባ

የወንጀል ይግባኝ መ. ቁ. 1515/71
ኅዳር 6 ቀን 1972 ዓ. ም.

ዳኞች ፦ 1.
2.
3.

ይግባኝ ባዮች 1. ቶ.አ. አልቀረበም
2. በ. ኃ. አላቀረበም

መልስ ሰጭ ፦ ዐቃቤ ሕግ አቶ ብዙዓለም መርሻ ቀርበዋል
ዐቃቤ ሕግ ጥቅምት 13 ቀን 1972 ዓ. ም. በተጻፈ

ማመልከቻ መልስ ሰጥቷል ። ጉዳዩን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል ።

ፍ ር ድ

ይግባኝ ባዮች ኅዳር 12 ቀን 1971 ዓ ም ከቀኑ በግምት 8 ሰዓት ሲሆን በጭላሎ አውራጃ በአሰላ ከተማ የማታለል ወንጀል ለመፈጸም ተስማምተው ካልተያዙ 3 ግብረ አበሮቻቸው ጋር ከአዲስ አበባ ወደ አሰላ ከተማ ሄደው በ05 ቀበሌ ውስጥ አቶ ተስፋዬ አበበ የተባለውን ነጋዴ ለማታለል አስበው ያልተያዘው ስሙ ያልታወቀ ሰው መንግሥት ለድሀ ገበሬና ነጋዴ ገንዘብ ይሰጣል አልሰማ ሀም ? በማለት ጠይቆ ወደአንደኛው ይግባኝ ባይ ዘንድ ወስዶት ከአገናኘው በኋላ አንደኛው ይግባኝ ባይ ደግሞ ከሁለተኛ ይግባኝ ባይ ጋር ገንዘብ ትወስዳ ለህ በማለት አገናኝቶት ሁለተኛውም ይግባኝ ባይ ይህንኑ የማታለል ዘዴአቸ ውን በመቀጠል በዘጠኝ ሰዓት ና ቦታውን አሳይሃለሁ ብሎ የማይደረገውን ይደ ረጋል ፣ የማይሆነውን ይሆናል በማለት ለማታለል በመሞከራቸው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32 (1) ሀ/27(1)/656 (ሀ) መሠረት ጥፋተኞች ሆነው ሊቀጡ ይገባል ተብለው አርሲ ክፍለ ሐገር አሰላ ከተማ ካስቻለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሰሱበት ወንጀል ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው ይኸው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕጉ እንደክሱ አቀራረብ ያሰማውን ማስረጃ በመመልከትና ይግባኝ ባዮች፣ በዐቃቤ ሕጉ በኩል የተሰማባቸውን ማስረጃ ለማፍረስ መከላከያ ማስረጃ ለማቅረብ አለመቻላቸውን በመገንዘብ በዐቃቤ ሕጉ ማስረጃ እና እነሱም በፖሊስ ጣቢያ ወንጀሉን በማመን የሰጡትን ቃል መሠረት በማድረግ ይግባኝ ባዮችን በተከሰሱበት ወንጀል በክሱ ላይ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ጥፋተኞች አድርጎ አንደኛው ይግባኝ ባይ በአምስት ዓመብ ጽኑ እሥራትና በአምሳ ብር መቀጫ እን ዲቀጣ ፣ ሁለተኛው ይግባኝ ባይ በሁለት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ ፈርዶባቸ ዋል ። ይግባኙ የቀረበው ይህንኑ ፍርድ ለማስለወጥ ነው ።

ይግባኝ ባዮች ይግባኝ ያሉበትን ምክንያት ሐምሌ 2 ቀን 1971 ዓ. ም. በተ ጻፈ የይግባኝ ማመልከቻ ዘርዝረዋል ። ዐቃቤ ሕጉም ጥቅምት 13 ቀን 1972 ዓ. ም. በተጻፈ ማመልከቻ ለይግባኙ መልስ ሰጥቷል ።

ይግባኝ ባዮች በይግባኝ ማመልከቻቸው ላይ አንደኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጠላት ምስክር ነው ። በፖሊስ ጣቢያ የሰጠነው ቃል ሳንወድ በግድ የሰጠነው ነው ። ሌሎች የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የደረጃ ምስክሮች እንጂ የዐይን ምስክሮች አይደሉም ። ስለዚህም ማስረጃው በቂና አስተማማኝ ስላልሆነ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ ተሰርዞ በነጻ ልንሰናበት ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል ።

ዐቃቤ ሕጉ በበኩሉ በጻፈው መልስ ይግባኝ ባዮች ድርጊቱን ለመፈጸማቸው የተሰማው ማስረጃ በቂና አስተማማኝ የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም ። ማስረጃው አጠራጣሪ አይደለም ። ወንጀሉን ለመፈጸማቸው ራሳቸው አምነዋል ። የእምነት ቃላቸውን የሰጡት ደግሞ ወደውና ፈቅደው ለመሆኑ ፖሊስ ጣቢያ ድረስ ይዘዋቸው የሄዱት የጥበቃ ጓዶች መስክረውባቸዋል ። እንደሚሉት ሁሉ በግዳጅ የሰጡት ቃል ለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም ። ስለዚህም ድርጊቱን በመፈጸማቸው ረገድ ያለው ነጥብ አከራካሪ ሊሆን አይችም ። ድርጊቱን ፈጽመውታል ። በሕጉ ረገድ ግን የግል ተበዳዩ የማያጠግብ ተስፋ ተነግሮት ጊዜውንና ጉልበቱን ሰውቶ ገንዘብ ይገኝበታል ወደተባለው ሥፍራ ሂዶ ቀጠሮ ከተሰጠው በኋላ ተከታታይ ፈልጎ እንዲያዙ ከማድረጉ በቀር በግል ተበዳዩ ንብረት ላይ ወንጀል ለመሥራት በማሰብ የግል ተበዳዩን የሀብት ጥቅም በሚጎዳ አኳኋን በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ለማሠራት መሞከራቸው በስውር ካልሆነ በቀር በጉልህ አይታይም ። ይህም ይግባኝ ባዮች በንብረት መብቶች ላይ የማታለል ወንጀል ለመፈጸም ሞክረዋል የሚለውን እውነት ነገር ከማቋቋም ይልቅ የግል ተበዳዩ በግል ሀብቱ ጥቅም ላይ ጉዳት እንዲያደርስ የአፈጻጸሙ ሁኔታዎች እንዲከናወኑ ለማድረግ የወንጀል አፈጻጸምን የመጀመሪያ ደረጃ ማለትም የመሰናዳት ተግባሮችን ፈጽመዋል ማለቱ ሳይቀል አይቀርም ። ስለሆነም የይግባኝ ባዮች አድራጎት ጥፋተኛ በተሰኙበት አንቀጽ የማይሸፈን መሆኑን ዐቃቤ ሕግ አጥብቆ እየተከራከረ የይግባኝ ባዮችን ዝንባሌና አዝማሚያ እና ሊከተል የሚችለውን ጥፋት አስተውሎ ሕጋዊና ፍትሐዊ ውሣኔ እንዲሰጥ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ይጠይቃል ሲል ተከራክሯል ።

በበኩላችንም ነገሩን መርምረነዋል ። ከሕግም ጋር አገናዝበን ተመልክተነዋል ። ነገሩን እንደመረመርነውና ከሕግም ጋር አገናዝበን እንደተመለከትነው ይግባኝ ባዮች መንግሥት ለተቸገረ ሰው ገንዘብ ይሰጣል በማለት ያገኙትን እታልለው ሕገወጥ ብልጽግናን ለማግኘት አቅደውና ተስማምተው የአሰላ ከተማ ሕዝብ ሞኝ ነውና ይታለላል ብለው ከአዲስ አበባ ከተማ ተነስተው ወደ አሰላ ከተማ መሄዳቸውን ፣ እስከዛሬ ድረስ ያልተያዘው የይግባኝ ባዮች ግብረ አበር የግል ተበዳዩን እንዳገኘው እዚህ ከተማ ሰው ታውቃለህ ወይ? ብሎ ጠይቆት አላውቅም የሚል መልስ እንደሰጠው ሥራህ ምንድር ነው? ብሎ ጠይቆት ነጋዴ ነኝ የሚል መልስ እንደሰጠው አንድ ወሬ ሰምተሃል ወይ? ብሎ የጠየቀው መሆኑን ፣ አልሰማሁም ፣ ወሬው ምንድር ነው? ብሎ መልሶ ቢጠይቀው መንግሥት ለድሀ ገበሬና ነጋዴ ለተቸገረ ሰው ሁሉ ገንዘብ ይሰጣል ብሎ ፈንጠር ብሎ ቆሞ ወደነበረው ወደ አንደኛው ይግባኝ ባይ እንደወሰደው ፣ አንደኛው ይግባኝ ባይ መንግሥት ለተቸገረ ሰው ገንዘብ የሚሰጥበትን ሥፍራ እኔ አሳያችኋለሁ ብሎ በኸርሮንድ ጽሕፈት ቤት አካባቢ ይጠባበቅ ወደነበረው ወደ ሁለተኛው ይግባኝ ባይ ግብረ አበራቸው ዘንድ ይዘውት መሄዳቸውን ፣ እንደሄዱም ሁለተኛውን ይግባኝ ባይ አግኝተውት ሁለተኛው ይግባኝ ባይ ደግሞ ተሸቀዳድሞ አንደኛውን ይግባኝ ባይ አንተ ጠዋት ወስደህ የለም ወይ ? እንደገና ለምን መጣህ? ብሎ ነገሩን እውነት ለማስመሰል መሆኑ ነው ቢጠይቀው እኔማ ተሰጥቶኛል ፣ ለነርሱ ሥፍራውን ላሳይ ብዬ ነው

ጌታዬ ብሎ የመለሰለት መሆኑን ፣ በዚህን ጊዜ ሁለተኛው ይግባኝ ባይ እናንተ የምታገኙት ማለትም የሚሰጣችሁ በዘጠኝ ሰዓት ነው ፣ በዘጠኝ ሰዓት ተመለሱ ብሎአቸው እንደተለያዩ የግል ተበዳዩ ለፐበቃ ጓዶች ጠቁሞ በክትትል የዛሬዎቹ ይግባኝ ባዮች ብቻ ሊያዙ መቻላቸውን ፣ ተይዘው ወዲያውኑ ፖሊስ ጣቢያ እንደ ደረሱ አላንዳች ግዳጅ ድርጊቱን አምነው በሰው ንብረት ላይ ያደረሱት በደልና ውጤት ያገኘ ድርጊት ስለሌለ መንግሥት ይቅርታ እንዲያደርግላቸው መማጸናቸውን ዐቃቤ ሕጉ በማያጠራጥር አኳኋን ያስረዳውን ማስረጃ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መቀበሉንና በዚሁ መሠረት ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ መስጠቱን ተረድተናል ። በፍሬ ነገሩ ረገድ ላለው ክርክር የቀረበውን ማስረጃ ብቁነትና አስተማማኝነት ሊያፈርስ የሚችል ተቃራኒ ማስረጃ በይግባኝ ባዮች በኩል ባለመቅረቡና ሊቀርብም የሚችል ማስረጃ አለና ይቅረብ ተብሎ የተጠቆመ ባለመኖሩ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበውን ማስረጃ እምነን የማንቀበልበት ምክንያት አይኖረንም ። አምነን ተቀብለነዋል ።

በሕጉ ረገድ ከላይ የተጠቀሰውን ድርጊት ይሸፍናል ተብሎ የተጠቀሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 27 (1) እና 656 (ሀ) የተጻፈው ነው ። እነዚህም እንደሚከተለው ይነበባሉ ።

> አንቀጽ 27 (1) « ማንም ሰው አስቦ ወንጀልን ለመሥራት ጀምሮ የወንጀሉን ተግባር እስከመጨረሻው ያልተከታተለ ወይም ለመከታተል ያልቻለ ወይም የወንጀሉ ሥራ አፈጻጸም ሥራውን እስከ መጨረሻው ተከታትሎ አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላገኘ ቢሆንም በመሞከሩ ብቻ ጥፋተኛ ይሆናል ።
> «የወንጀሉ ሥራ እንደተጀመረ ያህል የሚቆጠረው የተፈጸመው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ ወንጀሉን ለመፈጸም ወደ ታሰበበት ግብ ለማድረስ የተሠራ በሆነበት ጊዜ ነው » ሲል ፤
>
> አንቀጽ 656/ሀ/ « ማንም ሰው ሕገ ወጥ የሆነ ብልጽግናን ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ሲል አጭበርብሮ የራሱን ወይም የሌላውን ሰው የሀብት ጥቅም በማድረግም ሆነ ባለማድረግ በሚጎዳ አኳኋን አንዱን ሰው ለማሠራት በማቀድ ፣ እውነቱን ወደ ሐሰት በመለወጥም ሆነ ሐሰተኛውን ነገር እውነት አስመስሎ በማረጋገጥ ያልሆነውን እኔ ነኝ ብሎ ወይም በማታለል ዘዴ ተበዳዩን ወደ ስህተት በመምራት ወይም ደግሞ እርግጠኛውን ነገር እንዳይገለጽ በተንኰል በሙሸፈን ቅን ልቡናንና የልማዳዊ ደንብ ሥርዓት እንዳይደበቅ የሚከለክለውን ነገር የሰወረ እንደሆነ በእሥራት ወይም እንደነገሩ ሁኔታ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራትና በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል » ይላል ።

ወንጀሉን ለመሥራት የተደረጉት የሙከራ ተግባሮች ራሳቸውን የቻሉ ወንጀሎች ሆነው የተገኙ ሲሆኑ ለእነዚሁ ወንጀሎች የተወሰኑት ቅጣቶች የሚፈጸሙ ካልሆነ በቀር በመሠረቱ ሙከራ የሚያስቀጣው በመደቡ ለመፈጸም ለተፈለገው ወንጀል የተወሰነው ቅጣት እንዲሚፈጸም በማድረግ እንደሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር 27/3/ እና 30 የተጻፉት ድንጋጌዎች ያስረዳሉ ። በያዝነው ጉዳይ ይገባኝ ባዮች ፈጽመውታል የተባለውን ድርጊት ይሸፍናሉ ተብለው ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች መካከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 27/1/ የተጻፈው በዚሁ ሕግ በቁጥር 656 (ሀ) ከተጻፈው ጋር ተጠቅሶ የቀረበው ይግባኝ ባዮች ለመፈጸም የሞከሩት ወንጀል

ማታለልን የሚመለከት በመሆኑ በማታለል ለተመሠረተ ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 656 (ሀ) የተመደበው ቅጣት በይግባኝ ባዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል በሚል አስተሳሰብ ነው ።

ከፍ ብለን የጠቀስነውና በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 656 (ሀ) የተጻፈው ድንጋጌ ለአንድ ድርጊት ተፈጻሚ የሚሆነው ተበዳዩ ተታልሎ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ በራሱ ወይም በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳትን የሚያስከትል ተግባር ፈጸሞ ሲገኝ ነው ። በያዝነው ጉዳይ የግል ተበዳዩ ለተቸገረ ሰው መንግሥት ገንዘብ ይሰጣል ወደተባለበት ሥፍራ ተታልሎም ይሁን ሳይታለል ይግባኝ ባዮችን ለማስያዝ እንዲረዳው ሲል ከመሄዱ በቀር የራሱን ንብረት ወይም የሌላ ሰው የሆነውን ንብረት በሚጎዳ አኳኋን በማድረግም ሆነ ባለማድረግ አንድም ዓይነት ድርጊት እንዲፈጽም አላደረጉትም ። አልሞከሩትም ። እንደሚሰማው ሁሉ « ቁጭ በሉ » በሚል መጠሪያ የታወቀው የወንጀል ሥራ የሚፈጸመው ወንጀል ሠሪዎች አንዱን ሞኝና ተላላ ሰው ሲያገኙ መንግሥት ለድሀ ገንዘብ ወይም ልብስ ወይም ሞግብ ይሰጣል ብለው ካሳመኑት በኋላ ተታላዩ እውነት መስሎት እንግዲያውስ የሚሰጥበትን ሥፍራ አሳዩኝ እኔም ማግኘት አለብኝ በሚልበት ወቅት የለበስከውን ልብስና የያዝከውን ንብረት አስቀምጠህ ና ድሃ መሰለህ ካልታየህ በቀር አይሰጥህምና ንብረተህን ፡ ልብስህን ማንኛውንም ነገር እኛ ዘንድ አስቀምጥ በለው እንዲሰጣቸው አሳምነው ሰጥቶአቸው ይዘውበት ሲጠፉ ነው ። በያዝነው ጉዳይ ያልተያዘው ሶስተኛው ግብረ አበር የግል ተበዳዩን መንግሥት ለተቸገረ ሰው ገንዘብ እንደሚሰጥ አልሰማህም ወይ? ብሎት ወደ አንደኛው ይግባኝ ባይ ፣ አንደኛው ይግባኝ ባይም ኑ የሚሰጥበትን ሥፍራ አሳያችኋለሁ ብሎ ሁለተኛው ይግባኝ ባይ ወደሚገኝበት የወሰዱትና እንደወሰዱትም ምንም ነገር ሳይጠይቁት ገንዘብ የሚሰጠው በዘጠኝ ሰዓት ነው ብሎ ሁለተኛው ይግባኝ ባይ ተናግሮ ከመለያየታቸውና የተቀረጠውም ሰዓት ሳይደርስ የግል ተበዳይ ነኝ ባይ ያስያዛቸው ከመሆኑ በቀር በንብረቱ ላይ ጉዳት በሚያደርስ አኳኋን አንድ ድርጊት እንዲፈጽም አልጠየቁትም ።

ምናባት የግል ተበዳይ ይግባኝ ባዮችን ሳያስይዛቸው ቀጠሮውን አክብሮ ቢገኝ ኖሮ በተጠቀሰው ዓይነት እንዲፈጽም ይጠይቁት ነበር ይሆናል የሚል ግምት እናሳድር ይሆናል ። በአንጻሩ ደግሞ የግል ተበዳዩ ነጋዴ መሆኑን ስለገለጸላቸው ነጋዴ የሆነ ሰው በቀላሉ አይታለልም በሚል አስተሳሰብ በቀጠሮው ሳይገኙ ቀርጠው በቀጠሮ እንደሚገናኙ አድርገው አሰናብተውታል ሊባል ይቻላል ። እንደዚህ ዓይነቱ የተለያየ አስተያየት ሊያሰጥ የሚችል ሁኔታ በመኖሩ ይግባኝ ባዮች የፈጸሙት ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ የማታለል ወንጀል ለመፈጸም ወደአሰቡበት ግብ ለመድረስ የፈጸሙት ተግባር ነው ብሎ መደምደም አይቻልም ብለን እናምንበታለን። የጠቅላይ ፍ/ቤት ዐቃቤ ሕግም የተፈጸመው ተግባር መሰናዳትን የሚመለከት ነው እንጂ ሙከራን የሚመለከት አይደለም ያለውም በዚሁ አስተሳሰብ ነው ። በኛ አስተያየት ጉዳዩ ወደ ሙከራ ደረጃ አይድረሰ እንጂ በመሰናዳት ላይ ብቻ የተወሰነ ወይም የተቀጨ አይደለም ። ስለሆነም ይግባኝ ባዮች የፈጸሙትን ወንጀል ለመሥራት በማሰብ የመሰናዳት ተግባር ነው ብለን በነጻ እንለቃቸውም ። ይግባኝ ባዮች የማታለል ወንጀል ለመሥራት አስበው የአስላ ከተማ ሕዝብ ሞኝ ነውና በአፈጮሌነት የማይደረገው ይደረጋል ብለን ወንጀል እንስራ ብለው ተስማምተው ስምምነታቸው በወሬ ተነግሮ ብቻ ሳይቀር ከአዲስ አበባ አሰላ ድረስ ሄደው ተግባርም ላይ ለማዋል የግል ተበዳይን አግኝተው የማታለሉን ዘዴ ይፋ እውጥተውታል ። በሌላ አነጋገር ወንጀል ለመሥራት ያደረጉትን ስምምነት ሥራ ላይ ለማዋል በተ

ግባር ጀምረውታል ። እንደዚህ ዓይነቱ ስምምነት ራሱ እንደሚያስቀጣ በሕግ ተደ
ንግጓል ። ለዚህም አግባብነት ያለው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 472 ንኡስ
ቁጥር (1)የተጻፈው ሆኖ አግኝተነዋል ። በዚህ ቁጥር በአማርኛው ቅጅ የተጻፈው
በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ቅጅ እንደተጻፈው ዐይነት እንዳልተጻፈና ይህም በት
ርጉም ስህተት ምክንያት የተፈጠረ ስህተት እንጂ ድንጋጌው ልክ በእንግሊዝኛው
እና በፈረንሳይኛው እንደተጻፈው ስለሆነ የዚህ ቁጥር ትክክለኛው ድንጋጌ እንደሚ
ከተለው ይነበባል ፤

> 472(1) « በሕዝብ ጸጥታ ፣ ሕይወት ወይም በሰው ወይም በንብረት ከፍ
> ያለ ወንጀል ለመሥራት ወይም ለማዘጋጀት ካንድ ሌላ ወይም ቁጥራ
> ቸው ካንድ ከበለጠ ሌሎች ጋር ያደመ ወይም ሌላውን ከአድማው እን
> ዲገባ ያደረገ ፣ አድማው በተግባር ላይ ከዋለ (በተግባር ከተገለጸ) ከሶ
> ስት ወር በማያንስ እስራትና በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
>
> « በዚህ የሕግ ቁጥር ውስጥ ከፍ ያለ ወንጀል የሚባለው በአምስት
> ወይም ከአምስት ዓመት በላይ በሆነ ጽኑ እሥራት የሚያስቀጣ ወን
> ጀል ነው ።»

በያዝነው ጉዳይ ይግባኝ ባዮች ለመሥራት የተስማሙበትና በተግባርም የገለጹት
ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 656 እንደተገለጸው ሁሉ እንደነገሩ ክብ
ደት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራትና በገንዘብ መቀጮ የሚ
ያስቀጣ ስለሆነ ድርጊታቸው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 472 (1).የተሸፈነ
ይሆናል ። ስለዚህ ይግባኝ ባዮች ጥፋተኛ መባልና መቀጣትም የሚገባቸው በክሱ
ላይ በተጠቀሰባቸውና በከፍተኛውም ፍርድ ቤት ጥፋተኞች ሆነው በተገኙበትና
በተቀጡበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 27/656 መሰረት ሳይሆን በዚሁ ሕግ
በቁጥር 472(1) በተደነገገው ነው ብለናል ።

በቅጣቱ ረገድ አንደኛው ይግባኝ ባይ ከዚህ ቀደም አጥፍቶ በመገኘቱ ጠቅ
ላላ የቅጣት ማክበጃ ሕግ ተፈጻሚ ሆኖበት እንደተቀጣ ተመልክተናል ። የከፍተ
ኛው ፍርድ ቤት ጥፋትን ሞያ አድርጎ ይዟል ሲል እንደተቸም ተመልክተናል ። አንደ
ኛ ይግባኝ ባይ ቀደም ሲል ጥፋተኛ ሆኖ በ15 ዓመት እንዲቀጣ የተፈረደበት በሰው
መግደል ወንጀል ነው ። አሁን ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ደግሞ በሌላ ተመሳሳይነት በሌ
ለው ወንጀል ነው ። ስለሆነም አንደኛ ይግባኝ ባይ ጥፋትን ሞያ አድርጎ ይዟል ማለት
አይቻልም ። ጥፋትን ሞያ አድርጎ ይዟል ከማለት ይልቅ ቀደም ሲል ወንጀል
ሠርቶ የተቀጣ በመሆኑ የወትሮ ታሪኩ አደገኛነቱን ይገልጽበታል ማለቱ ለነገሩ
አግባብነት ይኖረዋል ። ይህም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 81(1)(ሐ)ተገልጿል።
አንደኛ ይግባኝ ባይ ወትሮ የተቀጣውን የእሥራት ዘመን በሙሉ አልፈጸመውም ፣
ሁለት ሶስተኛውን ከፈጸመ በኋላ ዓመሉን ለመፈተን ሲባል በሁለት ዓመት የጊዜ
ገደብ ተለቋል ሲል የከፍተኛው ፍርድ ቤት በፍርዱ ላይ ሲገልጽ አንደኛው ይግ
ባኝ ባይ ይህን ወንጀል ሆን ብሎ የፈጸመው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መሆን
አለመሆኑን አጣርቶ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 204(2) በተደነገገው መሠ
ረት የሰጠው ውሣኔ የለም ። አንደኛው ይግባኝ ባይ ይህን ወንጀል የፈጸመው ቀ
ድሞ በገደብ ለቆየለት እሥራት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከሆነ በገደብ ተን
ጠልጥሎ የነበረውን የእሥራት ተመን እላንዳች ርኅራኄ መፈጸም እንደሚገባው
የታወቀ በመሆኑ አሁን እንደገና በፈጸመው ወንጀል ሲቀጣ የቅጣት አወሳሰኑ
በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ.204(3) በተደነገገው እንደተመለከተው በዚሁ ሕግ
በቁጥር 193 መሠረት መወሰን እንዳለበት ግልጽ ነው ። የከፍተኛው ፍርድ ቤት
ይህን ሁሉ የተገነዘበው አይመስልም ። በከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍርድ ሐተታ

ላይ እንደተገለጸው ከሆነ አንደኛ ይግባኝ ባይ በወትሮ ጥፋት ከተቀጣ በኋላ ሁለት ሶስተኛውን እንደፈጸመ በአመክሮ የተለቀቀው በሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ነው ። የተለቀቀው በ1967 ዓ.ም. ሲሆን ይህን ወንጀል የፈጸመው በ1971 ዓ.ም.ነው ስለሆነም በወንጀለኛ መቅጫ ሕገ በቁጥር 204(2)(3) የተጻፈው ተፈጻሚ ላይሆን በት ነው ። የቅጣቱ አወሳሰን አሁን በፈጸመው ወንጀል አንጻር ብቻ ሊታይ ነው ማለት ነው ። የወትሮ ታሪኩ ማክበጃ ብቻ ይሆናል ማለት ነው ።

ይግባኝ ባይ በዚህ ፍርድ ቤት ፍርድ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘበት የወን ጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 472 (1) ከሶስት ወር በማያንስ እሥራትና በገንዘብ መ ቀጫ ያስቀጣል ። ይህ ድንጋጌ በቁጥር 105 እና 88 ከተጻፉት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌዎች ጋር ሲነበብ ከሶስት ወር እስከ ሶስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራት እና ከአንድ እስከ አምስት ሺህ ብር ሊደርስ በሚችል መቀጮ ያስቀጣል ማለት ነው ። የይግባኝ ባይ የወትሮ ታሪክ አደገኛነቱን ስለሚገልጽ ቅጣቱ የሚከ ብድበት መሆኑ ቢታወቅም የቅጣቱ መጠን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 188 እንደተገለጸው ሁሉ በቁጥር 472(1) ከተወሰነው ከፍ ተኛ ቅጣት ማለፍ አይችል ምና ቅጣቱ መወሰን የሚገባው በዚሁ ክልል ወይም እስከመጨረሻው ድረስ ብቻ ይሆናል ማለት ነው ።

አንደኛ ይግባኝ ባይ በወትሮ ቅጣት ያልታረመ አደገኛ ወንጀለኛ ነው ቢባ ልም ባሁኑ ወንጀል ያደረሰው ጉዳት የለም ። እነዚህን ሁኔታዎች ሁሉ በማመዛ ዘን ነገሩን ስንመለከተው አንደኛው ይግባኝ ባይ በሁለት ዓመት እሥራትና በ50 ብር (አምሳ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ ቢደረግ ቅጣቱ ለድርጊቱ ተመጣጣኝ እና ማረሚያ እንዲሁም ለሌላው ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሆናል ብለን እናምንበታለን ።

ሁለተኛው ይግባኝ ባይ ከዚህ ቀደም አጥፍቶ የተቀጣ ስለመሆኑ የቀረበ ማስ ረጃ ስለሌለ አደገኛ ወንጀለኛ ነው ብሎ መደምደም አይቻልም ። ባሁኑ ወንጀል በንብረት ላይ ያደረሰው ጉዳት የለም ። ስለዚህ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘበት ድንጋጌ በተወሰነው መሠረት በአንድ ዓመት እሥራትና በ50 ብር (አምሳ ብር) መቀጮ ቢቀጣ ቅጣቱ ለድርጊቱ ተመጣጣኝና ማረሚያ እንዲሁም ለሌላው ብርቱ ማስጠ ንቀቂያ ይሆናል ብለን እናምንበታለን ።

ከላይ በዝርዝር በተገለጡት ምክንያቶች ሁሉ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባዮችን ጥፋተኛ ያደረገበትን ድንጋጌ ሠርዘን ይግባኝ ባዮችን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 472(1) ጥፋተኞች አድርገን በዚሁ ድንጋጌ መሠረት አንደኛ ይግባኝ ባይ ቶ. አ. በሁለት ዓመት እሥራትና በ50 ብር መቀጫ እንዲቀጣ ፣ ሁለተኛው ይግባኝ ባይ በ. ኃ. በአንድ ዓመት እሥራትና በ50 ብር መቀጫ እንዲቀጣ የከፍተ ኛው ፍርድ ቤት የወሰነውን ቅጣት ዝቅ በማድረግ ፈርደናል ።

የገንዘቡን መቀጮ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከቁጥር 91 እስከ 96 የተጻፉትን በቅደም ተከተል ተፈጻሚ በማድረግ ገቢ እንዲያደርግ ፣ አን ደኛው ይገባኝ ባይ ከኅዳር 12 ቀን 1971 ዓ. ም. ጀምሮ በሁለት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ የተወሰነበትን እንዲያስፈጽም ለወህኒ ቤቱ እንዲጻፍ ፣ ሁለተኛው ይግ ባኝ ባይ ከኅዳር 12 ቀን 1971 ዓ. ም. ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በወህኒ ቤት በመቆየቱ በዚህ ፍርድ ቤት የተወሰነበትን የአንድ ዓመት የእሥራት ዘመን ፈጽሞታልና የዚህ ፍርድ ትክክል ግልባጭ ባስቸኳይ ተልኮ ከወህኒ ቤቱ እንዲፈታ ፣ የገንዘቡ መቀጮ በሕጉ መሠረት ገቢ የሚደረግ እንጂ በቀጥታ ወደ እሥራት መለወጥ የማ ይቻል በመሆኑ ገንዘቡ ገቢ ካልተደረገ ተብሎ የመፈቻቸው ጊዜ እንዳይራዘም ብለን መዝገቡን ዘግተናል ። ይጻፍ ።

የፍርድ ጉዳይ ትችት ።

በዮሴፍ ገ/ እግዚአብሔር*

ይህ ጉዳይ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከተወሳሰቡና አከራካሪ ከሆኑ ጥያቄዎች አንዱን ፣ ይኸውም ፣ አንድ ወንጀል ተሞከረ የሚባለው መቼ ነው ? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል ። በቁጥር 27 (1) [1]በሁለተኛው ድንጋጌ (ፕሮቫይዞ) « የወንጀል ሥራን ስለመጀመር » የተሰጠው መለኪያ ሙሰናዳትን ከመሞከር ለመለየት የሚያስችል ግልጽና ብቁ መለኪያ ነው ወይ ? የሚለውን ጥያቄም የግድ አብሮ ያስነሳል ።

የተሞከሩ ወንጀሎችን « ፍጻሜ ያላገኙ ሙከራዎች » እና « ፍጻሜ ያገኙ ሙከራዎች » ብሎ መከፋፈል የተለመደ ነው[2] ። ወንጀለኛው ለወንጀሉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ የተወሰኑ ድርጊቶችን ካደረገ በኋላ ፣ በሁኔታዎች ልማዳዊ ሂደት መሠረት የታሰበውን ውጤት ሊያመጣ ይችል የነበረው « ወሳኝ ድርጊት » ላለመፈጸም በማሰብ የወንጀሉን ተግባር እስከ መጨረሻው ላለመከታተል ራሱ የወሰነ እንደሆነ ፤ ወይም በሁኔታዎች ልማዳዊ ሂደት መሠረት የታሰበውን ውጤት ሊያመጣ ይችል የነበረው « ወሳኝ ድርጊት » ከመፈጸም ከአቅሙ በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ያገዱት እንደሆነ ፤ ሙከራው « ፍጻሜ ያላገኘ ሙከራ » ይባላል ።

ጉዳዩ እንደዚህ ሊሆን ይችላል ፣ ለምሳሌ « ሀ » « ለ » ን ለመግደል ከወሰነ በኋላ ሽጉጡን አጉርሶ ወደ « ለ » ቤት በመሄድ የግቢውን በር ያንኳኳል ፣ በሩ ይከፈ ትለታል ፤ በቀጥታ ወደ « ለ » መኝታ ቤት በመግባት በ « ለ » ላይ ሽጉጥ ይደገንበታል ፤ ይሁን እንጂ « ለ » ከልጁ ጋር መሆኑን በማየት « ሀ » ለልጁ በመራራት ሐሳቡን ይለውጥና « ለ » ን ከልጁ ጋር ትቶት ይሄዳል ። በዚህ ጉዳይ ላይ ወሳኝ ድርጊት ሊሆን የሚችለው የ « ሀ » ወደ « ለ » ቤት ሽጉጡን አጉርሶ መሄድና በ « ለ » ላይ መደገኑ ነው ።

ይህ « ወሳኝ ድርጊት » ነው የሚባልበት ምክንያት በኑሮ ልማድ እውቀት ሰዎች በጠላታቸው ላይ ከደገኑ በኋላ የነፍስ መግደል ወንጀልን ከመፈጸም ወደ ኋላ ስለማይሉ ነው ።

ሁኔታው ለየት የሚለው ፣ ወንጀለኛው የታሰበውን ውጤት ለማስገኘት አስፈላጊ የሆኑ ድርጊቶችን ሁሉ ከፈጸመ በኋላ ፣ ከአቅሙ በላይ በሆኑ ሁኔታዎች የወንጀል አላማውን ከግቡ ሳያደርስ የቀረ እንደሆነ ነው ። ይህ « ፍጻሜ ያገኘ ሙከራ » እየተባለ የሚጠራ ው ነው ።

ጉዳዩ እንደዚህ ሊሆን ይችላል ፣ ለምሳሌ « ሀ » « ለ » ን ለመግደል ወስኖ ወደ « ለ » ቤት በመሄድ ይተኩስበትና ይስተዋል ።

ወንጀለኛው የታሰበውን ውጤት ለማስገኘት የሚያስችሉትን አስፈላጊ ድርጊቶች በተሳካ ሁኔታ ከፈጸመ በኋላ የተወሰኑ ሌሎች ድርጊቶችን በመፈጸም የታ

ሰበው እንዳይደርስ ቢያደርግ ይህን የመሰለውን ሁኔታ በዚህ ክፍል ውስጥ ማጠቃለል ይቻል ይሆናል[3] ። ይሁን እንጂ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ወንጀለኛው መደረግ የሚገባውን ሁሉ ያደረገና ፤ በሚገባም የፈጸመ ስለሆነ ፣ ይኸ ቃሉን ያለቦታው መጠቀም ይመስላል ። በሌላ አነጋገር ወንጀለኛው የመሞከርን ደረጃ አልፎ የወንጀል ተግባሩን ከፍጻሜ አድርሶታል ።[4] የወንጀሉ ተግባር ከፍጻሜ ከደረሰ ደግሞ ሙከራ አለ ማለት እንደማይቻል የታወቀ ነው ።

ይሁን እንጂ ይህ የተሞከሩ ወንጀሎችን ፍጻሜ ያገኙና ፍጻሜ ያላገኙ ወንጀሎች ብሎ መከፋፈሉ መሰናዳትን ከሙከራ ለመለየት እምብዛም አይረዳም ።[5] ፍጻሜ ያገኙ ሙከራዎችን በምንመረምርበት ጊዜ ፍጻሜ ያገኘ ሙከራ የፈጸመው ወንጀለኛ የመሰናዳትን ደረጃ ያለጥርጥር ማለፉ ግልጽ ይሆናል ። በመሆኑም « ሀ » በ « ለ » ላይ ጥይት ተኩሶ ቢስተው ጉዳዩ ግልጽ የሆነ መሞከር ይሆናል ። የ « ሀ » በ « ለ » ላይ ጥይት መተኮስ ተግባር ወንጀሉ የመግደል ሙከራ ወይም በአካል ላይ ጉዳት የማድረስ ሙከራ ነው ብሎ መወሰን ቀላል ላይሆን ይችላል ። « ሀ » ወንጀል ለመፈጸም መሞከሩ ግን ግልጽ ጉዳይ ይመስላል ።

ነገር ግን ፍጻሜ ያላገኘ ሙከራን በምንመረምርበት ጊዜ « የወንጀሉ ሥራ » እዚህ ላይ ተጀመረ ለማለትም ሆነ መሞከርን ከመሰናዳት የሚለይ ግልጽ የሆነ መገምገሚያ ለማስቀመጥ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል ። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ አነጋገር[6] ወንጀል ለመፈጸም መሰናዳት ራሱን የቻለ ወንጀል ካልሆነ በቀር በሕግ ስለማያስቀጣ ፍጻሜ ያላገኘን ሙከራ ከመሰናዳት መለየት አስፈላጊ ይሆናል ።

አንድን ጉዳይ መሰናዳት ወይም ሙከራ ነው ብሎ በመለየት በኩል ያለውን ቀላልነትና አስቸጋሪነት ለማብራራት የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንይ ። « ሀ » « ለ » ን ለመግደል አስቦ ሽጉጥ ይገዛል ። « ሀ » መጣሪያውን በይዞታው ለማስቀመጥ አስፈላጊው ፈቃድ የለውም እንበል ። « ሀ » « ለ » ን ለመግደል ያለውን አሳብ የወሰድን እንደሆነ መሰናዳት መሆኑ ግልጽ ይሆናል ፤ ምክንያቱም ፣ የ «ሀ» ሽጉጥ መግዛት የነብስ ግድያ ወንጀል ለመፈፀም በማሰብ የመፈፀሚያውን መሣሪያ ማዘጋጀት መሆኑ ነው ። ነገር ግን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 763ን የወሰድን እንደሆነ ፍጻሜ ያገኘ ወንጀል ይሆናል ። ይህ ሁኔታ ከቁጥር 26/ንኡስ ቁጥር ሀ/ ጋር አብሮ ይሄዳል ። ምክንያቱም አስፈላጊው ፈቃድ ሳይኖረው የጦር መሣሪያ መያዝ በሕግ ተገልጾ የተደነገገ ራሱን የቻለ ወንጀል ነው[7]።

በሌላ በኩል መሐከል ላይ ያሉት ተቀራራቢ ጉዳዮችን የወሰድን እንደሆነ አንድ ጉዳይ መሰናዳት ነው ወይም ሙከራ ነው ብሎ ለመመደብ የቱን ያህል አስቸጋሪና አከራካሪ እንደሆነ ግልጽ ይሆናል ። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ፣ « ሀ » « ለ » ን ለመግደል ሆነ ብሎ አስቀድሞ በማሰብ ሽጉጡን አጉርሶ ወደ « ለ » ቤት ይሄዳል ፣ የ « ለ » ን ግቢ በር ያንኳኳል ፤ በሩ ይከፈትለታል ፤ በሩን የከፈተው ሰው « ለ » መኝታ ቤት ውስጥ እንደሆነ ለ « ሀ » ይነግረውና «ሀ» በቀጥታ ወደ « ለ » መኝታ ቤት ይሄዳል ፣ « ለ » ከልጁ ጋር መሆኑን በማየት « ሀ » ሐሳቡን ይቀይራል፤ ለልጁ በነበረው ርሕራሄ « ለ » « ሀ » ን ከልጁ ጋር ትቶት ይሄዳል ።

መሰናዳትን ከመሞከር (ፍጻሜ ያላገኘ) ለመለየትና « የወንጀል ሥራን ስለ መጀመር » በሕግ ፈላስፎች የተለያዩ ቲኦሪዎች ተሰንዝረዋል ።[8] ይሁን እንጂ ለእኛ ዓላማ ሊፈጸም የማይችል ወንጀል[9] ከሚቀጣው ሕጋችን መዋቅር ወንጀልን የሞከረ ሰው የሚቀጣበት ዋናው ምክንያት ለህብረተሰብ አደገኛነቱን በማንጸባረቁ ነው ማለቱ በቂ ነው።[10] በመሆኑም « የወንጀል ሥራ መጀመር » መታየት

ያለበት የወንጀለኛው ድርጊት ሊያስከትል ከሚችለው ከፍ ካለ አደጋ አኳያ ሳይ ሆን ከሰውየው አደገኛነት መንጸባረቅ አኳያ መሆን አለበት ።

የአደጋው መድረስ ግምት ውስጥ ገብቶ መወሰድ ያለበት ወንጀለኛው ወንጀሉን ለመፈፀም ያለውን ቁርጠኝኘት ለመወሰን ሊረዳ እስከቻለ ድረስ ብቻ ነው ።

ነገር ግን « የወንጀል ሥራ መጀመርን » ብዙም አልገለጽነውም ። በጣም ሰፊና አጠቃላይ የሆነ መመሪያ ከመጠቆም በቀር ብዙም ልንገልጸው አንችልም ፤ ምክንያቱም የሰውን ባህርይ በምንመለከትበት ጊዜ «የወንጀል ሥራ መጀመር» ወይም « የቁርጠኛነት ውሳኔ » ማለት « ወሳኙ ድርጊት » ከተፈጸመ በኋላ በኑሮ ልማድ ዕውቀት አድራጊው ወንጀሉን ከመፈጸም ወደ ኋላ አይልም ብሎ ለመደም ምደም እንደሰውየው ባህርይና የቀድሞ ታሪክ ስለሚለያይ ነው ። ስለዚህ «ፍጻሜ ስላላገኙ » ወንጀሎች በምንነጋገርበት ጊዜ አንድ ሰው ወንጀል ለመፈጸም መሞከሩ ወይም አለመሞከሩ በሚያጋጥመን በእያንዳንዱ ጉዳይ መሠረት የሚወሰን እንጂ የሰውን ባህርይ እስከመተንበይ ድረስ ሄደን በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚችል መገምገሚያ ልናወጣ እንደማንችል መስማማት ይኖርብናል[11]።

በያዝነው የፍርድ ጉዳይ ትችት ጉዳዩ ሲመረመር ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች በማስረጃ እንዳረጋገጠ ይታያል ፡-

ሀ. ይግባኝ ባዮች ከሌሎች ሶስት ሰዎች ጋር በመሆን የአሰላን ሕዝብ ለማታለል ከአዲስ አበባ ወደ አሰላ መሄዳቸውን ፤

ለ. በአሰላ ከተማ በቀበሌ 05 አንድ ነጋዴ ማግኘታቸውን ፤

ሐ. ከሶስቱ ሰዎች አንዱና እስከአሁን ያልተያዘው መንግሥት ለድሃ ገበሬና ነጋዴ፣ ለተቸገረው ሰው ሁሉ ገንዘብ ይሰጣል ብሎ ለነጋዴው መንገሩን እና ወደ አንደኛው ይግባኝ ባይ የወሰደው መሆኑን ፤

መ. ያልተያዘው ሰውና አንደኛው ይግባኝ ባይ ነጋዴውን ወደ ሁለተኛው ይግባኝ ባይ የወሰዱት መሆናቸውን ፤

ሠ. ሁለተኛው ይግባኝ ባይ አንደኛውን ይግባኝ ባይ አንተ ጥዋት ገንዘብ ወስደሀ የለም ወይ ? ለምን መጣህ ብሎ የጠየቀው መሆኑን ፤

ረ. አንደኛው ይግባኝ ባይ ለሁለተኛው ይግባኝ ባይ እርግጥ ነው ጥዋት ገንዘብ ወስጃለሁ ኣሁንም የመጣሁበት ምክንያት እንደገና ገንዘብ ለመውሰድ ሳይ ሆን ለሰዎቹ (ለነጋዴውና ላልተያዘው ሰው) ገንዘብ የሚሰጥበትን ሥፍራ ላሳያቸው ነው ብሎ መናገሩን ፤

ሰ. ሁለተኛው ይግባኝ ባይ ነጋዴውና ያልተያዘው ሰው በዘጠኝ ሰዓት መጥተው ገንዘብ እንዲወስዱ የነገራቸው መሆኑን ፤

ሸ. በኋላም ነጋዴው ሁኔታውን ለተረኛ አብዮት ጥበቃ ጓዶች ጠቁሞ በዚህ ምክንያት ሁለቱ ይግባኝ ባዮች መታሰራቸውን ፤ እና

ቀ. ሁለቱ ይግባኝ ባዮች ያለአንዳች ግዳጅ ለፖሊስ የእምነት ቃላቸውን ሰጥተው ድርጊታቸው ያስገኘው ውጤት ባለመኖሩ ይቅርታ እንዲደረግላቸው መማጸናቸውን ።

ከነዚህ ፍርድ ቤቱ ካረጋገጣቸው ፍሬ ነገሮች በመነሳት ምን ዓይነት ሕጋዊ ውሳኔ ሊሰጥ ይቻላል ? ውሳኔው የማታለል ወንጀል ሙከራ አይደለም ፣ መሰናዳት እና አድማ ነው የሚል መሆን አለበት ፣ ወይስ የተገኙት ፍሬ ነገሮች የተፈጸመው ተግባር በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ የማታለል ወንጀል ለመፈጸም የታለመ መሆኑን ስለሚያረጋግጡ በወንጀለኛ መቅጫ

ሕግ ቁጥር 27/656/ ሀ እና ቁጥር 472 መሠረት የተጣመሩ የአታላይነት ሙከራና የአድማ ወንጀሎች ተፈጽመዋል የሚል መሆን አለበት ?[12]

ይግባኝ ባዮች ካልተያዙት ሶስት ሰዎች ጋር በመሆን የአሰላን ሕዝብ ለማታለል ወስነው ከአዲስ አበባ ወደ አሰላ መሄዳቸው ራሱ እንደ ወንጀል ሙከራ ሊቆጠር የማይችል ይመስላል ። ይህ ግልጽ የሆነ ወንጀል ለመፈጸም የተደረገ መሰናዳት ነው ፤ በመሆኑም ፣ ለጊዜው መሟላት የሚገባቸውን የሥነ ሥርዓት ሕግጋት ወደ ጐን ተወት በማድረግ ፣ ይግባኝ ባዮች ተግባራቸውን በመቀጠል ተጨማሪ ድርጊቶች ባይፈጽሙ ኖሮ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 472 መሠረት ብቻ ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ ነበር ።

ይሁን እንጂ ይግባኝ ባዮች ተግባራቸውን በመቀጠል አንድ ሰው አነጋገሩና ነጋዴ እንደሆነ ነገራቸው ። ከዚያም ላይ ኣልቆሙም ። መንግሥት ለድሀ ነጋዴዎችና ገበሬዎች ገንዘብ ይሰጣል በማለት ሐሰተኛውን ነገር እውነት አስመስለው በማረጋገጥ ሰውየውን ለማሳመን የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል ።

የማታለል ወንጀል የመፈጸም ሐሳባቸውን እውን ለማድረግ በመቀጠል ፤ ከይግባኝ ባዮች አንዱ ራሱን የመንግሥት ባለሥልጣን በማስመሰል የግል ተበዳዩን ወደ ስህተት ለመምራት ፣ መንግሥት ለድሀ ነጋዴዎችና ገበሬዎች ገንዘብ እንደሚሰጥና ገንዘቡ ከሚሰጥበት ሥፍራ በዘጠኝ ሰዓት ከመጣ እሱም ገንዘቡን ለመውሰድ እንደሚችል ነጋዴውን ለማሳመን ሞክሯል ። ሁኔታው ይህ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ እንዳደረገው ሁሉ የይግባኝ ባዮች ድርጊቶች በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ የአታላይነት ወንጀልን ለመፈጸም የታለሙ አይደሉም ተብሎ መወሰን አለበት ወይ ?

ከላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ሊፈጸሙ የማይችሉ ወንጀሎች ከተሞከሩ ያስቀጣሉ ። በመሆኑም በሕይወት ያለ መስሎት በሞተ ሰው ላይ ጥይት የተኩሰ ሰው ይቀጣል ።[13] ይሁን እንጂ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ከጥይቱ ተኩስ ሊከተል የሚችል ምንም ዓይነት ጉዳት የለም ። እንደዚህ ያለ ሰው ይቀጣ ከተባለ የሚቀጣው ድርጊቱ ሊያስከትል ለሚችለው አደጋ ሳይሆን አደገኛነቱን በማንጸባረቁ ነው ። እንደዚህ በመሆኑም « የወንጀል ሥራ መጀመር » መኖርና አለመኖሩን መርምሮ ሙከራ መኖር አለመኖሩን ለመወሰን የበለጠ ሙተኮር ያለበት በተከሳሹ አደገኛነት መንጸባረቅ እንጂ በወንጀል ሥራ መጀመር በሚለው ጥሬ ንባብ ላይ መሆን የለበትም ።

ነገር ግን ፍርድ ቤቱ የወንጀሉ አፈጻጸም « በእርግጥ » ካልተጀመረ በቀር የመሞከር ወንጀል ሊኖር አይችልም የሚል ሐሳብ የሚሰነዝር ይመስላል ። ፍርድ ቤቱ ይህን ሐሳ ብ የሚሰነዝር እንደሚመስል ከአባባሉ መረዳት ይቻላል ፤ ይኸውም እንደዚህ ይላል ፡— « በያዝነው ጉዳይ የግል ተበዳዩ ለቸገረው ሰው መንግሥት ገንዘብ ይሰጣል ወደ ተባለበት ሥፍራ ተታልሉም ይሁን ሳይታለል ይግባኝ ባዮችን ለማስያዝ እንዲረዳው ሲል ከመሄዱ በቀር የራሱን ንብረት ወይም የሌላ ሰው የሆነውን ንብረት በሚጐዳ አኳኋን በማድረግም ሆነ ባለማድረግ አንድም ዓይነት ድርጊት እንዲፈጽም አላደረጉትም

« በያዝነው ጉዳይ ያልተያዘው ሶስተኛው ግብረ አበር የግል ተበዳዩን መንግሥት ለተቸገረ ሰው ገንዘብ እንደሚሰጥ አልሰማህም ወይ ? ብሎት ወደ አንደኛው ይግባኝ ባይ ፣ አንደኛው ይግባኝ ባይም ኑ የሚሰጥበትን ሥፍራ አሳያችኋለሁ ብሎ ሁለተኛው ይግባኝባይ ወደሚገኝበት የወሰዱትና እንደወሰዱትም ምንም ነገር ሳይጠይቁት ገንዘብ የሚሰጠው በዘጠኝ ሰዓት ነው ብሎ ሁለተኛው ይግባኝ ባይ

ተናግሮ ከመለያየታቸውና የተቆረጠውም (የቀጠሮው) ሰዓት ሳይደርስ የግል ተበዳይ ነኝ ባይ ያስያዛቸው ከመሆኑ በቀር በንብረቱ ላይ ጉዳት በሚያደርስ አኳኋን አንድ ድርጊት እንዲፈጽም አልጠየቁትም »

ነገር ግን ይህ « የወንጀል ሥራ መጀመር » ገንዛቤ በጣም ጠባብ ከመሆኑም በላይ ሕግ አውጪው የወንጀል ሙከራ በሕግ ያስቀጣል እንዲል የገፋፋትንና ግምት ውስጥ ያስገባቸውን የፖሊሲ ጉዳዮች በሚከተለሉት ምክንያቶች ይቃረናል ፡፡

ቃሉ ራሱ እንደሚያመለክተው የተሞከረ ወንጀል ማለት ሙሉ በሙሉ በገቢር ያልተገለጸ(ያልተፈጸመ) ወንጀል ማለት ነው ፡፡ ሕጉ የተሞከሩ ወንጀሎች ያስቀጣሉ ብሎ በሚደነግግበት ጊዜ እግምት ውስጥ ያስገባው ዋናው የፖሊሲ ጉዳይ ሕብረተሰብን ከአደገኛ ሰዎች ማለትም በሕብረተሰብ ላይ ጉዳት ለማስከተል ቁርጠኛ ሐሳባቸውን ለመጨረሻው ድርጊት ወይም የተከለከለውን ጉዳት ለማስከተል አስፈላጊ ለሆኑት ድርጊቶች ቅርብ በሆኑት ድርጊቶቻቸው ከአንጸባረቁት ሰዎች ለመጠበቅ መሆን አለበት ፡፡

መሰናዳትን ከሙከራ ለመለየት የምንጠቀምበት መገምገሚያ ሙከራ አለ ከመባሉ በፊት የወንጀሉን ድንጋጌዎች የሚጥሱ የተወሰኑ ድርጊቶች የግድ መፈጸም አለባቸው የሚል ከሆነ ፣ ሕግ አስፈጻሚው የመንግሥት አካል ወንጀልን ለመከላከል አያስችለውም ይሆናል ፡፡[14]

በተጨማሪም እንደተባለው ሁሉ ይህ « የወንጀል ሥራ መጀመር » ግንዛቤ ወንጀሉን ለመሥራት መፈጸም የሚገባቸው ድርጊቶች ከአንድ በላይ ካልሆኑ ወይም ከድርጊቱ መፈጸም አስቀድሞ በሚመጣ በሕግ በተገለጹ ሁኔታ ከባድ ወንጀል ካልሆነ[15] የሙከራ ወንጀሎች ሊኖሩ አይችሉም ወደሚል ግምት ያስገባል ፡፡

ሁኔታውን ለማብራራት ስርቆትን እንደ ምሳሌ እንውሰድ ፡፡ ስርቆት የሌላ ሰው ሀብት የሆነውን ተንቀሳቃሽ ንብረት መውሰድ ነው[16] ፡፡ በመሆኑም ይህን ወንጀል በሚመለከት ረገድ ወንጀለኛው እጅ ከፍንጅ ካልተያዘና ከአቅሙ በላይ የሆነ ሁኔታ የሰረቀውን ንብረት ከመውሰድ ካላገደው ወይም የሠረቀውን ንብረት ከእጁ ካገባ በኋላ ሃሳቡን ለውጦ ንብረቱን ለባለ ሃብቱ ትቶ ካልሄደ በቀር ሙከራ ሊኖር አይችልም ፡፡ የኋለኛው ሁኔታ በእውነት ሊሆን መቻሉ አጠራጣሪ ነው ፡፡ ነገር ግን ለመሥረቅ ማሰብን ወይም ስርቆትን እና የኃይል ሥራን የሚያጠቃልለውን ወንበዴነትን በሚመለከት ረገድ[17] ሙከራን በተለያየ መልኩ ይኸውም ፍጻሜ ያላገኘና ፍጻሜ ያገኘ ብሎ በትክክለኛው መንገድ መገንዘብ ይቻላል ፡፡ ይህ አባባል ትክክል የሚሆነው ፣ በቀላሉ መገንዘብ እንደሚቻለው ስርቆትና የኃይል ሥራ መፈጸም የሚለውን የወንበዴነትን ትርጓሜ ብንወስድ ወንበዴነት ፍጻሜ ያገኘ ወንጀል ለመሆን ከአንድ በላይ የሆኑ ድርጊቶች መፈጸም አለባቸው ፡፡ ይኸውም የሌላውን ሰው ንብረት መውሰድና የንብረቱን መወሰድ በመቃወም የሚነሳውን መከላከል ለማስወገድ የኃይል ሥራ መጠቀም ወይም ለመጠቀም ማስፈራራት መኖር አለባቸው ፡፡ ነገር ግን ከላይ በምሳሌ እንደተገለጸውና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ልዩ ክፍልን ስንመረምር እንደምንረዳው ሁሉም ወንጀሎች ፍጻሜ ለማግኘት ከአንድ በላይ የሆኑ ድርጊቶችን መፈጸም አይጠይቁም ፡፡ በመሆኑም «የወንጀል ሥራ መጀመር» አለ ለማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ልዩ ክፍል ከተከለከሉት ድርጊቶች ቢያንስ አንዱ ድርጊት መጣስ አለበት ከተባለ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 27 (1) በሁለተኛው አዲስ ዓረፍተ ነገር በአጠቃላይ የተገለጸውን «የወንጀል ሥራ መጀመር» ያለ ጥርጥር መቃረን ይሆናል ፡፡ ምክንያቱም አንድን ተግባር ወንጀል የሚያደርጉ

ትን ሁኔታዎች በሚዘረዝረው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ልዩ ክፍል መሠረት አንድ ወንጀል ፍጻሜ ለማግኘት የአንድ ድርጊትን ወይም ከአንድ የበለጡ ድርጊቶችን መፈጸም የሚጠይቅ ቢሆንም ይህ በቁጥር 27 (1) የተሰጠው ድንጋጌ ምንም ልዩነት ሳያደርግ በአጠቃላይ በሁሉም ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን የታለመ በመሆኑ ነው ።

በሌላ መንገድ ፣ « የወንጀል ሥራ መጀመር » ግንዛቤን ፍርድ ቤቱ በተረዳው መልክ እንውሰድ ብንል እንኳ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተሳሳተ ይመስላል ። ፍርድ ቤቱ እንደዚህ ይላል :— « . ምናልባት የግል ተበዳይ ይግባኝ ባዮችን ሳያስይዛቸው ቀጠሮውን አክብሮ ቢገኝ ኖሮ በተጠቀሰው ዓይነት እንዲፈጽም ይጠይቁት ነበር የሚል ግምት እናሳድር ይሆናል ። በአንጻሩ ደግሞ የግል ተበዳዩ ነጋዴ መሆኑን ስለገለጸላቸው ነጋዴ የሆነ ሰው በቀላሉ አይታለልም በሚል አስተሳሰብ በቀጠሮው ላይገኙ ቆርጠው በቀጠሮ እንደሚገናኙ አድርገው አስናብተውታል ሊባል ይቻላል ።

« እንደዚህ ዓይነቱ የተለያየ አስተያየት ሊያሰጥ የሚችል ሁኔታ በመኖሩ ይግባኝ ባዮች የፈጸሙት በማያጠራጥር ሁኔታና በቀጥታ የማታለል ወንጀል ለመፈጸም ወደ አሰቡበት ግብ ለመድረስ የፈጸሙት ተግባር ነው ብሎ መደምደም አይቻልም ብለን እናምንበታለን »

ፍርድ ቤቱ ያስቀመጠውን ሁለተኛ አማራጭ ይቻላል ብለን ብንወስድ እንኳ ፣ ይግባኝ ባዮቹ የግል ተበዳዩ ሊታለል የሚችል ወይም የማይችል መሆኑን ለማየት መሞከራቸው ግልጽ ነው ። ያልተያዘው ሰውና አንደኛው ይግባኝ ባይ ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 656 አባባል መሠረት ሐሰተኛውን ነገር እውነት አስመስለው በመናገር የግል ተበዳዩን ለማሳመን ሙከራ አድርገዋል ። ሁለተኛው ይግባኝ ባይ ከሁለቱ ሌሎች ሰዎች ጋር በመተባበር በቁጥር 656 አባባል መሠረት « ያልሆነውን እኔ ነኝ ብሎ » የመንግሥት ባለሥልጣን በመምሰል ቀርቧል ። ይህ ወንጀሉ መጀመሩን በግልጽ ያሳያል ። ምክንያቱም ቁጥር 656 የሚከለክላቸው ድርጊቶች ተጥሰዋልና ። በመሆኑም ሁለተኛውን አማራጭ ብንወስድም መደረስ የነበረበት መደምደሚያ ይግባኝ ባዮች የግል ተበዳዩን ማታለል እንደማይችሉ ስላመኑ የወንጀል ተግባራቸውን እስከ መጨረሻው ለመከታተል አልቻሉም የሚል ይመስላል ። ማታለል እንደሚችሉ አምነው ቢሆን ኖሮ ለግል ተበዳዩ ሌላ ቀጠሮ ባልሰጡት ነበር ። የወንጀል ተግባራቸው የከሸፈው የግል ተበዳዩን ለማታለል አንችልም ከሚለው እምነታቸው የተነሣ መሆን አለበት ።

በመሆኑም ፣ ጠባብ የሆነውን የፍርድ ቤቱን « የወንጀል ሥራ መጀመር » ግንዛቤ ብንወስድ እንኳ ፍርድ ቤቱ የማታለል ወንጀል ሙከራ ነበር ከሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ ነበረበት ።

በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤቱ የተቸበት ሌላው ጭብጥ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን በተለያዩ ቅጂዎች ፣ ማለትም በአማርኛ ፤ በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛው የሚታየውን ልዩነት ነው ። በቁጥር 472(1) በእንግሊዝኛውና በፈረንሳይኛው ቅጂ « በዚህ የሕግ ቁጥር ውስጥ ከፍ ያለ ወንጀል የሚባለው በአምስት ወይም ከአምስት ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው » የሚለው ዐረፍተ ነገር ፍርድ ቤቱ በትክክል እንዳመለከተው በአማርኛው ቅጂ የለም ።

በሌላ በኩል የቁጥር 472(1) የአማርኛው ቅጂ « ከፍ ባሉ ወንጀሎች » ብቻ ላይ የተወሰነ አይደለም ፤ ነገር ግን የእንግሊዝኛው ቅጅና ፍርድ ቤቱ እንደተመለከተው የፈረኔንሳይኛው ቅጂ የቁጥር 472(1) ን ተፈጻሚነት ከፍ ባሉ ወንጀሎች ብቻ ላይ ይወስኑታል ፣ ይኸውም ቢያንስ በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት በሚያስ ቀጡ ወንጀሎች ላይ ነው ።

ጉዳዩ ይህ ሆኖ ፤ ፍርድ ቤቱ እንዳደረገው « ይህ በትርጉም ስህተት ምክንያት የተፈጠረ ስህተት እንጂ ድንጋጌው ልክ በእንግሊዝኛውና በፈረንሣይኛው ቅጂ ዎች እንደተጻፈው ነው » ብሎ ለማረጋገጥ ይቻላል ወይ ?

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ያወጣው ሕግ አውጪው አካል ተወያይቶ ሕጉን ያጸደቀው በአማርኛ ቋንቋ መሆኑ እርግጥ ነው ። አማርኛ ቋንቋ የአገራችን ብሔ ራዊ ቋንቋ መሆኑ ደግሞ ሌላው እውነት ነው ። ሕግ ፤ በተለይም የወንጀለኛ መቅ ጫ ሕግ ብሔራዊ ሕግ ስለሆነ ተቃራኒ ማስረጃ ከሌለ በቀር አንድ ሰው እንደ አገ ራቱ ሕግ አድርጎ መውሰድ ያለበት የአማርኛውን ቅጅ ነው ።

በቁጥር 472(1) በአማርኛው ቅጅና በእንግሊዝኛውና በፈረንሣይኛው ቅጅ ዎች ያለው ልዩነት የትርጉም ስህተት ለመሆኑ በእንግሊዝኛውና በፈረንሣይኛው ቅጅዎች ያለው ፣ ወንጀሉ ከፍ ያለ ወንጀል መሆን አለበት የሚለው መለኪያ ፣ በአማርኛው ቅጅ የቀረው ሆን ተብሎ አለመሆኑን ለማስረዳት ፍርድ ቤቱ ከሕግ አርቃውቂ ኮሚሲዮንም ሆነ ከሕግ አውጪው ቃለ ጉባኤ አንድም ማስረጃ አልጠ ቀሰም ። እንደዚህ ያለ ማስረጃ ከሌለ በቁጥር 472 (1) በእንግሊዝኛውና በፈረንሣ ይኛው ቅጂዎች የተገለጸውን ወንጀሉ « ከፍ ያለ ወንጀል » መሆን አለበት የሚ ለውን መለኪያ በአማርኛ ቅጅ ሕግ አውጪው ሆን ብሎ ብሎ አስቀርቶታል ብሎ መደምደሙ ትክክል ይመስላል ።[18]

ቁጥር 472(1) የአማርኛው ቅጅ የተተረጐመው በስህተት ነው ብለን ከፍርድ ቤቱ ጋር እንስማማ ብንል እንኳ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይህን ጭብጥ ከዚህ ላይ ማንሣት አግባብነት የለውም ። ምክንያቱም የቁጥር 472 (1) ን የአማርኛውን ቅጅም ይሁን የእንግሊዝኛውንና የፈረንሣይኛውን ቅጂዎች ብንወስድ ይግባኝ ባዮች ከቅጣት አያመልጡም ። በቁጥር 656 የተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት ከአምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ያነሰ ቢሆን ኖሮ ይህ ነጥብ አግባብነት ይኖረው ነበር ። ይህ የሚያሳየው ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት የሌለውን ጭብጥ አንስቶ ውሳኔ መስጠቱን ነው ።

በአንደኛው ይግባኝ ባይ ላይ ቅጣት መወሰንን አስታኮ ፍርድ ቤቱ አንስቶ የተቸበት ሌላው ነጥብ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 204(2) ፤ 204/3 እና 193 ን ነው ። ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ እንዳመለከተው ከፍተኛው ፍርድ ቤት አንደኛው ይግ ባኝ ባይ የአሁኑን ወንጀል የፈጸመው በተሰጠው የጊዜ ገደብ መሆን አለመሆኑን አለማጣራቱ እውነት ነው ። አንድ ሰው በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወንጀል ከ ፈጸመ ለአዲሱ ወንጀል የሚወሰነው ቅጣት በገደብ ተነስቶ በነበረው በድሮው ቅጣት ላይ ተዳምሮ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 193 መሠረት የሚፈጸም መሆ ኑም እርግጥ ነው ።[19]

ነገር ግን ፍርድ ቤቱ እንደተቸው ሁሉ አንደኛው ይግባኝ ባይ የአድማውን ወንጀል በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አልፈጸመውም ። ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ ፣ ይህን ጭብጥ ከዚህ ላይ ማንሳት በአንደኛው ይግባኝ ባይ ላይ መወሰን በነበረበት ቅጣት አወሳሰን ላይ በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን ስለማይረዳ አግባብነት የለ ውም ።

ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባዮችን ባልተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ማድረጉ ሌላው የሚታይ ነጥብ ነው ። ጉዳዩ እንደሚያመለክተው ይግባኝ ባዮች የተከሰሱት በማታለል ሙከራ ነበር፤ይሁንና በይግባኝ ደረጃ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር472 (1)ን በመተላለፍ በአድማ ወንጀል ጥፋተኞች ሆነው ተገኝተዋል ።

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አፈጻጸም መሠረታዊ መርህ አንድ ሰው ባልተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም[20] የሚል ነው ፤ ይህ አንድን በወንጀል የተከሰሰ ሰው ራሱን እንዲከላከል የሚያስችለውና ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የታለመ መርህ በዚህ ጉዳይ ላይ ለምን አስፈላጊ እንዳልሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሕጋዊ ምክንያት አልሰጠም ።

የዚህ ትችት ዓላማ ለማታለል ሙከራ ወንጀል የሚሆን መከላከያ ይህን ወንጀል ለመፈጸም ለሚደረግ አድማ ወንጀልም እንደሚሆን ፍርድ ቤቱ አልተረዳውም ለማለት አይደለም ። ዓላማው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓታችን እንደማንኛውም የሥነ ሥርዓት ሕግ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትህ በመስጠት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን ማሟላት ስለሆነ ፍርድ ቤቱ የደረሰበትን ውሳኔ ለማጠናከር በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓታችን የተደገፈ ምክንያት መስጠት ነበረበት ለማለት ነው ። በተለይ ቁጥር 472(3) የአድማ ወንጀልና በንብረት ላይ የሚፈጸም ወንጀል ተደራራቢ ወንጀሎች መሆናቸውን ስለሚደነግግ « ላንድ ጥፋት አንድ ቅጣት » የሚለው እዚህ ላይ አግባብ እንደሌለው ያመለክታል ። ይህ እንደገና የሚያመለክተው የወንጀለኛ መቅጫሕግ ሥነ ሥርዓታችን ቁጥር 113[21] ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችልና መጀመሪያውኑ የተጣመረ ክስ መመሥረት እንደነበረበት ነው ። ስለዚህም ፍርድ ቤቱ ጣምራ ክስ ሳይኖር ይግባኝ ባዮችን ባልተከሰሱበት ተደራራቢ ወንጀል ጥፋተኞች ናቸው ብሎ ለመወሰን ያስቻለውን ሕጋዊ ምክንያት መግለጽ ነበረበት ።

መ ደ ም ደ ሚ ያ

1. መሞከርን ከመሰናዳት ለመለየት የሚያስችል አጠቃላይ የሆነ መገምገሚያ መሰጠት የማይቻል ቢሆንም እያንዳንዱን ጉዳይ በመመርመር ሙከራ መኖር አለመኖሩን መወሰን ይቻላል ። በዚህ ጉዳይ ለወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን ተቃራኒ የሆነውንና ጠባቡን የመሞከር ግኔዛቤ ብንወስድ እንኳ ፍርድ ቤቱ በቁጥር 27/656(ሀ) መሠረት የማታለል ሙከራ ፣ በቁጥር 472 (1) መሠረት የአድማ ወንጀል ተፈጽሟል ከሚል ውሳኔ ላይ መድረስ የነበረበት ይመስላል ።

2. በቁጥር 472(1) ሕጉ በአማርኛው ቅጅ እንደተጻፈው ሳይሆን በእንግሊዝኛውና በፈረንሣይኛው ቅጅዎች እንደተጻፈው ነው የሚለው የፍርድ ቤቱ መደምደሚያና « ከፍ ያለ » የሚለው ሐረግ በቁጥር 472(1) በአማርኛው ቅጅ ሆን ተብሎ ላለመቱው እንዲሁም ይህ ድንጋጌ ማንኛውንም ዓይነት ወንጀል ለመፈጸም በሚደረግ አድማ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ላለመወሰኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ የፍርድ ቤቱ አባባል አስተማማኝ አይደለም ።

3. ፍርድ ቤቱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 204 ን እና ቁጥር 193 ን መጥቀሱ አግባብነት የሌለው ይመስላል ፤ ምክንያቱም በአንደኛው ይግባኝ ባይ ላይ ቅጣት ለመወሰን ሁለቱም ቁጥሮች አግባብነት የላቸውም ።

4. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓታችን የተደገፈ ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር ፣ ይግባኝ ባዮች ባልተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ጥፋተኞች ናቸው ተብሎ የተሰጠው የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አፈጻጸም መሠረታዊ መርህን የሚቃረን ይመስላል ።

የግርጌ ማስታወሻ ፤

*ረዳት ፕሮፌሰር ፥ ሕግ ፋኩልቲ ፥ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

1. ለቁ. 27(1) ሙሉ ቅጅ ፍርዱን ይመለከቷል ።

2. ግራቨን ፥ አን ኢንትሮዳክሽን ቱ ኢትዮጵያን ፒናል ሎው (ሕግ ፋኩልቲ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ማተሚያ ቤት ጋር በመተባበር አዲስ አበባ—ናይሮቢ 1965 (እ.ኤ.አ) ፤ ገጽ 27

3. ከላይ በተጠቀሰው መጸሐፍ ውስጥ ግራቨን ምሳሌ ሲሰጥ « ለ » « ሀ » መርዝ የጨመረበትን ቡና ከጠጣ በኋላ «ሀ» «ለ» እንዳይሞት በማለት ማርከሻ ይሰጠዋል ። » ይሁን እንጂ እንደዚህ የመሳሰሉትን ጉዳዮች « ፍጻሜ ያገኘ ሙከራ » ውስጥ መመደብ አሳሳች ሊሆን ይችላል ። እዚህ ላይ የምናየው መጸጸትና በኑሮ ልማድ ዕውቀት የታሰበውን ውጤት ያለጥርጥር ሊያመጣ ይችል የነበረውን፥ የወንጀል ሥራ መቅጨትን ነው ።

4. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 28/3

5. « ቁ. 26 የመሰናዳት ተግባሮች።

የሕግ መጣስን ሥራ ለማሰናዳት ወይም ለማድረግ እንዲቻል ይልቁንም መሣሪያዎችን በመሰብሰብ ወይም የአፈጻጸም ሁኔታዎች እንዲከናወኑ ለማድረግ የተደረጉት ተግባሮች ማስቀጣት የሚችሉት ፤

ሀ/ ተግባሮቹ እራሳቸው የሕግ መጣስ ሥራ ሆነው የሚያስቀጡ መሆናቸው በሕግ የተደነገገ እንደሆነ፥
ለ/ ከሚያስከትለው ከባድ ጥፋት የተነሳ ወይም በጠቅላላው በሚያደርሰው አደጋ መጠን ልዩ የሕግ መጣስ መሆናቸው በሕግ ተገልጾ የታዘዘ እንደሆነ ነው ፡ »

6. ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 የተጠቀሰውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. 26 (ለ) ን ይመለከቷል ።

7. ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 የተጠቀሰውን ቁ. 26(ሀ) ን ይመለከቷል ።

8. ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2 የተጠቀሰው ፥ ገጽ 71 ይመለከቷል ።

9. በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 8 የተጠቀሰውን እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. 27ን ይመለከቷል ።

10. በኮሞን ሎው የሙከራ ወንጀልን የፈጸመ ሰው የሚቀጣበት ምክንያት ይኸው ለመሆኑ ተርነር (አታሚ) ከኔይስ አውትላይንስ ኦፍ ክሪሚናል ሎው (የካምሪጅ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት፥1952), ገጽ 79 — 83 ይመለከቷል ።

11. በማስታወሻ ቁጥር ሁለት የተጠቀሰው ፥ ገጽ 73 ፡ እንዲኒያስ ፥ ዘ ጄኔራል ፓርቲ ኦፍ ዘ ክሪሚናል ሎው ኦፍ ኖርወይ (ሲዊት ኤንድ ማክስዌል ሊሚትድ ሎንዶን ፥ ኒው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ ኒውዮርክ ፥ 1965) ፤ ቅጽ 3 ፡ ገጽ 288—290 ።

12. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. 472 (3) ን ይመለከቷል ፤ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ወንጀል ለመፈጸም ማደምና ወንጀል መፈጸም « ላንድ ጥፋት አንድ ቅጣት » በሚለው መርህ እንደማይዋሐድ ተደንግጓል ።

13. ቁ. 27 ንና በማስታወሻ ቁጥር 2 የተጠቀሰውን ግራቨንን ከገጽ 87—91 ይመለከቷል ።

14 ውሊያምስ ፥ ፓሊስ ኮንትሮል ኦፍ ኢንተንዲንግ ክሪሚናልስ፥ዘ ክሪሚናል፥ሎው ሪቪዩው (1955) ፤ ገጽ 66—70 ።

15 ግራቨን ፥ በማስታወሻ ቁ 2 የተጠቀሰው ፥ ገጽ 71

16 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ 630 ን ይመለከቷል ።

17 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. 636ትን ይመለከቷል ። ነገር ግን ሥርቆት ለመፈጸም ሐሳብ መኖሩ ብቻ በቂ መሆኑን ይገነዘቧል ።

18. ይህ አባባል የሕጉ የአማርኛ ቅጂ አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች የሕጉን ሌላ ቅጂ ማየት የለባቸውም ለማለት አይደለም ። የአማርኛ ቅጂው አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ የፈረንሳይኛውን ቅጂ ማየት ፥ መቀጠል ያለበት ትክክለኛ አሠራር መሆኑን ተቺው ያምናል ።

19. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ. 204 (3) ሁለተኛው አዲስ አረፍተ ነገር ።

20. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 108(1) ይመለከቷል ።

21. ቁ. 113 የተፈ ጸመው ወንጀል ዓይነት የሚያጠራጥር በሆነ ጊዜ ።

(1) ለተፈጸመው ተግባር ወይም ተግባሮች የሚቀርበው ማስረጃ ከአያሌ ወንጀሎች ውስጥ የትኛውን እንደሚያረጋግጥ ለማወቅ ባጠራጠረ ጊዜ ተከሳሹ ለፈጸመው ይበልጥ ማስረጃ ያለ በሚመስለው ወንጀልና እንዲሁም በተጨማሪ በማስረጃው ሊረጋገጥ ይቻላል በሚባሉት ወንጀሎች ሁሉ ይከሰሳል ።

(2) የቀረበው ማስረጃ ተከሳሹ በተጨማሪ የሚያስከስሰው ወንጀል ከሆነና ፍርድ ቤቱም ወንጀሉን ለማየት ሥልጣን ያለው ከሆነ ክስ ባይቀርብበትም በዚሁ ወንጀል በተከሳሹ ላይ ለመፍረድ ይቻላል ። ይኸውም ተጨማሪው ከክሱ ውስጥ ካለው ወንጀል አነስተኛ ወንጀል ሆኖ ሲገኝ ነው ።
(3) ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁ. 6 እና 9 መሠረት ከመፈጸም በዚህ ቁጥር ድንጋጌ አይታገድም ።

JOURNAL OF ETHIOPIAN LAW

Published by the Faculty of Law, Addis Ababa University, in Co-operation
with the Ministry of Law and Justice
(to be cited as 12 J. Eth. L.)
1982

The Editors encourage all interested persons to submit to them any material which would be appropriate for publication in the journal such as works of scholarly reaserch in the field of law, comments on court decisions and commentaries on legislation.

Our address- Journal of Ethiopian Law
Addis Ababa University, Faculity of Law
P.O.Box 1176
Addis Ababa, Ethiopia
Telephone 11-17-33 or 11-08-44 (108)

JOURNA OF ETHIOPIAN LAW

Published by the Faculty of Law,

Addis Ababa University, in co-operation with the

Ministry of Law and Justice.

Editorial Board

Getachew Kibret	Chairman, Minister, Ministry of Law and Justice
Kebede Gebre Mariam	Permanent Secretary, Ministry of Law and Justice
Assefa Liben	President, High Court
Daniel Haile	Dean, Faculty of Law, Addis Ababa University
Fasil Nahum	Associate Professor, Faculity of Law, Addis Ababa University

Editors

Fasil Nahum	Editor-in-chief
Yoseph Gebre Egziabher	Cases and Current Issues Editor
Michael Herman	Artucles Editor
Negatu Tesfaye	Managing Editor

Law Faculty Staff (1982)

The following are the staff members of the Faculty of Law of Addis Ababa University established in 1963 which offers courses leading to the LL.B Degree and Diploma in Law.

Daniel Haile;	LL.B, LL.M, Assistant Professor, Dean
Efrem Yemaneberhan;	LL.B, Lecturer, Assistant Dean
Andargachew Teruneh;	LL.B, LL.M, Lecturer
Belayneh Seyoum;	LL.B,LL.M, Lecturer, (on study leave)
Fasil Nahum;	LL.B,LL.M, J.S.D., Associate Professor
Girma Woldeselassie;	LL.B,LL.M, J.S.D., Assistant Professor
Horst Kellner;	LL.B,LL.M, LL.D, Visiting Professor
Mesfin Gebreheywot;	LL.B, Lecturer
Michael Herman;	LL.M, LL.D, Visiting Professor
Negatu Tesfaye;	LL.B, Assistant Lecturer
Selamu Bekele;	LL.B, Assistant Professor
Solomon Jiru;	LL.B, LL.M, Lecturer (on study leave)
Worku Tefara;	LL.B, LL.M, Assistant Professor
Yittayih Zelalem;	LL.B, Lecturer (on study leave)
Yoseph Gebre Egziabher;	LL.B, Assistant Professor
Zekarias Keneaa;	LL.B, Assistant Lecturer

TABLE OF CONTENTS

Page

Progress Report from the Dean (1981)
byDaniel Haile 111

ARTICLES

Punishement and Society: A Developmental Approach
by Fasil Nahum 119

Irreconcilablity Between the Ethiopian Commercial Code and Contracts of Insurance with Special Emphasis on personal Accident and Life Policies
byBelayneh Seyoum 137

The 1976 Monetary and Banking Proclamation: Innovations and Implications
by Befekadu Degefe 153

Products Liablitiy in Ethiopia
by George Krzecunowicz 167

CASES AND COMMENTS

Criminal Appeal No. 4/71 Supreme Court 185

Involuntary Confession: A Case Comment on Criminal Appeal No. 4/71
by Yoseph Gebre Egziabher 191

Criminal Appeal No. 1515/71 Supreme Court 197

Criminal Attempt and Incidantal Issues: A Case Comment on Criminal Appeal No. 1515'71
by Yoseph Gebre Egziabher 203

This Vol. 12 (1982) *J. Eth. L.* is the Second
issue since the Revolution. The precious
issue, i.e. Vol. II, came out in 1980. The
last pre-revolution issue of J. *Eth. L.* that
came out in 1973 was Vol. 9, No. 2.

Addis Ababa University
Faculty of law

Annual Report from the Dean
1980-81 (1973 Ethiopian Calendar)
by DANIEL HAILE

Assistant Professor and Dean, Faculty of Law.

This academic year, the year in which we celebrated the 30th anniversary of University education in Ethiopia, has been quite a remarkable one. Not only have we, as a University, come of age by celebrating our 30th anniversary, but we have taken decisive steps to ameliorate the academic standards by reverting to some of the better methods of our old educational system. Thus, in the Faculty of Law, the duration of legal studies has been increased by one additional year, which will certainly enable us to produce more competent and mature lawyers.

The brief report hereunder gives the basic facts about staff and students, and highlights of major activities in terms of research, curriculum review, and efforts to form an alumni association, and concludes by pointing out some of our major needs and problems.

I. **Students**

At the opening of the school year 1980-81 there enrolled in the Law Faculty 214 students in our regular degree programme and 176 students in our evening diploma programme.

The breakdown of students by year and academic status is shown in the table hereunder.

Students Enrolment in the LL.B. Programme of the taculty of Law,
Academic vear 1980-81
Semester One

	Enrolment	Warning	Probation	Dismissal	Drop-outs	Withdrawal
Law I	78	7	7		2	3
Law II	84	24	4	4	3	1
Law III	43	14	1			
Law IV	9					
	214	45	12	4	5	4

Semester Two

	Enrolment	Warning	Probation	Dismissal	Drop-out	Withdrawal
Law I	73	2	5	2	1	
Law II	84	8	9	4	1	2
Law III	45		1			
Law IV	8				1	1
	210	10	15	6	3	3

Evening Diploma Programme

During the academic year 1980-81, the diploma programme ran at full capacity. In the 1st semester we had 101 first year students, and 75 in the second year.

At the close of the academic year 7 students were granted LL.B. degrees and 61 were granted diplomas.

The academic performance of many LL.B. students during the 1st semester was not quite satisfactory, and as a result the faculty was compelled to start a system whereby students who were placed on warning and probation were assigned faculty advisors. Every faculty member was assigned three or four students in need of advice, and from the performance of these students during the 2nd semester we are convinced that the advisory system has been quite successful.

